# ና ተከተለኝ

## የአማካሪው መመሪያ

ሁለተኛ እትም፣ ዓለም አቀፍ ቅጂ ፣ 2017 እ.ኤ.አ

በቲም ግሪን

የመጀመሪያው እትም በዩናይትድ ኪንግዶም (እንግሊዝ) ውስጥ በ2014 በሉሉ.ኮም ተደረገ
ይህን ሁለተኛ እትም ከ come-follow-me.org ላይ በነጻ ማውረድ ይቻላል
የቅጂ መብት © ቲም ግሪን 2014፣ 2017። የቅጂው መብት የተጠበቀ ነው።

ይሁን እንጂ የአማካሪውን መመሪያ ያለምንም ክፍያ ለግል ጥቅም ማተም እና ማባዛት ይቻላል።

**ማሳሰቢያ ለአንባቢዎች**

ይህ በመጀመሪያው እትም ላይ በብዙ ሰዎች አስተያየት እና ምክር በመታገዝ ማሻሻያ ተደርጎበት የቀረበ፣ የና ተከተለኝ የአማካሪው መመሪያ ሁለተኛ እትም ነው። አንተም ምንም ዓይነት ምክር ወይም አስተያየት ቢኖርህ፣ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለውን የአስተያየት መስጫ ቅጽ በመጠቀም በቅንነት እንድትልክልን እንጠይቃለን።

ይህ ትምህርት ከሙስሊሙ ዓለም በተወሰደ ጥናቶች፣ ምስክርነቶች፣ እውነተኛ የህይወት ታሪኮች፣ ግጥሞች እና ስዕሎች ላይ በብዙ የተመረኮዘ ነው። አንተም ለወደፊቱ ትምህርት ዝግጅት እኛን እንዲረዳን፣ አብዛኛው ሙስሊሞች ከሆኑበት ሀገር ወይም ከምዕራብ ያገኘኸውም ቢሆን ከእስልምና ለመጡ አማኞች የሚመጥኑ ማንኛውም ተመሳሳይ ምሳሌዎችን እባክህ ላክልን። እባክህ ለጥናት መጽሐፉ አጋዥ መሆን የሚችሉ አጫጭር ቪዲዮዎችን ያካተቱ የድህረ-ገጽ መረጃዎችንም ተጠቀም።

ና ተከተለኝ ከሚለው በተጨማሪ፣ በአሁን ሰዓት በwww.bmbtraining.org ያሉትን አካቶ በድህረ-ገጽ ላይ የተመሠረቱ ከሙስሊም ለመጡ ደቀ መዛሙርት ተዘጋጅተው የቀረቡ ብዙ ጽሑፎች አሉ። የአማካሪው መመሪያ ክፍል ሁለትን ከ come-follow-me.org. (ድህረ-ገጽ) እያንዳንዱን ትምህርት በተናጥል ማውረድ ይቻላል።

**ከምስጋና ጋር!** **ቲም ግሪን** **comefollowmecourse@gmail.com**

ለእግሊዝኛው እትም፡ ሁሉም ጥቅሶች በተለየ መንገድ ካልተገለጸ በስተቀር በዞንደርቫን ፈቃድ ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተወሰዱ ናቸው®, NIV®. የቅጂ መብት ©1973, 1978, 1984, 2011 በቢብሊካ (Biblica, Inc.™). የቅጂው መብት የተጠበቀ ነው። "NIV" and "አዲሱ መደበኛ ትርጉም" በሀገረ አሜሪካ እንደ ንግድ ምልክት ተመዝግቦ ያለ እና የቢብሊካ ቢሮ ንግድ ምልክት ነው።

በNLT የተቀመጡ ጥቅሶች በቲንዳሌ አታሚዎች ፈቃድ ከ "New Living Translation" መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው። የቅጂ መብት, © 1996, 2004, 2007. የቅጂው መብት የተጠበቀ ነው።

የሽፋን ስዕል በዴቪድ ሾዝበርግ / www.zagmediaarts.com

# ምስጋና

ይህን  የስራ ዕቅድ ላበረታቱ፣ ሂስ ለሰጡ እና በጸሎት ለደገፉ ሁሉ  ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለው።  ብዙ ሰዎች በና ተከተለኝ የጥናት መጽሐፍ ላይ ላደረጉት እገዛ አመሰግነናል፣ ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ (እንደ ሱ እና ራሔል ያሉ) ለዚህም የአማካሪው መምሪያ፣ እስኮት እና ማልኮም እንዳደረጉት ዋጋ ያለው ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ያዕቆብ የመጀመሪያውን እትም ቅርጽ በመስጠት እና በተለይም ‘ከባህል መገለጫዎች’ አኳያ የሙስሊምን ንጽረተ-ዓለም እና ባህል በመግለጽ በርካታ የፈጠራ ሃሳቦችን አበርክቷል። ለሁለተኛው እትም ደግሞ፣ ፔኒ የትምህርቱን መመሪያ የማስተካከል ሂደት ሲጀምር እና ጄን እነዚህን ወደፊት እንዲዳብሩ በማራመድ፣ በርካታ ኣዳዲስ ሃሳቦችን በማበርከት እና ለሕትመት በማቅረብ ድንቅ ስራ ሰርቷል።

ቤተሰቤን በተለይም ደግሞ ባለቤቴ ራሔልን አመሰግናለው። ለብዙ ዓመታት ኢየሱስን ለመከተል እንዳንድ ጊዜ ረጅሙን ጉዞ ለብቻቸው የሚሄዱ፤ ከእስልምና ወደ ክርስትና ከመጡ አማኞች የብዙዎችን ደስታ እና ሀዘን ተካፍለናል። ራሔል ይህንን ሰፊ ስራ ወደ ሚጠናቀቅበት ቀን እንዲመጣ ለማድረግ (ከአሰር ዓመት በፊት የጀመርኩት ነው!)  እና በክለሳም ይሁን በአርትኦት ዋጋው እጅግ የላቀ ድጋፍን ቸራለች።

ለሁላችሁም ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለው

# እባክዎ በቅድሚያ ይህንን ያንብቡ

ና ተከተለኝ ትምህርት መነሻቸው የእስልምና ሃይማኖት ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ለጀመሩ ሰዎች የተዘጋጀ ነው። የዚህም ዓላማው እነሱ  በክርስቶስ እና በክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ በእምነት ጠንክረው እንዲያድጉ ለመርዳት ነው።

ና ተከተለኝ ትምህርት ሦስት ይዘቶች አሉት፡

1. የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ፣ ይህም በቤት ውስጥ እያጠኑት ለውይይት እንዲዘጋጁ ይረዳል፤
2. ይህ የአማካሪው መመሪያ፣ የውይይት ጊዜዎችን እንድትመራ ይረዳሃል፤
3. አንተ አማካሪው! መጽሐፍት ደቀ መዝሙር አያደርጉም ። ደቀ መዝሙር ደቀ መዝሙርን ያፈራል።

አንተ በእግዚአብሔር እጅ ስር ሆነህ እንደ አማካሪ፣ አስተማሪ፣ አበረታች፣ ምሳሌ፣ አማላጅ እና ጓደኛ፤ በአዲስ አማኝ ሕይወት ውስጥ ታላቅ ተጽእኖ ሊኖርህ ይችላል። ና ተከተለኝ በደቀ መዝሙር የግንኙነት አውድ ውስጥ የሚጠቅም መሳሪያ ነው። ይህም የአማካሪው መመሪያ ከአንድ ወይም በቡድን ካሉ አማኞች ጋር በመሆን፣ መሳሪያውን በሚገባ እንድትጠቀምበት ይረዳሃል።

ይህ የአማካሪው መመሪያ ሁለት ክፍሎች አሉት። **በክፍል አንድ ውስጥ፣ 'ይህን ትምህርት እንዴት መጠቀም አለብህ' የሚለውን ርዕስ ለማንበብ እባክህ አምስት ደቂቃዎችን ውሰድ።** ለአንተም የጥናቱ ዘዴ እና አውዱ አዲስ ሊሆንብህ ስለሚችል ይህን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚያም በኋላ እንደ ፍልጎትህ የክፍል አንድ ሌሎች ርዕሶችን አንብብ። **'የባህል መገለጫዎች'** የሚለው ምዕራፍ ለእስልምና ባህል አነስተኛ ዕውቀቱ ላላቸሰዎች አስፈላጊ መመሪያን የያዘ ነው። እነዚህ መገለጫዎች በትምህርት የተከፋፈሉ ስለሆኑ በየሳምንቱ እንድታነባቸው እናሳስብሃለን።

**ክፍል ሁለት ለእያንዳንዱ ትምህርት የሚሆን መመሪያ ቀስ በቀስ ይሰጠናል።** እነሱም ሁለት ዓይነት ክርስቲያን አማካሪዎችን ማለትም ስለእስልምና ምንም የማያውቁ እና የመወያያ ጥያቄዎችን ደግሞ በማዘጋጀት ልምዱ የሌላቸውን ለመርዳት ታስቦ፤ የመወያያ ጥያቄዎችን እና ዝርዝር መመሪያዎችን ያካተቱ ናቸው። አንተ ግን አስቀድመህ ሁለቱንም የምታውቅ ከሆንክ ለትምህርቱ ዝርዝር መመሪያ ያለህ ፍላጎት አነስተኛ ሊሆን ይችላል። አሁንም ግን የራስህን የመወያያ ጥያቄዎች ለማዳበር እነሱን እንደ መነሻ ነጥብ ልትወስዳቸው ትችላለህ።

በማንኛውም ሁኔታ ግን በትምህርቱ መጽሐፍ ላይ 'ለውይይት' ወይም 'ለግል መልስ' የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ከተማሪዎቹ ጋር መወያየትህን እባክህ አረጋግጥ።

የጭንቅላት ዕውቀት ብቻውን በቂ አይደለም እናም ይህ ትምህርት ከእስልምና ለመጡ አማኞች በሦስት ደረጃ እንዲለወጡ ይረዳቸዋል፡

- 'ጭንቅላት'፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ የንጽረተ ዓለም ተሃድሶን የያዘ፤
- 'ልብ'፣ የስሜት፣ የምክንያት እና የዝንባሌ አቅጣጫዎችን የሚዳስስ፤
- 'እጅ'፣ ተማሪዎች በተግባር የሚያውሉት ሳምንታዊ ተግባራዊ ስራ ነው።

ይህን የአማካሪው መመሪያ ለግል መጠቀሚያ በነጻነት ማባዛት ይቻላል፤ በፒዲፍ (PDF) ፎርማት ከፈለጉ እባክዎ በታች ባለው አድራሻ ኢሜል ያድርጉልን። ለማሻሻል እንዲረዳንም አሳቦትን ይላኩልን። ይህን የአማካሪው መመሪያ ያለምንም ክፍያ ከ come-follow-me.org ላይ በነጻ በማውረድ ለግል ጥቅም ማተም እና ማባዛት ይቻላል።

ከምስጋና ጋር! ቲም ግሪን comefollowmecourse@gmail.com

# ማውጫ

## ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ መመሪያ

ርእስ ገጽ

ይህን ትምህርት እንዴት መጠቀም አለብን ... 7
አንተ እንደ አማካሪ ያለህ ሚና ... 9
እያንዳንዱን ትምህርት እንዴት እንምራ ... 10
ትምህርት 9፡ የስደት ምክንያቶች ... 10
የቡድን ውይይት መምራት ... 13
ከእስልምና የመጡ አማኞችን ደቀ መዝሙር ማድረግ ... 13
የሙስሊም ቃላት እና ባህል ነክ ጉዳዮች ... 16
በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች ... 17
አስተያየት ቢሰጡን ... 18
ባህላዊ ፍንጮች ... 19

## ክፍል ሁለት ፡ ባህላዊ ፍንጮች

ትምህርት አንድ ... 19
ትምህርት ሁለት ... 19
ትምህርት ሦስት ... 20
ትምህርት አራት ... 20
ትምህርት አምስት ... 21
ትምህርት ስድስት ... 21
ትምህርት ሰባት ... 22
ትምህርት ስምንት ... 22
ትምህርት ዘጠኝ ... 23
ትምህርት አሥር ... 23
ትምህርት አሥራ አንድ ... 23
ትምህርት አሥራ ሁለት ... 24
ትምህርት አስራ ሦስት ... 24
ትምህርት አስራ አራት ... 26
ትምህርት አስራ አምስት ... 26
ትምህርት አስራ ስድስት ... 27
ትምህርት አስራ ሰባት ... 28
ትምህርት አስራ ስምንት ... 28
ትምህርት አስራ ዘጠኝ ... 29
ትምህርት ሃያ ... 30
የመግቢያ ስብሰባ ... 31

# ክፍል ሦስት ፡ ባህላዊ ፍንጮች

ትምህርት 1፡ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ........ 33
ትምህርት2: በክርስቶስ ያለ አዲስ ሕይወት ........ 35
ትምህርት 3: እግዚአብሔር አባት ........ 37
ትምህርት 4: በመንፈሱ ኃይል ክርስቶስን መታዘዝ ........ 39
ትምህርት 5:ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር /ጸሎት/ ........ 41
ትምህርት 6፡ የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ ........ 43
ትምህርት 7: የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ........ 45
ትምህርት 8: የሁለት ማህበረሰብ አባላት ........ 47
ትምህርት 9: የስደት ምክንያቶች ........ 49
ትምህርት 10፡ ለስደት ምላሽን መስጠት ........ 51
ትምህርት 11፡ ባሎችና ሚስቶች ........ 53
ትምህርት 12፡ ግጭቶቻችንን መፍታት ........ 55
ትምህርት 13፡ ምስክር መሆን ........ 57
ትምህርት 14፡ ጥምቀት ........ 59
ትምህርት 15፡ ቀጥተኛው መንገድ ........ 61
ትምህርት 16፡ የመውደድ ህግ ........ 63
ትምህርት 17፡ ጾም እና መስጠት ........ 65
ትምህርት 18፡ ዕጣ ፈንታ እና ምትሃት ........ 67
ትምህርት 19፡ የእርስ በርስ አገልግሎት ........ 69
ትምህርት 20፡ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ መንግስተ ሰማይ ........ 71
ማጣቀሻ፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ የተጠቀምናቸው በቃል የሚጠኑ ጥቅሶች ........ 73

# ክፍል አንድ ፤

# አጠቃላይ መመሪያ

# ይህን ትምህርት እንዴት መጠቀም አለብን

እባክህ ይህንን ርዕስ ጉዳይ በሚገባ አንብብ። ይህም ከትምህርቱ የምታገኘው ጠቀሜታ የላቀ እንዲሆን ይረዳሃል።

**ይህ ትምህርት ለማን እና ለምን?**

ይህ ትምህርት ከእስልምና ለመጡ የክርስቶስ ተከታዮች ወይም የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን ለውሳኔ ለተቃረቡ ሰዎች የተዘጋጀ ነው። ይህም በደቀ መዝሙርነት የመጀመሪያውን እርምጃ እንዲወስዱ ይረዳቸዋል። ትምህርቱም ያደጉ አማኞችን ከእስልምና ባህል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥልቅ ጉዳዮች እንዲያውቁ እና እነዚህንም ከሌሎች ጋር እንዲወያዩባቸው በመርዳት ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል።

**የትምህርቱ ዘዴ ምንድነው?**

ይህ ትምህርት <u>በግለ-ጥናት ሊጠናቀቅ አይችልም</u>። ከሌሎች ጋር በመሆን ሊጠቀሙት የሚገባ ነው። ትምህርቱም ለተማሪዎች በየሳምንቱ ያለው ዘዴ፤

1. በመጀመሪያ፣ ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉን በቤታቸው በግል ሊያጠኑ ይገባል፤
2. ሁለተኛ፣ በየሳምንቱ ከአንተ (እና ከተቻለም ከሌሎች) ጋር ይወያያሉ፤
3. ሦስተኛ፣ በዕለት የሕይወት አውድ ውስጥ ትምህርቱን ተግባራዊ ያደርጋሉ።

ለበለጠ ዝርዝር ደግሞ፤

- 'የቤት ውስጥ የጥናት ጊዜ' ያለፍላጎት የሆነ ንባብ ሳይሆን ንቁ የመማር ሂደትን ያካተተ ነው። ተማሪዎችንም ከእያንዳንዱ አጫጭር ትምህርቶች በኋላ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ያዛቸዋል፤
  - አንዳንዱ ጥያቄ ተማሪዎቹ ምን እንዳጠኑ ለማስታወስ ይረዳቸዋል፤
  - አንዳንዱ ጥያቄ ትምህርቱን እንዲረዱ እና በህይወታቸው እንዲተገብሩት ያግዛቸዋል፤
  - አንዳንዱ ጥያቄ ስላላቸው አመለካከት እንዲገልጹ እና ስለእነሱም ለእግዚአብሔር ለመንገር ይረዳቸዋል፤
  - አንዳንዱ ጥያቄ በውይይት ጊዜ ያገኙትን ልምድ ለማካፈል ዝግጁ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል፤
  - ስዕሎቹ እና ምሳሌዎቹ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ከሕይወት ልምምዳቸው ጋር እንዲያዛምዱ ይረዳቸዋል።
- የዚህ መማሪያ መጻሃፍት ጠቀሚነት እና አስፈላጊነት የሚታወቀው በውይይት ጊዜ ነው። አጥኚዎቹ ሃሳባቸው መናገር እና የሌሎችን ሃሳብ ይሰማሉ። ይህም የድሮን አመለካከታችን ያስቀይራል እና አዲስ መነሳሳትን ያስገኝልናል።
- በፊት አንድ ነገር ተግብረው እንዲመጡ የተግባር ትምህርቱ እድል ይሰጣቸዋል። ይህም ትምህርቱ ንድፈ ሃሳብ ብቻ እንዳይሆን ያስቀራል እንዲሁም በህይወታችን የምንኖረው አንድ ክፍል ያደርጋዋል።

**ትምህርቱን የምንጠቀመው በግል ወይስ በቡድን ነው?**

ይህንን ትምህርት በሁለቱም መንገድ መጠቀም ይቻላል፣ እናም እያንዳንዱ የራሱ የሆነ በጎ እና መጥፎ ጎን አለው። አንተም ትምህረቱን ለመማር ፈቃደኛ በሆኑ ሰዎች ሁኔታ ትመራለህ። ከእስልምና የመጡ አማኞችን በአነስተኛ ቡድን በአንድነት ማድረግ ከተቻለ፤ ይህ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ሊያጠናክረው እና ወይይት የመምራት ልምድ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በግል ማማከር ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነው። የአንድ ለአንድ ውይይት ወደ አንድ አቅጣጫ ይመራናል፣ እና ሁሉንም ጥያቄ በምታቀርብ ጊዜ ግን እነሱም ሁሉንም መልስ ሲሰጡ፤ ስለዚህ ይህንንም የምትጋሩት ልምድ ለማድረግ ስትሞክሩ፣ ሁለታችሁም ከእግዚአብሔር ቃል እና እርስ በርስ ትማማራላችሁ።

በዚህ የአማካሪው መመሪያ ውስጥ ብዙ ጊዜ 'ተማሪዎች' ብለን ስንናገር በነጠላ ወይም በብዙ ቁጥር ማለታችን ነው። 'እሱ' ወይም 'እሷ' በማለት ፈንታም ወንድ እና ሴትን የሚያካትትልንን 'እነሱ' የሚለውን ተውላጠ ስም እንጠቀማለን፡ ፡ ምንም እንኳን ጥቂት የመማር ሂደቶች በቡድን እንድንሆን ቢፈልጉም፣ ሁሉም የመወያያ ጥያቄዎች በቡድን ውስጥ ወይም በግል ልንጠቀምባቸው ይገባል።

**ሃያዎቹም ርዕሶች በአንድ ጊዜ መሸፈን አለባቸውን?**

የግድ አይደለም። ያለምንም እረፍት ለሃያ ሳምንቶች ትምህርት መስጠት በጣም ረጅም ነው! ስለዚህ በመሃል እረፍት ለማድረግ ርዕሶቹን ሁለት ቦታ መክፈል ወይም ለተማሪዎችህ ወሳኝ የሆኑትን ርዕሶች በመምረጥ ትምህርቱን ለመስጠት ነፃነቱ ይሰማህ።

**የወይይቱም አቀራረብ እና የጊዜው ድልድል እንዴት ነው?**

ለውይይቱ የተወሰነ አቀራረብ ወይም የጊዜ ድልድል የለም። እንደ አስፈላጊነቱ ልትለዋውጠው ትችላለህ፣ ነገር ግን መደበኛ የውይይቱ ክፍለ ጊዜ ቢያንስ እስከ 1 ሰዓት ተኩል ባለው ጊዜ ውስጥ (ሻይ ቡናን አካቶ) ሊጠናቀቅ ይችላል እና ይህም የሚያካትተው፤

- ሻይ ቡና እና የጭውውት ጊዜ (በመጀመሪያ ወይም በመጨረሻ ላይ)
- የመክፈቻ ጸሎት
- ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ
- የዚህን ሳምንት የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ
- ከርዕሱ ውስጥ በተመረጡ ጥያቄዎች ላይ መወያየት
- የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውይይት
- አንዳንድ ጊዜ በአጭር ቪድዮ ወይም ተግባራት ይቀርባሉ
- ያሰላሰልነው ጥቅስ ልምምድ
- የግል የጸሎት ጥያቄን ያካተተ፣ የመዝጊያ ጸሎት

| |
|---|
| በውይይት ጊዜ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን ሃሳቦች ሁሉ ዝም ብለህ አታንሳ። ይህም አሰልቺ ይሆናል። ተማሪዎቹ ለውይይት ከመምጣታቸው በፊት ይህንን አድርገው ስለሚመጡ ሁሉን መከለስ አይጠበቅብህም። ወይም ደግሞ በስብከት መልክ ብዙ አዳዲስ ትምህርቶችን መጨመር የለብህም። በዚህ ፈንታ ግን፣ ለተማሪዎቹ የህይወት ለውጥ በማምጣት የሚረዷቸው ተግባራዊ የመወያያ ነጥቦች ላይ አተኩር። |

**ይህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ነውን?**

አዎን በሚገባ። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በማመን እና እኛም እንደ ክርስቶስ ተከታዮች (ተማሪዎቹ እና አማካሪው) ልንረዳው እና ልንታዘዘው የተገባ ነው። ና ተከተለኝ በ1ኛ ጴጥሮስ ላይ የተመሠረተ፣ ከጅምሩ በጫና ውስጥ ያለ አዲስ አማኝን ለመምራት የተጻፈ ነበር።

የ1ኛ ጴጥሮስ ዝርዝር ጥናት፣ ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ተራ በተራ እስከ መጨረሻው ምዕራፍ ድረስ የትምህርቱ የጀርባ አጥንት ነው። እንደ ጎድን ከዚህ የጀርባ አጥንት ላይ የወጡት ሃያ የትምህርት አርዕስቶች ከእስልምና ለመጡ አማኞች አስፈላጊ ናቸው። እነዚህም ጎድኖች ከሌሎች ወሳኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር የተገናኙ ናቸው።

እያንዳንዱ ትምህርት ጭብጡ የሚጠቃልልበት የምናሰላስለው ጥቅስ አለው። እነዚህም ጥቅሶች ከ1ኛ ጴጥሮስ እና ከሌሎች መጽሐፎች የተወጣጡ እና ለአንተም እንዲመችህ በዚህ የአማካሪው መመሪያ ላይ ባለው ማጣቀሻ ውስጥ ተሰብስበው ተቀምጠዋል። ለማስታወስም እንዲረዳን፣ ለማሰላሰል አጫጭር ጥቅስ ወይም የረጅም ጥቅስ አጭር ክፍል ይመረጣል።

**የመማሪያ መጽሐፉ ቀላል የመሰለው ለምንድነው?**

በመጀመሪያ የተጻፈው ጥቂት ሰዎች ብቻ የከፍተኛ ትምህርት ዕድል በሚያገኙበት አውድ ነበር። ስለዚህ ጽሑፉ በተጨባጭ ምሳሌዎች እና ስዕሎች በመታገዙ፣ ለመጠቀም - ለማንበብ ቀላል ነው። ይህ ሲባል ግን ሀሳቡ ቀላል ነው ማለት አይደለም። የዚህ ትምህርት ግለ ጥናት ጥልቀት ወዳለው ሃሳብ፣ የንጽረተ ዓለም ተሃድሶ እና ተግባራዊ ደቀ መዝሙር ወደ መሆን እየመራን በውይይት ጊዜ የሚረዱንን የመንደርደሪያ ሃሳቦች ይሰጠናል። ተጨባጭ ምሳሌዎች ከረቂቅ ትምህርት በላቀ ሁኔታ ውይይቱን እና ትግበራውን ቀላል ያደርጉታል። በዚህ ትምህርትም አማካኝነት ደቀ መዝሙር የሆነ ሰው ሌሎችንም ደቀ መዝሙር ለማድረግ ቀላል መሳሪያ አለው። ይህም ደቀ መዝሙር ማፍራትን ባለ ብዙ ርቢ ያደርገዋል።

**ይህ የአማካሪው መመሪያ ዝርዝር የሆነው ለምንድነው?**

ይህ የተጻፈው በርካታ አማካሪዎችን ለመርዳት ነው። አንዳንዶች የመወያያ ጥያቄዎችን ከመፍጠር አኳያ ብዙ ድጋፍ ሲፈልጉ፣ ሌሎች ደግሞ የባህል መመሪያን ይፈልጋሉ። ለውይይት ጥያቄዎች እንደ ሃሳብ የቀረቡ ምላሾች አሉን። ልምድ ያለው አማካሪ ይህንን አይፈልግም፣ ነገር ግን ለአንተ ምቹ የሆነውን መምረጥ እንድትችል ሁሉም በአንድ ላይ እዚህ ተቀምጧል።

በሳምንቱ የውይይት ጊዜ መሸፈን ያለብህ በጣም ብዙ ጥያቄዎች ከሆኑ፣ ለተማሪዎችህ ተገቢ የሆኑትን ብቻ ምረጥ። ነገር ግን በመማሪያ መጽሐፉ ላይ 'ለውይይት ጊዜ' ወይም 'በግልህ መልስ ስጥ' የሚሉትን ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ለማካተት ሞክር፡

**እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ የሆነ የመማሪያ መጽሐፍ ያስፈልገዋልን?**

አዎን፣ እያንዳንዱ አማካሪን ጨምሮ። አንተም ይህንን come-follow-me.org (ድህረ ገጽ) ልታገኝ ትችላለህ፡

# አንተ እንደ አማካሪ ያለህ ሚና

**መጽሐፍ አስተማሪ ነው**

መጽሐፉ ራሱ ትምህርቱን በቀላል መንገድ ያቀርበዋል። ቀላል ጥያቄዎችን በመጠየቅ በእያንዳንዱ ትምህርት ማብቂያ ላይ መልሱን ይሰጠናል። የመምህሩ ምስል ዋና ዋና ነጥቦችን ለተማሪዎቹ ያስታውሳል። አንተ ራስህ ትምህርቱን መጻፍ ስለማይጠበቅብህ ይህ ስራህን ቀላል ያደርገዋል። የውይይቱን ጊዜ ተማሪዎች በመጽሐፉ የተሰጣቸውን ትምህርት እንዲያስተውሉት እና እንዲተገብሩት ለመርዳት እንጂ ስብከት ለማቅረብ መጠቀም የለብህም።



**አንተ አማካሪ አሰልጣኝ እና ጓደኛ ነህ**

ተማሪዎች አንተን እንደ አማካሪ አሰልጣንኝ ያዩሃል። አንተ የእነሱ ምሳሌ፣ አማካሪ እና ጓደኛ ነህ። እነሱም በጥንቃቄ ይመለከቱሃል። የአንተ ምሳሌነት ከዕውቀትህ በላይ አስፈላጊ ነው። አንድ የአፍጋኒስታን አማኝ እንደተናገረው፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እንዳጠና በምጠየቅ ጊዜ … የማጠናው ደቀ መዝሙር ያደረገኝን ሰው ነበር"።

ተማሪዎቹ ትልልቅ ሰዎች እንጂ ልጆች አለመሆናቸውን አስተውል። እነሱም ለቡድኑ ሊያበረክቱ የሚችሉት ብዙ የሕይወት ተሞክሮ አላቸው። ስለዚህ እነሱን በውይይት ጊዜ ብዙ ጥያቄዎች አቅርብላቸው። የእነሱን አስተያየት እና ልምድ ጠይቅ፡ ፡ ለራሳቸው እንዲያስቡ እርዳቸው። በየሳምንቱ 'ተግባራዊ ስራውን' መስራታቸውን አረጋግጥ። ለእነሱ ጥሩ ምሳሌ ሁን። ስለእነሱ ግድ ይበልህ። ጸልይላቸው። ደስታ እና ሀዘናቸውን ተካፈል። ቀውስም በተፈጠረ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ሃሳብ መቆም እንዲችሉ እርዳቸው።

ከሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜህ ውጪ ከጓደኛህ ጋር ተገናኝ። ከእነሱም ጋር ምግብ ተገባበዝ ወይም በአንድነት የሚያዝናና ነገር ለማድረግ ወጣ በሉ። የተለመዱ ነገሮችን በአንድነት አድርጉ። እነሱም አንተ ለጭንቀት እንዴት መፍትኄ እንደምታመጣ፣ ሌሎችን እንዴት ይቅር እንደምትል፣ ከልምድህ፣ ከቤተሰብ ሕይወትህ ድርጊት እና ምላሽህን በመመልከት እንዴት እንደሚማሩ ትገረማለህ።

**ደቀ መዝሙር ደቀ መዝሙር ያደርጋል**

የመማሪያ መጽሐፍ ደቀ መዝሙር ማድረግ አይችልም። ደቀ መዝሙር ማድረግ የሚችሉት ደቀ መዝሙር የሆኑ ብቻ ናቸው። አንተ እንደ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር እንድታድግ አንዳንዶች አግዘውሃል። አሁን ደግሞ ሌሎች እንዲያድጉ መርዳት የአንተ ተራ ነው። በርካታ ሙስሊሞች በአሁን ሰዓት ካለፈው ጊዜ በተለየ መልኩ ወደ ኢየሱስ እየተመለሱ (እየመጡ) ናቸው። ግን ወንጌል ስርጭት ያለደቀ መዝሙር ፍሬው ደካማ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ከእስልምና ለመጡ በእግዚአብሔር ውድ ህዝቦች ሕይወት እና ቤተሰቦቻቸው ውስጥ የሚበዛ ፍሬን ለማየት፣ እግዚአብሔር እንደ አብሮ ሰራተኛው እንዲጠቀምብህ እንመኛለን።

# እያንዳንዱን ትምህርት እንዴት እንምራ

**ከእያንዳንዱ ስብሰባ በፊት**

1. ከስብሰባው ቢያንስ ከሁለት ቀን በፊት፣ አንተ ራስህ እንደተማሪ ሆነህ ትምህርቱን አዘጋጅ። ለሁሉም ጥያቄዎች የራስህን መልሶች ጻፍ። አቋራጭ መንገድ አትሂድ።
2. የትምህርቱን 'ዓላማዎች' አንብብ። እኛ እንደ ዓላማ ያስቀመጥነው በእያንዳንዱ ሳምንት መመሪያ ውስጥ ባለው የትምህርት መጀመሪያ ላይ በስተ ግራ በተቀመጠው ሳጥን ውስጥ ያሉ ናቸው። ለምሳሌ፡ የትምህርት 9 ዓላማዎች እነሆኝ

<table>
<tr><th colspan="2">ትምህርት 9: የስደት ምክንያቶች</th></tr>
<tr><td rowspan="2">የእያንዳንዱ ተማሪ ዓላማዎች:<br>ሀ. ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ነገር እንደማይለየን እርግጠኛ እንሆናለን።<br>ለ. ስደት በእውነት እንደሚከሰት እና እግዚአብሔር ግን ለበጎ እንደሚያደርግለን እንረዳለን።<br>ሐ. አላስፈላጊ ስደት እንዲወገድ የጥበብ እርምጃን መውሰድ ትማራለህ።<br>መ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡21 አሰላስል።</td><td>የባህል መገለጫዎች፡<br>በስደት ያሉትን ማማከር</td></tr>
<tr><td>አዘጋጅ: በወረቀት ላይ ከሮሜ 8፡36 ቃል (ለጥያቄ 12)</td></tr>
</table>

እነዚህ ሁሉ ዓላማዎች አባላት በዚህ ሳምንት የሚያደርጉት አንድ ነገር አላቸው፡

- 'እርግጠኛ ሁን' የአመለካከት ጉዳይ ነው፤
- 'እንረዳለን' ሲል የዕውቀት ጉዳይ ነው፤
- የጥበብ እርምጃን መውሰድ ትማራለህ' ሲል ወደ ተግባር የሚለወጥ ክህሎት ነው፤
- 'አሰላስል' ሲል የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ወደ ልብ እና ሕይወት ለማስገባት መልካም መንገድ ነው።

3. በመቀጠልም የዚህን ትምህርት መመሪያ አንብብ። ቀስ በቀስ አንተን ለመርዳት ዝርዝር መመሪያዎችን ሰጥተንሃል። <u>የአንተን</u> ተማሪዎች የሚመጥን የመወያያ ጥያቄዎች ምረጥ። በኋላ ላይ የበለጠ ልምድ እያገኘህ ስትሄድ፣ እንደ አባሎችህ ፍላጎት እና እንደ ትምህርቱ ዓላማዎች መሠረት የራስህን የውይይት ጥያቄዎች ለመጻፍ ነጻ ሁን።
4. በተለይ ለእስልምና ባህል ዕውቀቱ ከሌለህ፣ 'የባህል መገለጫ' የሚለውን ርዕስ እንብብ።
5. በሳጥን ውስጥ ያለውን የትምህርት እንቅስቃሴ ለማድረግ ካቀድክ የተጠቀሱትን ነገሮች አዘጋጅ።
6. በመጨረሻም፣ ለእያንዳንዱ የቡድን አባለት ጸልይ። ጥሩ አማካሪ እንድትሆን እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጠይቀው።

**በእያንዳንዱ ስብሰባ ወቅት**

1. ሰዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ በል። ከፈለክ ሻይ ቡና በል።
2. ስብሰባውን ለመጀመር 'መክፈቻ' በሚለው ስር ያሉትን እርምጃዎች ተከተል። የትምህርት 9 ምሳሌ

## *መክፈቻ*

***ለትምህርቱ መጸለይ።*** ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራን መከለስ: ማህበረሰባችንን፣ የተቸገሩ ሰዎችን ወይም በስልጣን ላይ ያለ አንድን ሰው ለመርዳት ምን ታደርግ ነበር? የሌላው ሰው ምላሽ እንዴት ነበር?

**የትምህርት 9 የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ**

**ጥያቄ 1:** ለእናንተ, ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ (1 ኛ ጴጥሮስ 2:21).

**ጥያቄ 2:** 1) ዓለም፣ ይጠላችኋል; 2) እግዚአብሔር፣ ያሳድዷችኋል; 3) ሞኝ መሆን፤ 4) የክርስቶስ እርምጃ

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** የዛሬው ርዕስ ስደት ሲሆን እና ከባድም ርዕስ ነው። የእኛም ውይይት ካለፉብን ጉዳት የተነሳ እምባን ሊያስከትል ይችላል። እኛም ስለነዚህ ነገሮች ስንናገር ፣እግዚአብሔር ግን ስደትን ለበጎ በመለወጥ ህመማችንን ይፈውስልናል።

'ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ' አስፈላጊ ነው። በዚህም ተማሪዎች ይህ ትምህርት እውነት ለመማር ብቻ ሳይሆን በተግባር ላይ ለማዋል የተዘጋጀ መሆኑን ያያሉ። እነሱም በደቀ መዝሙር ሕይወት ውስጥ እንዴት ዕድገት እንደሚያመጡ እና አሁንም የቱ ጋር ተግዳሮት እንዳለባቸው ለአንተ ያሳይሃል። ተማሪዎቹ ተግባራዊውን ስራ እንዴት እንዳጠናቀቁ የሚገልጽ ዘገባ እንዲያቀርቡልህ ጠይቃቸው፣ ነገር ግን በአዲሱ የትምህርት ርዕስ መቀጠል ስላለብህ የባለፈውን ሳምንት የመወያያ ርዕስ ደግመህ አታንሳ።

'የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ' ዓላማው ተማሪዎች የቤት ውስጥ ጥናታቸውን እንደ ጨረሱ ለማረጋገጥ እና እነሱም የትምህርቱን ዋና ሃሳብ ማስታወስ እንዲችሉ ነው። ትምህርቱን የምትሰጠው በኢመደበኛ ዘዴ ከሆነ፣ ተማሪዎቹ መጽሐፋቸውን ዘግተው በቃላቸው እንዲመልሱ ጠይቅ። በመደበኛ ዘዴ ውጤት ለመያዝ ከሆነ የምትሰጠው፣ የትምህርቱን ማጠቃለያ ፈተና በጽሑፍ አዘጋጅተህ በማባዛት እያንዳንዱ ተማሪ መጽሐፉን ዘግቶ እንዲሰራው አድርግ። የእነሱም ፈተና በኋላ ላይ (በአንተ) ወይም ወዲያውኑ (ከተማሪው ጎን በተቀመጠ ሌላ ተማሪ፣ ፈተናቸውን በመለዋወጥ) እርማት ሊሰጠው ይችላል።

3. አንተ አስቀድመህ የመረጥካቸውን የመወያያ ጥያቄዎች በመጠቀም፣ ውይይቱን ምራ። ጊዜ ከሌለህ ደግሞ ቢያንስ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ 'ለውይይት' ወይም 'በግል የሚሰጥ ምላሽ' ተብለው የቀረቡትን ጥያቄዎች መሸፈንህን አረጋግጥ። አንተም በቡድን የውይይት ዘዴ ልምዱ ከሌለህ፣ 'የቡድን ውይይት መምራት' የሚለውን መመሪያ አንብብ። ለምሳሌ፡ ተጋቦት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ያካተቱ ጥያቄዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምልክት የተደረገባቸው ናቸው።

1ኛ ጴጥሮስ 1፡3-7 አንብብ

በቁጥር 4 መሠረት. የእኛ ርስት የት ነው? በሰማይ

- ይህም የሚጠፋ፣ የሚያልፍ ወይም እድፈት ያለበት ነውን? አይደለም - እንደ እኛ ምድራዊ ርስት አይደለም
- በቁጥር 5 መሠረት፣ እኛ በዚህ ጊዜ የሚጠብቀን ጋሻ ምንድነው? የእግዚአብሔር ኃይል

4. አንተ እንደ አማካሪ ብዙ ጊዜ መናገር የለብህም። በዚህም ፈንታ ተማሪዎቹ ብዙ ሊናገሩ ይገባል። ስለዚህ ከመማሪያ መጽሐፉ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚነበብ አንቀጽ በሚኖርበት ማንኛውም ጊዜ፣ ይህን አንተ ሳትሆን ተማሪዎቹ ቢያነቡት የተሻለ ነው።
5. ለውይይት ጥያቄዎች የሚሆኑ አንዳንድ መልሶች ለአንተ እንዲረዳህ፣ ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሠረት በግራጫ ኢታሊክስ (ጠመም ያለ ጽሑፍ) ተሰጥቶሃል። በመጀመሪያ አንተ ራስህ መልሱን ከመስጠትህ በፊት ጥያቄውን በመደጋገም ወይም ወደ ትክክለኛው ጥቅስ በመጠቆም፣ ተማሪዎችህ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ በተቻለ መጠን አበረታታቸው። እነዚህ ግራጫ ኢታሊክሶች ባጠቃላይ አንተን በትምህርት ውስጥ ለመርዳት ተጨማሪ ልምድ እና ማስታወሻ ይሰጥሃል። ለምሳሌ፡

ጥያቄ 17፡ ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ።

- በዚህ ጥያቄ ላይ የአንተ አስተያየት ምንድነው? ትክክል ወይም ስህተት የሆነ መልስ በሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ ነው። ህይወቱ አደጋ ላይ የወደቀ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ወደ ሌላ ቦታ መሄድን ሊያስብ ይገባል። ይሁን እንጂ ሁኔታው አደገኛ ካልሆነ መሻሻልን እስኪያሳይ ድረስ በተቻለ መጠን በቤቱ በዝግታ ለመኖር መሞከር አለበት። ምንም እንኳን እነሱ ኢየሱስ ክርስቶስን ቢከተሉም አሁንም ግን ለቤተሰቦቻቸው ያላቸውን ታማኝነት ለማረጋገጥ መሞከር አለባቸው።

6. በአንዳንድ ትምህርቶች ውስጥ ለመማሪያ የሚረዱ ተግባራትን፣ ወይም የሚታይ አጭር ቪዲዮ በአስተያየት መልክ አካተናል፡

እነዚህም በስተግራ ባለው የኳስ ምልክት ይወከላሉ። ለእነዚህም ተግባራት ዝግጅት ያስፈልጋል፣ ይህም በትምህርቱ ርዕስ ሳጥን ውስጥ ‘አዘጋጅ’ በሚለው ክፍል ይጠቀሳል። አንተም ከትምህርቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ሌላ ጥሩ አጭር ፊልም ወይም የመማሪያ ተግባራትን ካገኘህ፣ እባክህ እኛም እንወቃቸው።

ብዙዎቹ የውይይት ጊዜዎች የዚያን ሳምንት የቃል ጥናት ጥቅሶች ለመከለስ የሚረዱ ናቸው። በአንዳንድ የዚህ የማጥኛ መጽሐፈ የኋለኛ ትርጉሞች የቃል ጥናት ጥቅሶቹ በቀኝ በኩል በተመለከተው የቃል ጥናት ጥቅስ ምልክት ተመላክተዋል። ለማመሳከር እንዲቀል፣በመጽሓፉ የመጨረሻ ገጽ ላይ ቀርበዋል።

ተማሪዎችህ ለማጥናት እንዲመቻቸው ለመርዳት አንድ ሰው እንዲያነባቸው በማድረግ በድምጽ ቀርጸህ ልትልክላቸውና ሳምንቱን ሁሉ እንዲያጠኑት ልታደርግ ትችላለህ። ይህም በተለይ በቃል ብቻ ለሚማሩቱ በጣም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

7. በመጨረሻም በሳጥን ውስጥ ያሉትን ደረጃዎች በመከተል ስብሰባውን አጠቃልል። በትምህርት 9 ማብቂያ ላይ የሚኖረውን ሳጥን እንደ ምሳሌ እንመልከት።

| ማጠቃለያ | |
|---|---|
| **ዛሬው ትምህርት መታዘዝ:**<br>• የዛሬው ትምህርት በህይወትህ ላይ የሚያጣው ልዩነት ምንድነው?<br>• **ተግባራዊ ስራውን በአንድነት አንብቡ።** ተማሪዎች ለዛሬው ምላሻቸው በየዕለቱ አንድ ጥቅስ የሚያሰላስሉበትን አንድ ዓይነት ሂደት መጠቀም ይችላሉ። | **የአንድነት ጸሎት:** እግዚአብሔር በስደት ጊዜ ስለሰጠን ብርቱ ተስፋ በአጭር ጸሎት እንዲያመሰግኑት ሰዎችን ጠይቅ። በሌሎች ሀገሮች በስደት ምክንያት እየተሰቃዩ ላሉ አማኞች በተለይም ደግሞ ከእስልምና ለመጡ የክርስቶስ ተከታዮች ጸልይ። |

**ከስብሰባው በኋላ**

1. የአንተ ቡድን በሙከራ ፈተናዎች ወይም በተገኙበት ቀን ውጤት የሚያዝላቸው ከሆነ ይህንን መዝግበህ ያዝ፡

ሀ) የቤት ስራ ሲጨርሱ (በተለይም የቡድን ውይይት ጥያቄዎችን ሲሰሩ)፣

ለ) በውይይት ጊዜ ሲሳተፉ እና

ሐ) ተግባራዊ ስራውን ሲሰሩ፤ ነጥብ ቢያዝላቸው መልካም ሃሳብ ይሆናል። ይህ በአንዳንድ ሁኔታ ውስጥ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ንቁ ተሳትፎን እንዲያደርጉ እና የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። በሌላ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ይህን መደበኛ ባልሆነ መንገድ መከታተሉ የተሻለ ሊሆን ይችላል።

2. አንተም ውይይቱን በሚገባ መምራትህን ለመገንዘብ፣ እነዚህን አራት ጥያቄዎች ለራስህ አቅርብ፡

- “እኔ ብዙ አውርቼ ነበር?”
- “ዝምተኞቹን እና አይናፋሮቹን ጨምሮ ሁሉም አባላት በውይይቱ ላይ ተሳትፈው ነበር?”
- “ጥያቄዎቹ ለመረዳት ግልጽ እና ለውይይትም የሚመቹ ነበሩ?”
- “ትምህርቱ ግቡን መቷል እና በህይወታችንም መተግበር የሚችል ነበር?”
- ከልምድህ ተማርና የተኛውንም ደካማ ጎንህን በቀጣይ ሳምንት ለማሻሻል ሞክር።

3. በሳምንቱ ውስጥ ለተማሪዎች መጸለይህን ቀጥል።

# የቡድን ውይይት መምራት

አንተም የቡድን ውይይት የመምራት ልምዱ ከሌለህ፣ አንዳንድ መመሪያዎች እዚህ ተቀምጠዋል።

- ራስህ ብዙ አታውራ! ጥያቄ አቅርብ እንጂ ትምህርት አትስጥ። አዋቂ ሰዎች በዚህ ዓይነት መንገድ የበለጠ ይማራሉ እናም ይረኩበታል። ጥሩ ጥያቄዎች መሆን ያለባቸው፣
  - ለመረዳት የቀለሉ
  - ከትምህርቱ ጋር አብረው የሚሄዱ
  - ወይይት ከፋች(‘አዎን’ ወይም ‘አይደለም’ ተብሎ በአንድ ቃል የሚዘጋው መሆን የለበትም)

- እያንዳንዱ አባላት በውይይቱ እንዲሳተፉ ዕድልን ስጣቸው። ወሬኛውም ብዙ እንዳይናገር ጠይቀው። አይናፋር የሆነውን ደግሞ ቀላል ጥያቄ በመጠየቅ እርዳው (በእሱም ፈንታ ሌሎች እንዲመልሱ አትፍቀድ)
- የቡድኑ አባላት ጥያቄውን መረዳት ካልቻሉ፣ ያንኑ ጥያቄ በተለየ መንገድ ደግመህ አቅርብላቸው እንጂ አንተ ራስህ መልሱን እንዳትሰጥ።
- ውይይቱ ከዋናው ሃሳብ አፈንግጦ እንዲወጣ አትተወው።
- አንዱ አባል ‘ስህተት’ የሆነ ወይም ለውይይቱ የማይረዳ መልስ ቢሰጥ፣ ልክ አይደለህም በማለት አታሳፍረው። በዚህ ፈንታ ግን ሌሎች አባላት ምን እንደሚያስቡ ጠይቃቸው። እነሱም ብዙ ጊዜ የተሻለ መልስ ይሰጣሉ። ሳተ ለምንለው ግን እንደ አማራጭ፣ ‘ስለአስተዋፆህ አመሰግናለው፣ የሚደነቅ ነው ግን ይህንንስ ገጽታ አገናዘበህዋል?’ ማለት እንችላለን።
- ከእያንዳንዱ ትምህርት የቡድኑ አባላት በተናጠል በህይወታቸው የሚተገብሩትን አንድ ነገር ይዘው መሄድ እንዲችሉ፣ በተግባራዊው ክፍል ላይ አተኩር።
- አባላት አንተን ጥያቄ እንዲጠይቁህ ፍቀድ። መልሱንም ካላወከው ከሚቀጥለው ስብሰባ በፊት እንደምታገኘው ንገራቸው፤ ፣ መልሱን አውቀዋለው ብለህ ከምታስመስል ይልቅ እንዲህ ብትነግራቸው ያከብሩሃል። በቀጣይ ስብሰባም መልስህን በማምጣት የገባኸውን ቃል እንደምትፈጽም አረጋግጥ።
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም ከመማሪያው መጽሐፍ አንድ ክፍል የማንበቢያ ጊዜ ሲሆን፣ አንድ የቡድኑ አባል ይህን እንዲያደርግ ጠይቅ። ይህም ለእነሱ በንቃት ለመሳተፍ የበለጠ ዕድልን ይሰጣቸዋል። ይህም አይናፋር አባላት በውይይቱ እንዲሳተፉ መልካም መንገድ ነው።

  እየሰራ ያለኸው ብዙ ቋንቋ በሚነገርበት መካከል ከሆነ፣ እያንዳንዱ የቋንቋ ማህበረሰብ በራሱ አፍ እንዲያነብ ልትጋብዘው ትችላለህ። ወይም አንተ አንድ ጊዜ በአማርኛ ካነበብከው በኋላ ተማሪዎቹ በራሳቸው ቋንቋ እንዲያነቡት ጊዜን ልትሰጣቸው ትችላለህ።

# ከእስልምና የመጡ አማኞችን ደቀ መዝሙር ማድረግ

ከእስልምና የመጡትን ደቀ መዝሙር በማድረግ ያለህ ልምድ አነስተኛ ከሆነ እናም በተለይ አንተ ከምዕራብ ሀገራት ከሆንክ፣ እባክህ ይህንን ርዕስ አንብብ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም ነገድ (የራሳቸው ባህል ያላቸው) ሰዎችን ደቀ መዝሙር እንድናደርግ እኛን ጠርቶናል። ይህ ሲባል ግን እነሱን የምዕራባውያን ክርስቲያኖች እናደርጋቸዋለን ማለት አይደለም። በሁሉም ባህል ውስጥ ጠቃሚና ጎጂ ነገሮች አሉ። ሁላችን ከምዕራብም እንሁን ከምስራቅ በእኛ ባህል ውስጥ በማይገቡን ነገሮች ላይ የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን እንዲወጣበት ልንፈቅድ ይገባል። ለምሳሌ፣ የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሚሆነው የምስራቃውያንን ልብስ መልበስ ወይስ የምዕራባውያንን? መብላትስ ያለብን በእጃችን ነው ወይስ በቢላና ሹካ? ስንጸልይስ የእጆቻችን መዳፎችን በአንድነት ወደላይ ዘርግተን መሆን አለበት? ዋጋ መስጠት ያለብን ለግላችን ወይስ ለጋራ ለሆነ ነገር? አትኩሮታችንስ በእኛ ቤተሰብ ላይ ብቻ ነው መሆን ያለበት ወይስ ለዘመድ አዝማዶቻችን በሙሉ ግድ ሊለን ይገባል? እግዚአብሔር ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ጋር የባህል ልዩነትን ይቀበላል፣ እና ከእነሱም በአንዳንዶቹ ውስጥ መልካም ነገሮች እንዳሉ ከእስልምና ከመጡ አማኞች መማር እንችላለን።

ይሁን እንጂ በሰው ኃጢያት ምክንያት እነዚህ የባህል መገለጫዎች በተበላሹ ማንኛውም ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ይሞግታቸዋል። ደቀ መዝሙርነት ታማኝነትን ከክበር በላይ ዋጋ ሰጥጠን መማርን፣ የበደሉንን ይቅር ማለትን፣ ለተቃራኒ ጾታ ትክክለኛ አመለካከት መያዝን፣ በውሳኔ ሁሉ እግዚአብሔርን ማስቀደም እና የመሳሰሉትን ያካትታል። እነዚህ እና ሌሎች ጉዳዮች በግል ከመጣንበት እና ከባህል ጥምረት የሚመነጭ ነው። ለጓደኞችህ የሚመጥን ጉዳይ ማግኘት የምትችለው እንዴት ነው? ይህም ከእነሱ ጋር ጊዜን በመውሰድ፣ እነሱን በመስማት እና ለእነሱ በመጸለይ የሚሆን ነው። ስለራሳቸው አስተዳደግ እና የቤተሰብ ሕይወት ጠይቃቸው። ሁሉም ግለሰቦች የተለያዩ መሆናቸውን አስታውስ። ስለዚህ በመጠየቅ ለመረዳት ሞክር፡

በብዙ የሙስሊሞች ባህል ውስጥ በርካታ የጋራ የሆኑ ነገሮች አሉ። እንደሚለያዩም ግን አስታውስ፣ ፓኪስታኖች፣ ኢራኖች እና አረቦች አንድ ዓይነት አይደሉም! በእነዚህም ባህል ውስጥ እንኳን በተለያዩ ብሔረሰቦች እና የማህበረሰብ መደብ መካከል ልዩነት አለ። ስለዚህ ጓደኛህን ስላደገበት ባህል፣ ምን እንደሚወዱ እና ምን እንደሚጠሉ ጠይቀው። አንዳንድ ጊዜ ክርስቶስን ከተቀበሉ በኋላ የቀድሞ ባህላቸውን የሚቃወሙ አሉ። ነገር ግን ዘላቂ ስነልቦናዊ ጤንነታቸው እንዲጠበቅ የቀደሞ ባህላቸውን በአንድነት ከመጣል ይልቅ አንዳንዶቹን ከአዲሱ ባህል ጋር በማጣመር በተሻለ መንገድ ሊገለገሉበት ይገባል።

'ከእስልምና የመጡ አማኞች' የሚጋፈጡትን የሕይወት ትግል ፈልግ። እነሱም ወደ ክርስቶስ ዞር ካሉ በኋላ የሚጋፈጧቸው አንዳንድ የተለመዱ ጉዳዮች፡ -

- ከቀድሞ ቤታቸው፣ ቤተሰባቸው እና ባህላቸው ለቆ መውጣት። ይህም ወደ ጥልቅ ብቸኝነት እና የማንነት ጥያቄ ሊመራ ይችላል።
- የቤተሰባቸው አባላት ያሳድዷቸዋል። ይህም እጅግ ወደ ሚነካ የመጣል ስሜት ሊመራ ይችላል።
- በቀድሞ ማህበረሰባቸው እፍረትን ይከናነባሉ።
- ሰዎችን ተከታይ ለማድረግ ግልጽ መዋቅር ከሚሰጠው እስልምና ጋር ሲወዳደር፣ የክርስትና እምነት የመዋቅር ችግር አለበት።
- እነሱ ቀድሞ ከለመዱት ጋር ሲወዳደር በክርስቶስ ተከታዮች መካከል ጠንካራ ማህበረሰብ አይታይም።

እነዚህም ሰዎች በምዕራባውያን አካባቢ ባንዳንድ ሁኔታዎች ከሚገጥማቸው ተግዳሮት በስተቀር የሚጋፈጡት ችግር አነስተኛ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡ አንድ ስደተኛ ሙስሊም በምዕራቡ ዓለም የክርስቶስ ተከታይ ሲሆን፣ በአንድ ጊዜ ከሁለት የማንነት ሽግግሮች ጋር አብሮ ሊሄድ ይገባል ይህም አንዱ ከስደተኝነት ጥያቄው የሚመጣ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከመዳኑ ጋር የተያያዘ ነው።

የና ተከተለኝ መጽሐፍ በእነዚህም ጉዳዮች ምክንያት፣ በማንነት ጥያቄ ላይ ልዩ ትኩረት ለማድረግ በ1ኛ ጴጥሮስ ላይ ሃሳቡን ያዳብራል። እኛ በእግዚአብሔር የተመረጥን ሕዝብ፣ ለእሱ የተለየን እና እርስ በርሳችን በክርስቶስ የተሳሰርን መሆናችንን ያስተምረናል።

ለዚህ ትምህርት ስኬት የሰዎችን ታሪክ መረዳት ቁልፍ ነገር ነው። ይህም አንተ አንደ አማካሪ ያ ቀድሞ ሙስሊም የነበረ ሰው ኢየሱስን በመከተሉ ያለፈበትን ብዙ ደስታ እና ችግሮች እንድትረዳ ያስችልሃል። ይህ በመማሪያ መጽሐፉ እና ደቀ መዝሙር እያደረከው ባለው ተማሪ ሕይወት መካከል ግንኙነት እንድትፈጥር ይረዳሃል። ከዚህም በተጨማሪ፣ መጽሐፉ ብዙ ጊዜ በሌሎች የደቀ መዝሙር መርጃ መጽሐፍት ላይ የማናያቸው እንደ ስደት ያሉ ርዕሶች ላይ ለምን እንዳተኮረ ለመገንዘብ ይረዳሃል። ከውይይት በፊት ወይም በኋላ የሚኖረው የሻይ ቡና ጊዜ ከተማሪዎች ጋር የሚኖርህን ወዳጅነት እና አመኔታ በእውነት ሊያዳብረው ስለሚችል፣ እነሱም ታሪካቸውን ለማካፈል ይችላሉ።

በመጨረሻም፣ ይህ ሁሉ ስሌሎች ማሰብ ነው። ፍቅር ትልቅ ተጽህኖ ያመጣል። ፍቅር በርካታ የባህል ስህተቶችን ይሸፍናል! ፍቅር ጓደኛህ ገራ በተጋባ እና በተጎዳ ጊዜ ለእሱ መገኘት ነው። ይህም ሲባል እነሱ ቤተሰባቸውን ባጡ ጊዜ ለእነሱ እንክብካቤ ማድረግ ማለት ነው። እነሱንም ደንብን በተከተለ የኢሜል እና የቀጠሮ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን፣

በስልክ እና በአጭር የጽሑፍ መልዕክት እነሱን ማግኘት ነው። አንድ ከእስልምና የመጣ አማኝ እንዲህ ብሏል፣ "ኢየሱስን ለመከተል ብዬ የገዛ ቤተሰቤን ተውኩ፣ በምትኩ ግን ያገኘሁት ነገር ቢኖር ስብሰባ ብቻ ነው!"

ክርስቲያኖችን በማስታጠቅ ከእስልምና የመጡ አማኞችን ለመንከባከብ እና ደቀ መዝሙር ለማድረግ የሚረዱ ብዙ ጽሑፎች እና ስልጠናዎች ቀስ በቀስ በሽ እንደሚሆኑ ተስፋ ይደረጋል። ይህም በምዕራቡ ዓለም ይበልጥ አግባብነት ያለው ነው። በዚህም ጉዳይ መረጃን ለማግኘት በኤሜል አድርሻችን መልዕክትህን ላክልን። comefollowmecourse@gmail.com

**ለአንተ ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትምህርቶች**

***በመጀመሪያ ወዳጅነት*** ስድስት ክፍሎች ያሉት ዲቪዲ እና ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ወዳጅ በመሆን ለእነሱም ወንጌልን መናገር እንዲጀምሩ ልበ-ሙሉነትን እና ክህሎትን ለማግኘት የሚረዳ ነው። ይህም ትምህርት ስለ እስልምና ምንም ግንዛቤ ለሌላቸው፣ ስለ ሙስሊሞች መሠረታዊ ዕውቀትን እየሰጠ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል፤ በና ተከተለኝ ትምህርት ውስጥ ላሉም ጠቃሚ ነው። friendshipfirst.org ተመልከት።

**ቤተሰቡን መቀላቀል** ስድስት ክፍሎች ያሉት ዲቪዲ እና ከእስልምና የመጡ አማኞችን ክርስቲያኖች እንኳን ደህና መጡ እንዲሏቸው፣ እንዲረዷቸው እና ከእነሱ እንዲማሩ ለማገዝ የተዘጋጀ የመወያያ ትምህርት ነው። የትምህርቱም ይዘት በቁጥር 25 ከሚሆኑ ከእስልምና ከመጡ አማኞች እና ልምድ ያላቸው አማካሪዎች በቪድዮ ከተቀረጸ ቃለ ምልልስ የተወሰደ ነው። እያንዳንዱ ትምህርት አልፎ ወደ ሚቀጥለው ከመሄዱ በፊት በተግባር የመማር እንቅስቃሴዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ። በ joiningthefamily.org ላይ ይህን በይበልጥ ከማስታወቂያ አጭር ቪድዮ ጋር ተመልከት።

# የሙስሊም ቃላት እና ባህል ነክ ጉዳዮች

## የሙስሊም ቃላት አጠቃቀም ገደቦች

ተማሪዎች አዲስ ሃሳብን እንዲረዱ፣ ከእነሱ የቀድሞ ሃሳቦች እንደ ድልድይ መጀመር የሚረዳ ሊሆን ይችላል። ይህም እነሱ አዲሱን ከድሮው ጋር ለማወዳደር እና ለማነጻጸር ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ክርስቲያናዊ መልዕክታቸውን ለሙስሊም ጓደኞቻቸው ስሜት ሊሰጥ በሚችል እና እንግዳ ነገር በማይሆንበት መልኩ ለመግለጽ ይረዳል።

ስለዚህ ይህ ትምህርት በተወሰነ ደረጃ ጥቂት የሙስሊም ቃላትን ለመነሻነት እና እነሱንም በክርስቲያናዊ ትምህርት ከለመዱት ዓለም ወደ አዲሱ ዓለም ለማምጣት እንደ ድልድይ ይጠቀማል። ለምሳሌ፥ ስለክርስቶስ ሸሪያ (ህግ) በምናወራበት ጊዜ፣ ተማሪዎች እንደ ሙስሊም ቀድሞ የነበራቸውን ሸሪያ እዲገልጹ እና ክርስቶስን እንደ ጌታ የታዘዙበት አዲስ መንገድ የተለየ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል።

## አጭር መዝገበ ቃላት

የሚከተሉት የአረቢኛ ቃላት በዚህ ትምህርት ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነሱንም ያለምን ስነ-ልሳናዊ ጥናት እና መሠረታዊ ፍቺ ተዛምዶ አስቀምጠናቸዋል። በተመሳሳይ መጻህፍት ላይ ወስብስብ ፊደሎች እና ትርጓሜዎች ሊኖሩ ይችላሉ። መስቀል እና ጨረቃ በኮሊን ቻፕማን፣ በመጀመሪያ በስቲቭ ቤል የተጻፈውን ከክርስቲያኖች እይታ አንጻር ከእስልምና ጋር ጥሩ ትውውቅ ማድረግ ወዳጅነትን ያካተተ ነው የሚለውን ማየት ይቻላል።

| | |
|---|---|
| ዱአ (ም. 5) | ግለ ጸሎት |
| ሃጅ (ም.20) | መንፈሳዊ ጉዞ |
| ሃላል (ም. 15) | ንጹህ /የሚፈቀድ |
| ኢንጂል (ም. 1) | ወንጌል |
| ጂኒ (ም. 18) | መናፍስት |
| ካፊር (ም.2) | የማያምን |
| ካሊማ (ም. 1) | ለሸአዳ የሚጠቀሙበት 'ቃል' |
| ሙርታድ (ም. 2) | እስልምናን የካደ ሰው |
| ጀነት (ም. 1፣ 9፣ 20) | ገነት |
| ካባ (ም. 20) | ለሙስሊሞች በምድር ላይ የጸሎት መአከል የሆነ - መካ |
| ሰላት (ም. 5) | በሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ ጊዜ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ጸሎት |
| ፀዋም (ም. 17) | በረመዳን ወር ውስጥ በሙስሊሞች የሚደረግ ፆም |
| ሸሃዳ (ም 13፣20) | የእምነት እወጃ (ምስክር)። "አላህ አንድ ነው፣ መልዕክተኛውም ደግሞ ሙሐመድ ነው" የሙስሊሞች ዋንኛ የእምነት እውጃ ነው። |
| ሸሪያ (ም. 17) | ሃይማኖታዊ ህግ |
| ሽርክ (ም. 3) | አንድ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ማያያዝ፣ ጣዖት |
| ሱና (ም.17) | የህይወት ምሳሌ (ይህ ለሙስሊሞች የሙሐመድ ምሳሌነት ነው) |
| ተውራት (ም. 4) | የሙሴ መጽሐፍት፣ ፔንታተክ |
| ኡማ (ም. 7፣ 14) | ዓለም አቀፋ የሙስሊም አማኝ ማህበረሰብ |
| ዘቡር (ም. 6) | መዝሙር |
| ዘካት (ም. 17) | የሙስሊሞች የግዴታ ምጽዋት |

'አምስቱ ምሰሶዎች'፣ ሸሃዳ፣ ሰላት፣ ፀዋም፣ ዘካት እና ሃጅ ሲሆኑ በም. 20 ውስጥ ተጠቅሰዋል፣ እነዚህም አምስቱ የእስልምና መሠረታዊ ተግባራት ናቸው።

**የሙስሊሞች ባህላዊ ጉዳይ**

በዚህ ትምህርት ውስጥ ብዙ ርዕሶች የተጻፉት የተወሰኑ ባህላዊ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው። እነዚህም ለእያንዳንዱ ትምህርት በአማካሪው ማስታወሻ ላይ የተገለጹ ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሉም ከእስልምና የመጡ አማኞች በእነዚህ ነገሮች በእኩል ደረጃ ተጽህኖ የለባቸውም ስለዚህ ትምህርቱን መተግበር ያለብህ ለተወሰኑ ተማሪዎች ነው፡

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

**የመማሪያ መጽሐፉ እንደ ልብ የሚገኘው በየትኛው ቋንቋ ነው?**

ትምህርቱ በአሁን ሰዓት በእንግሊዝኛ፣ በጀርመንኛ፣ በአረቢኛ፣ በዳሪኛ፣ በፋርሲ፣ በቤንጋሊ፣ በሩስያ እና በመካከለኛው እስያውያን ቋንቋ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን ከሌሎች ቋንቋዎች ደግሞ አማርኛ፣ ኩርዱ እና ፓሽቱ ተካተው የትርጉም ስራው እየተካሄደ ይገኛል። ከ come-follow-me.org (ድህረ ገጽ ላይ) የእነዚህ ቋንቋዎች የቅርብ ስራ መመልከት እና በሽያጭ ላይ የሚገኙትን መግዛት ይቻላል።

**የመማሪያ መጽሐፉን በተለያዩ ሀገሮች ማግኘት የሚቻለው እንዴት ነው?**

come-follow-me.org ድህረ ገጽን በመጠቀም የአብዛኛው ቋንቋ እትም በጥያቄ ላይ በተመረኮዘ እትመት በዓለም አቀፍ ደረጃ ማግኘት (ሊጫን) ይችላል። አንዳንድ አታሚዎችም በሀገር ውስጥ ያትሙታል፣ ለምሳሌ፡ ጀርመንኛ፣ አረቢኛ እና ዳሪኛን በጀርመን ውስጥ ከ ኦሬንትረንግ፡ኤም ማግኘት ይቻላል። በዚህም ላይ የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን በድህረ ገጹ ማግኘት ይቻላል።

**ይህን ማግኘት የምንችለው በኢንተርኔት ቀጥታ ግንኙነት ላይ ነው ወይስ ከዚያው ላይ እንደሚጫን ሰነድ ሆኖ ነው?**

የመማሪያ መጽሐፉ ከምስለ-መስኮት ላይ ለመነበብ ሆኖ የተዘጋጀ ጽሑፍ አይደለም። ይሁንና ተማሪዎች ምላሻቸውን እንዲጽፉበት የተዘጋጀ እና በውይይት ጊዜ ይዘውት መጥተው ከአማካሪው ጋር በመሆን ስለትግበራው መወያየት የሚችሉበት የመልመጃ መጽሐፍ ነው። ትምህርቱንም በበለጠ ውጤታማ መንገድ ለመማር እንዲያው በቀላሉ ከማንበብ ይልቅ በንቁ የመማር ሂደት ቢሆን የተሳካ ይሆናል።

በዚህም ምክንያት የመማሪያ መጽሐፉን በቀጥታ ከኢንተርኔት ላይ የሚገኝ ለማድረግ ምንም ዓይነት ዕቅድ የለም። በኋላ ላይ ግን ሊጻፍበት የሚችል 'ታብሌት' ጥቅም ላይ እንዲውል ከግንዛቤ ውስጥ ልንከተው እንችላለን። ይሁን እንጂ ይህ የአማካሪው መመሪያን ያለምንም ክፍያ በድህረ ገጾችን ላይ ማግኘት ይቻላል።

ትምህርቱ ማንበብ እና መጻፍ ለማይችሉ ተማሪዎች የሚመች ነው?

በአንድ በኩል፣ የትምህርቱ ቁልፍ ክፍል የወይይቱ ጊዜ ስለሆነ የመማሪያው ዘዴ አንደበታዊ ነው። ተማሪዎች የቀለም ትምህርት ያልተማሩ ቢሆኑም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፣ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን ስዕሎች መወያየት እና ተግባራዊ ስራውን ማከናወን ይችላሉ።

ይሁን እንጂ የቤት ውስጥ ጥናት የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎትን ይጠይቃል። በቀላሉ ወይም በአጠቃላይ ማንበብ የማይችል ማንኛውም ተማሪ፣ እነዚህን መመሪያዎች ይከተል፡

- ለእነዚህ ሰዎች በተናጠል፣ ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ የእነሱ ረዳት የሚሆን ፈልግ። በቀላሉ ወይም በአጠቃላይ የማያነበው ሰው የትምህርቱን ዋና ሃሳብ መረዳት እንዲችል በመጀመሪያ ትምህርቱን በአንድነት በማየት ያግዙታል። በሰብሰባ ጊዜም አንድ ላይ በመቀመጥ፣ ረዳቱ በመጽሐፍ ውስጥ ትክክለኛውን ቦታ ወይም ስዕል እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ይህ ረዳት የቤተሰብ አባል ወይም ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል።

- በቡድኑ ውስጥ ያሉ ማንበብ የማይችሉ ሰዎች ልክ ማንበብ እንደሚችሉት ሁሉ በርካታ የሕይወት ልምድ እንዳላቸው ልናስታውስ ይገባል። የሚሰጡትም አስተያየት ዋጋ ያለው ነው። ሁሉንም የቡድን አባላት ተጠቃሚ ለማድረግ እነሱንም በውይይት ጊዜ የመሳተፍ እኩል ዕድል እንዳላቸው አረጋግጥ።

**ትምህርቱ በቀጥታ ስለእስልምና ይናገራልን?**

የመማሪያ መጽሐፉ ስለእስልምና በቀጥታ አይናገርም። ይህም በከፊል ለደህንነት ሲባል የተደረገ ነው፣ በመሠረቱ መጽሐፉ በመጀመሪያ ጥብቅ በሆኑ የሙስሊም ሀገሮች ውስጥ ላሉ አማኞች የተጻፈ ነበር፣ በዚያም ስለእስልምና ይናገራል ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውም በህትመት ያለ ነገር እነሱን አደጋ ላይ ሊጥላቸው ይችላል (ይህ በምዕራቡ ዓለም እምብዛም ችግር የለውም)። ይህም ትኩረቱ እስልምና ላይ ሳይሆን ኢየሱስ እና የእሱ ትምህርት ላይ ስለነበረ ነው። ይሁን እንጂ፣ ትምህርቱ ከእስልምና በመጡ የክርስቶስ ተከታዮች ላይ ለሚነሱ ጉዳዮች መፍትኄ ለማስቀመጥ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ነው። 'የሙስሊም ቃላት እና ባህል ነክ ጉዳዮች' በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ ተማሪዎችን ወደ አዲሱ የክርስቲያን ቃላት ትርጓሜ ለማምጣት የሙስሊም ቃላትን እንደ ድልድይ የመጠቀም ውስንነት አለ።

# አስተያየት ቢሰጡን

ይህንን ትምህርት በመጠቀም ዋጋ ያለው አስተያየታቸውን ለሰጡን ብዙ ሰዎች ምስጋናችን የላቀ ነው፣ እኛም በዚህ እርምት በተደረገበት የአማካሪው መመሪያ ሁለተኛ እትም ላይ አብዛኛውን አስተያየት አስቀምጠናል። ለቀጣዩ እትም መሻሻል ይረዳን ዘንድ አሁንም ሌሎች አስተያየቶችን እና ሃሳቦችን እንቀበላለን። ከዚህ በታች አስተያየት እንዲሰጡበት ካቀረብናቸው ጥያቄዎች ውስጥ ማንኛውንም ነጻ ሆነው ቢመልሱ እና ለእኛ ኢሜል ቢያደርጉልን ብለን በአክብሮት እንጠይቃለን።

1. መሻሻል ያለባቸው የመወያያ ጥያቄዎች የትኞቹ ናቸው እና እንዴት?
2. ሊሻሻል ወይም ሊጨመር የሚችለው 'የባህል መገለጫ' የትኛው ነው?
3. በማንኛውም ርዕስ ጉዳይ በዚህ መመሪያ ላይ መጨመር ያለባቸው መመሪያዎች አሉ?
4. ከዚህ ትምህርት ጋር አብሮ መሄድ ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ እትም የትኛው ነው? (በእርግጥ በአማርኛ ቋንቋ ብዙ አማራጭ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች የሉም)
5. ለትምህርቱ ቢሆኑ የምትላቸው አጫጭር ፊልሞች ወይም የመማሪያ ተግባራት ምንድናቸው?
6. ለሌሎች የዚህ ዓይነት ትምህርቶች ቢካተቱ የምትላቸው፣ ከሙስሊም ባህል የሆኑ ምሳሌዎች ወይም ከእስልምና በመጡ የክርስቶስ ተከታዮች ላይ የተደረገ አጫጭር ጥናቶች ምንድናቸው?

እባክዎ አስተያየትዎን በኢሜል አድራሻችን [comefollowmecourse@gmail.com](mailto:comefollowmecourse@gmail.com) ላይ ይላኩልን። ስለትብብርዎ እናመሰግናለን!

**ቲም ግሪን**

comefollowmecourse@gmail.com

Come-follow-me.org

Tim Green

# ባህላዊ ፍንጮች

የዚያን ሳምንትትምህርት ሲያዘጋጁ ለእያንዳንዱ ትምህርት ባህላዊ ፍንጮችን ያንብቡ ፣ እነዚህ የተጻፉት ስለ ሙስሊም ባህል ውስን ግንዛቤ ያለቸው ለነበሩት እና ለእያንዳንዱ ሳምንት ትምህርት ዳራ በመስጠት ረገድም አስፈላጊ ስለሆኑ ነው ።

# ትምህርት አንድ

## ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) ጋር ለመግባባት የመነሻ ነጥቦች

የዚህ ትምህርት መነሻ-ነጥብ በሙስሊምና በክርስቶስ ተከታይ መከከል የተደረገ ውይይት ነው። የዚህ ሙስሊሞች አመለካከት የተለመደ ቢሆንም ሁሉም ሙስሊሞች አንድ አይደሉም። 'ና ተከተለኝ' የተዘጋጀው ቀደም ሲል የክርስቶስ ተከታዮች ለሆኑ ሰዎች ነው። ትምህርት (፩) አንድ ግን ወደ እምነት የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ያብራራል ምክንያቱም፦

- ይህም እርስዎ አማካሪውን የተማሪዎን መንፈሳዊ ግንዛቤ ልክ ለማጣራት ይረዳዎታል።
- ከዚህ ቀደም ክርስቶስን ለመቀበል ያልጸለየ ማንኛውም ሰው ይህን የማድረግ እድል አለው።
- ክርስቶስን እንደግል አዳኙ አድርጎ ለመቀበል ለሚፈልግ ሙስሊም ቀላል የማብራሪያ መንገድ ይሰጣል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ የተገለፁት የእምነት እርምጃዎች በምዕራባውያን አቀራረቦች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ከማይገለው 'የክርስቶስ ማህበረሰብ ጋር ስለመቀላቀል' ከሚደረገው ከመጨረሻው የወንጌል እርምጃ በስተቀር በትክክለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ከሙስሊሞች ለሚመጡ ምእመናን ያለ ባልንጀሮቻቸው በሕይወት መቆየት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ለእነሱ፣ 'የክርስቶስ ማኅበረሰብ' የተደራጀ ቤተ ክርስቲያን፣ መደበኛ ያልሆነ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) ቡድን ወይም ከሌላ አማኝ ጋር በድብቅ የሚገናኙበት ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ አንድ ዓይነት ጓደኝነት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህን በትምህርት 7 ላይ የበለጠ እናጠናዋለን።

ሙስሊሞች ኢየሱስን ለመከተል ምን ያህል ከፍተኛ ዋጋ እንደሚከፍሉ መረዳት አስፈላጊ ነው ። ይሁን እንጂ ከሙስሊሞች የመጡ አንዳንድ አማኞች ይህን ጉዳይ ከመጠን በላይ ማጉላቱ ተገቢ እንዳልሆነ ይሰማቸዋል። ጥያቄ 13 ያን ዋጋ የሚገልጽ ቢሆንም ጥያቄ 14 ይህ ዋጋ እንዳለው በግልጽ ያሳያል ። እነዚህን እውነቶች ከተማሪው ሁኔታ ጋር በሚስማማ መንገድ እንዴት ሚዛናዊ ማድረግ እንደሚቻል የእግዚአብሔርን ምሪት ጠይቁ።

# ትምህርት ሁለት

## ጂሃድ (ትግል)

ምዕራባውያን 'ጂሃድ' የሚለውን ቃል ሲሰሙ ብዙውን ጊዜ በዜና ላይ ስለ ሃይማኖታዊ ጽንፈኞች ሲነገር የሚሰሟቸውን ያስባሉ። ነገር ግን ጂሃድ የሚለው የአረብኛ ቃል 'ትግል' ማለት ብቻ ነው። በእስልምና ውስጥ በቴክኒክ ደረጃ 'አነስተኛ ጂሃድ' ተብሎ የሚጠራውን የጦር መሣሪያ ግጭትን ያካትታል። <<ታላቁ ጂሃድ>> ለአላህ የስነ ምግባር መስፈርቶች ራስን ለማስገዛት የሚደረገው ትግል ነው። ከኃጢአት ጋር ከምናደርገው 'መንፈሳዊ ውጊያ' ጋር ተመሳሳይነት ያለው እሳቤ ነው። በዚህ መንገድ ማብራሪያ መስጠቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ ለተማረው ሰው አስተሳሰብ ትኩረት ስጥ። ጂሃድ የሚለው ቃል ለእነርሱ ሃይማኖታዊ ጽንፈኝነትን የሚያመለክት ከሆነ ያን
ንጽጽር አታድርጉት።

## የጸሎት አቋቋም

በ20ኛው ጥያቄ በስዕሉ ላይ እንደተገለጸው ላይ በጸሎት ጊዜ እጆች ወደ ይገለበጣሉ እንጂ እርስ በርስ አይጣበቁም። ክርስቲያኖች አብዛኛውን ጊዜ ሲፀልዩ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው፣ ዓይናቸውን የሚጨፍኑትና በእጃቸው የሚጨብጡበት ለምን እንደሆነ ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ? ምንም ስህተት የለውም ፤ ይሁን እንጂ ቅዱሳን ጽሑፎች በምንጸልይበት ጊዜ እንዲህ እንድናደርግ አያዝዙንም ፤ እንዲያውም የበርካታ አቋሞች ምሳሌዎችን ይዟል ። ሙስሊሞች ምእመናንን መዳፋቸውን ወደላይ ወደ አላህ በመክፈት/በመዘርጋት ይፀልያሉ። የእናንተ ምእምናንም በዚህ መንገድ የተለማመዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ወደ እግዚአብሄር እንዴት በባዶ እጅ እንደመጣን ለማሳየት ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል ። ከእርሱ ምህረትን እንደምንለምን የሚያሳይ ጠቃሚ መንገድ ሊሆን ይችላል። የሚፈልጉት ከሆነ ቀደም ሲል በዚህ መንገድ ይጸልዩ እንደሆነና የኢየሱስ ተከታይ ከሆኑም በኋላም በዚህ መልኩ መጸለይ ይፈልጉ እንደሆነና እንዳልሆነ ተማሪዎን ይጠይቁ።

# ትምህርት ሦስት

## እግዚአብሔርን አባት ብሎ መጥራት

ለሙስሊሞች አላህ (ሱ.ወ.) ፈጽሞ የላቀና መለኮትነቱንም ለማንም አያጋራም። ለእነሱ ሽርክ የሚለው የአረብኛ ቃል ማንኛውንም ፍጡር ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ማዛመድ ማለት ነው። ለሙስሊሞቹ አባትነት ከጾታ ግንኙነት ጋር የተያያዘ የሰው ጽንስ ሐሳብ ነው ብለው ያምናሉ። ስለዚህ አላህን 'አባት' ብሎ መጥራት ሽርክ (ማጋራት) ይሆናል ። ነገር ግን እኛ እግዚአብሄርን 'አባት' ስንለው ወደእኛ መቅረቡንእና በክርስቶስ በኩል ከእኛ ጋር ሊኖረው የሚፈልገውን ግንኙነት እያገላን ነው እንጂ እንደእኛ ሰው መሆኑን አያመለክትም። ይህ ተጨማሪ በትምህርት ሦስት(3) ተብራርቷል ።

## ወደ እግዚአብሔር መቅረብ

ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች አላህን ሩቅ ና ሊደረስበት የማይችል እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል። ምንም እንኳን 'በአንገታችን ውስጥ ካለው የደም ሥር ይልቅ ይቀርበናል ' ብለው ቢናገሩም ይህ ማለት በሁለት መንገድ የሐሳብ ልውውጥ ማድረግ ማለት ግን አይደለም። ከአላህ ጋር የጠበቀ ዝምድና/ቅርበት መመሥረት የሚለው አስተሳሰብ ለአብዛኛዎቹ ሙስሊሞች እንግዳ ነው። የሱፊ እስልምና ምስረታ ግን ከዚህ ሃሳብ ጋር የሚቀራረብ ቢሆንም ። የክርስትናው የእግዚአብሄር ሃሳብ በፍጹም የተለየ ነው – በእርግጥ እግዚአብሔር እንድንሆድን ፈልጓል። <<አባ>> ብለን እንድንጠራውም ጋብዞናል።

# ትምህርት አራት

## ሥላሴን መለማመድ/ ማወቅ

ሙስሊሞች መለኮታዊ ባሕርይውን ሙሉ በሙሉ ሳይረዱ ወይም ይህ በሥላሴ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ሙሉ በሙሉ ሳይረዱ ኢየሱስ ክርስቶስን ለቀበሉ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ ሊረዱት ይፈልጋሉ, ስለዚህ ትምህርት አራት (4) ስለ ሦስት እግዚአብሔር ትንሽ ያብራራል, ይህ የመግቢያ ትምህርት ብቻ እንደመሆኑ መጠን ሙሉ ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ. ዋናው ትኩረት ሙሉ በሙሉ ባናስተውለውም እንኳ እግዚአብሄር አብን፣ እግዚአብሄርን ወልድን እና እግዚአብሄርን መንፈስ ቅዱስን በህይወታችን እንዴት እንደምንለማመደው ነው። አንዳንድ ከእስልምና እምነትየመጡ ተከታዮች በከፊል ስለ ሥላሴ አጥጋቢ ማብራሪያ ስላልደረሳቸው ኢየሱስን ከመከተል ወደኋላ ተመልሰዋል። ስለሆንም በጣም አስፈላጊ የሆነ ርዕስ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ይህን አስተምህሮ ጥቃት ለሚሰነዝሩባቸው እስላሞችን ለመከላከል በቀላሉ የሚያስረዱበት መንገድ ያስፈልጋቸዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ ልናረካ አንችልም ፤ አንዳንዴም ለሥነ ምግባር ውድቀት ሰበብ ይሆናል ። አማካሪ እንደመሆንዎ መጠን በዚህ ጊዜ ከመምህርዎ ጋር በዚህ ውይይት ውስጥ ምን ያህል ጥልቅ ውይይት ማድረግ እንዳለብህ ማስተዋል ያስፈልግሃል። መንፈስ ቅዱስ ወደ አብ እንድንቀርብ እና ቀስ በቀስ እንደ ኢየሱስ እንድንሆን በማድረግ እግዚአብሄርን እውን እንዲሆን ያደርግልናል። ይህ ትምህርት በእስልምና ውስጥ ለእራስ ጥረት ትኩረት በመስጠቱ እግዚአብሄር በሚፈልገው መንገድ መኖር የምንችለው በመንፈስ ሃይል ብቻ መሆኑን ያጎላል። ይህ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) በጣም አስፈላጊ ነው ። በዚህ ትምህርት መሰረት በየቀኑ በእግዚአብሄር መንፈስ መሞላት ያስፈልገናል። ህይወታችንን ከጊዜ ወደ ጊዜ በብዙው እንዲቆጣጠርልን እንለምናለን። ይህ ትምህርት በጴንጤቆስጤ መሠረተ ትምህርቶች ላይ ውዝግብ እንዳይፈጠር ለማድረግ ይጥራል።

## መስዋዕትነትና ቃል ኪዳን

ምንም እንኳ ቁርአንና ሃዲስ መስዋዕት ኃጢአትን እንደሚያስወግድ በይፋ ባያስተምሩም በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው እስልምና ግን ብዙውን ጊዜ መስዋዕትነት በሆነ መንገድ ኃጢአትን እንደሚያስወግድ ያስተምራል። ይህ በሙስሊሞች የኢድ አልአድሃ ድግስ ላይ ተገልጿል። ሙስሊሞች ኢብራሂም ልጁን መስዋዕት ሊያደርገው የቀረበበትንያስታውሱ ፤ (ከዘፍጥረት 22 ጋር አወዳድር) ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሙስሊሞች መሥዋዕት ኃጢአትን ያስወግዳል ብለው ቢያስቡም እግዚአብሔር ከመስዋዕቱ ጋር ካደረገው ቃል ኪዳን ጋር አይዛመዱም።

በአንጻሩ ግን በዘፀአት 24 የእንስሳት መሥዋዕት ኃጢአትን ለማስወገድ ብቻ አልነበረም፤ የእግዚአብሔር ሕዝቦች 'ቃል ኪዳን' ብለን በምንጠራው ጠንካራ ትስስር ከእሱ ጋር እንደታሰሩ የሚያሳይ ምልክትና ማኅተም ነበር። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ አዲሱን ቃል ኪዳን በደሙ አተመው። ምንም እንኳን የክርስቶስ መስዋዕትነት ካለፈው ኃጢያት ነፃ ቢያወጣንም፣ እንደገና ሄደን ለኃጢአት ነፃ ነን ማለት እንዳልሆነ ተማሪዎችዎ ሊረዱት ይገባል! ከዚህ ይልቅ ከእሱ ጋር ጠንክር ያለ ቅርበት አለን። ይህን በተጨማሪ በትምህርት 15, ከጥያቄዎች 17-22 ላይ እናጠናለን።

## ደቀመዝሙርነት በሱፊ አስተሳሰብ ውስጥ

የሱፊ ተግባራት በበርካታ ሙስሊም አገሮች ውስጥ (ሁሉም አይደለም) የተስፋፋ ነው :: ሱፊን በጥብቅ የሚከተሉ ሰዎች በአረብኛ 'ሙርሺድ ' ወይም በኡሮሞ ቋንቋ 'ፒር ' የተባለ መንፈሳዊ መሪ/መምህር አላቸው ። ይህ ሰው በሁሉም ነገር እሱን ለመታዘዝ መሐላ በሚፈጽሙት 'ደቀ መዛሙርቱ' ላይ ጠንካራ ሥልጣን አለው።
እንደ ተማሪዎችዎ መረዳት ልክ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን 'ሙርሺድ' ብሎ ለመጥራት ባይወዱም ይህ ንፅፅር እኛ ኢየሱስ ክርስቶስን ስንከተል ምን ያህል ጠንክር ያለ ቁርኝ እንዳለን እንዲገነዘቡ ሊረዳቸው ይችላል።

## ሙስሊሞች፣ መንፈስ ቅዱስ እና ገብርኤል

በዚህ የጥናት መፅሐፍ ጥያቄ 8 መልሱን ሀ) እንደሆነ ይጠቅሳል ምክንያቱም ብዙ ሙስሊሞች መንፈስ ቅዱስ የመልአኩ ገብርኤል (በአረብኛው ጂብሪል) ስም ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው።

# ትምህርት አምስት

## የጸሎት ሥነ-መለኮት

በምዕራፍ 3 ውስጥ ክርስቲያናዊው እግዚአብሔርን እንደ አባት በተቀራረበ እና በግል መንገድ የማወቅ ፅንሰ-ሀሳብ ለሙስሊሞች እንግዳ ነገር መሆኑን አስተውለናል ። ክርስቲያኖች ጸሎትን እንደ ጥልቅ ዝምድና ስለሚመለከቱት ይህ ጸሎትንም ይነካል ። ለሙስሊሞች የግዴታ የአምልኮ ሥርዓቶች በዋናነት ቀኑን ሙሉ አላህን ለማስታወስ እና የእርሱን ሞገስ ለማግኘት እንደ አንድ መንገድ ይታያልና ። ምንም እንኳን ሙስሊሞች እንዲሁ (<ዱዓ> የሚባል) መደበኛ ያልሆነ ጸሎት ሲኖራቸው አንዳንዶቹ የተወሰኑት ምስጢራዊ ማሰላሰል ቢያደርጉም የክርስቶስ ተከታዮች የሚሆኑት ግን ከዚህ በፊት ከማያውቁት ከእግዚአብሄር ጋር አዲስ ግንኙነት በማግኘታቸው ደስ ይላቸዋል ። ተማሪዎን ክርስቶስን ከመቀበላቸው በፊት እና በኋላ ስለ ፀሎት ልምምዳቸው መጠየቅ ይችላሉ ።

## የሱፊ ማሰላሰል

የሱፊ ወግ ሚስጥሮች በአንዳንድ ሙስሊሞች ባህል ውስጥ ትልቅ ተጽዕኖ ነበራቸው ። የሱፊ ቅኔዎች የሰውን ፍቅር የነፍስ እግዚአብሔርን የመፈለግ ናፍቆትን ለማስረዳት እንደ ምሳሌ ይጠቀማሉ፤ እግዚአብሔርን የሚፈልግ ሰው የወደደውን እንደሚፈልግ አፍቃሪ ነው (በክርስትና ግን በተቃራኒው ነው!) ። የሱፊ ማሰላሰል ዓላማው ምትሃታዊ የመሰለ እና የእግዚአብሔርን መገኘት እንዲሰማ የማድረግ ሁኔታን ለማሳካት ዚክር Dhikr (በአረብኛ) ወይም ዚክር Zikr (በኡርዱ) የሚባለውን የቃላት ድግግሞሽያካትታል ።

## ሙስሊሞች ፣ ጸሎት እና <ውዱእ> መንጻት

ሙስሊሞች ሁል ጊዜ የአምልኮ ሥርዓቱን ከመፈጸማቸው በፊት ውዱእ የተባለውን የተወሰነውን ስርዓተ መታጠብ ያደርጋሉ ። ይህም ወደ ጸሎት ከመመጣቱ በፊት ራስን የማፅዳት መንገድ ተደርጎ ይታያል ። ተማሪዎ (ችዎ) ኃጢአታችንን መናዘዝ እንደ መንፈሳዊ መንፃት ነው ብሎ ማሰብ ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኘው ይችላል ፣ ምንም እንኳን በእርግጥ እኛ የሚያነፃን እግዚአብሔር ራሱ እንጂ የእምነት ድርጊቱ አይደለም። ሆኖም ፣ ይህ ተመሳሳይነት ለተማሪው/ ዎቹ የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ ፣ በዚያ መንገድ መግፋት አያስፈልግም።

## የጸሎት ዝርዝር ማውጣት

በአንዳንድ የሙስሊም ሀገሮች ሳምንታዊ በዓል ስለሆነ የሚመከረው የጸሎት ዝርዝር በዓርብ ቀን ይጀምራል ። በሌሎች ቦታዎች እሑድ ነው ። ተማሪው አብሯቸው የሚኖር ከሆነ እና የኮርሱን መጽሐፍ ካወቁ ጥሩ ላይሆን ስለሚችል የሙስሊም ጓደኞችን እና የቤተሰብ አባላትን ስም መፃፍ አይመከርም ። እንዲሁም የጸሎት ርዕሶችን ለመፍጠር የሚያስችለውን እና በየቀኑ የሚቀያየር <<PolMate>> ን ጨምሮ ለስማርት ስልኮች ከሚቀርቡ አንድ ወይም የተለያዩ የጸሎት ዝርዝር መተግበሪያዎች ውስጥ አንዱን መጠቀም ይችላሉ ።

# ትምህርት ስድስት

## ሙስሊሞች እና የቅዱሳት መጻሕፍት አነሳሽነት

ሙስሊሞች ስለ ቅዱሳት መጽሑፎች ከክርስቲያኖች የተለየ ግንዛቤ አላቸው ። ለእነርሱ ፣ ቁርአን በሰማይ የተጻፈ እና በመልአኩ ገብርኤል በኩል ለመሐመድ የተገለጠ የአላህ የዘላለም ቃል ነው ። መሐመድ ገብርኤል ያዘዘውን ብቻ በትክክል በአረብኛ ፅፎታል ። ክርስቲያኖች ግን እግዚአብሔር የቅዱሳት መጻሕፍትን ለመጻፍ በመንፈስ አነሳሽነት ወይም ቃሉን 'በሰው ውስጥ እንዳስገባ' ያምናሉ ። እግዚአብሔር የሰውን የጽሑፍ ሂደት ለመለኮታዊ ዓላማው ተጠቅሞና ከስህተት አድኖ አኑሮታል ። ሙስሊሞች የአረብኛን ቁርአን ብቸኛው የአላህ ቃል አድርገው ይመለከቱታል ። ሁሉም ትርጉሞች ከዚህ ደረጃ የሚጎላቸው ናቸው ። ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ቋንቋ ሊተረጎም እንደሚችልና አሁንም የእግዚአብሔር ቃልነቱን ጠብቆ እንደሚቆይ ያምናሉ ።

አብዛኞቹ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ እንደተለወጠ ያምናሉ ። ተማሪዎ (ዎችዎ) በአስተማማኝነቱ ቢያምኑም ነገር ግን ያንን ለሙስሊም ጓደኞቻቸው ለማስረዳት አሁንም እገዛ ሊያስፈልጋቸው ይችላል ። ደግሞም ፣ የተለያዩ ትርጉሞች በቃላት ላይ ስላለው ልዩነት ወይም አብዛኛው መለኮታዊ ጥቅስ የሰዎችን እንቅስቃሴ የሚገልጸው ለምን እንደሆነ ግራ ሊጋቡ ይችላሉ።

## ታሪኮች እና የእግዚአብሔር ራስን መግለጥ

መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ - ድረስ ከፍጥረት እስከ አዲስ ፍጥረት ድረስ እንደ አንድ ታላቅ ታሪክ የተዋቀረ ነው ፡ ፡ የዚህ ታሪክ ዋና ነገር እግዚአብሔር ራሱን ወደ እኛ ስለመላኩ የሚተርክ ነው ። ቁርአን ስለ አላህ ባህሪ መግለጫዎችን እና በአላህ ደረጃዎች መሠረት ለመኖር የሚያስችሉ መመሪያዎችን ይዟል ። በአጠቃላይ የአጫጭር ታሪኮች ድብልቅ ነው ፣ ግን በቅደም ተከተል ውስጥ አይደሉም እና በእሱ ውስጥ የሚሄድ አንድ ወጥ የሆነ ትረካ የለም። እስልምና ውስጥ እግዚአብሔር አንድ

መጽሐፍ በመላክ ራሱን ገልጧል ፣ነገር ግን በክርስትና ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን በመላክ ራሱን ገልጧል ፣ እናም ይህ ራስን የመላክ ሂደት የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊው ታሪክ ነው።

# ትምህርት ሰባት

## ሁለት ልዩ ድንጋዮች

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ወደ መካ ሐጅ ለማድረግ ተጉዘዋል ፣ እዚያም የካባ ጥቁር ድንጋይ የአምልኮታቸውን ማዕከል ያሳያል። ለእኛ ግን ፣ ክርስቶስ ራሱ በእውቀታችን ማእከል ውስጥ የበለጠ የከበረ ድንጋይ እና 'የመንፈሳዊ ቤታችን' የማዕዘን ድንጋይ ነው!

## የተከፋፈለ ማንነትን መፈወስ

አንዲት ፓኪስታናዊት የእንግሊዝ ሴት በእንግሊዛዊ ማንነቷ እና በፓኪስታን ሙስሊም ማንነቷ ክፍል መካከል ስለ ማንነቷ ግራ ተጋብታ ነበር ። ወደ ክርስቶስ ስትመጣ አንድ አዲስ ማንነት አገኘሁ አለች ፣ እናም ይህ 'አስደናቂ' ነገር ነበር። ስለዚህ ጉዳይ በጣም በኃይል ለእሷ የተናገራት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አሁን ያጠናነው የ1ኛ ጴጥሮስ 2 ፡ 9-10 ነው ።

## ኡማህ (ወገን ሕዝብ)

ሙስሊሞች ኡማ ብለው የሚጠሩት ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የመሆን ጥልቅ ስሜት አላቸው ። ለእነርሱ ተስማሚው ኡማ የአላህን ሕግ (ሸሪዐ) የሚከተል ማህበረሰብ ነው እናም በንድፈ ሀሳብ በእስልምና መሪዎች (ከሊፋዎች) መተዳደር አለበት ። ከብዙ አገሮች የመጡ ሙስሊሞች በመካ ሲሰባሰቡና ሁሉም ተመሳሳይ ልብስ ለብሰው ሲወጡ ይህ ዓለም አቀፋዊ ማኅበረሰብ በዓመታዊ የሐጅ ጉዞው ወቅት በግልጽ ይታያል ። በተግባር ግን መከፋፈል እና መድልዎ (የዘር መድልዎን ጨምሮ) የእስልምናው ኡማ ከሚመኘው አንድነት በእጅጉ ያንሳል ማለት ነው ። በአንዳንድ መንገዶች ይህ በዓለም ዙሪያ ያሉ ክርስቲያኖች ሁል ጊዜ የማይኖሩትን የቤተክርስቲያኗን ዓለም አቀፋዊ ማህበረሰብ ተስማሚነት የሚመስል ነው። አንዳንድ የአረብኛ ትርጉሞች የ 1ኛ ጴጥሮስ 2: 9ን <ዑማህ> የሚለውን ቃል ለእግዚአብሄር ሕዝብ የሚጠቀሙ ሲሆን ከተማዎ (ዎችዎ) ተመሳሳይነቶች እና ልዩነቶች ጋር መወያየቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ።

## አደጋውን መመዘን

በአንዳንድ የሙስሊም ሀገሮች አማኞች አንድ ላይ ሲገናኙ አደጋ አለ ። አንዳንድ ጊዜ መረጃ ሰጭዎች እራሳቸውን አማኞች በማስመሰል ወደ አንድ ቡድን ውስጥ ዘልቀው ይገባሉ ። እነሱን ለማጋለጥ የአማኞችን ስም ፣ የመታወቂያ መረጃ እና ፎቶግራፎችን ያገኛሉ ፣ ይህ ደግሞ ብዙ ጉዳቶችን ሊያመጣ ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ አማኞች ፣ ወዲያውኑ እራሳቸውን ባያሳውቁና በዝግታ እና በጥንቃቄ እነሱን ለማወቅ ቢሞክሩ ለሁሉም ለማንም አያጋልጡምና ጥበበኞች ናቸው ። መንፈስ ቅዱስ ማንን በበለጠ ሊተማመኑባቸው እና ማንን በጥቂቱ ማመን እንዳለባቸው ያሳያቸዋል ። የቡድናቸው ማንኛውም ፎቶግራፎች እና ቪዲዮዎች ስለመኖራቸው በጣም ሊጠነቀቁ ይገባል። ሆኖም ፣ በሌላ መንገድ አደጋም አለ ። ሁሉም ሰው እንደ ማጂድ ከሆነ እና ሌሎችን ለማመን ፈቃደኛ ካልሆነ የአማኞቹ ማህበረሰብ በጭራሽ ማደግ አይችልም ። እንዲሁም የተለዩቱ አማኞች በእምነታቸው ይቀዘቅዛሉ ። በችግር ጊዜም የሚረዳቸው አይኖርም ። እናም ልጆቻቸው በጭራሽ ወደ አማኞች ማህበረሰብ ካልገቡ ወደ ቀደመው ሃይማኖት ይመለሳሉ ። አማኞች ለልጆቻቸው የወደፊት ሕይወት ጥሩውን ከፈለጉ በክርስቶስ ማህበረሰብ ውስጥ ቦታቸውን ማግኘት አለባቸው። ስለሆነም ፣ ከሌሎች የኢየሱስ ተከታዮች ጋር ከተገናኘን አደጋው ጥቂት ነው ፣ ግን ካላደረግነው የበለጠ አደጋ አለ። በምዕራቡ ዓለም ከሙስሊም እምነት ተከታዮች ወደ ቤተ ክርስቲያንን የሚቀላቀሉ አማኞች በአብዛኛው በአካላዊ አደጋ ውስጥ አይደሉም ። ነገርግን በአንዳንድ ሁኔታዎች አሁንም ልባም መሆን ይፈልጉ ይሆናል (ለምሳሌ ፣ በቤተሰቦቻቸው ላይ ሀፍረትን ላለመፍጠር) ። ምርጫቸውን መቼ እና ለማን እንደሚናገሩ መምረጥ አለባቸው ። ክርስቲያኖች ስለእነሱ ለሙስሊሞች ማውራት/ ማማት የለባቸውም ።

# ትምህርት ስምንት

## ከእ. የመ. አ.(ከእስልምና የመጡ አማኞች) እና የሙስሊሙ ማኅበረሰብ

ወደ ክርስቶስ የሚመጡ ሙስሊሞች በቀድሞ የሙስሊም ማህበረሰባቸው እና በክርስቶስ ውስጥ ባለው አዲስ ማህበረሰባቸው መካከል እንደተለያዩ/ እንደተከፋፈሉ ይሰማቸዋል ። በእስልምና ውስጥ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ትስስር በጣም ጠንካር ያለ ነው ፣ እናም ክርስቶስን የሚከተሉ ሰዎች በጣም በሚወዷቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ጎጂ የሆነ መገፋት/ ውድቀት ይገጥማቸዋል ። እነዚህን ግንኙነቶች ከጊዜ በኋላ ለማስተካከል ቢፈልጉ እንዴት ይችላሉ? እና እንደ ቀድሞው የቅርብ የሆነ አዲስ 'ቤተሰብ' በክርስቶስ ማህበረሰብ ውስጥ ያገኙትን ? እነዚህ ለአብዛኞቹ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) አንገብጋቢ

እና አሳማሚ ጥያቄዎች ናቸው ። ትምህርት 8 የክርስቶስ ተከታዮች የአሮጌ እና የአዲሱ የሁለቱ ማህበረሰቦች እንደሆኑ እና በተቻለ መጠን በሁለቱም በኩል የድርሻቸውን ለመወጣት በተቻለ መጠን መሞከር እንዳለባቸው ያስተምራል ።(ይህ ለሁሉም የመጀመሪያ ትውልድ አማኞች እውነት ነው ፣ ግን ግጭቶቹ ብዙውን ጊዜ ከሙስሊም በኩል ለሚመጡት በጣም ከባድ ናቸው።

# ትምህርት ዘጠኝ

## በስደት ላይ ያሉ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞችን) ማማከር

በምዕራቡ ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ ስለስደት የተዛባ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል ። ተጽዕኖዎቹን በዝርዝር እናስተውለው ይሆናል ወይም ልናሞቀው እንችላለን ። ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) ስደት ሲደርስባቸው በተግባርም ሆነ በስነልቦና ደረጃ በጥበብ መምከር አስፈላጊ ነው ። በተግባራዊነት ደረጃ ፣ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) እስኪረጋጉ ድረስ በትእግስት ምላሽ በመስጠት በቤተሰቦቻቸው እና በአካባቢያቸው ቢቆዩ ጥሩ ነው ። ከባድ አደጋ በሚኖርበት ሁኔታ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) ደህንነት ወደሚያገኙበት መሸሸ ብልህነት ሊሆን ይችላል ፣ ከዚያም ከጊዜ በኋላ ግን ከቤተሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት እንደገና ለማዳበር መሞከር ተገቢ ነው። በምዕራቡ ዓለም ለሚኖሩ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) የሕይወት አደጋ የተለመደ አይደለም ።
በስነልቦናዊነት ፣ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) በቤተሰቦቻቸው ሲጠሉ ምን ያህል እንደሚጎዱ እና ከዚያ በኋላ ምን ያህል እንደሚናፍቋቸው መገንዘብ አስፈላጊ ነው ። የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ ስደትን ወደ ጥሩ የማዞር ቁልፍ ገጽታ ፣ የሆነውን የእግዚአብሔርን አመለካከት ማግኘት ላይ ነው ።

# ትምህርት አሥር

## በቀል እና ይቅር ባይነት

ይህ ትምህርት በመጀመሪያ የተጻፈው 'የበቀል ሁደት' በአንድ ትውልድ ሙሉ ላይ አስከፊ ውጤት ላስከተለባት ሀገር ነበር። ምንም እንኳን ሁሉም ሙስሊሞች በቀልን የሚደግፉ ባይሆኑም ፣ በብዙ የሙስሊም ባህሎች ውስጥ ከበድ ያለ ነው ። በባህላዊ ማህበረሰቦች ውስጥ <ጠንካራ ለመምሰል> እና <ክብርን ለመመለስ> ካለው ፍላጎት ጋር ተዳምሮ በሁሉም ባህሎች ውስጥ የሚኖር ኃጢአተኛ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ብዙ ሙስሊሞች መበቀልን ተፈጥሮአዊ ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል ። ስለሆነም ጠላቶቻችንን እንድንወድ የክርስቶስን ትእዛዝ የተቀበሉ ሙስሊሞች (የዚህ ሳምንት የማስታወሻ ጥቅስ /በቃል የሚጠና) ሥር-ነቀል አዲስ ትምህርት ሆኖ ያገኙታል እናም በዚህም ምክንያት ብዙዎች ወደ እርሱ ቀርበዋል ።
ብዙ ከእ. የመ. አ. (ከእስልምና የመጡ አማኞች) በእምነታቸው ምክንያት ስላሳደዷቸው ወይም እምቢ ባሉት ላይ በልባቸው ላይ ቂምና ቁጭት ይይዛሉ (ለምሳሌ በጥያቄ 15 ውስጥ) ። በክርስቶስ ወደፊት እንዲራዱ ለማገዝ ከዚህ መላቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው ። በዚህ ትምህርት ውስጥ ርዕሱ ትኩረት የተሰጠውና እና በተደጋጋሚ በምስል የተቀመጠው ለዚህ ነው:::: የዚህ ርዕስ ውይይት ጠንካራ ስሜትን ሊለቅ ይችላል ፣ ግን ይህ ወደ ፈውስ የሚመራ ይሁን!
ጥያቄ 5 አሳዳጆቹን ይቅር በማለቱ በሞተው በኢየሱስ መካከል እና በጦር ሜዳ ጠላቶቻቸውን በመርገም ከሞቱት መሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል ። ፍንጩ በ 680 ዓ.ዓ. በካርባላ ጦርነት ላይ መሞታቸው በሺአ ሙስሊሞች በጥብቅ የሚታወሰውን እና ከክርስቶስ ሞት በተቃራኒ የቆመውን መሪ ሁሴንን ለማስታወስ ነው ። ለሺአ እስልምና ባላቸው አመለካከት ላይ በመመርኮዝ ይህንን ለተማሪዎ (ዎችዎ) መጥቀስ ተገቢ ላይሆን ይችላል ።

# ትምህርት አሥራ አንድ

## ጋብቻ በእስልምና

በሁሉም ባህሎች እንደሚሆነው በሙስሊሞች መካከልም አንዳንድ ትዳሮች እርስ በርሳቸው የሚስማሙ እና አንዳንዶቹ በግጭቶች የተሞሉ ስለሆኑ በአጠቃላይ መደምደም ከባድ ነው ።ብዙውን ጊዜ የሙስሊም የቤተሰብ ሕይወት በብዙ ገፅታዎቹ የሚሰብ ነው ፣ ምንም እንኳን የተደበቀ በደል እና የልብ ስብራት ሊኖር ይችላልም ። የእስልምና ምሁራን ስለ ጋብቻ የቁርአን ትምህርት በሚሰጡት ትርጓሜ ይለያያሉ፤ እንዲሁም አንዳንድ የወንዶች የበላይነት ባላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ከእራሱ ከቁርአኑ በበለጠ ሁኔታ ሴቶች ይጨቆናሉ ። ሆኖም ይህ ኮርስ በሙስሊም ህብረተሰቦች ውስጥ በስፋት የሚከናወኑትን ፅንሰ-ሀሳቦችን ይመለከታል ፣ ለምሳሌ ። አንድ ሰው ሚስቱን መምታት ወይም በቀላሉ ሊፈታት እንደሚችል ፣ እስከ አራት ሚስቶችን ሊያገባ ይችላል ፣ እና ሌላ ሚስት ለማግባት አንድ ትክክለኛ የሚሉት ምክንያት የመጀመሪያዋ ወንድ ልጅ ካልወለደች ነው ።፣ ምንም እንኳን እነዚህ ከባልየው ያነሱ ቢሆኑም ሚስትም በእስልምና ውስጥ መብቶች አሏት ። በመርህ ደረጃ ጋብቻቸው ከቃል ኪዳንነቱ ይልቅ የውል ዓይነት ነው ።

## አዳዲስ ምእመናን እና የሚያስከፍለውን ዋጋ መተመን

ይህ ትምህርት የተማሪዎ (ዎችዎ) የጋብቻ አስተሳሰባቸውን እንደገና እንዲመረምሩ እና የበለጠ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ እንዲገነቡ ለመርዳት ነው ። የተለመዱ የሙስሊሞች ፅንሰ-ሀሳቦች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በተቃራኒው የፊተሸሉ ፣ እና ጥያቄ 10 ሆን ተብሎ በሰፊው የታወቀ የቁርአን አንቀፅ በመጠቀም <ሴቶቻችሁ እርሻዎቻችሁ ናቸው> የሚለውን በመጠቀም እነዚህን ትኩረት ያደርጋቸዋል (ሱራ 2 ፡ 223) ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንድ ሰው ከአንዲት ሴት ጋር ተጋብቶ እስከ ዕድሜ ልክ መቆየት እና በተለይም ባል ለሚስቱ የመስዋእትነት ፍቅር የመስጠት አስፈላጊነት

የሚታይበት ነው ። ትምህርት 11 ለዚህ ሰፊ ርዕስ መጀመሪያ ብቻ ነው። እናም ተማሪዎ ቀድሞውኑ ያገባ ወይም ለጋብቻ እየተዘጋጁ ከሆኑ የበለጠ ትምህርት መስጠቱ ጥሩ ሊሆን ይችላል። ልጆችን ለማምጣት የሚፈልጉ ከሆነም በዚያ ላይ የበለጠ ውይይት ማድረጉ እንዲሁ ይሠራል ።

## እናትነት በኢስላም

በእስልምና ውስጥ እናት በጣም የተከበረች ናት ። ሙስሊም ወንዶች ለእናቶቻቸው ከፍተኛ አክብሮት እና ታማኝነት እንዲሰጡ ታዝዘዋል እናም አብዛኛውን ጊዜ ከአባት ይልቅ ከእናት ጋር የበለጠ ስሜታዊ ትስስር አለ ። እንዲሁም በተለምዶ በአብዛኛዎቹ የሙስሊም ባህሎች ውስጥ ሙሽራይቱ በትዳር ውስጥ የራሷን ወላጆች ትታ ከባለቤቷ ቤተሰቦች ጋር ትቀላቀላለች ፣ ግን ለእርሱ ‘መተው እና መያያዝ’ የለም ። ስለሆነም የእሱ ስሜታዊ ታማኝነት ከሚስቱ ይልቅ ለእናቱ ጠንካራ ሆኖ ሊቆይ ይችላል ፣ እና እናቷ ይህንን ለእሷ ጥቅም እና ለሙሽሪት ኪሳራ ሊጠቀሙበት ይችላሉ ። ይህ ትምህርት እነዚህን ጉዳዮች ይመለከታል ። ግን እነዚህ አጠቃላይ መግለጫዎች ብቻ ናቸው ፣ እና የበለጠ ምዕራባዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የጋራ የቤተሰብ ስርዓት በጣም ጠንካራ አይደለም።

# ትምህርት አሥራ ሁለት

## ክርክሮች እና እንዴት መፍታት እንደሚቻል

በሁሉም ህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ክርክሮች ያሏቸው ሲሆን የሙስሊም ማህበረሰቦችም እንዲሁ የተለዩ አይደሉም ። ከጥያቄ 7-10 ላይ የተገለጹት ሦስቱ ‘አለመግባባቶችን ለመፍታት መጥፎ መንገዶች’ በሙስሊም ማኅበራት ውስጥ ፣ በበቀል ፣ በማስወገድ ወይም በደረጃ ተዋረድ ባህላዊ እሴቶች ቅደም ተከተል የተጠናከሩ ሆነው በብዛት ይገኛሉ ። ሐሜትም ጉዳዮችን ያወሳስበዋል ። በእርግጥ እነዚህ ችግሮች በሌሎች ህብረተሰቦችም ውስጥ ይገኛሉ ።

ብዙ ሙስሊሞች ከክብር / እፍረት ባህላዊ አውዶች የሚመጡ ናቸው ። ማለትም ፣ ትክክልና ስህተት የሚለው ሀሳባቸው በአካባቢያቸው ማህበረሰብ ውስጥ ካሉበት ደረጃ ጋር በጣም የተቆራኘ ነው ። አንድ ቤተሰብ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በይፋ የሚያፍር ከሆነ በቀልን በመመለስ ክብራቸውን ማስመለስ እንደ ጽድቅ ሊሰማቸው ይችላል። በኢየሱስ ዘመን የነበረው የቅርብ ምስራቅ ባህል የእነዚህ ዝንባሌዎች ሊኖሩት ይችላል ። በምዕራቡ ዓለም ላሉት የኢየሱስ ይቅርባይነትን ማስተማር አብዛኛውን ጊዜ ከግል ደረጃ ጋር ይጋጫል ። ሆኖም ለእነዚያ የክብር / የዕፍረት ባህሎች ፣ የኢየሱስ ትእዛዝ በተለይም ለቤተሰብ ደረጃ ሊናገር ይችላል ፣ ይህም በቀል ከትውልድ እስከ ትውልድ ጠብ ሊፈጥር ይችላል ።ከእስልምና የመጡ የክርስቶስ ተከታዮች ማህበረሰብን በመቀላቀል ከመጀመሪያ ደስታ በኋላ ፣ ብዙውን ጊዜ ግጭት ያጋጥማቸዋል እናም ተስፋ ይቆርጣሉ ።በዚህ ላይ በመሥራት በመማር እና ከሌላው በኩል መውጣት ለደቀመዝሙርነታቸው እጅግ አስፈላጊ እርምጃ ነው ። ይህ አለመግባባቶችን በአጥፊ ሳይሆን ገንቢ በሆነ መንገድ እንዴት መፍታት እንደሚቻል መማርን ያጠቃልላል ። ትምህርት 12 ይህንን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚረዱ አንዳንድ ተግባራዊ እርምጃዎችን ይዘረዝራል ።

## እግዚአብሔር ስሜቶች አሉት?

በእስልምና ውስጥ ፈጣሪ ከፍጥረታቱ ውጪና ከእነሱ የተለየ ነው ። ሙስሊሞች የሰው ድርጊቶች እሱን ሊያስደስተው ወይም ሊያሳዝነው መቻሉን ፣ ወይም ህመማችን ይሰማዋል ብሎ ማመንን ይክዳሉ ፣ ምክንያቱም ይህ ዕርሱን ወደ እኛ ደረጃ እንደመጎተት ወይም በራሳችን አምሳል እንዳደረነው ይመስላል ስለሚሉ ነው ። ሆኖም ለክርስቲያኖች ፣ ትስጉት/ ስጋ መሆኑ ወደ ደረጃችን ወርዶ ህመማችንን ለመካፈል ፈቃደኛ የሆነን እግዚአብሔር ያሳያል ። ኢየሱስ ክርስቶስ ጠንካራ ስሜትን (ርህራሄን ፣ ንዴትን ፣ ደስታን ፣ ሀዘንን) ተሰምቶት ያውቃል እናም እግዚአብሔር ምን እንደ ሆነ የሚያሳይን ስዕል ይሰጠናል። ከእ. የመ. አ. ይህንን ሲገነዘቡ ህመማቸው ስለሚሰማው (ትምህርቱን 11 ፣ 18 ን ይመልከቱ) እና ኃጢአት ሲሰሩ በጣም ማዘኑ (በትምህርት 12 ላይ እንዳለው) ለእግዚአብሄር ያላቸውን አመለካከት ይለውጠዋል ።

# ትምህርት አስራ ሦስት

## ሙስሊሞች እና ምስክር (ሻሃዳ)

ለሙስሊሞች ምስክርነት በዋነኝነት የሚያመለክተው “ከአላህ በቀር ሌላ እግዚአብሔር የለም ፣ መሐመድም የእርሱ መልዕክተኛ ነው” የሚለውን የእስልምና እምነት (ሻሃዳ) ን ማንበብን ነው ። ሸሃዳ የእስልምና ማንነት ማዕከላዊ ሲሆን ሙስሊም የመሆን ‘ምሰሶዎች’ አንዱ ነው ። አዲስ በተወለደ ሕፃን ጆሮ ውስጥ በሹክሹክታ እና በየቀኑ ለአምስት ጊዜ በጸሎቱ ጥሪ ላይ በጩኸት ይነገራል ።

ለክርስቲያኖች ቀደምት ምስክር የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ እና እርሱ በእርግጥ ጌታ መሆኑን (ሮሜ 10 ፡ 9) ነው ። ይህ ምስክርነት ለክርስቲያናዊ ማንነታችን ማዕከላዊ ነው ፣ ስለሆነም ስለ ትንሳኤ እና ስለ ጌትነቱ የመመስከር ተግባርን ለ ከእ. የመ. አ. ለመግለጽ ሻሃዳ የሚለውን ቃል መጠቀሙ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ሆኖም ፣ ተማሪዎ(ዎችዎ) የእስልምናን የቃላት አጠቃቀም በዚህ መንገድ መጠቀም አይወዱ ይሆናል ፣ ስለዚህ ምርጫውን ለእነሱ ለመተው ንቁ ይሁኑ፣

በአዲስ ኪዳን ውስጥ <ምስክርነት> የሚለው የግሪኩ ቃል እንዲሁ <ሰማዕትነት> የሚገልፅ ትርጉም ያለው ሲሆን ተመሳሳይ ትስስር በአረብኛው ውስጥ ይገኛል ። ምስክርነት (ሻሃዳ/ shahada) የሚሰጥ ምስክር (ሻሂድ / shahid) ሰማዕት (ሻሂድ / Shaheed) ሊሆን ይችላል።

ይህ ትምህርት እንደ መሀዲ ዲባጅ ለእምነታቸው ሲሉ ለሚሞቱት ከእ. የመ. አ. ይህ ተምህርት ቃል በቃል እውነት ነው ፤ ፤ ብዙ የኢራናውያን ክርስትያኖች በእሱ እና በሌሎች የኢራናውያን ሰማዕታት አርአያነት ለክርስቶስ ተነሳስተዋል ። ትምህርት 13 እነዚህን ግንኙነቶች የሚያሳይ ሲሆን ተማሪዎቹ ትርጉም ያላቸው ሆነው ሊያገኙአቸው ይችላሉ ።

ከእ. ለመ. አ. ፣ ለሙስሊም ቤተሰቦቻቸው ስለ ክርስቶስ እንዴት ፣ መቼ እና ለማን እንደሚናገሩ ማወቅ እውነተኛ ትግል ነው ።ስለ ምስክርነት ፍርሃት ሊሰማቸው ይችላል ወይም ስለአለመስከርም የጥፋተኝነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ተማሪው (ተማሪዎቹ) በዚህ አካባቢ ስላጋጠሟቸው ተጋድሎዎች ፣ እና የቤተሰባቸው አባላት ክርስቶስን ለማግኘት ያላቸውን ጉጉት ሲናገሩ በጣም ስሜታዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ያ ስሜት ይገለፅ ።

## ድፍረት ወይስ ጥንቃቄ?

አንዳንድ ከእ. የመ. አ. ስለ ክርስቶስ ለሌሎች ለመናገር በጣም ስለሚፈሩ ምስክራቸውና መንፈሳዊ እድገታቸው ይጎዳል። በአንጻሩ ግን ሌሎች በድፍረትና በፍጥነት ይናገሩና አላስፈላጊ ነውጥ ባላስፈለጊ ጊዜ ያስነሳሉ ። በመሆኑም ብዙ ተሞክሮ ያካበቱ ደቀ መዛሙርት ከእ. የመ. አ. አዲሱን እምነታቸውን ለማስረዳት ሁኔታዎችን ቀስ በቀስ ማዘጋጀታቸው የተሻለ እንደሆነ ይሰማቸዋል፤ ሆኖም ለዘላለም በምሥጢር መቆየት የለባቸውም። የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናቸው መጠን በፍጥነት 'መውጣት/መገለጥ' የቤተሰብ አመለካከትን ጨምሮ በሁኔታዎች ላይ የተመካ ነው፣ እናም በዚያች አገር ያለው ነፃነት በጣም የተገደበ ወይም (በምዕራቡ ዓለም እንደሚታየው) ይበልጥ ግልጽ በመሆኑ ላይ የተመሠረተ ነው።

በተጨማሪም 'በምሥጢርነት' እና 'በግልፅነት' መካከል መካከለኛ ቦታ እንዳለ አስታውስ። ብዙ ከእ. የመ. አ. እምነታቸውን ለሚያምኑባቸው ሰዎች ግልጽ የመሆናቸውን ያህል ለሌሎች ደግሞ የተዘጉ ናቸው ። መገለጥ ቀስ በቀስ የሚከናወን ሂደት ነው ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከእ. የመ. አ. እምነታቸው በአጋጣሚ ወይም በድንገት ለሙስሊም ዘመዶቻቸው ይጋለጣል። ለዚህም ዝግጁ መሆን እና ለዚህም ተገቢ ምላሾችም ሊኖራቸው ይገባል።

ይህ ምሥክርነትን እንዴት መስጠት እንደሚቻል የሚያስረዳው ትምህርት ሙሉ ርዕሰ ጉዳይ ከእ. ለመ. አ. በጣም አስፈላጊ ነው. ትምህርት 13 ጉዳዮቹን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለመክፈት ይፈልጋል፤ ነገር ግን እነዚህ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ ከተማሪ ተማሪ ይለያያል። በመሆኑም እያንዳንዱን አማኝ በመምከር ረገድ ብዙ ጥበብና ጸሎት ያስፈልጋል ።

## የ'ብሪጅ' ሥዕላዊ መግለጫ

በማጣቀሻ 2 ውስጥ ያለው ስዕል በሰፊው ከሚታወቀው 'የድልድይ ስዕል' ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በሚከተሉት መንገዶች ለሙስሊሞች ባህል በሚስማማ መልኩ የተቀናበረ ነው፦

•ምንም ዓይነት የእግዚአብሔርን ስዕል አያሳይም።

• እግዚአብሄርን ከእኛ በላይ ያሳየናል እንጂ በእኛ ደረጃ አይደለም።

• ስለ ቀጥተኛው መንገድ እንጂ ስለ ድልድዩ አይናገርም።

ይሁን እንጂ ስዕሉን እንደ ባህላዊው የድልድይ ስዕል አግድም ማስቀመጥም ይቻላል። እናም ወደ ገነት የሚያደርሰንን ጠባብ ድልድይ ማቋረጥ አለብን የሚለውን የሙስሊሙ ጽንሰ ሐሳብ ላይ መገንባትም ይቻላል። አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ይህ ድልድይ <<ከሰው ፀጉር ይልቅ ጠባብ>> እንደሆነ ተምረዋል። በርካቶችም ከዛ ላይ ወድቀው ወደ ገነት ሳይደርሱ እንዳይቀሩ ይጨነቃሉ።

ይህን ድልድይ በሰላም ማቋረጥ የሚያስችለን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ማስረዳት እንችላለን። ታሪኩ የናያጋራን ፏፏቴ አቋርጦ ሌሎችን በ ጀርባው ሊያሻግር ስለተናገረ አንድ ሰው ይተርካል። አብዛኞቹ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቢቀሩም አንዱ በእሱ ላይ እምነት በመጣል ጀርባው ላይ ወጣ ። ብሎንዲንም በደህና ወደ ማዶ አሻገረው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላም ወደ ገነት ሊወስደን ቢጠብቅም ራሳችንን በአደራ ልንሰጠው ይገባናል ። በዚህ ትምህርት ውስጥ በትምህርቱ እቅድ ላይ እንደተገለጸው ስለ ብሎንዲን አጭር የቪዲዮ ክሊፕ ማሳየት ትፈልጉ ይሆናል።

አስተያየትዎን እንጠቃለን፦

እባክዎን በሁለቱም ትርጉሞች ላይ ያለውን ሥዕላዊ መግለጫ ለተማሪዎችዎ ያሳዩአቸው፦ ቀጥ ያለ (በኮርስ መጽሐፍ ውስጥ እንዳለ) እና አግድም (ወደ ገነት የሚያደርሰውን ድልድይ ያህል)። ከሙስሊሞች ጋር የተሻለ ግንኙነት የሚኖረው የትኛው ነው? አስተያየታችሁን comefollowmecourse@gmail.com ላይ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በኋላ የኮርስ መጽሐፉን መቀየር እንድንችል ስጡ፤

# ትምህርት አስራ አራት

## ከእ.ለመ. አ (ከእስልምና የመጡ አማኞች ) እና ጥምቀት

ጥምቀት ከእ.ለመ. አ ( ከእስልምና ለመጡ አማኞች ) ወሳኝ እርምጃ ነው ። ይህም ለክርስቶስና ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ታማኝነት የሚጠቁም ነው ። ይሁን እንጂ ሙስሊሞች ቤተሰቦቻቸውና ማኅበረሰባቸው ይህንን እርምጃ የክህደት ምልክት አድርገው ይመለከቱታል ። በእነሱ አመለካከት የሚጠመቀው ግለሰብ የቀድሞ ቤተሰባቸውን አይቀበልም ፤ እንዲሁም በእነሱ ላይ ከፍተኛ ውርደት ያመጣል ። ይህም ቤተሰቡንና ማህበረሰቡን በጣም ያናድዳል። በአንዳንድ ሙስሊም ሀገራትም አማኙን እንኳን ሊገድሉት ይችላሉ። በምዕራቡ ዓለም ያለው አደጋ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ አሁንም ቢሆን ከባድ ጉዳትና ተቀባይነት አለመቀበል ሊኖር ይችላል። ይህን መገንዘብና በተቻለ መጠን በቤተሰብ ላይ የሚደርሰውን ድንጋጤና ኀፍረት ለመቀነስ መጣር አስፈላጊ ነው ።

እንግዲህ ከእ.የመ. አ ( ከእስልምና የመጡ አማኞች ) ለጥምቀት ስታዘጋጁ ስለ መንፈሳዊ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ስለ ማህበራዊ ተጽእኖውም ጭምር አስቡ። ከግለሰቡ ጋር ተወያዩ፦

• የሚጠመቁበት ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው? (አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ይህን በመንፈሱ ያሳያቸዋል፣ ስለዚህ ሂደቱን አታቸኩሉት፤ ነገር ግን ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስም ወደኋላ አትበሉ።)

• በጥምቀት ወቅት የትኞቹ ሰዎች መገኘት አለባቸው? (ቢያንስ አንድ የቅርብ ታማኝ ጓደኛ፤ ግን ስለ ሰፊው ቤተ ክርስቲያንስ ምን ማለት ነው? ወይስ ሙስሊም ዘመዶች ቢገኙስ ምን ይላሉ? ሁኔታዎች ስለሚለያዩ እነዚህን ጥያቄዎች ከአማኙ ጋር ተወያዩበት።)

• አማኙ ለሙስሊም ቤተሰቦቻቸው አስቀድሞ ይነግራቸው ይሆን? (ይህ በብዙው በቤተሰብ ሁኔታ ላይ የተወሰነ ነው)

• በጥምቀት ወቅት ፎቶዎች ይነሳሉ? በስርጭታቸው ላይስ ቁጥጥር ይኖር ይሆን? (በዲጂታል ፎቶዎች እና በፌስቡክ ይህ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው! የጥምቀት ፎቶግራፎችን በሕዝብ ፊት ማሰራጨት በአማኞች ላይ አደጋ ሊያመጣና በቤተሰባቸው ላይ ሃፍረትን እንደሚመጣ ምንም ጥርጥር የለውም ። ከሁሉ ይበልጥ በቀላሉ ቁጣ የሚቀሰቅሰው ነገር ከእ. የመ. አ ( ከእስልምና የመጣው አማኝ ) ከውሃው በታች በሚገባበት ጊዜ ነው ። በተለይ ወንድ ሴቷን የሚያጠምቅ ከሆነ ፤ እንደነዚህ ያሉት ፎቶዎች በጥብቅ ቁጥጥር ሥር ሊሆኑ ይገባል። ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ አዲስ የተጠመቀውን ሰው ከክርስቲያን ጓደኞቻቸው ጋር በፎቶግራፍ ማንሳት ያን ያህል አይከብዳቸውም።)

• ለሴት ከእ.የመ. አ ( ከእስልምና የመጡ አማኞች ) ከውሃ በሚወጡበት ጊዜ ልከኝነታቸውን/ ክብራቸውን ለመጠበቅ ምን እርምጃዎች ይወሰዳሉ? (በእርጥበት ጊዜ ቀጭን ልብሶች ከሰውነት ጋር ይጣበቃሉ። ወፍራም ልብስ ልበስና ከውኃው እንደወጣች ለመጠቅለል የተዘጋጀ ፎጣ ይኑርህ።)

• የጥምቀት የምስክር ወረቀት መስጠት ይቻላል? (ይህ በምዕራቡ ዓለም ችግር አይደለም ነገር ግን ጥብቅ ሙስሊም በሆኑ ሀገሮች ውስጥ ለአጥማቂውም ሆነ ለተጠመቂው አደገኛ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ጥምቀት እንዳለ የሚያሳዩ አንዳንድ ማስረጃዎች አስፈላጊ ናቸው ። ተወያዩበት.)

## ሃይማኖታዊ መታጠብ በእስልምና

በኢስላም ውስጥ በየቀኑ ከተቀመጠው አምስት ወቅት ሶላት በፊት የዉዱ (የጭንቅላት፣ የእጆቻቸውንና የእግሮቻቸውን በስርዓት መታጠብ) ስርዓት የማድረግ ግዴታ ነው። ዋነኛ ንጽሕናን እንደሚያስገኝ የሚታመነው ሙሉ ገላን መታጠብ ወይም ጉሳል እምብዛም አይደጋገምም። አዳዲስ ሙስሊሞች የድሮ ኃጢአታቸው ሁሉ ወደ እስልምና ሲለወጡ እንደሚታጠቡ ይማራሉ። ብዙዎቹም ይህን ተምሳሌት አድርገው ሙሉውን ገላቸውን ይታጠባሉ/ ጉሳል ያደርጋሉ/። ይሁን እንጂ ከእስልምና ወደ ክርስቶስ የሚመጡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ይበልጥ ኃጢአትን ከመታጠብ ይልቅ ወደ አዲስ ሕይወት የመነሳት ምልክት አድርገው የሚያተኩሩት በጥምቀት ላይ ነው ።

# ትምህርት አስራ አምስት

## ሸሪዓ እና ህግን መጠበቅ በእስልምና ውስጥ

ከ15-17 የሚሆኑ ትምህርቶች ከእስልምና ወደ ክርስቶስ ለሚመለሱ በጣም አስፈላጊ የሆነን ርዕስ ይመለከታሉ። የዚህ ምክንያቱም <ሕግ> በእስልምና ውስጥ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ነው ። በእርግጥ <ሻሪዓህ> የሚለው የአረብኛ ቃል በጠባብ ትርጉሙ ሕግ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የሕይወት መንገድ ነው ። ሙስሊሙ ምሁር ባድሩ ካትሬጋ እንደፃፈው ሸሪአህ \ "ሙስሊሞች በግልም ሆነ በህዝባዊ ህይወታቸው ሊከተሏቸው የሚገቡበት ዝርዝር የስነምግባር መመሪያ ነው። '' ለአንድ ሰው“ እንዴት መብላት ፣ ጎብኝዎችን መቀበል ፣ እንስሳትን ማረድ ፣ መሸጥ ፣ ማረድ ፣ ራሱን ያፀዳል ፣ ይተኛል ፣ ወደ መጸዳጃ ቤት ይኄዳል ፣ መንግሥት ይመራል ፣ ፍትህን ይለማመዳል ፣ ይጸልያል ፣… ” ዘንድ እንደሚገባ ይደነግጋል። (ካትሬጋ

እና ሼንክ እስልምና እና ክርስትና ፣ ኡዚማ ፕሬስ ፣ ኬንያ (1980) ፣ ገጽ 67) ። ስለሆነም ቅን ሙስሊሞች የሚፈልጉት ሸሪአን የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ሳይሆን ፣ የመላውን ህብረተሰብ ሕይወትና እና ባህል ለመቀየስ ይፈልጉታል። ይህ ታዛዥነት በዚህ ሕይወት ውስጥ የአላህን በረከቶች እና በሚቀጥለው ሕይወት ሽልማት ያስገኛል ተብሎ ይታመናል ።

እስልምናን ለቀው የወጡ ሰዎች ከዚህ ዝርዝር የስነምግባር መመሪያ ነፃ በመሆናቸው ደስተኛ ሊሆኑ ይችላሉ ።ሆኖም ምን እንደሚሰሩ ካለማወቅ ግራ እንዲጋቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ይተውባቸዋል። በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ 'ሕግ' ካለ የሚኖርበት ቦታ ምንድን ነው? ቦታ ከሌለው እኛ የፈለግነውን ሁሉ የማድረግ ነፃነት አለን? ቦታ ካለውስ ተፈጥሮው እና ፍሬነገሩ ምንድነው? ለምን ይህንን 'የፍቅር ሕግ' እንታዘዛለን? ለሽልማት እና ለምስጋና ሲባል? ለምሳሌ ፣ መቼ መጾም እና ምን ያህል መስጠት እንዳለብን ልዩ ልዩ ነገሮችን ማዘጋጀት እንችላለን? ከእስልምናው ሸሪዓ ጋር ሲነፃፀር በጣም ጥቂት ዝርዝር መመሪያዎች ስለሆኑ ያሉን ክርስቶስን እንደ ጌታ ለመታዘዝ በምን ህግ ነው የምንመራው?

ስለሆነም ከ ትምህርት 15-17 ያለው ሥነ-መለኮታዊ ጻራ ከምዕራቡ የተለየ ነው ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ፣ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥነ-መለኮታዊ ጻራ ቅርብ ነው (ምንም እንኳን በሙሴ ሕግ እና በእስልምናው ሸሪዓ መካከልም ልዩነቶች ቢኖሩም)። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕግ ዓላማ ፣ በፈሪሳውያን የተሻረ ቢሆንም እና አዲሱ ኢየሱስ ያስተማረው 'የፍቅር ሕግ' ግን ለሁሉም ከእ. የመ. አ. በጣም ተስማሚ ናቸው ።

በእዚህ ምዕራፎች ውስጥ ያሉት ቁሳቁሶች ለእርስዎ አዲስ ከሆኑ ከእ. ለመ. አ. ጓደኛዎ (ጓደኞችዎ) ከእነሱ አመለካከት አንፃር አስተያየት እንዲሰጡዎ ይጠይቁ ። አንዳንድ የቀድሞ ሙስሊሞች በክርስቶስ ውስጥ በአዲስ ዓይነት ሸሪዓ ስር እንደምንኖር በማስረዳት ሊረዷቸው ይችላሉ ።ሌሎች ከቀድሞ ሸክማቸው የተነሳ ሸሪአህ በሚለው ቃል ላይ ስሜታዊ ምላሽ አላቸው ፣ ግን አሁንም አዲስ ጌታን እናገለግላለን እናም እኛ እንደፈለግነው ለማድረግ ነፃ አይደለንም የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ መረዳት አለባቸው፡

## ሙስሊሞች እና ቀጥተኛው መንገድ

ሙስሊሞች በየቀኑ "በቀጥተኛው ጎዳና ምራን" ብለው ይጸልያሉ ። በሺዎች የሚቆጠሩ የእግዚአብሔር ነቢያት ቀጥተኛውን መንገድ ለማስተማር እንደመጡም ያስተምራሉ ። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ብቻ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ ናቸው ፣ እና በሚያስደስት ሁኔታ ፣ አብዛኞዎቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው። አዳም ፣ ኖህ ፣ አብርሃም ፣ ሙሴ ፣ ዳዊት ፣ ኢየሱስ እና ሌሎች ጥቂቶች ። (ሙስሊሞች አደም ፣ ኑህ ፣ ኢብራሂም ፣ ሙሳ ፣ ዳውድ እና ኢሳ ይሏቸዋል) ።

ሙስሊሞች እነዚህ ሁሉ ነቢያት የመጡት የእግዚአብሔርን ሸሪዓ 'ቀጥተኛውን መንገድ' ለማሳየት እንደመጡ ያምናሉ ፣ ስለሆነም ይህን በመከተል ብድራቱን እና በረከቱን እናገኛለን ብለው ያስባሉ ። ሆኖም ፣ ቀጥተኛውን መንገድ ምን እንደ ሆነ ብናውቅና እሱን መከተል ብንፈልግ እንኳን በእውነቱ ይህን ማድረግ እንችላለን? ካልሆነስ ለምን አይሆንም? ይህ የትምህርት 15 ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት መነሻ ነው።

## 'ዋና' እና 'አናሳ' ኃጢአቶች

ሙስሊሞች አንዳንድ ኃጢአቶች ከሌሎቹ የበለጠ ከባድ እንደሆኑ ይማራሉ ። እግዚአብሔር እንደ <ውሸት> የመሰሉ <ጥቃቅን> ኃጢአቶችን ችላ ሊል ይችላል ፣ ነገርግን <ዐበይት> ኃጢአቶች ለቅጣት ይዳርጋሉ ። እንዲሁም ፣ አንድ ሰው 'ዓላማው' ካለው (ኒያ) አንድ ነገር ለማድረግ በልባቸው ውስጥ ግን በትክክል ባይፈፅመው ያ ፣ ኃጢአት አይሆንም። ይህ በልብ ውስጥ ያለው ምኞት ልክ እንደ ማመንዘር ኃጢአት ነው ከሚለው የክርበስቶስ ትምህርት ጋር የሚጋጭ ነው (ጥያቄ 13 ን ይመልከቱ)።

ይህ ክፍል የሚያስተምረው የክርስቶስ ቅዱስ ሕግ በእውነቱ እጅግ የላቀ መስፈርት መሆኑን ነው ። ከሥነ-ስርዓት አንፃር ቀላል ቢመስልም በሥነ-ምግባራዊ ሁኔታ ከእስልምናው ሸሪዓን የመጠበቅ ሕግ በጣም የላቀ ነው ።

# ትምህርት አስራ ስድስት

## የሙስሊሞች ለመታዘዝ ተነሳሽነት

ትምህርት 16 በክፍል 15 የጀመረውን የእግዚአብሔር ሕግ ውይይት ይቀጥላል (አጠቃላይ ማብራሪያ ለማግኘት በዚያ ተመልከቱ)። በዚህ ትምህርት መነሻ ውለታ ለሽልማት ወይም ለቅጣት ከመፍራት በመነሳት የእግዚአብሔርን ሕግ በመታዘዝ እና ለእኛ ላደረገልን ነገር ሁሉ ከአመስጋኝነት የሚመነጭ በመታዘዝ መካከል ያለው ልዩነት ነው። ይህ ሙስሊም ወደ ክርስቶስ በሚዞርበት ጊዜ መሠረታዊ የሆነ የአመለካከት ለውጥ ነው።

ሰዎችን እንወዳለን ምክንያቱም ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት እንዳሳየን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ስለወደደን ነው። ስለዚህ፣ በምላሻችንም እግዚአብሄርን በሙሉ ልባችን፣ ጎረቤቶቻችንንም እንደራሳችን መውደድ አለብን የሚለውን 'የፍቅር ህግ' በመታዘዝ ፍቅርን መግለፅ እንፈልጋለን።

## ሙስሊሞች፣ ከእ. የመ.አ. እና እንግዳ ተቀባይነት

ብዙዎቹ ከእ. የመ.አ. እንግዳ ተቀባይነትን ከፍ አድርገው ከሚመለከቱ ባሕሎች የመጡ ናቸው። ከዚህ በተቃራኒው በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ደግሞ ሰዎችን ወደ ቤታችን በማስተናገድ ረገድ ብዙ መማር የሚገባን ነገር አለ ። አንድ ከእ. የመ.አ. ሳያሳውቅዎ ወደ ቤትዎ ቢመጣ አስቀድሞ ቀጠሮ ባያቀርብ እንኳን ደስ ይላችሁ ይሆን? በቤት ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከእስልምና የመጣችን አማኝ 'ቤተሰቦቿ' እንደሆናቸሁ ቢነግሯትና ቤተሰቦቿ ሲጥሏት እና መኖሪያ ቤት ሲያስፈልጋት ወደ ቤታችሁ ብትመጣ ልትወስዷት/ልትቀበሏት ዝግጁ ናችሁ?

# ትምህርት አስራ ሰባት

## ከእ. የመ.አ. እና የሸሪዓ ዝርዝር መመሪያዎች

ከትምህርት 15 እና 16 በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ያለውን ዋናውን ትምህርት ካጠቃለለ በኋላ ይህ ትምህርት የክርስቶስ ተከታዮች በእስላም ውስጥ የሚገኙት ተመሳሳይ ዓይነት ዝርዝር መመሪያዎች በሌሉበት ሁኔታ ውስጥ እንዴት በዚህ ላይ እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ ይጠይቃል።

በተለይ ሙስሊሞች በትክክል ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሚነግሩአቸው ሁለት የእስልምና 'ምሰሶዎች' ሚባሉትን ህግጋት እንመለከታለን። በረመዳን ወር ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ መጾም አለባቸው፤ ከገንዘቦቻቸውም የተወሰነ መጠን ዘካት (የምፅዋት-ታክስ) አድርገው መስጠት አለባቸው። የክርስቶስ ተከታዮች በዚህ ረገድ ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል? ይህ ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ሥርዓቶች የሚያስተምር ሲሆን የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን መሠረታዊ ሥርዓቶች በተለያዩ መንገዶች ተግባራዊ እንደሚደረግ ይተማመናሉ። እንግዲህ እንደ መካሪ፣ የራሳችሁን የቤተ ክርስቲያን ልማድ ለማስተማር ነፃነት ይሰማችሁ፣ ነገር ግን ዋናው ነገር የምእመኑ መርሆዎቹን መረዳት መሆኑን አስታውሱ። ግለሰቡ ከፈለጉ የተወሰኑ መመሪያዎችን በመስጠት ሚዛናዊ ለመሆን ጥረት አድርጉ ፤ ይሁን እንጂ ሕይወታቸውን አትቆጣጠሩ ። ኢየሱስን ጌታ አድርገው እንዲታዘዙና ከሁሉም በላይ የእሱን አመራር እንዲከተሉ እርዷቸው።

## ከእ. የመ.አ. እና ረመዳን

በብዙ ሙስሊም ሀገራት ረመዳን ለቤተሰብ አንድነት ልዩ ወቅት ነው። ይህ ወቅት ከእ. የመ.አማኞች ቤተሰባቸውን ሊናፍቁ የሚችሉበት ወቅት እንደሆነ ተረዱ ። (ሌላው ብቸኛ ጊዜ የገና በዓል ነው። ክርስትያኖች ከገዛ ቤተሰቦቻቸው ጋር ተጠምደው የቀድሞው ሙስሊም ከማንም ጋር ሳያከብር ተገልሎ መቀመጡን የሚረሱበት ወቅት ነው።)

ከእ. የመ.አማኞች አሁንም ከሙስሊም ቤተሰቦቻቸው ጋር ለሚኖሩበት የፓርቬን ችግር ፣በረመዳን ጾም መካፈልም ሆነ አለመካፈል እውን ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ ለቤተሰብ ታማኝ ለመሆን የሚያስችል ተስማሚ መንገድ ሊሆን እንደሚችል ያምናሉ፤ አማኙ ስለ እስልምናው ግዴታ ሳይሆን ስለኢየሱስ ሲል በመጾም ። አስፈላጊ ባልሆነ ጉዳይ የሚከሰትን አላስፈላጊ ስደትን ያስወግዳል። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ አቋም በመውሰድ ከቤተሰቡ ጋር መለያየት ፣ ግልጽ የሆነ ምሥክርነት መስጠትና ከማታለል መቆጠብ አስፈላጊ እንደሆነ ያምናሉ ። ይሁን እንጂ ሙስሊሞች ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ሰነፍ እንደሆኑ እንዲያስቡ የሚያደርግ ከሆነ መጾሙ ጥሩ ምስክርነት አይደለምን?

በቤተሰባቸው ሁኔታ ላይ የሚወሰን መሆኑን በማስታወስ በእነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች ላይ ከተማሪዎቻችሁ ጋር ተወያዩባቸው ። በረመዳን ላለመፆም ከወሰኑ ጌታ እንደሚመራቸው በሌላ ጊዜ ለመጾም ይሞክራሉን?

## ሙስሊሞች እና መስጠት

በዘካት ወይም በምፅዋት-ታክስ ውስጥ የተወሰነው መጠን በየዓመቱ 2.5% የሙስሊሞች የተጣራ ካፒታል (ገቢያቸው ሳይሆን) ላይ ይወሰናል። ይህንን በዓመት አንዴ እንዴት ማስላት እንደሚቻል አንዳንድ ዝርዝር መመሪያዎች ይደነግጋሉ። ግለሰቦች ድሆችን መርዳት ወይም እስልምናን ለመስፋፋት የመሳሰሉ አንዳንድ መመዘኛዎችን እስካሟላ ድረስ የት መስጠት እንደሚገባቸው የመምረጥ ነፃነት አላቸው። በተጨማሪም ብዙ ሙስሊሞች በዓመቱ ውስጥ ለነዚህ ዓላማዎች ወይም ለመስጊድ ወጪዎች ወዘተ በፍቃደኝነት ይሰጣሉ።

# ትምህርት አስራ ስምንት

## ሙስሊሞች እና አስማት

የምዕራባውያን ሰዎች 'ዕድል' እና 'አስማት' በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ በርካታ ሙስሊሞች ጠቃሚ ጽንሰ ሐሳቦች መሆናቸውን ሲረዱ ይገረሙ ይሆናል። በታሪክ እንደሚታወቀው እነዚህ እምነቶች ቀደም ሲል ሕዝቡ ሙስሊም ከመሆኑ በፊት በብዙ ባህሎች ውስጥ ይገኙ ነበር። የዚህ ምህዳሩም <<ባህላዊ እስላም>> በመባል ይታወቃል። በተጨማሪም በኢስላም አላህ እራሱ ራቅ ብሎ ያለ እንደሆነ ይታሰባል። እርሱ ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ከወሰነና ሰዎች ለመለወጥ ምንም ማድረግ ካልቻሉ ይህ ደግሞ ዕጣ ፈንታሕይወታቸውን እንደሚቆጣጠር እንዲያስቡ ያደርጋል። ከዚህም በላይ አላህ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ተደርጎ ስለሚታይ ሙስሊሞች ስለችግራቸው በጥልቅ እንደሚያስብላቸው ወይም ጸሎታቸውን እንደሚሰማቸው እርግጠኞች አይደሉም። በመሆኑም ይበልጥ በቀላሉ የሚደርስላቸው ከሚመስላቸው ሌሎች መንፈሳዊ አስታራቂዎች እርዳታን ይፈልጋሉ። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በዛሬው ጊዜ በሙስሊሞች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ።

ለጸሎት ወይም ለመንፈሳዊ ኃይሎች ወይም ለተሰወረ እውቀት መልስ ለማግኘት ሲፈልጉ አንዳንድ ሙስሊሞች ወደ መናፍስታዊ ድርጊቶች እንዲገቡ አድርገዋቸዋል ። ወደ ክርስቶስ ከተመለሱ በኋላ ግን ከዚህ እስራት ነፃ መውጣት ያስፈልጋቸው ይሆናል።

ለሌሎች ደግሞ ይበልጥ አጠቃላይ ባህላዊ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፣ ለምሳሌ ክታቦችን በእጅ ወይም በተሽከርካሪዎች ላይ ለ'ጥበቃ' ብሎ ማሰር።ሌሎች ደግሞ ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ተጽዕኖ አላሳደረባቸው ይሆናል ።

ትምህርት 18 በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ይሰጣል። ይሁን እንጂ የተሳሳቱ ድርጊቶችን ብቻ መጥቀስ ከበስተጀርባ ያለውን ዓለም አቀፍ አመለካከት ከመመርመር ያነሰ ውጤት ነው የሚኖረው ። ከእ. የመ. አማ. እስከ እኛ ደረጃ ድረስ በወረደው (በዚህም ምክንያት ህመማችንን በሚሰማን) እና ከሁሉም መንፈሳዊ ሀይሎች በላይ ከፍ ብሎ ባረገው በክርስቶስ ላይ በእውነት መተማመን ከቻሉ (ስለዚህ በእነርሱ ላይ ድል በማድረግ)፣ በችግር ጊዜ ከአማራጭ ይልቅ እርዳታ ለማግኘት ወደ ራሱ ወደ ክርስቶስ የመዞር እድል ይኖራቸዋል። በተጨማሪም የክርስቶስ ሞት የጨለማን ኃይል አሸንፎ እነዚህን ክፉ ኃይሎች በመፍራት ከመኖር ነፃ አውጥቶናል ።

## ሙስሊሞች እና መንፈሳውያን ሃይሎች

ብዙ ሙስሊሞች በ'መንፈሳዊ ሃይሎች' ያምናሉ። እነርሱም፡-

- በመላእክት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰውን እንደ ገብርኤል (ጂብሪል) ያሉትን ጨምሮ እንዲሁም የእያንዳንዱን ሰው መልካምና መጥፎ ተግባር የሚመዘግቡትን የግል መላእክት፤
- 'ክፉ ዓይን' ቡዳ፣ በሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የማይታይ የቅናት ተፅዕኖ፣ ለምሳሌ ውብ በመሆኑ የሚወደስ ህፃን፤
- ዕጣ ፈንታ፣የሰዎች ዕጣ ፈንታ አስቀድሞ የተፃፈበትና ለመለወጥ ምንም ማድረግ የማይቻል መሆኑ፤
- ጋኔን፣በጎ ወይም ብዙ ጊዜ ክፉ ሊሆኑ የሚችሉ፣ ለምሳሌ በሽታን ወይም እብደትን የሚያመጣ መንፈስ፤
- ክፉ መናፍስት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጽንሰ ሐሳብ ጋር የሚመሳሰል ።

የቡድን አባላት እኩይ ተፅዕኖዎችን ለማስወገድ ሙስሊሞች የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ ተግባራት ሊገልፁ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል ለሰዎች ወይም ለተሽከርካሪዎች ክታቦች፣ የዐይን ስዕሎች ወዘተ ይገኙበታል።

በተጨማሪም ሙስሊሞች በተለምዶው በባርኮት (በረካ )በዓይን በማይታየው 'በረከት' ያምናሉ።ከቅዱሳን ሰዎች ወይም ከቅዱሳን መቃብሮች (የቅዱሳንን መቃብሮች ጨምሮ) ጋር የሚያያዘውንና በአካል በመቅረብ ሊውጡት/ወደራሳቸው ሊስቡት የሚፈልጉትን በራካ ያምናሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በእነዚህ ቅዱስ ስፍራዎች አቅራቢያ በሚገኙ ዛፎች ላይ ጨርቆች በማሰር ጸሎታቸውን ወይም ስእለታቸውን ለማስታወስ ሲሉ ያሰቅላሉ።

## ሐዘናቸውን ማጽናናት

በአብዛኛዎቹ የሙስሊም ባህሎች ሐዘን የደረሰባቸውን ሰዎች ወዲያው አንድ ሰው በመንብኘት፣ አብረዋቸው ቁጭ ብሎ ሐዘናቸውን በመካፈል ማጽናናት የተለመደ ነው። አንድነትን ለማሳየት ወሳኝ መንገድ ሲሆን በዛሬው ጊዜ ካለው የምዕራቡ ዓለም ይልቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ከነበረው ባሕል (ለምሳሌ ዮሐንስ 11) ጋር ይቀራረባል ።

ይሁን እንጂ ሙስሊሞች ማጽናናትን ሊያቀርቡ የሚሞክሩበት የተለመደው መንገድ 'የአላህ ፈቃድ ነበር' ፣ እኛ ግን ዕጣ ፈንታችንን መቀበል አለብን በማለት ነው። በጥያቄ 6 ላይ ከእ. የመ. አማ. ስለ እግዚአብሔር በተለየ አመለካከት ላይ ተመሥርቶ ጥልቅ የሆነ ማጽናኛ ሊሰጥ እንደሚችል ሐሳብ እናቀርባለን፤ ይኸውም ወደ እኛ ቅርብ የሆነና መከራችንን የሚጋራ እግዚአብሔር እንዳለን በማሳየት ነው።

# ትምህርት አስራ ዘጠኝ

## እግር መታጠብ በሙስሊሞች ባህል

ብዙ ሙስሊሞች የሚኖሩት በኢየሱስ ዘመን እንደነበሩት እግሮች በጣም ቆሻሻ እንደሆኑ ተደርገው በሚያስቡ ባሕሎች ውስጥ ነው። በአንድ ሰው ላይ 'ተረከዝ ማንሳት' ወይም በአንድ ሰው ላይ ጫማ መወርወር ትልቅ ስድብ እንደሆነ ተደርጎ ይታያል። እንግዲያው የሌላውን ሰው እግር ማጠብ ኢየሱስ ትሑት መሆኑን የሚያሳይ ግሩም ምሳሌ ነው።

## የአመራር ጉዳዮች ከእስልምና በመጡ ቡድኖች ውስጥ

በሙስሊሞች አገሮችም ሆነ በምዕራቡ ዓለም ከእስልምና በመጡ አማኞች ኅብረት ውስጥ መከፋፈል በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ የተለመደ ነገር ሆኗል ። ለአንድ ሙስሊም ግለሰብ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ከባድ ነው፤ ለእነዚህ ተከታዮች በቡድን ሆነው መሰባሰብ ደግሞ በጣም ከባድ ነው፤ ይህ ቡድን በኀለመሱ መሪዎች ሥር አንድ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ደግሞ አሁንም የበለጠ ከባድ ነው ። ከእ. ለመጡ የአማኞች ቡድኖች ጥሩ አመራር እጅግ አስፈላጊ ርዕሰ ጉዳይ ነው!

<<ና ተከተለኝ>> የሚለው አካሄድ ለአዳዲስ ምእመናን ነው። ስለሆነም በአመራር ጉዳዮች ላይ ጠልቆ አይዳስስም። እነዚህ በአጭሩ እዚህ ትምህርት ውስጥ ይገኛሉ።ነገር ግን ወደፊት ተማሪው(ዎቹ)ይበልጥ ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ ይህን ተጨማሪ ትምህርት መከታተል ይችላሉ።

# ትምህርት ሃያ

## ሙስሊሞች, ጉዞ እና ገነት

ለሙስሊሞች ከተቻላቸው በሕይወት ዘመናቸው ቢያንስ አንድ ጊዜ ወደ መካ ጉዞ ማድረግ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው። ይህ ግን ከዓለማችን ሙስሊሞች ለጥቂቶች ብቻ የሚቻል ና እንደ መብት የሚታይ ቢሆንም። ምንም እንኳን አንዳንድ ከእ. የመ. አማኞች ከእስልምና ጽንሰ ሃሳቦች የፀዳ እረፍት ማድረግ ስለሚመርጡና በእነርሱ ላይ ብዙ ውጥረት ላለመፍጠር ቢሞከርም። ይህ ኮርስ ስለ እስልምና 'ዓምዶች' በተለያዩ መንገዶች ጥቆማዎችን አድርጓል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ንጽጽሩ ወደ ሰማይ ጉዞ ማድረግን ከሚያስተምረው ከክርስትና ሕይወት ጋር (ፒልግሪምስ ፕሮገስ የተባለው ዝነኛ መጽሐፍም ይህን ያደርጋል። በኢስላም ውስጥ ሰማይ ብዙ ተድላዎች ያሉበት ገነት እንደሆነ ተገልጿል። በትምህርት 20 ላይ የሰማይ ዋነኛ ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር እንደምንሆንና በእሱ መገኘት ለዘላለም እንደምንደሰት ያስተምራል ።

## ኢየሩሳሌምና ጽዮናዊነት

ይህ ከሙስሊሞች ጋር የሚያወያይ ሞቅ ያለ ርዕሰ ጉዳይ ሲሆን ከእ. የመ. አማ፣ ብዙውን ጊዜ ግራ በመጋባት ውስጥ ይያዛሉ። የሙስሊም አስተዳደጋቸው አይሁዳውያንን እንዲጠሉና ጽዮናዊነትን አጥብቀው እንዲቃወሙ አስተምሯቸው ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን፣ የክርስቶስ ተከታዮች በመሆናቸው፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከአይሁድ ሕዝብ ጋር የገባውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ኪዳን መረዳት እና 'ጽዮንን' ከሚያከብሩ ጥቅሶች ጋር መታገዝ አለባቸው።

ከሁሉም በላይ ስለ አይሁዳውያን የተተነበዩትን ትንቢቶች በተመለከተ የተለያዩ ክርስቲያናዊ ትርጓሜዎች ያጋጥሟቸዋል፤ ከእነዚህም መካከል ዘመናዊው የእስራኤል ግዛት ያደረጋቸውን ነገሮች በሙሉ የሚደግፉና አረቦችን እንደ ጠላቶቻቸው አድርገው የሚመለከቱ አንዳንድ ክርስቲያኖች ይገኙበታል። ሆኖም ከእ. የመ. አማ. የእስራኤልን ደጋፊ የሆነ አቋም ከወሰዱ በሙስሊሞች ዘመዶቻቸው ዘንድ ከሃዲዎች መሆናቸውን ያረጋግጣል።

ይህ ሁሉ ከእ. ለመ. አማ. ግራ የሚያጋባና ጎጂ ሊሆን ይችላል። ታዲያ ሁሉንም ነገር በአእምሯቸውና በልባቸው ውስጥ እንዴት ሊገጣጠሙ ይችላሉ? ይህ ትምህርት በዚህ ጉዳይ ላይ በአጭሩ ብቻ የሚዳስስ ነው እናም በዝርዝር መሄድ አያስፈልግህም፣ ነገር ግን ስሜታዊነቱን መገንዘብ ይኖርብሃል።

# የመግቢያ ስብሰባ

| **የእያንዳንዱ ተማሪ ዓላማዎች:**<br>ሀ. ስለትምህርቱ ጉጉ መሆን እና የሳምንቱን የቤት ውስጥ ጥናት በመሰጠት ማጠናቀቅ።<br>ለ. ለእያንዳንዱ ትምህርት እንዴት የቤት ውስጥ ጥናት ማድረግ እንዳለባቸው መረዳት።<br>ሐ. ለመማሪያ መጽሐፋቸው ክፍያን ይፈጽማሉ ወይም በሚቀጥለው ሳምንት ለማምጣት ቃል ይገባሉ።<br>፡ | **ዝግጅት:** እያንዳንዱ ተማሪ የመማሪያ መጽሐፍ ማግኘት |
|---|---|

## መክፈቻ

**መግቢያ:** ይህ አዲስ ቡድን ከሆነ እያንዳንዱ ሰው ራሱን እንዲያስተዋውቅ ጠይቅ:: እነሱም ስለህይወታቸው፣ ስለሥራቸው ወይም ስለቤተሰባቸው እንደአስፈላጊነቱ መናገር ይችላሉ:: ይሁን እንጂ አንዳንድ የቡድኑ አባላት አመኔታን እስኪያዩ ድረስ ብዙ መናገር ባይፈልጉ፣ ምንም ማለት አይደለም:: .

***በጸሎት ክፈት:*** *ይህን ትምህርት በጋራ በምንማርበት ጊዜ እኛ ሁላችን ተጠቃሚ እንድንሆን እግዚአብሔር እንዲረዳን እንጠይቀው::*

## የና ተከተለኝ ትምህርትን ማስረዳት

### "ምንድነው?" – የትምህርቱ ይዘት

**የመማሪያ መጽሐፍ:** ለእያንዳንዱ ተማሪ አንድ የመማሪያ መጽሐፍ ስጥ።

*እነሱም የበለጠ ዋጋ እንዲሰጡት፣ ለመጽሐፉ አንድ ነገር መክፈል አለባቸው። ገንዘብ መጠየቅ በአንተ ምርጫ ላይ የሚወሰን ነው። በቀላሉ ወይም በአጠቃላይ ማንበብ ለማይችል ማንኛውም ተማሪ ደግሞ በዚህ የአማካሪው መመሪያ ክፍል አንድ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች የሚለውን ርዕስ ተመልከት።*

**የመማሪያ መጽሐፉን ክፈት ገጽ V:** የይዘት

የትምህረቱን ርዕሶች እንዲያነብ አንዱን የቡድን አባል ጠይቅ።

- አባላት ለማየት የጓጉት ርዕስ የቱ እንደሆነ እና ለምን እንደሆነ ሃሳባቸውን እንዲከፋፈሉ ጥንድ ጥንድ እንዲሆኑ ጠይቃቸው። ከዚያም ይህንን ለቡድኑ ሊያካፍሉ ይገባል።

### "ለምን?" – የትምህርቱ ዓላማ

**ምህርቱ ዓላማዎች:**

የዚህ ትምህርት ዓላማው እኛ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች እንድናድግ ነው።

- እኔም እናንተም፣ እኛ ሁላችን ተማሪዎች ነን። በአንድነት፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ፣ እሱን የበለጠ ለማወቅ፣ እሱን መታመን፣ እሱን መታዘዝ እና በክርስቶስ ማህበረሰብ ውስጥ የእኛን ሚና መጫወት እንፈልጋለን።
- "ይህን ትምህርት በአንድነት ያጠና የነበረ አንድ የአፍጋኒስታን ቡድን እንዲህ ሲል ተናግሯል የዚህ መጽሐፍ ጥንካሬው እያንዳንዱ ወንድም እና እህት፣ ወጣት ቢሆን ሽማግሌ፣ የእነሱን ሃሳብ፣ ጥያቄዎች፣ ችግሮች እና ህመሞች በህይወታቸው እንደገጠማቸው በነጻነት የሚያካፍሉበት ዕድል መስጠቱ ነው። ይህ ተማሪዎች ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ግድ እንዲላቸው እና ክፍት እንዲሆኑ እና መጸለይ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።" ይህን ግለጽ።

እናንተም ልክ እንደዚህ የአፍጋኒስታን ቡድን በአንድነት ለመማር ትፈልጋላችሁን? ብለህ ጠይቅ።

### "እንዴት?" – የትምህርቱ ዘዴ

**የመማሪያ መጽሐፉን ክፈት ገጽ iv** እና በአንድነት ስዕሉን ተመልከት።

- ይህ ትምህርት በእያንዳንዱ ሳምንት ሦስት ዘዴዎችን በጥምረት እንደሚጠቀም ግለጽ።

1. **የቤት ውስጥ ጥናት** ትምህርቱን እንድናስታውስ እና እንድንረዳ ያግዘናል፤
2. **ውይይት ሃሳባችንን እንድንገልጽ እና ከሌሎች እንድንማር ይረዳናል፤**
3. **ተግባራዊ ስራ** ደግሞ በዕለት ህይወታችን ውስጥ የተማርነውን እንድንታዘዝ ይረዳናል።

- የእያንዳንዱ ዘዴ: የቤት ውስጥ ጥናቱ፣ ውይይቱ እና ተግባራዊ ስራው ዓላማው ምንድነው?

*ይህ ጥያቄ ተማሪዎቹ የትምህረቱን ዓላማ እንዲረዱ የሚያግዝ ነው።*

**የመማሪያ መጽሐፉን ከፊት ገጽ Vi: የተማሪው መመሪያ**

- እያንዳንዱ ተማሪ ማንበብ ያለበት አንድ ዓረፍተ ነገር ነው።

ማንኛውም ነገር ያልገባው ሰው ካለ ጠይቅ።

## ትምህርት 1 - ተመልከት

**ሣህርት 1ን በአንድነት ክፈት:** የክርስቶስ ተከታይ መሆን (ገጽ 1)።

- የህይወታችን ዓላማ በሚለው ርዕስ ስር የመጀመሪያዎቹን ሁለት አንቀጾች አንብብ። በንግግር ሳጥን ውስጥ ቀጥሎ የሚመጣውንም አንብብ።
- የሕይወትህ ዓላማ ምንድነው? ብለህ በራስህ ቃል ጠይቅ። *ተወያዩ፤ ተማሪዎች የራሳቸውን አስተያየት ሊሰጡ ይገባል፡ ፡ አንተም እንደ አማካሪ የራስህን አስተያየት ልታካፍል ይገባል።*
- እያንዳንዱ ሰው ጥያቄ 2 በማንበብ መልሱን ሊናገር ይገባል። በትምህርቱም መጨረሻ ላይ መልሳቸውን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚችሉ አሳያቸው።

**መልስህን ማረጋገጥ:**

- መጽሐፉ አስተማሪህ ነው። ለዚህም ነው በእያንዳንዱ ትምህርት ማብቂያ ላይ መልሱን የሚሰጥህ፣ አንተም የራስህን መልስ በዚህ ማረጋገጥ ትችላለህ። ይህ ሲባል ግን መልሱን ከመጽሐፉ ገልብጥ ማለት አይደለም! በመጀመሪያ የራስህን መልስ ጻፍና ከዚያም በትክክል ማግኘትህን አረጋግጥ።
- መልሱም 'በግል የሚሰጥ ምላሽ' ወይም 'ለውይይት ተዘጋጅ' በሚል ጊዜ፣ ሁሉም ሰው የራሱ አስተያየት እና ልምድ ስላለው 'ትክክል' የሚባል አንድ መልስ የለም።

**የውይይት ጥያቄዎች:**

- በትምህርት 1 መልሶች ውስጥ፣ ለጥያቄ 5 ወይም 13 የሰጠው መልስ ምንድነው?
- ይህ ሲባል ግን ጥያቄዎቹን ክፍት አድረገን መተው ወይም ምንም መጻፍ የለብንም ማለት ነው?
- ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች የግላችንን ምላሽ የምንሰጠው እና ክፍት አድርገን የማንተውበት ምክንያት ለምንድነው?

*በግል የሚሰጥ መልስ'*

*ይህን ማለት አይደለም! እያንዳንዱ አባል አሁንም የራሳቸውን አስተያየት በመጻፍ በውይይት ጊዜ ለመናገር ሊዘጋጁ ይገባል።*

*አንድ ነገር በመንጻፍበት ጊዜ ስለነገሩ የበለጠ በጥልቀት እንድናስብበት ያደርገናል። በተሻለ መልኩም እናስታውሰዋለን። በውይይትም ጊዜ ከሌሎች ጋር የምንካፈለው አንድ ነገር ይኖረናል፡*

## የቤት ውስጥ ጥናት

- እባክህ ከሚቀጥለው ስብሰባችን በፊት በሙሉ ትምህርት 1ን በራስህ ጊዜ አጠናቅ።
- በመጨረሻም የትምህርቱን ክለሳ ስራ። በትምህርቱ ክለሳ ውስጥ ያሉ ጥያቄዎችን አስቀድመህ በትምህርቱ ውስጥ ያየሃቸው ውይይት ናቸው። ስለዚህ የእነዚህን መልሶች ለአንተ አልሰጠንህም። መልሱንም ካለወቅህ ትምህርቱን ከልስ፡

<table>
<tr><th colspan="2">ማጠቃለያ</th></tr>
<tr><td>የመግቢያ ስብሰባውን ለማጠቃለል:<br>ጥያቄ ያለው ሰው ካለ ጠይቅ።<br>የቀጣዩ ስብሰባ ጊዜ እና ቦታን ግለጽ<br>ተማሪዎች ከቀጣዩ ስብሰባ በፊት ትምህርት 1ን ከመማሪያ መጽሐፉ ላይ ዲያዩት አስታውሳቸው።</td><td>በአንድነት ጸልይ:<br>እኛ በዚህ ሳምንት ይህን አዲስ ትምህርት ስንጀምር እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችንን እንዲናገረን ጠይቅ፡</td></tr>
</table>

# ትምህርት 1፥ የክርስቶስ ተከታይ መሆን

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ራሱን እንደ ክርስቶስ ተከታይ ማየቱን ወይም አለማየቱን ይመዝናል።
ለ. እስካሁን የክርስቶስ ተከታይ ካልሆነ፣ እንዴት መሆን እንደሚቻል ያውቃል።
ሐ. ማቴዎስ 11:28 ያሰላስል (በቃል ያጥና)።

**የባህል መገለጫ:**

- መነሻ ነጥቦች ከእ.የመ.እ
- አዳዲስ አማኞች እና ዋጋውን መተመን

**ዝግጅት:** ለጥያቄ 15-18 እንደ አማራጭ አጭር የፊልም ቅንብር

## መክፈቻ

***ላዛሬው ትምህርት ድድጸልይ።***

***ትምህርት 1- የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:***

**ጥያቄ 1:** በቃል የሚጠናውን ጥቅስ (ማቴዎስ 11:28) በጋራ ለማለት ተለማመድ። አነበብከው፣ የሚሰማህ ምንድነው?

**ጥያቄ 2:** ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ ምን እንደጻፉ ጠይቅ።

*እነሱም ተራ በተራ መልስ ሊሰጡ ይችላሉ ወይም መጽሐፋቸውን በመለዋወጥ እርስ በርስ መልሳቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።*

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዖን ጴጥሮስ የእሱ ተከታይ እንዲሆን እንዴት እንደጠራው እና እኛም እንዴት የክርስቶስ ተከታዮች መሆን እንደምንችል ዛሬ እንማራለን።

*ሁሉንም ጥያቄዎች ለመወያየት በቂ ጊዜ እንደሌለ አስረዳ። ነገር ግን ሰዎች ካለፍካቸው ጥያቄዎች ውስጥ ያልገባቸውን ማንኛውም ጥያቄ ካለ ወይም በግላቸውም ሌላ ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ አበረታታ።*

## ውይይት

### መግቢያ (እና ጥያቄ 1-2)

**መግቢያ:**

የሁለቱን ሰዎች የሕይወት ዓላማ ሁለት ሰዎች እንዲያነቡት ጠይቅ። በንግግር ሳጥን ውስጥ ያለውን የአስተማሪውን ጥያቄ ጠይቅ።



- የሕይወትህ ዓላማ ምንድነው?

*በመጨረሻም የራስህን የሕይወት ዓላማ አካፍል።*

### የኢየሱስ ተከታይ መሆን (ጥያቄ 3-4)

**ጥያቄ 3:** በሳጥን ውስጥ ያለውን ክፍል አንብብ፣ ጠይቅ:

- አንድ ሰው በራሱ ቃል የሆነውን ነገር በድጋሚ ይናገር፡.
- ስምዖን ነኝ ብለህ አስብ. ኢየሱስ ይህንን ታምር ሲያደርግ ብታይ የሚኖርህ የተለየ ስሜት ምንድነው?
- ስምዖን ጴጥሮስ የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን የወሰዳቸው አራት እርምጃዎች ምንድናቸው?

*ሌሎችም ክፍተትን መሙላት ይችላሉ።*

*ምንአልባት: በኃይሉ ይደነቃል። በፊቱ ኃጢያተኛ ነው፡፡. ለመጠራት የታደለ ነበር።*

*1. ከኃጢያት ተመለስ 2. ዋጋውን ተምን*
*3. ራስህን ለክርስቶስ አደራ ስጥ*
*4. የክርስቶስን ማህበረሰብ ተቀላቀል።.*

### የመጀመሪያው እርምጃ፥ ከኃጢያት መመለስ (ጥያቄ 5-11)

**ጥያቄ 8-10:** የጥያቄ 8 የመጀመሪያ አንቀጽ አንብብ እና ከጭማሪ 2 ላይ ተመልከት (ገጽ 151)

*በቂ ጊዜ ካለ ተማሪዎች ጭማሪ 2ን እርስ በርስ እንዲያስረዱ መጠየቅ ትችላለህ።*

- የኢምራን እና የሻፊቅ ንግግርን እንዲያነቡ ሁለት ሰዎችን ጠይቅ። ኢየሱስ የሚያነጻው የትኛውን ነው? ለምን?

*ሻፊቅን፣ ምክንያቱም ኢየሱስ እንደሚያስፈልገው ያውቃል፡፡*

- እያንዳንዳችን ስለራሳችን እናስብ። እኛ ብዙ የምንመስለው ኢምራንን ወይስ ሻፊቅን?

*በግል የሚሰጥ ምላሽ*

- እንደው በጸጸት እና በእውነተኛ ንስሐ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

*ጥያቄ 9ን ተመልከት፣ ንስሐ በአዲስ አቅጣጫ መሄድ፣ የሕይወት ዘዬ ለውጥ ነው።*

- ሻፊቅ በእውነት ንስሐ ገብቶ ከሆነ፣ እኛ የምናውቀው እንዴት ነው?

*የሕይወት ዘዬው መለወጥ ነው።.*

## ሁለተኛ እርምጃ፡ ዋጋውን መረዳት (ጥያቄ 12-14)

**ጥያቄ 12:**

- ስምዖን ኢየሱስን የመከተል ዋጋ የተመነው እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ?
- አንተም በራስ ሕይወት ተመሳሳይ ውሳኔ ገጥሞሃል ውሳኔውንስ አድርገሃል

*ተማሪዎቹ እርስ በርስ የሚተማመኑ ከሆነ ክርስቶስን መቀበላቸውን ወይም እስካሁን ዋጋውን እየተመኑ መሆናቸውን ሊናገሩ ይችላሉ።*

**ጥያቄ 13-14:** ከሳጥን ውስጥ የኢየሱስን ቃል አንብብ።

- በአንተ አስተያየት የዚህ ታሪክ ትርጉም ምንድነው?
- ለጥያቄ 13 የጻፍከው መልሶች ምን ነበሩ
- ኢየሱስን ለመከተል ይህን ያህል ከፍተኛ ዋጋ መከፈል የተገባ ነው?
- ለጥያቄ 14 የሰጠህው መልስ ምን ነበር?

*. ክርስቶስን መከተል ብዙ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል፣ ነገር ግን እሱ ይገባዋል። እሱ ከእንቁ ይልቅ ዋጋው እጅግ ውድ ነው! እሱን ብንከተል ይገባዋል።*

*እሱም ታላቅ ዋጋን ከፍሏል።*

## ሦስተኛ እርምጃ፡ ራስን ለክርስቶስ መስጠት (ጥያቄ 15-18)

**የታምነኛለህ ጨዋታን ማጫወት:** *ይህ እንቅስቃሴ ለሁሉም ሳይሆን በተወሰነ ዕድሜ ውስጥ እና ለአንዳንድ ሰዎች የሚሆን ነው። ለተማሪዎችህም የሚመች መሆኑን ወስን። ወይም ስለ ቻርለስ ብሎዲን የዩቱዩብ አጭር ፊልም ተመልከት እና ጥያቄዎችን አቅርብ።*



- የቡድኑን አባላት ባላቸው ቁመት እና ክብደት ተመሳሳይ የሆኑትን እና አንድ ዓይነት ጾታ ያላቸውን ጥንድ ጥንድ አድርጋቸው: : አንድ ሰው የሚወድቀው ሲሆን ሌላው ደግሞ የሚይዘው ይሆናል፡፡ የሚወድቀው ሰው ለሚይዘው ሰው ጀርባው በመስጠት እግሩን ገጥሞ ይቆማል፡፡ የሚይዘውም አንድ እግሩን ቀደም በማድረግ፣ እጁን ዘርግቶ የሚወድቀውን ለመያዝ ራሱን ያዘጋጃል: :
- *የሚወድቀውም የሚይዘው ዝግጁ መሆኑን ሊጠይቀው ይገባል፣ ከዚም ሰውነቱን ሰብሰብ በማድረግ ወደ ኋላ ይወድቃል። የሚዘውም ሰው እነሱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ከመውደቃቸው በፊት በጥንቃቄ መያዝ አለበት።*
- *የሚይዘውን እና የሚወድቀውን ሰው ቦታ አቀያይር።*

**የሚይዘውን ሰው ማመን:**

- *ራስህን ሙሉ ለሙሉ ለሚይዘው ሰው መስጠት የሚኖረው ስሜት እንዴት ነው?*
- *ራሳችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት ለሚይዘው ሰው ራስን ከመስጠት ጋር በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል። በመጀመሪያ አስፈሪ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሁል ጊዜ ስንያዝ የበለጠ ማመንን እየተማርን እንሄዳለን።*

**ጥያቄ 16:** የተሰጡትን ሦስት ምሳሌዎች አንብብ. *የደከመው ልጅ, ታማሚው እና መንገደኛው።*

- እነዚህ ሦስት ሰዎች አንዱ ሌላውን የሚያምነው ለምንድነው? *ሌላው ሰው የታመነ ነው ብለው ስለሚያስቡ*
- እኛም ኢየሱስን በተመሳሳይ መንገድ ልንታመነው እንችላለን? *አዎን፣ እሱ ከሁሉ ሰው ይልቅ ይታመናል*
- እኛ እሱን የታመነው ምን እንዲያደርግልን ነው? *ለምሳሌ፡ ኃጢታችንን ይቅር እንዲልልን፣ ወደ ህይወታችን እንዲመጣ፣ መልካም ማድረግ የምንችልበትን ኃይል እንዲሰጠን፣ እንዲጠብቀን፣ እንዲመራን፣ ወደ ገነት እንድንገባ፡*
- ስለመውደቅ እንቅስቃሴ እንዴት ይሰማ እንደነበር አስታውስ። አንተም ኢየሱስን በተመሳሳይ መንገድ በህይወትህ ሁሉም አቅጣጫ ልትታመነው ተችላለህ? *በግል የሚሰጥ ምላሽ*

## አራተኛ እርምጃ፡ ከአማኞች ጋር ህብረት ማድረግ (ጥያቄ 19-20)

**ጥያቄ 20:** በንግግር ሳጥን ውስጥ ያለውን የአስተማሪው ቃል አንብብ።

- አስተማሪው የገለጸው ሦስት የሰው ዓይነቶች ይትኞቹ ናቸው?
- አንተም ከእነዚህ ሰዎች የትኛው ነህ?



*የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ፣ የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን የተዘጋጁ፣ ስለዚህ ለማሰብ ብዙ ጊዜን የሚፈልጉ። ተማሪዎች አሁን እንዲናገሩ ወይም በዝግታ እንዲያሰቡበት፣ የተሻለውን መወሰን ትችላለህ።*

## ማጠቃለያ

| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ለዩነት ምንድነው? **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።**<br>• ይህን ስራ አብረኸ ልትሰራው የምትችለው ጓደኛ አለህ ?<br>• ከቀጣይ ሳምንት ስብሰባ በፊት ትምህርት 2ን አጠናቁ። | **በአንድነት ጸልዩ:**<br>እግዚአብሔርን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በግላችን ማወቅ ስለቻልን አመስግኑ። |
|---|---|

# ትምህርት2: በክርስቶስ ያለ አዲስ ሕይወት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. በክርስቶስ ባላቸው አዲስ ህይወት ይደሰታሉ።
ለ. 2 ቆሮንቶስ 5:17 ያሰላስላሉ
ሐ. እኛ አዲስ የሆነ ማንነትን፣ ውልደትን እና ፍጥረትን መቀበላችንን ይረዳሉ።
መ. ከአሮጌው ፍጥረት ጋር መንፈሳዊ ውጊያን ለማድረግ ዝግጁ ይሆናሉ።

**የባሕል መገለጫዎች:**

- ጅሃድ
- የጸሎት አቀማመጥ

**ዝግጅት:**
ለጥያቄ 19 አጭር ፊልም

## መክፈቻ

***ላዛሬው ትምህርት ጸልይ። የባለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:***

- ከትምህርት 1 ውስጥ አንድ ሰው ተግባራዊ ስራውን ያነባል።
- ስለዚህ በጥንቃቄ አስበሃል? በዚህም ጉዳይ በዛሬ ውይይታችን በኋላ እንነጋገርበታለን።

***ትምሕርት 2- የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:***

**ጥያቄ 1:** ሀ) አዲስ፤ ለ) የተመረጠ ሕዝብ
**ጥያቄ 2:** አሮጌ፣ አዲስ
**ጥያቄ 3:** በግል የሚሰጥ ምላሽ *ሁሉም ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ አንድ ነገር መጻፋቸውን ተመልከት*
**ጥያቄ 4:** ክርስቶስ፣ አዲስ፣ አሮጌ፣ አዲስ

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** ዛሬ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ስለሰጠን አዲስ ሕይወት እንማራለን። ይህም አዲስ የሆነ ማንነትን፣ ውልደትን እና ፍጥረት መሆንን ያካትታል። ደስ የሚል ነው!

## ውይይት

### መግቢያ እና ጥያቄ 1-4

**Questions 1-4:** Read together 1 Peter 1:1-2. *If learners don't yet have a Bible, print out the passage.*

- ይህን ደብዳቤ በእግዚአብሔር ምሪት የጻፈው ማነው? *ሐዋሪያው ጴጥሮስ ነው። ይህም በትምህርት 1 ላይ የተማርነው ያው ስምዖን ጴጥሮስ ነው።.*
- ጴጥሮስ ይህንን ደብዳቤ የተቀበሉትን ሰዎች የሚገልጻቸው በምን ቃል ነው? *'በእግዚአብሐር ለተመረጡ' (ለተመረጡ) ነገር ግን ይህች ዓለም ቤታቸው ላልሆነች ፣ 'ለተበተኑ', 'መጻተኞች እና እንግዶች' ብሎ ነው።*
- ከቤት እርቆ በእንግድነት መኖር የሚኖረው ስሜት እንዴት ነው? *በግል የሚሰጥ ምላሽ። /ጥያቄ 3/*

### የእኛ አዲሱ ማንነት (ጥያቄ 5-7)

**ጥያቄ 5:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- አንተ የማያምን (*ካፊር*) ወይም ከሃዲ (*ሙርታድ*) ተብለህ ታውቃለህ? ይሰማህ የነበረው እንዴት ነው?
- ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የእኛ አዲስ ማንነት ምንድነው?
- "በእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ" መሆን ስሜቱ እንዴት ነው?


*እነዚህ ከዚያ ለመጡ አማኞች የተለመዱ ጥቃቶች ናቸው።*

*በተለይ ማህበረሰባችን ቢገፋን፣ ይህ ድንቅ ነው።*

### የእኛ አዲስ ውልደት (ጥያቄ 8-13)

**ጥያቄ 8:** የአባ ጨጓሬውን እና የቢራቢሮውን ስዕል ተመልከት

- አባ ጨጓሬ ቢራቢሮ በሚሆንበት ጊዜ፣ የቀድሞ ማንነቱን እንደያዘ ነው ወይስ የተለየ ይሆናል?
- ይህ ምሳሌ እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ካገኘነው አዲስ ውልደት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?



*በአንድ በኩል ይህ አንድ ዓይነት ነው፣ ነገር ግን አዲስ ውልደትን በሚመስል ሂደት ውስጥ በማለፍ ሙሉ በሙሉ የተለየ እና ከፍ ብሎ መብረር የሚችል ይሆናል፥ ፤*

*በአንድ በኩል የቀደመውን ሰው ያንኑ ብንሆንም በመንፈስ ያደረግነው ለውጥ ግን አባጨጓሬ ወደ ቢራቢሮነት እንደ ተለወጠበት ሂደት በጣም ታላቅ ነው። እኛም በእግዚአብሔር መንፈስ በአዲስ አቅጣጫ በመኖር ልዩነቱም በሕይወታችን የሚታይ ነው።*

**ጥያቄ 11:** ከሳጥን ውስጥ (1ኛ ጴጥሮስ 1:3) አንብብ

- ክርስቶስን ለሚከተሉ አዲስ ውልደት የሚሰጥ ማነው?
- እሱ ይህን የሚያደረገው ለምንድነው?
- ይህ አዲስ ውልደት ለእኛ የሚሰጠን ምንድነው?

*የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ እግዚአብሔር ራሱ ከታላቅ ምህረቱ የተነሳ።*

*የሕይወት ተስፋ፣*
*ይህም ከሞት በኋላ እንኳን የሚቀጥል ስለሆነ፣ ባለን አዲስ ሕይወት ልበ ሙሉ መሆን ይቻላል።*

**ጥያቄ 12:** ዶክተሩ ያለውን አንብብ እና ሦስት ሰዎች ሦስቱን ምላሾች እንዲያነቡ ጠይቅ

- በመንፈስ ለታመሙ ሰዎች አዲስ ውልደትን እንደሚሰጠው ኢየሱስ የተመሰለውን ዶክተር አስብ
- ታማሚ ሀ ምን ዓይነት ሰው ነው?
- ታማሚ ለ ምን ዓይነት ሰው ነው?
- ታማሚ ሐ ምን ዓይነት ሰው ነው?
- ስለዚህ እኛ መንፈሳዊ አዲስ ውልደትን የምንቀበለው እንዴት ነው?



*ሀ: በክርስቶስ አምኖ ግን ለመከተል የሚፈራ*

*ለ: በክርስቶስ ፈጽሞ የማያምን*

*ሐ: የክርስቶስን ግብዣ አምኖ፣ በህይወቱ እሱን ያመነ እና የተቀበለ*

*ልክ እንደ ታማሚ ሐ የክርስቶስን ግብዣ በመታመን፣ እሱን እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ እንለዋለን። /ጥያቄ 13/*

**ጥያቄ 13:** የንግግር ሳጥኑን አንብብ። *ይህን እርምጃ ያልወሰደ ማንም ሰው አንተን በግል እንዲያናግርህ ጋብዝ፡*

## አዲስ ፍጥረት መሆናችን (ጥያቄ 14-16)

የተለያዩ ተማሪዎች በንግግር ሳጥን ውስጥ ያሉትን የተለያዩ አስተያየቶች ያንብቡ።

- እኛስ እንዴት ነን፣ የክርስቶስ ተከታዮች ከሆንበት ጊዜ ጀምሮ ስሜቶቻችን ወይም ባህሪያችን እየተለወጠ ነው? በጥያቄ 15 ውስጥ የጻፍከው ምን ነበር? *ተማሪዎች የሚያካፍሉት አንድ ነገር እንዲኖራቸው በጥናት ጊዜ የሰጡትን የግል መልስ እንዲጽፉት አስታውሳቸው። ክርስቶስን እስካሁን መከተል ያልጀመረ ተማሪ ይህን መመለስ አይችልም ነገር ግን በሌሎች አማኞች ሕይወት ውስጥ ያዩትን ለውጥ መናገር ይችላሉ።*
- *ይህን ከተከፋፈሉ በኋላ ወይም በክፍለ ጊዜው ማብቂያ ላይ፣ በእኛ ሕይወት ስለሆኑት እነዚህ ለውጦች እግዚአብሔርን በአንድነት አመስግኑ።*

## መንፈሳዊ ውጊያችን (ጥያቄ 17-20)

**ጥያቄ 17-18:** በጥያቄ 18 ውስጥ ያለውን ስዕል ተመልከት፡

- አሮጌውን ፍጥረት የሚያሳዩት ሰዎች የትኞቹ ናቸው? አዲሱን ፍጥረት የሚያሳዩት ሰዎች የትኞቹ ናቸው?
- አንተ የምትታገልበት 'የአሮጌው ፍጥረት' ነገሮች ምንድናቸው?
- በጥያቄ 17 ውስጥ ያለውን ጥቅስ አንብብ። ከአሮጌው ፍጥረታችን ጋር የምናደርገውን ውጊያ ለማሸነፍ ማድረግ ያለብን ምንድነው?



*ልክ ልብስ እንደመቀየር - አሮጌውን አውልቀህ አዲሱን ልበስ.*

**ጥያቄ 19:** የገበሬውን ምሳሌ አንብብ።

- ፍየሎቹ የሚወክሉት ምንድነው?
- ጥቁሩን ፍየል የምትመግበው በምን መንገድ ነው?
- በዚህ ፈንታ ነጩን ፍየል ለማጠንከር ማድረግ የምትችላቸው ነገሮች ምንድናቸው?

*አማራጭ፡ ከዩቲዩብ ላይ የነጭ እና ጥቁር ፍየል የውጊያ ፊልም አሳይ* [http://www.youtube.com/watch?v=HG24G-dGzrQ](http://www.youtube.com/watch?v=HG24G-dGzrQ) *እንደ አማካሪ የራስህንም የሕይወት ውጊያዎች አካፍል። ወጊያውም ቀጣይ መሆኑን ግለጽ። እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካኝነት በእኛ ውስጥ በመኖር የምናሸንፍበትን ጉልበት ይሰጠናል። ፊልጵስዩስ 4:13*

**በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ ተለማመዱ (በሉት):** *ጥያቄ 20 አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽ. ቅዱስ ይጠቀማል* "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤" (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17)

## ማጠቃለያ

| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ። | **በአንድነት ጸልይ:** |
| --- | --- |
| • የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?<br>• የቤት ውስጥ ጥናትህን ቀጥል! ምን እንደተማርክ ለማካፈል በየሳምንቱ ተዘጋጅቶ መምጣት በእውነት አስፈላጊ ነው። | እግዚአብሔርን በእኛ ውስጥ ስላኖረው ለውጥ አመስግነው እና በየቀኑ ላለብን መንፈሳዊ ውጊያ እንዲረዳን ጠይቅ። |

# ትምህርት 3: እግዚአብሔር አባት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. እግዚአብሔርን በደስታ አባታችን ነው ይላሉ።
ለ. የክርስቶስ ተከታዮች ለምን ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሉ መግለጽ፡፡
ሐ. 1ኛ ዮሐንስ 3፡1 ማሰላሰል።
መ. የእግዚአብሔርን ቀድመ-ሁኔታ የለሽ ፍቅር በመያዝ ይህንንም የፍቅር ምሳሌ በልጆች ላይ ለመተግበር መሞከር።

**የባህል መገለጫዎች:**

- እግዚአብሔርን 'አባት' ብሎ መጥራት
- ለእግዚአብሔር ያለን ቅርበት

**ዝግጅት:**
'የአባት የፍቅር ደብዳቤ' አጭር ፊልም ወይም በማጠቃለያው ላይ መዝሙር.

## *መክፈቻ*

*ላዛሬው ትምህርት ጸልይ። የባለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:* ***አንተ ከአሮጌው ፍጥረት ሦስት መጥፎ ልምዶች ጋር ትዋጋለህ? ይህ ለአንተ እንዴት ነበር? ትግል ነበር? መሻሻል እያመጣህ ነው?***

***ትምህርት 2- የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:***

**ጥያቄ 1:** ሀ) አባት፤ ለ) አባት

**ጥያቄ 2:** ሀ) እውነት፤ ለ) እውነት፤ ሐ) እውነት

**ጥያቄ 3:** ታላቅ ፍቅር፣ አባት በእኛ ያለው ፍቅር፣ የእግዚአብሔር ልጆች፣ እኛ የሆነው ነው።

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** ሙስሊሞች ወደ እግዚአብሔር እንደ አባት መጸለይ እንደ መዘበት ወይም ሽርክ ነው ብለው ያስባሉ! (የባህል መገለጫዎችን ተመልከት)። ይህ ግን በመንፈሳዊ መንገድ ይቻላል። እንደ ክርስቶስ ተከታይ፣ይህ ለእኛ ታላቅ ዕድል ነው።

## *ውይይት*

### ኢየሱስ እግዚአብሔርን 'አባት' ብሎ ጠራው (ጥያቄ 3-9)

**ጥያቄ 4:** በሳጥን ውስጥ ያለውነ ክፍል አንብብ።

- ልጅ እና አባት የሚለውን ምን ያህል ጊዜ አከበብክ?
- የእኛ ሙስሊም ጓደኞቻችን ልጅ እና አባት የሚለውን ስያሜ የሚቃወሙት ለምንድነው?

- *ልጅ የሚለው 4 ጊዜ፣ አባት የሚለው 4 ጊዜ*
- *እነሱም ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ልጅ እንዲኖረው ከሴት ጋር ተገናኝቷል የሚል ትምህርት አላቸው ብለው ያስባሉ። ይህ ሃሳብ ግን ለክርስቲያኖችም የሚያስቆጣ ነው።*

**ጥያቄ 6:** ብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ቀርበው የኖሩ፣ የእሱን ልቀት ያሳዩ ወይም በእሱ ስልጣን የገዙ አንዳንድ የተለዩ ሰዎችን እንዴት 'ልጅ' እያለ እንደጠራቸው አይተናል።

- በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር አብ ቅርብ እንደሆነ የሚናገረው ሐረግ የቱ ነው?
- ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብን ልቀት ተካፋይ እንደሆነ የሚናገረው ሐረግ የቱ ነው?
- ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ስልጣን ገዢ እንደሆነ የሚናገረው ሐረግ የቱ ነው?

- *'አብ ወልድን ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል'*
- *'...ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና'፣ 'አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና።'*
- *'ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።'. 'የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው።'*

**ጥያቄ 7:** የመጀመሪያውን ክፍል አንብብ።

- *በአንተ ባህል ውስጥ አንድ ሰው ልጅ ተብሎ ሲጠራ በእርግጥ በስጋ ያልተወለደ ሊሆን የሚችል ምሳሌን ማሰብ ትችላለህ?*

**ጥያቄ 8:** የመጀመሪያውን ክፍል አንብብ።

- ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ባህሪ ተካፋይ ለመሆኑ ያስቀመጠው ምንድነው?

በጥያቄ 8 ውስጥ የቀረኸን አንብብ። *ጥንድ ጥንድ በማድረግ ከፋፍል። አንድ ሰው የክርስቶስ ተከታይ ሚናን ይጫወታል። ሌላውን ሰው ደግሞ ክርስቲያን እንዳልሆነ በመውሰድ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ለምን 'የእግዚአብሔር ልጅ' ብለን እንደምንጠራው ለሦስት ደቂቃ ያህል ማብራሪያ ይስጥ። አሁን ደግሞ ይቀያየሩና ሁለተኛው ሰው ለአንደኛው ሰው ተመሳሳይ ነገር ያብራራለት።*

## እኛም እግዚአብሔር አባት ብለን ልንጠራ እንችላለን (ጥያቄ 10-18)

**ጥያቄ 11:** 1ኛ ዮሐንስ 3፡1 እና የጥያቄ 11 የመጀመሪያ ክፍል አንብብ።

- ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ ብለን መጥራት እንችላለን። እኛም ደግሞ በክርስቶስ እግዚአብሔርን አባታችን ብለን ለመጥራት የወሰድነውን ትልቁን እርምጃ ተወያዩበት።
- እኛ እግዚአብሔርን በመንፈሳዊ መንገድ እንደ አባታችን ማነጋገር የቻልነው ለምንድነው?

*ምክንያቱም እግዚአብሔር 'በእኛ ታላቅ ወንድም' በሆነው ኢየሱስ በኩል መንፈሳዊ ልጆቹ አድርጎ ስለተቀበለን ነው።*

.

***በቃል የተጠናውን ጥቅስ 1ኛ ዮሐንስ 3፡1 በተግባር እንዲቀመጥ አድርግ።.***

- ቃላቱን በተለያዩ አነስተኛ ወረቀቶች ላይ ጻፍ እና ቀላቅላቸው።
- ተማሪዎቹ በትክክለኛ ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡት እና ጥቅሱን በቃል እንዲሉት ጠይቅ።
- ከዚያም 2 ወይም 3 ወረቀቶችን አስወግድ እና ጥቅሱን በድጋሚ በቃል እንዲሉት አድርግ።
- ምንም ወረቀት ሳይኖር ተማሪዎቹ ሙሉ ጥቅሱን በቃል ማለት እስኪችሉ ድረስ ቀጥል፡ቃላቱን በተለያዩ ፡

**ጥያቄ 12:** *ሙሉ ጥያቄውን አንብብ።*

- በእኛ ምድራዊ አባታችን ፍቅር እና በሰማያዊ አባታችን ፍቅር መካከል ያለ አንድ ልዩነት ምንድነው?
- እግዚአብሔር የሚወደን ሁል ጊዜ ነው ወይስ እኛ ጥሩ በሆንን ጊዜ?
- እኛስ ልጆቻችንን መውደድ ያለብን ሁል ጊዜ ነው ወይስ እነሱ ጥሩ በሆኑ ጊዜ ብቻ?

*የእኛ ምድራዊ አባታችን የሚወደን እንዳገኘነው መከናወን ልክ ሊሆን ይችላል፣ ሰማያዊው አባታችን የሚወደን ግን እንደትም ብንሆን ነው።*
*ሁል ጊዜ።*
*ሁል ጊዜ።*

**ጥያቄ 13 ሀ:** ከምድራዊ አባቱ ጋር ፍጹም የሆነ ግንኙነት ያለው ሰው የለም፡ ፡

- ልጅ ሆነህ በምታድግበት ጊዜ ምድራዊ አባትህ ምን እንደሚመስል መናገር ትፈልጋለህ?

*ሰዎች እንዲያከናሉ አበረታታቸው፣ ነገር ግን የማያስደስት ትውስታ ላላቸው አንዳንዶች፣ ምንም ማለት ስለማይፈልጉ ወይም አባታቸውን ማዋረድ አድርገው ሊያስቡ ስለሚችሉ ጥንቃቄ አድርግ።*

**ጥያቄ 13 ለ:** የጥያቄ 13ን ሁለተኛ እና ሦስተኛ አንቀጽ አንብብ

- እግዚአብሔርን ልክ ቅስማችን እንዲሰበር እንዳደረጉን አባቶች እንፈራዋለን?

*ተማሪዎች ፍርሃታቸውን በታማኝነት እንዲናገሩ ይሁን፤ እግዚአብሔርም ፈጽሞ እንደሚይጥለን አረጋግጥላቸው! እሱም 'አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና (ዕብራውያን 13:5) ብሎ ተስፋ ሰጥቶናል።*

**ጥያቄ 14-15:** የጥያቄ 15ን ሳጥን አንብብ (ሉቃስ 15:20-24)

- ኢየሱስ በተናገረው ታሪክ ውስጥ ስለ አባቱ ያለው በጣም አስደናቂ ነገር ምንድነው?
- በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእግዚአብሔር ያስተማረን ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

*ለብዙ ውርደት ምክንያት የሆነበት ልጁን እንኳን ደህና መጣ ብሎታል።*
*እግዚአብሔር እንደዚህ ቸር አባት ነው። እኛ በብዙ ባናስከብረውም እንኳን ስንመለስ ይቀበለናል ደግሞም ይቅር ይለናል።*

**ጥያቄ 16:** በሳጥን ውስጥ ያለውን የናስር ታሪክ አንብብ።

- ከመሃከላችን እንደናስር ገጠመኝ ያለው ሰው አለ?
- በናስር አባት እና በሰማያዊ አባታችን መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

*እነሱም ለጊዜው አልተገሩ ይሆናል ነገር ግን ቤተሰቦቻቸው በክርስቶስ ያላቸውን አዲስ እምነት በኋላ ሲያውቁ ይህ ሊሆን ይችላል።*
*የሰማዩ አባታችን ፈጽሞ አይጥለንም!*

**ጥያቄ 18:** *ሙሉ ጥያቄውን አንብብ።* ይህንን ጥቅስ በጋራ ከዘቡር (ከመዝሙር) ላይ ድገሙት። ***"አባቴና እናቴ ትተውኛልና፥ እግዚአብሔር ግን ተቀበለኝ።"***

## *ማጠቃለያ*

| | |
|---|---|
| ***ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:*** የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው? ***ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ***<br>• ይህንን ስራ አብሮህ ሊሰራ የሚችል ጓደኛ አለህ?<br>• የቤት ውስጥ ጥናትህን ቀጥል! | **ተመልከት:** ''የአባት የፍቅር ደብዳቤ' አጭር ፊልም በተለያዩ ቋንቋዎች በዩቱዩብ ላይ ማግኘት ትችላለህ።<br>**ወይም ዘምር:** ስለአባት ፍቅር የሚገልጽ ፍቅር.<br>**በአንድነት ጸልይ:** እግዚአብሔር ከማንኛውም ምድራዊ ኣባት በላይ ልንደገፈው የምንችለው አባት ስለሆነ እና እሱ ሁል ጊዜ ወላጆቻችን በተዉን ሰዓት ስለሚቀበለን አመስግነው። |

# ትምህርት 4: በመንፈሱ ኃይል ክርስቶስን መታዘዝ

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ለጌታ በሃሳብ፣ በቃል እና በስራ በሙላት ለመታዘዝ ይወስናል፡
ለ. 1ኛ ጴጥሮስ 1፡15 ማስላሰል።
ሐ. እግዚአብሔር ሦስትም አንድም መሆኑን ለማስረዳት የሚረዳ ምሳሌ መስጠት።
መ. ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን እንዲናፍቁ።

**የባህል መገለጫዎች:**

- ስላሴን መረዳት
- መስዋት እና ቃል ኪዳን
- ደቀ መዝሙርነት በሱፊ እሳቤ
- መንፈስ ቅዱስ እና ገብርኤል፣ ሙስሊሞች

**ዝግጅት:** ለማሳያ፡ ብርጭቆ፣ ትሪ (ጎርጓዳ ሳህን)፣ ትንሽ ቆሻሻ ድንጋይ፣ ውሃ በጆግ.

## መክፈቻ

**በማሳያው ጀምር:** *ቆሻሻ ድንጋይ በሞላበት ብርጭቆ ውስጥ ውሃ አፍስስ። .*



*ይህን የብርጭቆ ውሃ የሚፈልግ ማነው? ለምን? ይህንን በኋላ ላይ እንወያይበታለን። ለበኋላም ቆሻሻውን ብርጭቆ ወደ ጎን አስቀምጥ። ለሁሉም በንጹህ ብርጭቆ ውሃ ቅዳ።*

**ላዛሬው ትምህርት ጸልይ። የባለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** ለልጆች ቅደመ-ሁኔታ የሌለው ፍቅር የምናሳይበት መንገድ ምንድነው? እነሱንም በተግባር ላይ ያዋልከው እንዴት ነበር?

### *ትምህርት 3 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:*

**ጥያቄ 1:** ሀ)፣ ለ)፣ ሐ) እና መ) ሁሉም ትክክል ናቸው
**ጥያቄ 2:** ለ)
**ጥያቄ 3:** የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ። (1ኛ ጴጥሮስ 1:15)
**ጥያቄ 4:** ለ)

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:**
ጌታ ኢየሱስ እና መንፈሱ በእኛ ሕይወት እንዴት እንደሚሰራ እንማራለን። አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እንዴት አንድ እውነተኛ አምላክ እንደሆኑ አንድ ነገር ለመማር እንሞክራለን።

## ውይይት

### ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ሕይወት ይሰራል (ጥያቄ 2-6)

**ጥያቄ 4:** የመጀመሪያውን ክፍል አንብብ።

- 'ቃል ኪዳን' ምን ማለት ነው?
- እግዚአብሔር ይህን ትስስር ከእኛ ጋር ያደረገው እንዴት ነው?
- እኛ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ እሱ ሕዝብ ከተሳሰርን፣ ይህ ለእኛ ምን ማለት ነው?

'ይህም መተሳሰር' ብሎ የሚጀምረውን ሁለተኛ አንቀጽ አንብብ።

- ይህ ዓረፍተ ነገር ለእኛ ምን ማለት ነው?

*ቃል ኪዳን ጽኑ መስጠት ወይም መፍረስ የሌለበት ትስስር ነው (ጥያቄ 3 ተመልከት)*

በመስቀል ላይ ስለእኛ በፈሰሰው ክርስቶስ ደም ነው።

*እሱ በእሱ በኩል ቃሉን እንደማያፈርስ ሁሉ እኛም በእኛ በኩል ልናፈርስ አይገባም። እኛ በእሱ የተመረጠን ሕዝብ ነን።*

*ለኢየሱስ ያለን መስጠት ለቅዱስ ሰው ደቀ መዝሙር ከመሆን የበረታ ሊሆን ይገባል፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ማንም ቅዱስ ሰው ለእኛ ካደረገልን በላይ ነው!*

**ጥያቄ 5:** ሦስቱን ስዕሎች ተመልከት።

- ጌታ ኢየሱስን መታዘዝ በጣም አስፈላጊ የሚመስልህ በየትኛው ነው፣ በስራችን ወይስ በቃላችን ወይስ በሃሳባችን? *ሦስቱም በጣም አስፈላጊ ነው እና ከእነሱም ውስጥ የትኛውንም መተው አንችልም!* አንተ በሃሳብህ፣ በቃልህ ወይም በስራህ ክርስቶስን እንድትታዘዘው እሱ የረዳህ እንዴት ነው?

### መንፈስ ቅዱስ በእኛ ሕይወት ውስጥ ይሰራል (ጥያቄ 7-12)

**ጥያቄ 8:** ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ።

- በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት፣ መንፈስ ቅዱስ ማነው?
- የክርስቶስ ተከታይ ከሆንክ ጀምሮ፣ በሕይወትህ የእግዚአብሔር እልውና ከቀድሞ ይልቅ የበለጠ ተጨባች ነው? እባክህ ይህን ልምድህን አካፍል።

*በዓለም ውስጥ፣ በተለይም በክርስቶስ ተከታዮች ውስጥ የእግዚአብሔር እልውና አለ።*

**ጥያቄ 11:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- ለክፍል ሀ) የሰጠኸው መልስ ምንድነው እና ለምን?
- ለክፍል ለ) የሰጠኸው መልስ ምንድነው እና ለምን?
- በዚህ ትምህርት ውስጥ ያሉ ምሳሌዎች የረዱህ እንዴት ነው?



*ሀ) ፀሐይን ያለጨረር ወይም ሙቀት በፍጹም ልናያት ወይም ልትሰማን እንደማትችል በሳይንስ የተረጋገጠ ነው።*
*ለ) እግዚአብሔር ልጁን ባይልክ ኖሮ፣ እሱ ምን እንደሚመስል ማወቅ አንችልም ነበር። እሱ መንፈሱን ባይልክ ኖሮ፣ በእኛ ሕይወት ውስጥ ልናየው አንችልም ነበር።*lives.

**ስላሴን ማወቅ:** 1ኛ ጴጥሮስ 1:2-9 አንብብ።

*እኛ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ መረዳት ባንችልም እንኳን ይህ ጥቅስ እሱን እንደ ስላሴ እንዴት ማወቅ እንደምንችል ያሳየናል።*

- በቁጥር 2 እና 3 ውስጥ፣ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ያደረጉት ምንድነው?
- በቁጥር 5 መሠረት፣ በምድር ባለን ሕይወት የጠበቀን ምንድነው?
- በቁጥር 6 መሠረት፣ በፈተና ጊዜ መመለስ ያለብን እንዴት ነው?
- እግዚአብሔርን ማየት ባንችልም ወይም በሙሉ እንደ ስላሴ ባንረዳውም እንኳን፣ ስለእሱ የሚሰማን እንዴት ነው? (ቁ. 8-9)

*አብ አስቀድሞ አውቆናል፣ መርጦናል፣ አዲስ ውልደትም ሰጥቶናል በመንፈስም ቀድሶናል ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት.*

*የእግዚአብሔር ኃይል።*

*ልንደሰት ይገባል።*

*እንወደዋለን፣ እናምነዋለን፣ ሊገለጽ በማይችል እና ክብር ባለበት ደስታ እንሞላለን የነፍሳችንን መዳን እንቀበላለን።*

**ጥያቄ 12:** የመጀመሪያውን አንቀጽ በዝርዝር የተቀመጡትን ነጥቦች ጨምሮ አንብብ።

- ከዝርዝር ውስጥ ካሉት መካከል እስካሁን መንፈስ ቅዱስ እንድታደረግ ያስቻለህ የትኛውን ነው?
- ስለዚህ በእኛ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ መስራቱ አስፈላጊ ነው ወይስ አማራጭ?

## መንፈስ ቅዱስ ይቀድሰናል (ጥያቄ 13-16)

**ማሳያውን ቀጥል:** *ድንጋይ ያለበትን ብርጭቆ አንሳና እንዲህ በል፡*

- *ይህን ቆሻሻ ውሃ ማንም መጠጣት አይፈልግም! እንደዚህም ብርጭቆ፣ የእኛም ሕይወት በኃጢያት እና ሃፍረት የተሞላ ከሆነ ልንነጻ ያስፈልጋል።*
- *ይህን ብርጭቆ ለማንጻት ምን ማድረግ እንችላለን? ድንጋዩን ማስወገድ፣* በንጹህ ውሃ ብርጭቆውን ማጠብ- ይህንንም ድንጋዩን ስታስወግድ እና ብርጭቆውንም ንጹህ ውሃ ስትሞላው አሳይ።

**ጥያቄ 14:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- መቀደስ ማለት ምን ማለት ይመስልሃል? ምሳሌ ስጥ

*በሁለንተና መቀደስ እግዚአብሔርን መምሰል ነው! ለምሳሌ፡ ሃሳባችን ንጹህ ነው፣ ሌሎች እናንጻለን፣ መጥፎ ነገር አናደርግም እና የመሳሰሉት*

**ጥያቄ 15:**

- እኛ ዓላማ ያደረግነው ልክ ምንድነው?
- ለሰው እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆን ይቻላል?
- አስቀድመን ባነበብነው መሠረት የሚቀድሰን ማነው?

*በእግዚአብሔርን መለኪያ – እሱ ቅዱስ እንደሆነ እኛም ልንቀደስ ይገባል፡ ፡*

*አይቻልም፣ ይህ በራሳችን ብርታት የማይቻል ነው። በብዙ ሃይማኖቶች ውስጥ ለመቀደስ በብዙ የሚደከሙ ሰዎች በወደቁ ጊዜ እጅግ ያዝናሉ።*

*ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ እኛን ይቀድሰናል (ቁ. 2)። ንጹህ ውሃ ቆሻሻውን ብርጭቆ እንደሚያነጻው፣ እኛም በመንፈሱ እንነጻለን።*

**ጥያቄ 16:** በሳጥን ውስጥ ያለውን ጥቅስ በቃል ይጠና (1 ጴጥሮስ1:15) እና እጆቻችሁን ወደ ላይ በመዘርጋት በአንድነት ጸልዩ፣ እግዚአብሔር የበለጠ በመንፈሱ እንዲሞላህ ጠይቀው፡



## መንፈስ ቅዱስ ህይወታችንን ይሞላል (ጥያቄ 17-20)

**ጥያቄ 20:** ጥያቄ 20 ን በሙሉ አንብብ። *ይህንን ክፍል ብርጭቆ እና ውሃ በመጠቀም አሳይ። የጆግ እና የብርጭቆ ውሃ ተጠቀም፣ ሞልቶ የሚፈሰውን ወሃ ለመያዝ ትሪ ወይም ጎርጓዳ ሳህን ተጠቀም።*

- በየዕለቱ እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲሞላን በጸሎት በፊቱ እንቅረብ። ይህም መሞላት እንዳንድ ጊዜ ወዲያኑ፣ እንዳድ ጊዜ ደግሞ ቀስ እያለ የሚሆን ነው። የእሱ ትዕዛዝ በመሞላት እንድንቀጥል ነው። በየዕለቱ የበለጠ በመሞላት መቀጠል አለብን!

## *ማጠቃለያ*

| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** | **በአንድነት ጸልይ:** አሁን ጊዜው በህይወታችን ንጹህ እንዳንሆን ያደረጉንን ቆሻሻ ድንጋዮች በእግዚአብሔር ፊት የምንናዘዝበት ዕድል ነው። *ሰዎች ይህንን በራሳቸው ማድረግ እንዲችሉ የዝምታ ጊዜ ይኑር። ይህን ለማሳየት ድንጋዮችን መጠቀም ትችላለህ።* እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲያነጻን፣ እንዲቀድሰን እና በየዕለቱ አትረፍረፎ እንዲሞላን ጠይቀው። |
|---|---|
| • የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?<br>• ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።<br>• ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን ካለህ በሚቀጥለው ሳምንት አምጣ።<br>*የሚቻል ከሆነ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ ኪዳን ለሌላቸው ተማሪዎች እንዲኖራቸው እረዳቸው። /በቋንቋቸው/* | |

# ትምህርት 5:ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር /ጸሎት/

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**
ሀ. በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይችላል።
ለ. ጸሎት ሃይማኖታዊ ጉዳይ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር መሆኑን ይረዳል።
ሐ. የንስሐ፣ የምስጋና እና የልመና ጸሎቶችን ይማራል።
መ. የጌታን ጸሎት ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)።

**የባህል መገለጫዎች:**
- የጸሎት ስነ-መለኮት
- የሱፊ ተመስጦ
- የሙስሊሞች ጸሎት እና 'ውዱ' መንጻት
- የጸሎት ዝርዝር ማዘጋጀት

**ዝግጅት:** ወደ (ጥያቄ 14) በማምራት፣ ወረቀት፣ ፍላሽ ካርድ፣ እስክሪብቶ፣ መቀስ እና ማያያዥ ሽቦ።

## መክፈቻ

**አንድነት ጸልይ። የባለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲሞላህ በየቀኑ ትጸልያለህ? በአንተ ህይወት ውስጥ በየዕለቱ የሚኖረውን የመንፈስ ቅዱስ ስራ እንዴት ታየዋለህ?

**ያለፈው ሳምንት የጥቅስ የቃል ጥናት ክለሳ (1 ጴጥሮስ 1:15):** እያንዳንዱ ሰው ጥቅሱን እንዲለው ጠይቅ።

**ትምህርት 5 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**
ጥያቄ 1: ሀ) ጥያቄ 2: ይቅርታን መጠየቅ፣ማመስገን፣ መለመን።
ጥያቄ 3: ሳታቋርጡ ጸልዩ ጥያቄ 4: የጌታ ጸሎት በጥያቄ 14 ላይ እንደተቀመጠው

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** በጥያቄ 1 ውስጥ ያለውን ስዕል ተመልከት። እግዚአብሔር እንደ ታላቅ ንጉስ ነው። እሱ እኛን የሚሰማን ለምንድነው? *ምክንያቱም እሱ ልጆቹን መስማት የሚወድ ሰማያዊ አባታችን ነው!*

## ውይይት

### እግዚአብሔርን እንደ አባት ማነጋገር (ጥያቄ 2-5)

**ጥያቄ 3:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብቡ።
- እኛን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ቅዱሳን የተባሉ ሰዎች ምልጃ የማያስፈልገን ለምንድነው? *እኛ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆቹ ነን፣ ስለዚህ በፊቱ የመቅረብ መብት አለን!*

**ጥያቄ 4:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብቡ።
- ምልክት ያስቀመጥከው በየትኞቹ መልሶች ላይ ነው? *ለእግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር መናገር እንችላለን!*
- ለእግዚአብሔር መንገር ከባድ ሆነው ያገኘሃቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ለምን?

### የስርዓት እና የግል ጸሎት (ጥያቄ 6-10)

**ጥያቄ 9:**
- ሰዎች ስርዓታዊ ጸሎት እና ቀለል ያሉ ጸሎቶችንስ የሚያካሂዱት ለምን ዓላማ ነው *ለምሳሌ፡ ሰዎች ብዙ ጊዜ ሰላት (ስርዓታዊ ጸሎት) የሚያካሂዱት ምግብን ለመቀበል ነው ወይም ዱአ (ቀለል ያለ ጸሎት) ደግሞ ፍላጎታቸውን ለማግኘት ነው።*
- በጸሎት ውስጥ ከፍተኛ መሻታችን መሆን ያለበት ምንድነው? *እግዚአብሔርን ለመቅረብ እና ከእሱ ጋር ለመኖር*

**ጥያቄ 10:** የመጀመሪያውን አንቀጽ እና ሳጥን አንብብ (1 ጴጥሮስ 1:8)።
- ይህ 'ሊገለጽ የማይችል እና ክብር የሞላበት ደስታ' ተሰምቶህ ያውቃል? ምን እንደተሰማህ ግለጽ።
- አንዳንድ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ቀረቤታ በውዳሴ (በመድገም) ለመግለጽ ይሞክራሉ፣ ነገር ግን እኛ ወደ እግዚአብሔር ልብ መቅረብ የምንችለው እንዴት ነው? *በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፣ እሱ ወደ አባታችን ልብ መቅረቢያ መንገድ ነው።*

### ሳታቋርጡ ጸልዩ (ጥያቄ 11-13)

**ጥያቄ 12-13:**
- 1ኛ ተሰሎንቄ 5:17 እንድናደርገው የሚያዘን ምንድነው? *ሳናቋርጥ እንድንጸልይ።*
- ይህን መተግበር የሚቻለው እንዴት ነው? *እኛ እግዚአብሔርን ቀኑን ሙሉ በመንፈሱ አማካኝነት ልንቀርበው እንችላለን። ለምሳሌ፡ በጥያቄ 13 ውስጥ ከሌላ የተወሰደውን ንግግር ወይም የተማሪዎቹን የሕይወት ምሳሌ እይ።*
- በጥያቄ 13 ውስጥ ካሉ ዝርዝሮች መካከል የምትመርጠው አማራጭ የትኛውን ነው?
- 'ከመመገብህ በፊት' የሚለው አማራጭ በመጨረሻ የተቀመጠ ነው። የአንተም ሁኔታ የሚፈቅድ ከሆነ፣ ይህንን ልምድህ አድርገኸዋል? *ይህ ሊዳበር የሚገባው ጥሩ ልምድ ነው። ከሙስሊሞች ጋር የሚኖሩ ተማሪዎች እድሉ ላይኖራቸው ይችላል፣ አንዳንዶች ግን ምስክር ለመሆን ሊያደርጉት ይችላሉ።*

- በጥያቄ 13 በስተመጨረሻ ያለውን የንግግር ሳጥን አንብብ፡፡

## የጌታ ጸሎት (ጥያቄ 14-15)

**የጌታን ጸሎት መማር:** የኢየሱስ ደቀ መዛሙር: "እንጸልይ ዘንድ አስተምረን" ብሎ ጠየቀው፡፡ እሱም የጌታ ጸሎትን አስተማራቸው፡፡ *በእያንዳንዱ ተማሪ ቋንቋ አንድ ሰው ማቴ 6:9-13 እንዲያነብ ጠይቅ፡፡ ከዚያም ተማሪዎችም በቋንቋቸው የጸሎቱን ዓረፍተ ነገሮች ለየብቻ በተናጠል በተዘጋጁ ወረቀቶች ላይ መጻፍ አለባቸው፡፡ እነዚህንም ወረቀቶች በጠረጴዛ ላይ (በመሬት ላይ መሆን የለበትም!) ቀላቅላቸው እና ተማሪዎቹ በትክክለኛ ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡት ጠይቃቸው፡፡* በትምህርቱ የሚሳተፉት ጥገኝነት ጠያቂዎች ከሆኑ፣ ኃላፊዎች ጉዳያቸውን በሚከታተሉ ጊዜ የጌታን ጸሎት ሊጠይቋቸው ይችላሉ፣ ስለዚህ በቃል መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡

- የጌታን ጸሎት በመጸለይ የምናገኘው ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ አለ? ይህንንም አንድ ጊዜ ይልቅ አስር ጊዜ ብናደርገው የሚሰጠን የበለጠ ጠቀሜታ አለ?
- ለጸሎት የሚሻለው ቋንቋ የትኛው ነው ብለህ ታስባለህ፤ በእንግሊዝኛ፣ በአረቢኛ ወይስ በራስ ቋንቋ?

*የለም! ጌታ ኢየሱስ 'አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ፡፡' (ማቴ 6:7).*

*አንዳንዶች በአረቢኛ የተሻለ ነው ሊሉ ይችላሉ፣ እኛ ግን ለአባታችን ያለንን ምስጋና እና ጥያቄ በራሳችን ቋንቋ ማቅረብ እንችላለን፡፡*

## ይቅርታ መጠየቅ፣ ማመስገን እና ልመና (ጥያቄ 16-22)

**ጥያቄ 15:** የጌታ ጸሎት ሦስት ዓይነት ጸሎቶችን ማለትም ይቅርታ መጠየቅ፣ ማመስገን እና ልመናን ያካትታል፡፡ *ተማሪዎቹም የጌታን ጸሎት ዓረፍተ ነገሮች፣ በሦስቱ የጸሎት ዓይነቶች ርዕስ ስር እንዲከፋፍሉ ጠይቅ፡፡ እነሱንም በግርግዳ ላይ ልታጣብቅ ወይም በጠረጴዛ ላይ ልታስቀምጥ ትችላለህ፡፡*

**ጥያቄ 17:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ፡፡

- እግዚአብሔርን ይቅርታ ስንጠይቅ፣ እሱ ይቅር እንደሚለን እና እንደሚያነጻን እርግጠኛ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

*ምክንያቱም እሱ ፣ በ1ኛ ዮሐንስ 1:9 'በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡' የሚል ተስፋን ሰጥቶናል፡፡*

**ጥያቄ 20:** ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማቴዎስ 7:7-11 በጋራ አንብቡ፡፡

*ተማሪዎች ክፍሉን ለማግኘት እርዳታን ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ትምህርት 6 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንዴት እንደምንፈልግ ያብራራልናል፡፡*

- በቁጥር 7፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? — *ለምኑ፣ ፈልጉ፣ እና አንኳኩ፡፡ ይሰጣችሁማል፣ ታገኙማላችሁ፣*
- በቁጥር 7፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ተስፋ ምንድነው? — *ይከፈትላችሁማል፡፡ እነዚህ ተስፋዎች በቁ. 8 ላይ ተደግመዋል፡፡*
- ኢየሱስ በቁጥር 9-11 ውስጥ ያስቀመጠው ነጥብ ምንድነው? — *የሰማዩ አባታችን መልካም እና ለልጆቹ መልካም ነገሮችን መስጠት የሚወድ ነው፡፡*
- እግዚአብሔር እንዴት ጸሎትህን እንደመለሰ የሚሳይ ምሳሌ ስጥ፡፡
- በምንጸልይበት ጊዜ የምንጠይቀውን ሁሉ የማንቀበለው ለምንድነው?

*አንዳንድ ጊዜ የምንለምነው ለራሳችን መልካም አይደለም፡፡ አባት ልጁ ዓሣን ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? በፍጹም፣ እኛም የለመንነውን ባንቀበልም እግዚአብሔርን ግን እንደሚወደን አባታችን ልንታመነው እንችላለን፡፡ እሱ የሚስፈልገንን ያውቃል፡፡*

**ጥያቄ 22:** እኛ መጸለይ የምንችለው የነማንን ፍላጎት ጨምረን ነው? በጥያቄ 22 ላይ ምርጫህ የቱ ነው?

## *ማጠቃለያ*

| | |
|---|---|
| **ትግበራ:** የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ለዩነት ምንድነው? የጸሎት መንገድህን የምትለውጠው እንዴት ነው? | **አበረታታ:** የቤት ውስጥ ጥናተህን ቀጥል! በሚቀጥለው ሳምንት መጽሐፍ ቅዱስህን ወይም አዲስ ኪዳን አምጣ |
| **ክለሳ: ተግባራዊ ስራውን ተመልከት፡፡** የጸሎት ርዕሶችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ተወያዩ፡፡ በሳጥን ውስጥ ስም መጻፍ ስጋት ከሌለው፣ እንዲጽፉ አበረታታቸው፡፡ 'የጸሎት አጋር' እንዲኖራቸው ሙከራ እንዲያደርጉ አስተያየት መስጠት ትችላለህ፡፡ | **ጸሎት:** የጌታን ጸሎት ተጠቀም፡፡ እግዚአብሔርን ቀርበነው እንድንናገር እና 'ሳናቋርጥ መጸለይ' እንድንችል እሱን ለምኑት፡፡ |

# ትምህርት 6፡ የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ፡**
ሀ. በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን መውሰድ መጀመር።
ለ. በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ሦስት እርምጃዎችን መማር።
ሐ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻን ማግኘት መቻል።
መ. መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ጉጉ መሆን።

**የባህል መገለጫዎች፡**
- ሙስሊሞች እና የቃሉ መገለጥ
- የታሪክ ክስተት
- የእግዚአብሔር መገለጥ

**ዝግጅት፡** ዘጋቢ ማስታወሻዎች (ከተቻለ እንደ ዜና የተቀናበረ ምሳሌን ማምጣት)። ተማሪዎቹ በራሳቸው ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌላቸው በማንኛውም መልኩ የራሳቸውን አንድ ቅጂ ማግኘት የሚችሉበት መንገድ ፈልግ።

## መክፈቻ

**ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ፡** የጌታን ጸሎት ባፉው ሳምንት ብለሃል? *አሁን በአንድነት ጸልዩ። ባለፈው ሳምንት በወረቀት የተዘጋጀትን ዓረፍተ ነገሮች በመጠቀም፣ እያንዳንዱ ተማሪ አንዱን ብቻ በማስከበብ መጸለይ ይቻላል።*

**ትምህርት 6 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ፡** **ጥያቄ 1፡** ሀ) አድናን፤ ለ) ደካማ ሆነው ያድጉና ይሞታሉ

**ጥያቄ 2፡** 'ለ' ብቸኛው የተሟላ ትክክል መልስ ነው። 'ሀ' ግን 'ብቻ' ብሎ ስለሚናገር ትክክል አይደለም።
**ጥያቄ 3፡** ብሉይ, አዲስ **ጥያቄ 4፡** ተዘጋጅ፣ አንብብ፣ ጸልይ

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡** አንድን ሰው በምትወደው ጊዜ፣ ፍቅርህን የምታሳየው እንዴት ነው? *ለምሳሌ፡ ጊዜን አብረህ ትወስዳለህ፣ ከእነሱ ጋር ታወራለህ፣ እነሱንም ትሰማለህ።* ባለፈው ሳምንት እኛ ለእግዚአብሔር እንዴት እንደምንናገር ተምረናል፣ ዛሬ ደግሞ እሱ በቃሉ አማካኝነት (በመጽሐፍ ቅዱስ) እንዴት እንደሚናገረን እንማራለን። *መዝሙር 19፡9-10 አንድ ሰው እንዲያነበው ጠይቅ።*

## ውይይት

### የእግዚአብሔር ቃል ጥማት (ጥያቄ 1-5)

**ጥያቄ 1 እና 2፡** በጥያቄ 1 ላይ ያለውን ስዕል ተመልከት። ከዚያም በሳጥን ውስጥ ያለውን ጥቅስ አንብብ።

- ህጻን ልጅ ወተትን ለመጠጣት እንደሚጠማ እኛም በእውነት የእግዚአብሔርን ቃል እንጠማለን?

### መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ጥያቄ 6-10)

**ጥያቄ 8፡** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ። አንዳንድ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ልብ ወለድ መጽሐፍ ያስቡታል። በሰው የተጻፈ እና የሰውን ታሪክ የሚያወራ ያደርጉታል።

- ይህም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ መግለጽ የምንችለው እንዴት ነው? ጸሐፊዎቹ *"በእግዚአብሔር ተልከው ... በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ"*
- እኛም አለመዛባቱን ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? *ለተርጓሚዎች በሺዎች የሚቆጠሩ ቀደምት ጽሑፎች በሙዚየም ውስጥ ይገኛሉ - እነሱም እኛ የመጀመሪያዎቹ ቅጂዎች እንዳሉን በማስረገጥ ልበ ሙሉነትን ይሰጡናል።*

**ጥያቄ 10፡** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ምንድነው?
- መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አንተ አፍ መፍቻ ቋንቋ ማን እንደተረጎመው ታውቃለህ? ቅጂው አለህ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ስንል የመጀመሪያውን ጽሑፍ መቀየር ማለት አይደለም። ይህም እግዚአብሔር በአፍ መፍቻ ቋንቋችን እንዲናገረን ያመቻል!

*በዊኪፒድያ ላይ ማን በተለያየ ቋንቋ እንደ ተረጎመ ማየት እንችላለን፣ ['bible translations by language'](bible translations by language) ፈልግ።*

*በብዙ ቋንቋዎች የተጻፉ መጽሐፍ ቅዱሶችን ከሀገርህ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ልትገዛ ትችላለህ። በኢንተርኔት ቀጥታ መስመር ላይ የብዙ ቋንቋዎች እትም የሆኑ ዲጂታል እና በድምጽ የተቀረጹ መጽሐፍ ቅዱሶችን እናገኛለን። ለምሳሌ www.biblegateway.com በተንቀሳቃሽ ስልኮቻችንም ላይ መሆን የሚችሉ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መተግበሪያዎች አሉ።*

### የመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ክፍሎች (ጥያቄ 11-15)

**ጥያቄ 12-14፡** *መጽሐፍ ቅዱስ በመጠቀም እያንዳንዱን ክፍል አሳይ።*

- ተውራት (የሙሴ መጽሐፍት) እና ዛቡርን (መዝሙር) የሚያካትት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የትኛው ነው?
- ኢንጂል (ወንጌል) ተብሎ የሚጠራው የትኛው ክፍል ነው?
- አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን አጥፍቶታል? ለምን?

*ተውራት እና ዛቡር = ብሉይ ኪዳን*

*ኢንጂል = አዲስ ኪሀዳን. ብዙ ጊዜ አዲስ ኪዳን በሙሉ አዲስ ኪዳን ተብሎ ይጠራል። እያንዳንዱ ወንጌል 'ኢንጂል' ነው ብሎ በደንብ መናገር ይቻላል። አላጠፋውም፣ ሁለቱም ያስፈልጉናል። በአንድነት የከበረው የእግዚአብሔር ቃል ናቸው - እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከሰው ጋር የሚደርገው መስተጋብር ነው።*

**ጥያቄ 15፡** መጽሐፍ ቅዱስህን 'ማውጫ' ገጹ ላይ ክፈት። *እያንዳንዱ ተማሪ ጥቅሱን ማግኘት አለባቸው።*

ተማሪዎች 1 ጴጥሮስ 1:3 እንዲያገኙ እርዳቸው እና አንድ ሰው እንዲነበው ጠይቅ።

- ከእግዚአብሔር ጋር በየቀኑ የተለየ ጊዜ እንዲኖረን ከወሰንን፣ በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ላይ እንዳለው ህጻን ልጅ ጠንካራ እና ጤናማ ሆነን እንድናድግ ይረዳናል።
- ይህን በተግባር ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?

*ተማሪዎቹ የተለያየ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ካላቸው፣ ጥቂት የቃላት ልዩነቶች እንዴት ሊኖሩ እንደቻሉ ግለጽ። ይህ ግን በመጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ልነቱን እንድናስተውል ይረዳናል።*

## በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ መውሰድ (ጥያቄ 16-22)

**ጥያቄ 18:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- ለክፍል ሀ) እና ለ) የጻፍከው ምንድነው?
- በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን ለመውሰድ፣ እያንዳንዳችን የሚመቸንን ጊዜ እና ቦታ መምረጥ አለብን። ይህም ቋሚ ልምድህ እንዲሆን የሚረዳህ ምንድነው?

*እያንዳንዱ ተማሪ እንዲመልስ ጠይቅ። ይህንን መልስ በመጽሐፋቸው ላይ ያላስቀመጡ ተማሪዎች ካሉ እንዲሞሉ አስታውሳቸው።*
*ይህንንም በምናደርግ ጊዜ፣ ስለአስተያየታችን ልናስብ ይገባል በዚህም የበለጠ እንማራለን።*

**ጥያቄ 22:** ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ። *እያንዳንዱ ተማሪ አስተያየቱን እንዲሰጥ ጠይቅ።*

## ጭማሪ 1: በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ ጊዜ

***ደረጃ 1: ተዘጋጅ:*** ንጉስን የምትገናኝ ከሆንክ፣ የምትዘጋጀው እንዴት ነው? *ሰውነትን መታጠብ፣ ጥሩ መልበስ።*

- *እግዚአብሔርን ለመቅረብ መዘጋጀት የምንችለው እንዴት ነው? ተማሪዎች ደረጃ አንድን እንዲገልጹ ጠይቅ።*

**በአንድነት ተዘጋጁ:** ለምሳሌ፡ ጸሎቱን በጋራ አንብቡ ግን እያንዳንዱ ኃጢያቱን በግሉ ለእግዚአብሔር እንዲናገር ጠይቅ።

- 1ኛ ጴጥሮስ 1:13-15 ከፍ ባለ ድምጽ ይነበብ። *ከዚያም ተማሪዎች ለራሳቸው እንዲያነቡ ጠይቃቸው።*

*በብዙ ቋንቋዎች የምትሰራ ከሆነ በእያንዳንዱ አንድ ሰው በተለያየ ቋንቋ እንዲያነብ መጠየቅ ትችላለህ።*

- በአንተ ላይ የተለየ ስሜት የፈጠረብህ ገለጻ የቱ ነው?
- ይህ አስፈላጊ ነጥብ ለማስታወስ የምታደርገው ምንድነው? *ለምሳሌ፡ በማስታወሻ ደብተር ላይ መጻፍ፣ ማሰላሰል እና የመሳሰሉት።* ***ዘገባን በመስጠት፣ ምሳሌ ማሳየት***
- እግዚአብሔር ዛሬ ለአንተ የተናገረውን ነገር ለመታዘዝ የምታደርገው ምንድነው?
- ማንም ህጻን በአፉ የጠባውን ወተት መልሶ አይተፋውም! የእግዚአብሔርንም ቃል አንብበን የማንታዘዘው ከሆነ ፣ የምናደርገው ግን እንዲሁ ነው!

*ተማሪዎች እንዴት መታዘዝ እንደሚፈልጉ፣ ጥቅሶችን ፣ ጸሎታቸውን እና የመሳሰሉትን በዘገባ መልክ መጻፍ እንዲጀምሩ አበረታታ። በዚህም ለማገዝ የማስታወሻ ደብተር ልትሰጣቸው ትችላለህ። የሚቻል ከሆነ የራስህን ዘጋቢ ጽሑፍ አሳያቸው።*

***ደረጃ 3: ጸልይ*** **በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ጊዜ ሦስተኛው ደረጃ ምንድነው?**

- ጸሎት ከሰማያዊ አባታችን ጋር መነጋገር ነው። ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር የምንችለው የተለያዩ ነገሮች ምንድናቸው? *ደመቅ ተደርገው የተጻፉ የደረጃ ሦስት የተለያዩ ሐረጎች ተመልከት።* ***ይህን ደረጃ በመጠቀም ጸልይ።***
- *ባለፈው ሳምንት ለሌሎች ስለመጸለይ የጸሎት ዝርዝሮች ተነጋገርና። ከእናንተ መካከል ከዝርዝሩ በዚህ ሳምንት የተጠቀመ ሰው አለ? እንዴት ነበር? ሁሉም ዝረዝሩን እንዲጸፉ አበረታታ። ለምሳሌ፡ በዘገባው ደብተር ጀርባ*
- ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ጊዜ ሊኖርህ እንደሚችል ሌላ ሃሳቦች ወይም ጥያቄዎች አሉህ?

<table>
<tr><th colspan="2">ማጠቃለያ</th></tr>
<tr>
<td>ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ: የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው? እያንዳንዱ ሰው (አንተም) አካፍል<br>• ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ። የዚህ ሳምንት ስራ በጣም አስፈላጊ ነው። የተማርከውን በቀጣይ ሳምንት እንድታካፍል እንጠይቅሃለን።<br>• ይህን ስራ አብረኸ በቋሚነት (ለምሳሌ፡ በየሳምንቱ) ልትስራው የምትችለው ሰው አለ?</td>
<td>በአንድነት ጸልዩ: በዚህ ሳምንት የተለየ ችግር ያለበት ሰው ካለ ጠይቅ እና ስለችግሩም ጸልዩ። እግዚአብሔር ስለወደደን እና በየቀኑ ከእኛ ጋር ጊዜን መውሰድ ስለሚፈልግ አመስግነው። ከእሱ ጋር ጤናማ ጊዜን የማሳለፍ ልምዱ እንዲኖረን እኛን እንዲረዳን ጸልዩ።</td>
</tr>
</table>

# ትምህርት 7: የክርስቶስ ቤት ክርስቲያን አባላት

| **ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:** | **የባህል መገለጫዎች:** |
|---|---|
| ሀ. በአካባቢ ካሉ አማኞች ጋር ለመቀላቀል ፈቃደኛ መሆን። <br> ለ. ከ1ኛ ጴጥሮስ 2 ላይ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ሦስት መገለጫዎች መማር። <br> ሐ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፥9 አስላስል። <br> መ. በ1ኛ ጴጥሮስ ላይ ያሉ የተለያዩ ክፍሎች ማግኘት ይችላሉ። | • ሁለት የተለዩ ድንጋዮች <br> • የተከፋፈለ ማንነትን መፈወስ <br> • ኡማ <br> • ስጋቶችን መፋለም |

**ዝግጅት:** ሌጎ ወይም ተገጣጣሚ የህንጻ ክፍሎችን፣ 'የማዕዘን ድንጋይ' መሆን የሚችል ትልቅ ጡብ አዘጋጅ። /መግቢያ/

## መክፈቻ

**ብሰባው መጸለይ። ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር በመስጠት ጊዜን ማሳለፍ ችለሃል? ም ወደ ሰማያዊ አባትህ መቅረብህን እንድትቀጥል ረድቶሃል? ይህን ማድረግ ላልቻሉት ደግሞ፣ እንቅፋቶቹ ምን ነበሩ? እነሱንም .ህ ሳምንት ማስተካከል የምትችለው እንዴት ነው?

**ትምህርት 7 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሀ) ቤት፣ b) የተመረጠ፣ c) ቤተሰብ **ጥያቄ 2:** ኢየሱስ ክርስቶስ

**ጥያቄ 3:** እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ (1 ጴጥሮስ 2:9).

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፥** የተለያየ ቀለም እና መጠን ያላቸውን ሌጎ ወይም ተገጣጣሚ የህንጻ ክፍሎች

- *አንድ ሰው በዚህ ክፍል መኖር ይችላል? አይችልም- ምክንያቱም ቤት ለመሆን ጡቡ መገጣጠም አለበት፣ በተለያዩ ጡቦች ቤት መገንባት ለመጀመር ትልቅ የመሠረት ድንጋይ ወይም ትልቅ ጡብ አስቀምጥ።*

ዛሬ ደግሞ ስለክርስቶስ ማህበረሰብ - ቤት ክርስቲያን፣ ወይም ስለ አማኙ ማህበረሰብ እንግራለን።

## ውይይት

### መግቢያ (ጥያቄ 1-2)

**ጥያቄ 1:** በንግግር ሳጥን ውስጥ ያለውን የመጂድ ሃሳብ እና ጥያቄ 1 ን አንብብ።

- ስለመጂድ የምታስበው ምንድነው? ለጥያቄ 1 የጻፍከው ምንድነው? *ከእስልምና ለመጡ የክርስቶስ ተከታዮች በአንዳንድ ሀገሮች በነጻነት መሰብሰብ ሲችሉ፣ በሌላ ቦታ ደግሞ አደገኛ ሊሆን ይችላል፡፡*
- ከጥያቄ 2 በኋላ የመምህሩን የንግግር ሳጥን አንብብ።

### መንፈሳዊ ቤት (ጥያቄ 3-10)

**ጥያቄ 3:** 1ኛ ጴጥሮስ 2:4-8 አውጣና *እንዲነበብ ጠይቅ፡፡*

- በቁ..5 ውስጥ እኛ እንደ ህያዋን ድንጋዮች አብረን ምንድነን?
- ቁጥር 6 እና 7 ስለ 'የማዕዘን ድንጋይ' ይናገራል። የማዕዘን ድንጋይ በህንፃ ውስጥ የሚኖረው ሚና ምንድነው?
- በዚህ ስፍራ እንደ ከበረ የማዕዘን ድንጋይ የተገለጸው ማነው ብለህ ታስባለህ? *በእግዚአብሔር የተመረጠው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ቁ.6) እና ለተከታዮቹ የከበረ ነው (ቁ.7) በሌሎች ግን የተናቀ (ቁ.7) በእሱም ፍርድን ይቀበላሉ (ቁ. 8)፡፡*

እያንዳንዱ ተማሪ 'መንፈሳዊ ቤት' የሚለውን ማግኘት መቻላቸውን አረጋግጥ።

*ከስር ማዕዘን ላይ የሚቀመጥ ሲሆን እና የሁሉንም ግርግዳ አቅጣጫ የሚወስነው ይህ ነው። በሌጎ ለተሰራው ህንጻ የመሠረት ድንጋይ የሆነውን አሳይ፥*

*ለአንተ ቡድን አመቺ ከሆነ ይህንን የማዕዘን ድንጋይ ከእስልምና ካባ ጋር አነጻጽር።*

- **ጥያቄ 6:** የመጨረሻውን አንቀጽ አንብብ።
- ትክክለኛው መልስ ምንድነው? *ለ)*
- በእኛ ከተማ ውስጥ፣ የክርስቶስ ተከታዮች ለስብሰባ የሚመቻቸው ቦታ የት ነው? *አማራጮች ላይ ተወያዩ*

- በአንዳንድ ሀገሮች ቤተክርስቲያን እንደ ተቋም የለችም፣ በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ አማኞች በርካታ የመሰብሰቢያ ቦታ አላቸው። ይህም ቢሆን ግን ከእስልምና የመጡ የክርስቶስ ተከታዮች በቤተክርስቲያን ህንፃ ውስጥ ከመሰብሰብ ይልቅ በቤት ውስጥ ህብረት ማድረግን ሊመርጡ ይችላሉ፥

- **ጥያቄ 7:** 'ጌታ ኢየሱስ ተከታዮቹን እንዲህ አላቸው…' ከሚለው በመጀመር ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ።
- ዛሬም በዚህ ስፍራ፣ ሁለት ወይም ሦስት ሆነን የተሰበሰብነው በኢየሱስ ስም ነው?
- ስለዚህ ኢየሱስ በተለየ መንገድ በመካከላችን ይገኛል? በአይናችን ባናየውም፣ በመንፈሱ ግን እሱ ከእኛ ጋር ነው።
- ከሌሎች አማኞች ጋር ለአምልኮ በምትገናኝ ጊዜ የእሱ ህልውና ይሰማሃል? (ጥ. 9 ተመልከት)

## የተመረጠ ሕዝብ (ጥያቄ 11-18)

**1ኛ ጴጥሮስ 2:9-10 አንብብ:** በቁጥር 9 ላይ በጣም የወደድከው ሐረግ የትኛውን ነው፣ ለምን?

- ቁጠር 10 ምን እንዲሰማህ ያደረግሃል? ይህ *ከእስልምና ለመጡ አንዳንድ አማኞች በክርስቶስ ያገኙትን አዲስ ማንነት እና የእሱን ማህበረሰብ በብርቱ ስለሚያረጋግጥላቸው ብዙ ትርጉም ይሰጣቸዋል።*

> በቃል የሚጠናውን የ1ኛ **ጴጥሮስ** 2:9 **ጥቅስ በጨዋታ መልክ መለማመድ።** *'እኛ ማነን?' ብለህ አንድ ሰው ጠይቅ። እነሱም 'የተመረጠ ሕዝብ' ብለው ይመልሳሉ። ያ ሰው ደግሞ አጠገቡ ያለውን ሰው 'እኛ ማነን?' ብሎ ይጠይቅ እና 'የንጉስ ካህን እና የመሳሰሉትን እያሉ ይመልሳሉ። እያንዳንዱ ሰው በልበ ሙሉነት ሐረጉን መናገር እስኪችሉ ድረስ እንዲደግሙት አድርግ።*

**ጥያቄ 14:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- አንተ የክርስቶስ ተከታዮችን የተቀላቀልከው ከየትኛው ሕዝብ ወይም ብሔር ነው?
- በእነሱ መካከል የጋራ ሆኖ ያገኘኸው ምንድነው ?
- በአንተ ሁኔታ ውስጥ፣ ለመገናኘት የተሻለ ሆኖ ያገኘኸው ከራስህ ብሔር አማኞች ጋር ነው ወይስ የተለያየ ብሔር ባለነበት ቡድን ውስጥ ?

*ልክ እንደነዚህ የተለያየ ቀለም እንዳላቸው ጡቦች እኛ ሁላችን ልዩ ልዩ ነን ነገር ግን ሁላችን በአንድነት ውብ የሆነ ዓለም አቀፍ የአማኝ ማህበረሰብ ልንፈጥር ይገባል።*

*ለሁለቱም ተግባራዊ የሆነ ጠቀሜታ እና ሁለቱንም በተለየ መንገድ የምናቀናጅበት አካሄድ ይኖራል። አማራጮቹን ተወያዩበት።*

**ጥያቄ 15:** የጥያቄውን የመጀመሪያ ክፍል አንብብ።

- በዚህ ጥቅስ መሠረት፣ እግዚአብሔር እኛን የጠራን ወደ ምንድነው?
- እግዚአብሔር እኛን የጠራን ለምን ዓላማ ነው?
- እኛ ስለዚህ ምን እናድርግ?

*ከጨለማ ወደ ብርሃን።*

*'የእሱን በጎነት እንድትናገሩ'፣ ቁ. 9 ተመልከት*

*ስለእግዚአብሔር ታላቅ እና በጎ ስራ ለሌሎች ሰዎች ለመናገር።*

**ጥያቄ 16:** ይህን ስዕል ተመልከት። እነዚህ ሁለት ብርቱ ሴቶች ስለ ክርስቶስ ብርሃን እንዲሆኑ እሱ እንደጠራቸው ያውቃሉ፡ ፡ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራ ለማንም ሰው ለመናገር ያለህ ዕድል ምንድነው?

## ቤተሰብ (ጥያቄ 19-22)

**ጥያቄ 22:** ጥያቄውን አንብብ። ደመቅ ባለ ጽሑፍ ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩበት።

- **በሳጥን ውስጥ ያለውን የመምህሩን ንግግር አንብብ።** ለሙስሊም ቤተሰቦችህ፣ ራስህን እና የአንተን እምነት የምትገልጸው እንዴት ነው?
- ለእነሱ ለመንገር የምትመርጠው ምን ብለህ ነው 'ክርስቲያን ሆኛለው' ወይም 'የኢሳ አል መሲህ ተከታይ ሆኛለው' ወይስ የተለየ ነገር?
- እነዚህ የተለያዩ ቃላቶች ለእነሱ እና ለሌሎች ሙስሊሞች ምንድናቸው?

*ለእግዚአብሔር ቃል ከታዘዝን እርስ በርሳችን በክርስቶስ እንደ ወንድማማቾች እና እህትማማቾች እንቀባበላለን። የብሔር ወይም ማህበራዊ ማንነታችንን አንጥልም ግን በክርስቶስ ያለን ማንነት ከሁሉ የላቀ ነው።*

*በአንዳንድ አውድ ውስጥ ክርስቲያን የሚለው ቃል ከአልኮል መጠጥ ጋር፣ ከአሳማ ስጋ ጋር፣ ከልቅ ወሲብ ጋር እና ፀረ-ሙስሊም ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። በሌሎች አውድ ውስጥ ደግሞ ስለ ክርስትና ትክክለኛ መረዳት ሊኖር ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ አማኞችን ለመጥቀስ የተለያዩ ቃላትን ይጠቀማል። ለዚህም ምርጫችን በግል የሚወሰን እና በሁኔታችን ላይ የተመረኮዘ ነው፡፤*

## የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ትፈልጋለህ? (ጥያቄ 23-25)

**ጥያቄ 24:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ። እዚህ የጻፍከው ምን ነበረ?

- መጂድስ፣ እንደ ክርስቶስ ተከታይ ከሌሎች ጋር በሞቅታ መቆየት የሚችል ይመስልሃል?
- በጥያቄ 1 ውስጥ የጻፍከውን በድጋሚ ተመልከት። ከዚህ በኋላ ለመጂድ የምትሰጠው ምክር ምንድነው?

**ጥያቄ 25:** ልክ እንደምንገነባው ቤት፣ ብርቱ የክርስቶስ ማህበረሰብ ለመሆን ጠንካራ ግንኙነት ያስፈልገናል።

- ይህን ማህበረሰብ እየገነባን መቀጠል የምንችለው እንዴት ነው?
- ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር ለመገናኘት ያለህ ወይም የምትችለው ዕድል ምንድነው?

## *ማጠቃለያ*

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?

- **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።**
- በዚህ ሳምንት ልታገኘው የምትችለው ቢያንስ ሌላ አንድ አማኝ አለ? አንዳንዶች ከሌላቸው፣ ከቡድኑ ውስጥ አንድ ሰው ወይም ከአንተ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ

**በአንድነት ጸልይ:** በክርስቶስ ስለሆኑት ስለእኛ ወንድሞች እና እህቶች *እግዚአብሔር አመስግነው እና እርስ በርስ መተማመን እንድንችል እንዲረዳን ጠይቀው።* እግዚአብሔር *እኛን* ብርቱ *መንፈሳዊ* ማህበረሰብ አድርጎ እንዲገነባን ጠይቀው።

# ትምህርት 8፡ የሁለት ማህበረሰብ አባላት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**
ሀ. የተወለደበትን ማህበረሰብ እና በክርስቶስ ያገኘውን አዲስ ማህበረሰብ ለማገልገል ይፈልጋል።
ለ. ስለጌታ ብለው በስልጣን ላይ ላሉ ሰዎች ለመገዛት ፈቃደኛ ይሆናሉ።
ሐ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡17 ማስላሰል።

**የባህል መገለጫዎች:**
- ከእ.የመ.አ እና የሙስሊሙ ማህበረሰብ

**ዝግጅት:** ወረቀት፣ ማርከር

## *መክፈቻ*

**በጋራ መጸለይ። *ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:*** ቢያንስ አንድ የክርስቶስ ተከታይን ተገናኝተሃል? ይህ አንተን የረዳህ እንዴት ነበር? መንፈሳዊ ብርታትን ሰጥቶሃል?

**ትምህርት 8 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**
***ጥያቄ 1:*** *ሀ) መንፈሳዊ ለ) ምድራዊ* ***ጥያቄ 2:*** *ተገዙ*
**ጥያቄ 3:** ሁሉን ማክበር ፣ ወንድሞችን መውደድ (1ኛ ጴጥሮስ 2፡17)

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡**እኛን የሚወክሉን ሁለት የተለያዩ ማህበረሰቦች ምንድናቸው? *(ለምሳሌ፡ ቤተሰብ፣ የስራ ቦታ፣ መንገድ፣ ቤተክርስቲያን)። ሁሉም ስለራሱ ማህበረሰብ እንዲያካፍል ጠይቅ፣ በመጨረሻም ለማመሳከር እንዲረዳ በማርከር ጻፋቸው።*
ዛሬ ደግሞ እኛ በአንድ ጊዜ እንዴት በሁለት ማህበረሰብ መወከል እንደምንችል እና ሁለቱንም እንዴት ለማገልገል መሞከር እንደምንችል እንወያያለን።

## *ውይይት*

### የሁለት ማህበረሰብ አባላት

**1ኛ ጴጥሮስ 2፡ 11-12 አንብብ:** *ሁሉም ክፍሉን ማግኘት አለበት።*
- ቁጥር 11 እኛን 'እንግዶች እና መጻተኞች' ወይም በሌላ ትርጉም 'ጊዜያዊ ነዋሪ' ብሎ የጠራን ለምንድነው?
- የማያምኑ ሰዎች ባህሪያችንን በቅርበት ይከታተላሉ። በቁጥር 12 መሠረት፣ እኛ በእነሱ መካከል መኖር ያለብን እንዴት ነው?

*ምክንያቱም የእኛ እውነተኛ ቤታችን ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም መኖር ነው። ጥ. 1ን*

*ምንም እንኳን እነሱ መጥፎ አደረጋችሁ ብለው ቢከሱንም ሊያዩት የሚችሉትን መልካም ኑሮ መኖር ነው።*

**ጥያቄ 2:** *የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።*
- እግዚአብሔር እሱን እንድናገለግለው የጠራን በየትኞቹ ሁለት ማህበረሰቦች ውስጥ ነው?
- አንድ ሰው 'መንፈሳዊውን እንጂ ምድራዊውን ማህበረሰብ ማገልገል አያስፈልገንም' ብሎ ቢናገር፣ አንተ የምትሰጠው መልስ ምንድነው?

*የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሆነውን መንፈሳዊ ማህበረሰብ እና የምንኖርበት ምድራዊ ማህበረሰብ (የተወለድንበት ማህበረሰብ)።*

*በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 መሠረት ተወያዩ፣ እግዚአብሔር በሁለቱም ማህበረሰብ ውስጥ እንድናገለግል ጠርቶናል።*

**ጥያቄ 4-5:** ጥያቄ 4 ለ) አንብብ።
- ለዚህ የጻፍከው ምን ነበር? እባክህ ልምድህን አካፍል። በጥያቄ 5 ውስጥ በጻፍከው መሠረት፣ 'የማያውቁትን ሞኞች ዝም ታሰኙ ዘንድ' የሚለውን ተግባረዊ ለማድረግ የተሻለው መንገድ ምንድነው?

*ሁሉም ለማካፈል የሚፈልጉ ከሆነ ጊዜን ስጣቸው። በጎ ማድረግ*

### መልካም ማድረግ (ጥያቄ 5-9)

**ጥያቄ 7:** *የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።*
- እዚህ ጋር ምልክት ያደረክበት መልስ የትኛው ነው?
- እኛ ለማህበረሰባችን እና ለህዝባችን 'በጎ ማድረግ' የምንችልበት ሌላ መንገድ ልታስብ ትችላለህ?

**ጥያቄ 8:** ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ።
- ለዚህ የጻፍከው ሃሳብ ምን ነበር?
- በጥያቄ 7 እና 8 ላይ ከጻፍካቸው ሃሳቦች ውስጥ, በተግባር ማስቀመጥ የምትችለው የትኛውን ነው?

*እያንዳንዱ ተማሪ ካለበት ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ ቢያንስ አንድ የተግባራ ነጥብ ሊመርጥ ይገባል።*

## ለመንግስታችን መገዛት (ጥያቄ 10-13)

**1ኛ ጴጥሮስ 2:13-17 አንብብ:** *አንድ ተማሪ ጽሑፉን እንዲያነብ ጠይቅ፣ ይህም በቅይጥ ቡድን ውስጥ ከሆነ በእያንዳንዱ ቋንቋ አንድ ጊዜ ይነበባል።*

- በቁጥር 13 ውስጥ፣ እግዚአብሔር እንድናደርገው ያዘዘን ምንድነው? *'ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ'።*
- እኛ የምንገዛው ለማን ብለን ነው? *'ስለ ጌታ ብላችሁ'።*
- በቁጥር 16 መሠረት፣ በክርስቶስ ነጻ መሆን ማለት፣ እኛ የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን ማለት ነው? *አይደለም፣ ክፉን ለማድረግ ነጻ አልወጣንም። በዚህ ፈንታ ግን እኛ* **'እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች'** *ነን። ስለዚህም በበለጠ በትምህርት 15 ውስጥ እንማራለን።*

**ጥያቄ 13:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- ለዚህ ጥያቄ የጻፍከው ምን ነበር?

*አማኞች በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቀልል ባሉ ጉዳዮች ላይ የት ጋር ማመቻመች እንደሚችሉ እና 'ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል' የሚሉበትን አስፈላጊ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ሊወስኑ ይገባል። (ሐዋ. ስራ 5:29)። ተወያዩ።*

- በሱቅ ውስጥ የምትሰራ ከሆንክ፣ አለቃህ ደንበኞችን እንድታጭበረብር ይነግርሃል፤ የምታደርገው ምንድነው? ከሐዋሪያው ጴጥሮስ ምሳሌ በተማርነው ብርሃን መሠረት ምላሽ ይሰጥ።

*ይህ ከባድ ነው! እግዚአብሔርን አለመታዘዝ አንፈልግም ግን ደግሞ ስራችንንም ማጣት አንፈልግም። ተወያዩ*

## ለአለቃ መገዛት (ጥያቄ 14-20)

**1 ጴጥሮስ 2:18 አንብብ**

- ይህ ክፍል የተጻፈው ለነማን ነው? *ባሪያዎች።*
- በአንተ አስተያየት፣ እንደ ባሪያ ሆኖ ለመስራት ከባዱ ነገር ምንድነው? *ለምሳሌ፡ ለፍተህ ትሰራለህ ነገር ግን የምታገኘው ክፍያም ይሁን ነጻነት የለም*
- በቁጥር 18 ውስጥ ያሉት ባሪያዎች ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻቸው ብቻ ነው ወይስ ለጠማሞቹም ደግሞ በፍርሃት መገዛት አለባቸው? *ለጌታ ብለን እንገዛለን (ቁ.13 & 18), ቁ.20: በጎ ለማድረግ መከራ የምንቀበል ከሆንን፣ ይህ በእግዚአብሔር ፊት የላቀ ነው።*
- እኛ የምንሰራውን የማያደንቅልን ጠማማ አለቃ ወይም ሕዝብ ቢኖረን፣ ከ1ኛ ጴጥሮስ 2 የምንወስደው መጽናናት እና ጥንካሬ ምን ሊሆን ይችላል? *ለእነዚህ ሁኔታዎች በመጨረሻ እንጸልያለን።*
- በእኛ ላይ ባለስልጣን ሆኖ ለተቀመጠ ሰው መገዛት ከባድ የሆነብን ሰዎች አለን? እባክህ አካፍለን።

**ጥያቄ 19:** ሁለቱን ሰዎች ተመልከት።



- ለልጅ የምትመርጠው ታማኝ ቆሻሻ ጠራጊ እንዲሆን ነው ወይስ *ያልታመነ መምህርነትን*?
- እግዚአብሔር የሚፈልገው የሚመስልህ ምንድነው?

**በቃል የተጠናውን ጥቅስ 1ኛ ጴጥሮስ 2:17 ልምምድ:** *ሁሉን አክብሩ፥ ወንድሞችን ውደዱ፥*

- ካሰላሰላችሁት ጥቅስ ውስጥ 1ኛ ጴጥሮስ 2:17 በቃሉ ማለት የሚችል ማነው? *ሁሉም በአንድ ጊዜ ማለት እንዲችሉ አበረታታ።*
- በእኛ ምድራዊ ማህበረሰብ ውስጥ የድርሻችንን እንድንወጣ የሚነግሩን ቃላት የትኞቹ ናቸው?
- በእኛ *መንፈሳዊ* ማህበረሰብ ውስጥ የድርሻችንን እንድንወጣ የሚነግሩን ቃላት የትኞቹ ናቸው?

| ማጠቃለያ | |
|---|---|
| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው? *ይህ ትምህርት በህይወቱ እየተገበረ ያለ ሰው አለ?*<br>**ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።**<br>**ማበረታቻ፥** በመጀመሪያ የጻፍካቸውን ማህበረሰብ ዝርዝር ተመልከት፡ እነሱን ማገልገል የምትችለው እንዴት ነው? ወደ ጥያቄ 7 እና 8 ተመለስና በቀጣይ ሳምንት ለአንድ ማህበረሰብ አንድ ስራ ለመስራት ወስን ወይም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡትን ተግባራዊ ስራዎች መካከል አንዱን አድርግ። በቤት ውስጥ የሚኖርህን ጥናት ቀጥል። | **በአንድነት ጸልይ:** ጥንድ በመሆን ወይም በቡድን ጸልዩ።<br>*ፍትሃዊ ላልሆነ መንግስት ወይም ለመጥፎ አለቃ ለመገዛት ከብዶባቸው ላሉ ማንኛውም የቡድኑ አባላት ጸልዩ።*<br>*በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር መንፈሳዊ እና ምድራ ማህበረሰባችንን ማገልገል እንድንችል እና ለክርስቶስ ስን ለሰው ስርአት ሁሉ እንድንገዛ እንዲረዳን ጠይቀት።* |

# ትምህርት 9: የስደት ምክንያቶች

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን ምንም ነገር እንደሌለ እርግጠኛ እንዲሆን።
ለ. ሰደት ሲከሰት እግዚአብሔር ለበጎ እንደሚያደርግልን መረዳት።
ሐ. አላስፈላጊ ስደቶችን በጥበብ ለማስወገድ መማር።
መ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡21 ማሰላሰል።

**የባህል መገለጫዎች:**

- በስደት ውስጥ ያሉ ከእ.የመ.አ ማማከር

**ዝግጅት:** ሮሜ 8፡35 የተጻፈበት ወረቀት (ለጥያቄ 12)

## *መከፈቻ*

**ለትምህርቱ መጸለይ። ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** አንተ ማህበረሰቡን ወይም ችግረኛ ሰውን ወይም በስልጣን ላይ ያለ አንድን ሰው ለማገልገል ያደረከው ምን ነበር? የሰውዬውስ ምላሽ ምን ነበር?

**ትምህርት 9 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**
**ጥያቄ 1:** ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ (1ኛ ጴጥሮስ 2:21).
**ጥያቄ 2:** 1) ዓለም፣ይጠላናል፤ 2) እግዚአብሔር ስደትን፤ 3) የሞኝነት ተግባሮቻችን፤ 4) የክርስቶስን ዱካ

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡**የዛሬው ርዕስ ስደት ነው እና ከባድ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ባለፍንባቸው ጉዳቶች ምክንያት ምንአልባት ውይይታችን በእምባ የተሞላ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን ስደትን ለነበጎ ያደርገው እና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በተነጋገርን ቁጥር ህመማችንን ይፈውስልናል።

## *ውይይት*

### የመጀመሪያው ምክንያት፡ ዓለም እኛን ይጠላናል (ጥያቄ 1-6)

**ጥያቄ 1-2:** ጥያቄ 1ን በሙሉ እና ጥያቄ 2ን በከፊል አንብብ።

- ለጥያቄ 2 ያስቀመጥከው መልሶች የትኞቹ ናቸው? ወይም በሌላ መንገዶች ያለፍክበት ስደት አለ? አንተ አሁንም በስደት ውስጥ ነህ?

*አሁን ቆም በሉና በስደት ውስጥ ላሉ ወይም እስካሁን ከመጡበት ጥቃት የሚደርስባቸው የቡድን አባላት ካሉ በጋራ እንጸልይላቸው።*

*እያንዳንዱ ሰው የራሱን ልምድ ይናገር፡ ፡ ይህ እምባም ሊኖርበት የሚችል አስፈላጊ ጊዜ ነው እና በዚህ ግር እንዳይሰኙ ተከታተል።*

**ጥያቄ 5:** በሳጥን ውስጥ የሐይምን እውነተኛ ታሪክ አንብብ። የሚሰማህ ስሜት ምንድነው?

### ሁለተኛው ምክንያት፡ እግዚአብሔር ስደትን ስለፈቀደ (ጥያቄ 7-13)

**1ኛ ጴጥሮስ 1:3-7 አንብብ**

- በቁጥር 4 መሠረት፣ የእኛ ርስት ያለው የት ነው? *በሰማይ*
- ይህም 'የሚጠፋ, የሚያድፍ ወይም የሚያልፍ' ነው? *አይደለም- ከእኛ ምድራዊ ርስት የተለየ ነው!*
- በቁጥር 5 መሠረት፣ በዚህ ዘመን እኛን የጠበቀን ምንድነው? *የእግዚአብሔር ኃይል*
- በቁጥር 6/7 መሠረት፣ 'ልዩ ልዩ ፈተናዎች' ሲያጋጥሙን መመለስ ያለብን እንዴት ነው? *በታላቅ ደስታ*
- ቁጥር 6/7 እምነታችንን የሚያመሳስለው ከምን ጋር ነው? *ከወርቅ ጋር*
- የወርቅ አንጥረኛ ወርቅን በእሳት ውስጥ የሚያሳልፈው ለምንድነው? *ለማጥራት፣ ለምሳሌ፡- 9ካራት ወደ 24 ካራት*
- ስለዚህ እግዚአብሔር በስደት ውስጥ እንድናልፍ የሚፈቅደው ለምንድነው? *እምነታችንን ለማጽናት እና እኛን ንጹህ፣ ታጋሽ እና ጠንካራ ለማድረግ ነው። እሱ የሚያጠራበት እሳት የእኛን 9ካራት እምነት ወደ 24 ካራት እምነት ይለውጠናል!*

**ጥያቄ 10:** ሙሉ ጥያቄውን አንብብ። ምልክት ያደረክባቸው መልሶች ምንድናቸው? ስለዚህ የሚሰማህ እንዴት ነው?

*ሀ) ብቻ ትክክለኛ መልስ ነው። ይሁን እንጂ የዚህ ውይይት ዓላማው ተማሪዎች ስለግል ስጋታቸው እና ትግላቸው ግልጽ እንዲሆኑ ነው። ከዚያም በታማኝነት ለእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን ክፍት በማድረግ፣ እሱ በመከራ ጊዜ እንኳን ሃሳባቸውን እየቀየረ መልካም እንደሆነ በእሱ እንዲታመኑ ብርታትን ይሰጣቸዋል።*

**ጥያቄ 11:** ሙሉ ጥያቄውን አንብብ። ለክፍል ለ) ጽፈህ የነበረው ምንድነው? *ከራስህም ሕይወት አካፍል!*

**ጥያቄ 12:** *አማኞች በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሲያልፉ፣ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሐሔር እነሱን እንደተዋቸው ወይም እየቀጣቸው እንደሆ ይሰማቸዋል። ቀጣዩ መልመጃ እግዚአብሔር እነሱን አሁንም እንደሚወዳቸው እና እንደማይተዋቸው የበለጠ ልበ ሙሉ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። በቅድሚያ በባዶ ወረቀት ላይ 'መከራ'፥ 'ጭንቀት'፥ 'ስደት'፥ 'ራብ'፥ 'ራቁትነት'፥ 'ፍርሃት'፥ 'ሰይፍ' የሚሉትን* **ቃላት ጻፍ።** *'ሊለየን ይችላል' እና 'ሊለየን አይችልም' በልና ደግሞ በሁለት የተለያዩ ወረቀቶች ጻፍ እና በጠረጴዛ ወይም በመሬት ላይ አስቀምጥ። በመጨረሻም፣ 'ሞት' የሚል ቃል በወረቀት ላይ ጻፍ።*

- **ሮሜ 8:35 አንብብ።** ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን የሚችል ነገር የቱ ነው? እያንዳንዱም ሰው አንድ ወረቀት ይወስድና

‘ሊለየን ይችላል’ ወይም ‘ሊለየን አይችልም’ በሚለው ርዕስ ስር ያስቀምጣል።

- ሮሜ 8:36 አንብብ። ይህ ጥቅስ ሞትን እየተጋፈጠ ያለውን የሐይም ቤተሰብ ይገልጻል?
- ሮሜ 8:37-39 ሁሉንም በአንድ ድምጽ አንብቡ። የሐይምን ቤተሰብ ሞት እንኳን ቢሆን ከክርስቶስ ፍቅር ሊለያቸው ችሎ ነበር? *አልቻለም! ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን በቀጥታ ሄደዋል።*

*‘ሞት’ የሚለውን ሌላ ወረቀት ‘ሊለየን አይችልም’ በሚለው ርዕስ ስር አስቀምጥ።*

- ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን የሚችል ነገር አለ? *የለም፣ ሞት እንኳን ቢሆን!*

## ሦስተኛው ምክንያት፣ የሞኝነት ተግባሮቻችን (ጥያቄ 14-17)

**ጥያቄ 14:** ከሻቅል ታሪክ በኋላ ጥያቄውን አንብብ: *ተማሪዎቹ በውይይት ጊዜ የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ የቤት ውስጥ ጥናት እንደሚረዳቸው አስታውሳቸው።*

- በዚህ ላይ የአንተ አስተያየት ምንድነው?
- ሻቅል ያጋጠመው ስደት አስፈላጊ ነው ወይስ አላስፈላጊ? *አላስፈላጊ ነበር፤ ለምሳሌ፡ በቤተሰቡ ላይ ሃፍረት አምጥቶ ነበር፣ ከቤት ወትቶ ሄደ፣ አባቱንም ሰደቧል።*
- አላስፈላጊ ስደት ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው? *በተቻለ መጠን ታላላቆችን በማክበር፣ ቤተሰቦቻችንን በመረዳት፣ እነሱን ላለማሳፈር በመሞከር።*
- አስፈላጊ ስደትን ማስወገድ እንችላለን? *የክርስቶስን ስም መካድ የለብንም። ነገር ግን ያለንበትን መልቀቅ ምርጫችን ሊሆን ይችላል፣ ቁ. 17 ተመልከት።*

**ጥያቄ 17:** ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ።

- በዚህ ጥያቄ ላይ አንተ አስተያየት ምንድነው? *ትክክል እና ትክክል ያልሆነ መልስ እንደ ሁኔታው የሚሰጥ ይሆናል። ህይወቱ አደጋ ላይ የሆነ ሰው አካባቢ መለወጥን ከግንዛቤ ሊከት ይጋባል። ይሁን እንጂ አደጋው እምብዛም ከሆነ በተቻለ መጠን ሁኔታው እስኪሻሻል ድረስ በዝግታ በቤታቸው ሊኖሩ ይገባል። ምንም እንኳን እነሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ቢሆኑም ለቤተሰቦቻቸው አሁንም ታማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሊሞክሩ ይገባል።*

## አራተኛ ምክንያት፣ የክርስቶስን ዱካ ስለምንከተል (ጥያቄ 19-22)

### 1 ጴጥሮስ 2:19-21 አንብብ:

- ቁጥር 20 አላስፈላጊ መከራን የሚገልጸው እንዴት ነው?
  *‘ለፈጸምከው ስህተት ቅጣት ብትቀበል የምትሰጠው ዋጋ እንዴት ነው?’*
- ይህ ቁጥር አስፈላጊ መከራን የሚገልጸው እንዴት ነው?
  *‘በጎ በማድረግህ መከራን ብትቀበል ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና አለው።’*
- በቁጥር 21 መሠረት፣ በስደት ምክንያት በመከራ ውስጥ ብንሆን የማንን ፍለጋ እየተከተልን ነው?

*የጌታችን ኢየሱስ መንገድ ‘የእሾክ መንገድ’ እና እኛም እሱ ባለፈበት ማለፋችን ለእኛ ክብር ነው!*

**ያሰላሰልነው ጥቅስ 1ኛ ጴጥሮስ 2:21 ላይ ክለሳ እና ያለን ሃሳብ:**

*ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ስንማር ልናሰላስለው, ይገባል። ይህም በቁጥሩ እሱ የሚናገረንን ለመስማት እና እኛ እንዴት ምላሽ እንድንሰጠው እንደፈለገ ለማወቅ ይረዳል። ለዚህም የሚከተሉትን እርምጃዎች በመጠቀም በትምህርቱ ጊዜ ማሳየት ይቻላል።*

1) እያንዳንዱ ሰው ልቡን በእግዚአብሔር ፊት ዝም እንዲያሰኝ ጠይቅ። እግዚአብሔር በቃሉ እንዲናገረን ጠይቅ
2) እያንዳንዱ ሰው ያሰላሰለውን ጥቅስ በዝግታ አንድ ጊዜ እንዲለው ጠይቅ።
3) እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ምን እንደሚለው በመስማት እና በጥቅሱ እያንዳንዱ ክፍል ላይ ያለውን ሃሳብ እያስቀመጠ፣ በልቡ ጥቅሱን ለራሱ ብዙ መደጋገም አለበት። *ለዚህ ቢያንስ 5 ደቂቃ ፍቀድ።*
4) እግዚአብሔር እያንዳንዳችን እንዴት ምላሽ እንድንሰጥ እንደፈለገ እንዲያሳየን ጠይቁ። *ለዚህ የተወሰነ ደቂቃ ፍቀድ።*
5) እግዚአብሔር በዚህ ጥቅስ ምን እንደተናገረህ እና እንዴት ምላሽ እንደምትሰጥ በቡድን ወይም ጥንድ በመሆን ሃሳብህን አካፍል

## *ማጠቃለያ*

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:**

- የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?
- **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** ተማሪዎች ጥቅሱን በየቀኑ ለማሰላሰል ያላቸውን ሃሳብ ያስቀመጡበትን የዛሬ ሂደት በተመሳሳይ መልኩ መጠቀም ይችላሉ።

*ማሳሰቢያ፡ በ2013 የመማሪያው መጽሐፍ እትም ላይ ሳይሆን በአሁኑ ትክክለኛ ጥያቄዎች 1፣3፣7፣9፣11፣15፣18፣20፣22 ናቸው።*

**በአንድነት ጸልዩ:** እግዚአብሔር በስደት ጊዜ ስለሰጠን ብርቱ ተስፋ አጭር የምስጋና ጸሎት እንዲጸልዩ ሰዎችን ጠይቅ። በሌሎች ሀገራት ውስጥ በስደት በመከራ ላሉ አማኞች፣ በተለይም ከእስልምና ለመጡ የክርስቶስ ተከታዮች ጸልዩ።

# ትምህርት 10፡ ለስደት ምላሽን መስጠት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ይቅርታ ከበቀል እንደሚሻል በእውነት ያምናል።
ለ. የበደለውን ሰው ይቅር ለማለት እርምጃን ይወስዳል።
ሐ. ማቴዎስ 5፡44 ን ያሰላስላል።

**የባህል መገለጫዎች:**

- በቀል እና ይቅርታ

**ዝግጅት:** ማቴዎስ 5፡44 ን ለጥያቄ 4 ቃሎቹን ነጣጥሎ በወረቀት መጻፍ

## መክፈቻ

**ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** በየቀኑ ለማሰላሰል የተሰጡትን ጥቅሶች ማለት ችለሃል? ይህ ለአንተ እንዴት ነበር? በጣም የነካህ ጥቅስ የቱ ነው?

**ትምህርት 10 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ይቅርታ
**ጥያቄ 2:** ጠላቶቻችሁን ውደዱ እና ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ።



**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** መግቢውን ተመልከት እና ሁለት ሰዎች የሁለቱን ሰዎች ንግግር ያንብቡ: ከእነዚህ ሰዎች እንደ አንዱ ተሰምቶህ ይውቃል? *ተማሪዎችን በዚህ ነጥብ ላይ ምንም ሳትሞግታቸው ስሜታቸውን እንዲያካፍሉ ፍቀድ።* እግዚአብሔር ለስደት እንዴት ምላሽ እንድንሰጥ እንደሚፈልግ እና በተለይም እንዴት ጠላቶቻችንን ይቅር ማለት እንደምንችል ዛሬ እንማራለን።

## ውይይት

### የበቀል ኡደት (ጥያቄ 1-3)

**ጥያቄ 2:** ስዕሉን በጋራ ተመልከቱ።

- ይህ የበቀል ኡደት በሚከሰትበት ጊዜ ያየኸው ምሳሌ ምንድነው?
- ይቅርታ ከባድ፣ በቀል ደግሞ ቀላል ነው። ነገር ግን አደጋውን የከፋ የሚያደርገው የትኛው ነው?

### በበቀል ፋንታ ይቅርታ (ጥያቄ 4-16)

*ማቴ. 5፡44 ቃሎቹን ነጣጥለህ ጻፍና እያንዳንዱ ተማሪ ቃሎቹን በትክክለኛ ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጥ ጠይቅ።*

**ጥያቄ 4:**

- ኢየሱስ ከበቀል ኡደት ነጻ እንድንወጣ ያስተማረን እንዴት ነው? *ጠላቶቻችንን በመውደድ እና ይቅር በማለት*

**ጥያቄ 5:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- ኢየሱስ የሮማውያን ወታደሮች እጆቹን በሚስማር በጠረቁት ጊዜ የጸለየላቸው ምን ብሎ ነበር? *‘ አባት ሆይ … ይቅር በላቸው’።*
- ኢየሱስ ክርስቶስ ደካማ መሪ ነበር ወይስ ጠንካራ? የእሱ ጥንካሬ እንዲያደርግ ያስቻለው ምን ነበር? *ይቅር እንዲል*
- ከእሱ ምሳሌ እኛ የምንማረው ምንድነው? *ይቅር ማለት የደካማነት ሳይሆን የጥንካሬ/ብርታት ምልክት ነው*
- ጠላቶቻችንን ይቅር እንድንል ጥንካሬውን የሚሰጠን ማነው? *ኢየሱስ፣ በእኛ በሚኖረው የመንፈሱ ኃይል.*

**1ኛ ጴጥሮስ 2:21-25 አንብብ:**

- በቁጥር 22 መሠረት፣ ኢየሱስ መከራ ይገባው ነበር? *በፍጹም፣ ‘እሱም ኃጢያትን አላደረገም’፡፡*
- ቁጥር 23 ን ተመልከት። በቀልን በመፈለግ ወይም የሚያሳድዱትን በመርገም ፈንታ፣ ኢየሱስ ያደረገው ምን ነበር? *ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ*
- ቁጥር 24-25 ተመልከት። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ምንድነው? *ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።*
- ይህን ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ እንዳደረገልህ ስታስብ የሚሰማህ ምንድነው?
- ጠላቶቻችንን መውደድ እና ለሚያሳድዱን መጸለይ በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ ይህ ለማድረግ የምንሞክረው ለምንድነው? *ክርስቶስ እኛን አስቀድሞ ይቅር ስላለን እና ነጻ ስላደረገን።  እሱ ራሱ ጠላቶቻችንን ይቅር ስለማለት ምሳሌን ስለሰጠን።  እሱ እንድናደርገው ስላዘዘን።  ይቅርታ የበቀልን ኡደት በመስበር ከምሬት ነጻ ያወጣናል።*

**ይቅርታ ለምን?** *ጊዜ ካለ በዚህ ርዕስ ላይ በጥልቀት ለመሄድ።*

ተማሪዎች **ማቴዎስ** 18:21-35 ን ጥንድ በመሆን ያንብቡ እና ለጥቂት ደቂቃ ምን እንደተማሩ በመወያየት ያገኙትን ሃሳብ ለቡድኑ ይሰጡ።  የሚመች ከሆነ ታሪኩን በድጋሚ መናገር ወይም በተግባር ማሳየት ይችላሉ።

**ጥያቄ 9:** የፋሪድን ታሪክ የመጀመሪያ ክፍል አንብብ።

- ፋሪድ የበቀል ዕቅዱን የሚተገበር ከሆነ፣ ውጤቱ ሊሆን የሚችለው ምንድነው?

*ለሰይጣን ታልፎ ሊሰጥ ይችላል። የስራ ባልደረባው መልሶ ሊበቀለው ይችላል፣ ይህም በበቀል ኡደት ላይ መጨመር ነው።*

**ጥያቄ 10:** የፋሪድን ታሪክ ሁለተኛ ክፍል አንብብ።

- ፋሪድ በበቀል ፈንታ ይቅር በማለቱ የመጣው መልካም ውጤት ምንድነው?

*የስራ ባልደረባው በጥልቀት ተነክቶ ነበር እና በኋላ ላይ የኢየሱስ ተከታይ ሆነ።*

**ምን እንደሆነም አንብብ:** ፋሪድ የይቅርታውን ደብዳቤ ከጻፈ በኋላ ወደ ቤቱ ሄደ። ይሁን እንጂ አሁንም የአንድ ወር ደመወዙ መጥፋቱ በጣም አስጨንቆታል። እሱም "በዚያ ምሽት፣ በመጨረሻ ለጸሎት እስከምነሳ ድረስ ስገለበጥ እና ስሽከረከር ያለእንቅልፍ ነው ይደርኩት። እኔም ወደ ውስጥ እየገባው እያለ አንድ ሰው ወደ መደርደሪያው ድንገይ ወረወረ። ከድንጋዩም ጋር ለወራት ለደህንነቴ ስል ካላገኘሁት ክርስቲያን የተጻፈ ደብዳቤ ተያይዞ ታስሯል። ይህም ደብዳቤ በውስጡ እኔ የማገኘውን ደመወዝ የሚያክል ገንዘብ ይዟል። እኔም ጌታ ምን ያህል በታማኝነት ስለእኔ ግድ እንደሚለው በማየት ተደንቄ ነበር! " አለ። (www.pneumafoundation.org/pi_7_2003.jsp)

- ይህን ደብዳቤ የተቀበልከው ፋሪድ አንተ ብትሆን፣ የሚሰማህ ምን ነበር? *ስሜቶቻችሁን ተወያዩበት*

**ጥያቄ 12:** የመሪየም ታሪክን እና ጥያቄውን አንብብ።

- እግዚአብሔር የመሪየምን ሳይሆን የፋሪድን የጠፋ ገንዘብ በአስደናቂ ሁኔታ የመለሰው ለምን ይመስልሃል?
- መሪየም ዘመዶቿን ከመጥላት ነጻ ያወጣት ምንድነው? *ይቅር ማለትን መርጣለች። ከዚያም ደስታ ልቧን ሞላው!*

*እኛ አናውቅም፣ እግዚአብሔር ግን ለእያንዳንዳችን የተሻለውን ያውቃል እናም ለበጎ በህይወታችን ይሰራል፡ አንዳንድ ጊዜ እንደ ፋሪድ እምነታችንን ለማጠንከር ታምራትን ያሳየናል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደ መሪየም በጽናት እንድንበረታ በፈታኝ መንገድ እንድንሄድ ያደርገናል።*

**ጥያቄ 13:** ጥያቄውን አንብብ። እዚህ ጋር የጻፍከው ምንድነው?

*አንዳንድ ጊዜ በተለይ ለሌሎች ክርስቲያኖች ስንል መቃወም አስፈላጊ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ አንዳንድ ጊዜ ያለአግባብ ሲያዝ ይቃወም ነበር (ለምሳሌ፡ ሐዋ. ስራ 16:35-37). ይህ ተቃውሞ ግን በህግ አግባብ እንጂ ከበቀል አኳያ መሆን የለበትም።*

**ጥያቄ 15:** ታሪኩን አንብብ። ይህ አማኝ የመቱትን ሰዎች ይቅር ማለት ቀላል ሆኖ አገኝቶታል? *አላገኘውም*

- እሱም የሚያሳድዱትን ይቅር ባለማለቱ በመከራ ማለፋን ተናግሯል። ይህን ማለቱ ምን ይመስልሃል? *ምንአልባት በውስጡ ካለው ምሬት የተነሳ በብዙ መከራ አልፎ ይሆናል*
- አንተም ቅሬታህን የምትይዘው እና ይቅር ማለትን እንቢ የምትለው መቼ ነው? ውጤቱስ ምንድነው?
- ሰውዬውን ይቅር ብትለው እና ቅሬታህን ብትተው፣ ይህ የሚያመጣው ልዩነት ምንድነው?

**አሁን ደግሞ ከሳጥኑ በኋላ ያለውን ዓረፍተ ነገር እና የንግግር ሳጥኑን አንብብ።**

- የንዳህን አንድ ሰው ማሰብ ትችላለህ? ስለዛም ሰው ስም አስብና በዝግታ ተናገረው። *ይህንን እንዲያደርጉ የጥሞና ጊዜ ስጣቸው። ተማሪዎች ያለባቸውን ስጋት ለማስቀረት ስሙን ከፍ ባለ ድምጽ እንዲሉት ወይም እንዲጽፉት አይጠየቁም።*
- ይህን ማድረግ ችለሃል? እነዚህን ቃላት መናገር ያለው ስሜት ምን ነበር?

## በመከራችን ውስጥ ያለ ሐሤት (ጥያቄ 17-19)

**1ኛ ጴጥሮስ 4:12-16 አንብብ።** *እያንዳንዱ ሰው ክፍሉን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማውጣት አለበት።*

- በዚህ ክፍል ውስጥ የምትመርጠው ጥቅስ ምን ነበር እና ለምን?
- በዚህ ክፍል ውስጥ የምትመርጠው ጥቅስ ምን ነበር እና ለምን?

### ማጠቃለያ

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:**

በዚህ ሳምንት ይቅር ማለት ያለብህ ሌሎችም ካሉ ጊዜን ውሰድ፡ይህም በራስህ ብርታት ልታደርገው የምትችለው ስላልሆነ ከባድ ነው። ለይቅርታ ማንም ሊያስገድድህ አይችልም፣ ነገር ግን ይቅር ማትን ከመረጥክ እግዚአብሔር ይህን የምታደርግበትን ጥንካሬ ይሰጥሃል። ከዚያም ይህ በሕይወትህ ታላቅ ደስታን ይሰጥሃል!

**የዛሬውን ርዕስ ልትነግረው የምትችለው ለማነው?**

ይቅር ያላለውን ባሪያ ታሪክ (ማቴዎስ 18፡23-35) ለሰውዬው ልታካፍል ትችላለህ።

**በአንድነት ጸልይ:**

ተማሪዎችን በጸሎት በዚህ እርምጃ ምራ፡

***በመጀመሪያ፡*** *እግዚአብሔር ይቅር የምንለውን አንድ ሰው እንዲያሳየን ጠይቅ።*

***ከዚያም፡*** *እርምጃ 1እና 2 ን በዝግታ አንብብ።*

***ጸሎት፡*** *በደረጃ 3 ላይ ያለውን ጸሎት በአንድነት በሉት እያንዳንዱም ሰው ይቅር ማለት የሚፈልገውን ሰው ስም በዝግታ ይጥራ።*

***ማንበብ፡*** *የመጨረሻውን እርምጃ። በዚህ ዓይነት መንገድ ብርታትን ተቀብለን ይቅር ማለትን እንድንቀጥል ለእያንዳንዳችን መጸለይ።*

# ትምህርት 11፣ ባሎችና ሚስቶች

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. እግዚአብሔራዊ የጋብቻ ንድፍ፣ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሕይወት ዘመን ጥምረት መሆኑን መረዳት።

ለ. የትዳር አጋራቸውን ከራሳቸው በላይ ማስደሰት ይፈልጋሉ።

ሐ. ወንዶች ከእናታቸው በላይ ለሚስቶቻቸው ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው ያምናሉ።

መ. ዘፍጥረት 2፡24 ን ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)።

**የባህል መገለጫዎች:**

- ጋብቻ በእስልምና ውስጥ
- እናትነት በእስልምና ውስጥ

**ዝግጅት:** በጥያቄ 3 ላይ ያሉትን ጉዳዮች ለመወያየት ከግንዛቤ በማስገባት ወረቀቶች እና እስክሪብቶዎች

## መክፈቻ

**ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** የጎዳህን አንድ ሰው ይቅር ማለት ችለሃል? ይህም በአንተ ሕይወት ያመጣው ለውጥ ምንድነው? *ከሚይናገሩ ወይም ይቅርታ ካባድ ከሆነባቸው አባላት ጋር በግል ተነጋገር።*

**ትምህርት 11 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። (ዘፍጥረት 2:24)

**ጥያቄ 2:** በሕይወት ዘመን ሁሉ፣ የአንድ፣ የአንድ **ጥያቄ 3:** ሀ) መገዛት፣ ለ) ማክበር **ጥያቄ 4:** እኔ

**ለዛሬው ትምህርት ጸልይ፣ የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡** ከወላጆቻችንም ይልቅ ከትዳር አጋራችን ጋር የሚኖረን ግንኙነት በጣም አስፈላጊ ሰዋዊ ግንኙነት ነው። የዛሬው ርዕስ እግዚአብሔራዊ የጋብቻ ንድፍ ነው። ***የዛሬውን ትምህርት ከራስ ጋር ማዛመድ አስፈላጊ ነው፣ ለምሳሌ፥ ተማሪዎችህ ያላገቡ ከሆኑ*** *የአንድ ጾታ የወይይት ቡድን እንዲኖር እንመክራለን፣ መሪዎቻቸውም ከተመሳሳይ ጾታ ይሆናሉ። ለተማሪዎችህ አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎች ላይ አተኩር። ይህ ርዕስ አስፈላጊ ስለሆነ በችኮላ ሄደህ በኋላ ስትፈልግ መመለስ አይሆንም። (አሁኑኑ በጥንቃቄ እየው*

## ውይይት

### የጋብቻ እግዚአብሔራዊ ንድፍ (ጥያቄ 1-11)

**ጥያቄ 2:** እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር አንብብ እና ጠይቅ:

- አንተ በግልህ ከዚህ ዓረፍተ ነገር ጋር ትስማማለህ?
- ለምን ወይም ካልተስማማህ ምክንያቱ ምንድነው?

*እነዚህ መልሶች ወንድ እና ሴት በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠሩ ከሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕይታ የመጡ ናቸው፣ ነገር ግን የክርስቲያኖች ዕይታ በአንዳንድ ጾታዊ ሚና ምክንያት ሊለያይ ይችላል።*

**ጥያቄ 3:** ያሰላሰሉትን ጥቅስ ዘፍጥረት 2:24 ከልስ።

- እግዚአብሔራዊ የጋብቻ ንድፍ ምንድነው? *ጥያቄውን ተመልከት*
- በእነሱ መካከል በስጋ፣ በነፍስ እና በመንፈሳቸው የሚሆነው ምንድነው ? *ይጣመራሉ - አንድ ስጋ ይሆናሉ፡፡*
- እኛ በምንኖርበት ባህል ውስጥ ጋብቻ የሚጀምረው መቼ እና እንዴት ነው?
- ይህም ክርስቶስን ለሚከተሉ የተለየ የሚሆነው እንዴት ነው? *በምትኖርበት አካባቢ ይህን ጉዳይ እና ተግዳሮቶቹን በተመለከተ ለመወያየት ጊዜን ውሰድ፣ ለምሳሌ፥ በምዕራቡ ዓለም የትዳር አጋር ማግኘት የሚቻለው፤ አብሮ በማደር፣ ከጋብቻ በፊት ወሲብ በመፈጸም ሊሆን ይችላል። ለክርስቲያኖች ግን ሊኖር የሚገባውን ልዩነት በግልጽ አስቀምጥ።*

## Question 5:

**ጥያቄ 5:**

ስዕሉን ተመልከት።

- ለጥ. 5 ሀ) እና ለ) እያንዳንዳችሁ የጻፋችሁት ምን ነበር?



*ይህ ብዙ ተማሪዎች የሚለዩት የተለመደ ሁኔታ ነው። ሚስት ቅድሚያ ሊሰጣት እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ሆና ተቀምጧል ነገር ግን በምዕራቡ ዓለም ብዙም ቦታ የማይሰጠው ለወላጆች ደግሞ እንክብካቤ እና አክብሮት መስጠት አሁንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው።*

***ጥያቄ 4 ን በጋራ አንብቡ።***

ቀጣዩን ርዕስ፣ ፍቺን በተመለከተ በፍቺ ውስጥ ካለፉ አማኞች ጋር በጥንቃቄ በመወያየት ስለእግዚአብሔር ጸጋ እና ይቅርታ አስተምር።

**ጥያቄ 7:** ማቴዎስ 19:3-6 አንብብ።

- በዚያን ዘመን ለወንድ ፍቺ መፈጸም ቀላል ነበር። ክርስቶስ በቁ. 5 ላይ የጠቀሰው ምንድነው?
- ባል እና ሚስት ጋብቻቸውን በአካል ብቻ ሳይሆን፣ በልባቸው እና በነፍሳቸው ማጠናከር የሚችሉት እንዴት ነው?
- ክርስቶስ በቁ. 6 ውስጥ ጋብቻን ሰዋዊ ጥምረት ብቻ አድርጎ ነው የሚናገረው ወይስ ከዚህም የሚበልጥ?
- በቁ. 6 ላይ ባሉ የክርስቶስ ቃላት መሠረት፣ ፍቺ?

*በእርግጥ፣ ሰው ሚስቱን ምግብ የምታሳርር ከሆነች ሊፈታት ይችላል ብለው አንዳንድ ፈሪሳዊያን ያስባሉ!*

*ዘፍጥረት 2:24.*

*በጋራ ጊዜ ማሳለፍ፣ እንደ እውነተኛ ጓደኞች አብሮ ማውራት እና ነገሮችን በጋራ መስራት።*

*እስልምና የጋብቻን እሳቤ እንደ ጊዜያዊ ስምምነት አድርጎ ያስተምራል ነገርን ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ለማፍረስ የማይቀል አድርጎ ያቀርበዋል።*

*ግዚአብሔር ያጣመረው በመሆኑ፣ ስለዚህ ሰው ሊለየው አይችልም (ቁ. 9 ተመልከት)። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ በክርስቶስ*

*ኮከታዮች መካከልም ቢሆን ጋብቻ ይፈርሳል።*

**ጥያቄ 9:** ጥያቄውን አንብብ። ምልከት ያደረከው በየትኛው መልስ ላይ ነው? ይህ የሆነው ለምን ይመስልሃል?

*ሀ) ፣ ለ) እና ሐ) በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ የተለመዱ ናቸው። ለ ሐ) ጥቂት ማሳያዎች ሊኖሩ ይችላሉ።*

**ጥያቄ 10:** የንግግር ሳጥኑን እና የመጨረሻውን አንቀጽ አንብብ። እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር?

*ይህ ሰው ሚስቱን እንደ ዕቃ ያስባታል፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱም እኩል ዋጋ እንዳላቸው ያስተምራል።*

**ጥያቄ 11:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ። እግዚአብሔር የእኛ ህመም እንደሚሰማው ማወቅ፣ እኛን የሚረዳን ምንድነው?

*ምንአልባት ተማሪዎችህ ከእነዚህ የማያስደስቱ ሁኔታዎች መካከል በአንዱ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ በመከራ ውስጥ ላሉ እንደሚራራ እና እኛም ስለጋብቻችን በሀዘን ውስጥ ከሆንን ህመማችን እንደሚሰማው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።*

## ባል እና ሚስት በ1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ውስጥ (ጥያቄ 12-22)

**ጥያቄ 13:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- አንዳንድ ጊዜ ሚስት ለባሏ መገዛት የሚከብዳት ለምንድነው?
- አንዳንድ ጊዜ ባል ሚስቱን ለማክበር የሚከብደው ለምንድነው?

*ለምሳሌ፡ ባል ራስ ወደድ፣ ጨቋኝ ወይም ጥበብ ሲጎድለው፤ ወይም ሚስት የራሷን መንገድ ስትፈልግ ነው።*

*ለምሳሌ፡ ብዙ ባሎች ሚስቶቻቸው የእነሱ አገልጋይ እንዲሆኑ ይጠብቃሉ።*

**ጥያቄ 15 & 20:** ጣሪቅ (ጥ. 20) እና ሚስቱ (ጥ.15) የተናገሩትን እንዲያነቡ ሁለት ሰዎችን ጠይቅ።

- ለማስደሰት የሚሞክሩት ማንን ነው፣ ራሳቸውን ወይስ የትዳር አጋራቸው?
- እግዚአብሔር የበለጠ ግድ እንዲለን የሚፈልገው ምንድነው: የትዳር አጋራችንን ማስደሰት የምንችለው እንዴት ነው ወይም እኛን እንዴት ሊያስደስተን ይችላል? የትዳር አጋርህን እንዴት ለማስደሰት እንደምትሞክር ምሳሌን ስጥ ወይም ከባድ ሆኖ ያገኘኸው ምንድነው



**ጥያቄ 21 & 22:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- ሰው ሚስቱን እና ልጆቹን ሳይመታ በቤት ውስጥ ያለውን ስልጣን ማስጠበቅ ይችላል?

*በአንዳንድ ባህል ውስጥ ሚስትን መደብደብ የተለመደ ነው ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ 'እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል።' ኤፌሶን 5:28.*

- 1ኛ ጴጥሮስ 3:7 ሚስት እንዴት መያዝ እንዳለባት የሚናገረው ምንድነው? *'በመረዳት' እና 'በአክብሮት'፡፡*
- ይህም በተግባር ምን እንደሚመስል ምሳሌ ስጥ።
- ጥያቄ 22: ጽፈህ የነበረው ምንድነው? *መልሱ ሊለያይ ይችላል፣ ነገር ግን ጥያቄው ባሎች ራስ ወዳድ ባልሆነ መንገድ ሚስቶቻቸውን መረዳት እንደሚችሉ የሚያግዝ ነው።*

## የትዳር አጋርህ እስካሁን በክርስቶስ ካልሆነ/ች... (ጥያቄ 23-26)

**ጥያቄ 24:** በሳጥን ውስጥ ያለውን እውነተኛ ታሪክ እና ከስር ያለውን ጥያቄ አንብብ። የአንተ አስተያየት ምንድነው?

*የትዳር አጋርህ ወደ ክርስቶስ ባትመጣ እንኳን በቤት ውስጥ ያለውን ጥምረት ለመጠበቅ መታገስ እና የፍቅር ሰው መሆን ይረዳል።*

**ጥያቄ 26 ሀ:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- ምልክት ያደረክበት መልስ የትኛው ነው፣ ለምን?
- ልጆችህንም በቅንጅት የኢየሱስ ተከታዮች ማድረግ የምትችለው እንዴት ነው?

*ለምሳሌ፡ የክርስቲያኖች ጥሩ ምሳሌ ሁን፤ ለልጆችህ ጊዜን፣ ትኩረትን፣ ፍቅርን፣ ከሰርዓት ጋር ስጥ፤ ስንወድቅ ይቅርታን ጠይቅ፣ በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስ አብረሃቸው አንብብ ፣ በአማኞች የስብሰባ ጊዜ ይዘሃቸው ተገኝ።*

**ጥያቄ 26 ለ:** የመምህሩን የንግግር ሳጥን አንብብ። **መልመጃውን እንደ ቡድንህ ሁኔታ ተግባራዊ አድርግ፡** ለተማሪዎቹ ወረቀት እና እስክሪብቶ ስጥ። በ5 ደቂቃ ውስጥ እንዲጻፍ አሳስብ:

- ከሚስት ወይም ከባል ጋር ያለን ግንኙነት የሚያጠናክሩ አምስት ተግባራዊ ሃሳቦች።
- **ወይም፣** ካለገባህ/ሽ ፣ ጥሩ ባል/ ሚስት ለመሆን የሚረዱ 5 ለማደግ የምትፈልግባቸው ነገሮች።

## *ማጠቃለያ*

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** ስለጋብቻ የተማርከው በጣም አስፈላጊ ነገር ምን ነበረ? ይህንንም ወደ ተግባር የምትለውጠው እንዴት ነው?

- ከጻፍካቸው ሃሳቦች ውስጥ በዚህ ሳምንት ውስጥ የምትተገብረው የቱን ነው?
- **አበረታታ፡** ተገቢ የሆነ የክርስቲያናዊ የጋብቻ ስልጠና ካለ እንዲሳተፉ ምከር። ሰዎች ስለዚህ ትምህርት ማንኛውንም ጥያቄ ይዘው በግል እንዲያነጋግሩህ ፍቀድ።

**በአንድነት ጸልይ:** በጾታ ጥንድ እንዲሆኑ ወይም ባለትዳር ጥንዶችን አንድ ላይ በማድረግ ስለጋብቻ በተማሩት ዙሪያ መታዘዝ እንዲችሉ የእግዚአብሔርን እርዳታ ይጠይቁ።

# ትምህርት 12፡ ግጭቶቻችንን መፍታት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:** ሀ. ግጭቶችን በመጥፎ ሳይሆን በተሻለ መንገድ ለመፍታት መምረጥ።
ለ. ግጭትን በተሻለ መንገድ የመፍታት ሦስት እርምጃዎችን በመረዳት ተግባራዊ ማድረግ።
ሐ. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡11 ን ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)፡

**የባህል መገለጫዎች:**
- ግጭቶች እና አፈታታቸው
- እግዚአብሔር ስሜት አለው?

**ዝግጅት:** ሚናን መጫዎት ከተማሪዎችህ ጋር አብሮ መሄዱን ከግንዛቤ ውስጥ አስቀምጥ። ለጸሎት ጊዜ የሚሆን መዝሙር እና መስቀል አዘጋጅ፡
፡ .

## መክፈቻ

**ያለፈው ሳምንት ተግባራዊ ስራ ክለሳ:** በዚህ ሳምንት ውስጥ ጋብቻህን ለማጠናከር ወይም የትዳር አጋርህን ደስተኛ ለማድረግ እንዲረዳህ ያደረከው ምንድነው? ካለገባህ ደግሞ፣ ያደረከው ተግባራዊ ስራ ምንድነው?

**ትምህርት 12 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሦስቱም ግጭቶችን የመፍታት መጥፎ መንገዶች ናቸው።
**ጥያቄ 2:** ስሜትን፣ ማውራት፣ ይቅርታን ሰጥቶ መቀበል።
**ጥያቄ 3:** ሰላምን ይሻ ይከተለውም (1ኛ ጴጥሮስ 3:11)

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡** እኛ እንደ አማኞች በፍጹም ሰላም ውስጥ ያለግጭት መኖር እንችላለን? *በመርህ ደረጃ ይቻላል በተግባር ግን የክርስቶስ ተከታዮች ልክ እንደ ሌሎች ሰዎች ግጭቶች አሉባቸው። ይሁን እንጂ እኛ እንደ አማኝ ከሌሎች ይልቅ የተሻለ ግጭቶችን የመፍቻ መንገድ አለን።*

## ውይይት

### በክርስቶስ ተከታዮች መካከል ያሉ ግጭቶች (ጥያቄ 1-5)

**ጥያቄ 5:**

- ከ ሀ) እስከ ሠ) ካሉት ምርጫዎች መካከል ምልክት ያደረክበት የትኛውን ነው?
- በ ረ) ላይ ከራስህ ልምድ የጻፍከው ምስሌ ምንድነው?

### እግዚአብሔር ግጭቶቻችንን እንድንፈታ ይናፍቃል (ጥያቄ 6)

**ጥያቄ 6:**

- የእኛ ድርጊት እግዚአብሔርን ሊያሳዝነው ይችላል ብለህ ታስባለህ? *እስልምና የእኛ ተግባራት በእግዚአብሔር ላይ ምንም ሊያመጡእንደማይችሉ ያስተምራል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሊያመጡ እንደሚችሉ ያስተምራል። ለምሳሌ፡ በዘፍጥረት 6:5-6 ውስጥ፣ እግዚአብሔር ኃጢያትን በሰሩ ሰዎች ማዘኑን እና ልቡ በሀዘን መሞላቱን ይናገራል።*
- የእኛ ግጭቶች እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው ለምንድነው ብለህ ታስባለህ? *ለምሳሌ፡ ክርስቶስ እኛ በሰላም እንድንኖር ስለሚናፍቅ እና ለእኛ ሰላምን ለመስጠት ከባዱን ዋጋ ከፍሏል። በእኛም መካከል ግጭቶች ሲኖሩ ለማያምኑ ሰዎች መጥፎ ምስክርነት ይሆናል።*

**1ኛ ጴጥሮስ 3:8-12 አንብብ:**

- እርስ በርስ በሰላም ለመኖር የሚረዱን መልካም ተግባሮች እና አመለካከቶች ምንድን ናቸው? (ቁ. 8)
- ማስወገድ ያለብን መጥፎ ተግባራት ምንድን ናቸው? (ቁ.9)
- በፈንታው ማድረግ ያለብን ምንድነው?
- በተጨማሪ በቁ. 10 ላይ ልናደርገው የሚገባን ምንድን ነው? ለምን?
- በቀጠይ ጊዜ ከሌላ ሰው ጋር ግጭት ሲኖርህ፣ ይህ ክፍል በባህሪህ ላይ የሚመጣው ልዩነት ምንድነው?
- ከክፍሉም በቃል እንደሚጠና ጥቅስ አድርገን የወሰድነው የትኛውን ነው? ሁሉም የሚያስታውሰውን ይድገም።

*ቁ. 8፣ እንደ ወንድሞች ተዋደዱ፥ ርኅሩኆችና ትሑታን ሁኑ*
*ቁ. 9፣ ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ፥.*
*ቁ.10፣ መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልክል፤*
*ምክንያቱም የብዙ ግጭት ማማሰያው ይህ ስለሆነ።*

### መጥፎ የግጭት አፈታት መንገዶች (ጥያቄ 7-10)

**ጥያቄ 7-10:** ስለ ሦስቱ መጥፎ የግጭት አፈታት መንገዶች ተወያዩ።

- እነሱም በሰዎች እና በግንኙነት ላይ የሚኖራቸው አሉታዊ ተጽህኖ ምንድነው?
- በእነዚህ መጥፎ መንገዶች ገጠመኝ ያለው ሰው አለ? አሉታዊ ውጤቶቹ ምን ነበሩ?

## የተሻለ የግጭት መፍቻ መንገድ (ጥያቄ 11-23)

**ግጭቶችን ለምፈታት መጠቀም የምንችላቸው ሦስት መንገዶች ምንድናቸው? እያንዳንዱን እንወያይበታለን።**

**እርምጃ አንድ፡ ስሜትን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ።**

**ጥያቄ 11-13:** ስሜታችንን ወደ ሌላ ሰው ሄደን ከመናገራችን በፊት በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ የተሸለ የሚሆነው ለምንድነው?

*በእግዚአብሔር እርዳታ ቁጣችንን መቆጣጠር እንችላለን። ከዚያም ከሌላ ሰው ጋር ዝግ ባለ መንፈስ ማውራት እንችላለን። በቁጣ ግን የምንሄድ ከሆነ ጉዳዩን ሊያብሰው ይችላል።*

**እርምጃ ሁለት፡ ከሌላው ሰው ጋር ማውራት።**

**ጥያቄ 14:** የንግግር ሳጥኑን አንብብ።

- ስለውይይታቸው ጥሩው ነገር ምንድነው?
- እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግጭቶቻቸውን ለመፍታት የረዷቸው ለምንድነው?

*እነሱም ቀዝቀዝ ብለው፣ በጥንቃቄ እየሰሙ፣ ሌላውን ሳይረብሹ፣ ስሜታቸውን በመግለጽ፣ አሁንም ወዳጅ እንደሆኑ በመታመን ነው።*

**ጥያቄ 17:**

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር? ለምን? *ችግርን ከብዙ ሰዎች ጋር በምናወራ ጊዜ በንፋስ ውስጥ እንዳለ ዘር፣ ጉዳቱን እየጨመረ እና እርቅንም ከባድ እያደረገው በርቀት እና በስፋት ይሰራጫል።*
- ሁል ጊዜ እንደ አስታራቂ ሦስተኛ ሰው ማስገባት መልካም ነው?

*ሁል ጊዜ ግጭቱ በሁለቱ ሰዎች መካከል በቀጥታ ቢፈታ የተሻለ ነው። ነገር ግን አልፎ አልፎ በራሳቸው መፍታተት ካልቻሉ ፣ በተለየም አንዱ ሌላውን እጅ እንዲሰጥ የሚጫን ከሆነ ሁለቱም የሚያከብሩት አስታራቂ ማግኘት መልካም ነው። (ጥ. 9 ተመልከቱ)። ተወያዩበት።*

**እርምጃ ሦስት፡ ይቅርታን ሰጥቶ መቀበል።**

**ጥያቄ 20:** የንግግር ሳጥኑን አንብብ።

- በንግግር ውስጥ ይቅርታ የጠየቀው ማነው፡ ዓሊ ወይስ ካሪም?

*ሁለቱም! እያንዳንዳቸው የራሳቸውን ስህተት በመለየት ለዚያም ይቅርታን ተጠያይቀዋል።*

**የትግበራ ክፍለ ጊዜ – ግጭትን የመፍታት የሚና ጨዋታ (5 ደቂቃ እና ከዚያ በላይ ውይይት)**



ቡድኑን ጥንድ ጥንድ አድርጎ በመከፋፈል፣ በሚና ጨዋታ 1 ወይም 2 ውስጥ መመደብ። አንደኛው ሰው ‘ሀ’ ይሆንና ሌላው ደግሞ ‘ለ’ በመሆን እና ጥንዶቹ እንዴት ይህንን ግጭት ለመፍታት እንደሚቀራረቡ ያሳያሉ። ከዚያም አንድ ወይም ሁለት ጥንዶች በበጎ ፈቃደኝነት የሚና ጨዋታቸውን ለአጠቃላይ ቡድኑ ያቀርባሉ።

1. ‘ሀ’ ለጓደኛው ‘ለ’ አስቀድሞ ብር አበድሮት ነበር፣ ብሩም በሰዓቱ አልተመለሰለትም። ስለዚህ ‘ሀ’ ስለ ‘ለ’ ለሌላ ሰው ቅሬታውን ያሰማል።
2. ባል እና ሚስት የባል ዘመዶችን ምግብ ግብዣ ይጠሯቸዋል። ሚስትም(‘ለ’) ምግቡን ዘግይታ አቀረበች፣ የእሷም ባል(‘ሀ’) በእንግዶች ፊት ተቆጣት። እሷም እሱ እንዳዋረዳት ተሰማት እና እሱም እሷ እንዳዋረደችው ተሰማው።

**ጨዋታው ከታየ በኋላ፡ ሦስቱን እርምጃዎች ተጠቅመው ነበር? ምን ይመስል ነበር? የተማርከው ምን ነበር?**

**ጥያቄ 22-23:**

- ይቅር የምንለው ለምንድነው ? *እግዚአብሔር እኛን ይቅር ስላለን፡፡*
- አንድን ሰው ይቅር ማለት ያለብን ምን ያህል ጊዜ ነው? ማቴዎስ 18:21-22 በጋራ በማንበብ ተወያዩበት።
- በጥ. 23 ውስጥ ያለውን ስዕል ተመልከት። ከአንድ ሰው ጋር በምትታረቅ ጊዜ ስሜትህን ግለጽ።
- አንድ ሰው ለእርቅ ፈቃደኛ ካልሆነ እኛ ማድረግ የምንችለው ምንድነው? *የመምህሩን የንግግር ሳጥን አንብብ።*

**እያንዳንዱ ሰው ያለውን ወይም የሚያውቀውን ግጭት በእግዚአብሔር ፊት እንዲያቀርብ የጥሞና ጊዜን**

## *ማጠቃለያ*

| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** | **በአንድነት ጸልይ: እኛ ይቅር እንደተባለን አስታውስ!** |
|---|---|
| • ዛሬ ግጭቶችን እንዴት መፍታት እንዳለብህ ለውጥ እድታደርግ የተማርከው ምንድነው?<br>• **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።**<br>• ተግባራዊ ስራው ከሰውዬው ጋር እንድትነጋገር መንገድ ማዘጋጀት ነው ግን አሁንም ልታደርገው ይገባል። እግዚአብሔር ይህ ትክክለኛው ጊዜ ነው ካለ፣ ሄድ እና ከሰውዬው ጋር ተነጋገር። | 1. ስለይቅርታ የሚናገሩ መዝሙሮችን በጋራ ዘምሩ። ትኩረት እንዳይገ መስቀሉን ለሰው አታድርግ። ክርስቶስ ለእኛ ያለውን ይቅርታ ለመግለጽ ለጥሞና የሚሆን ጊዜን ተው።<br>2. ሰዎች ሊታረቁ ከሚፈልጓቸው ጋር እርቅን መፈጸም እንዲችሉ የእግዚአብሔር እርዳታ በመፈለግ በዝግታ እንዲጸልዩ ጠይቅ።<br>3. በዚህ ሳምንት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በሚያደርገው የይቅርታ እና የእርቅ ሂደት የእግዚአብሔር ባርኮት እና ጥበቃ አብሮ እንዲሆን ጸልይ። |

# ትምህርት 13፥ ምስክር መሆን

| ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ: | የባህል መገለጫዎች: |
|---|---|
| ሀ. ስለክርስቶስ ለሌሎች መናገር መፈለግ። <br> ለ. ለማን እና መቼ እንደሚናገር በማወቅ ጥበበኛ መሆን። <br> ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛያደረገውን መግለጽ መቻል። <br> መ. 1ኛ ጴጥሮስ 3፥18 ማስላሰል (በቃል ማጥናት)። | • ሙስሊሞች እና ምስክርነት (ሽሃዳ) <br> • ድፍረት ወይም ስጋት? <br> • ‘ድልድይ‘ ስዕል <br><br> **ዝግጅት:** ለጥ. 13 አማራጭ የሚሆን አጭር ፊልም |

## መከፈቻ

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** ከአንድ ሰው ጋር ያለህን ግጭት መፍታት ችለሃል ወይስ አሁንም አመቺ ዕድል እስከታገኝ ድረስ እየጸለይክ ነው? የሆነው ምንድነው?

**እግዚአብሔርን ለእኛ ስላደረገልን ነገር በማመስገን፣ ለዚህም ትምህርት መጸለይ።**

**ትምህርት 13 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሀ) አትፍሩ፤ ለ) የተዘጋጃችሁ፤ ሐ) በየዋህነት፣ በአክብሮት

**ጥያቄ 2:** ሀ) መልስን ለመስጠት የተዘጋጀች፤ ለ) በየዋህነት፣ በአክብሮት **ጥያቄ 3:** ጥ.10 ተመልከት (1ኛ ጴጥሮስ3:18)

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፥** በክርስቶስ ስላለ አዲስ ሕይወት የነገረህ ማነው? *እያንዳንዱ ሰው እንዲያካፍል ጠይቅ*

እኛ አዲስ ሕይወት ያገኘነው ይህን የነገረን አንድ ሰው ስለነበረ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ሌሎችም እንዲያገኙት ስለእኛ አዲስ ሕይወት ማካፈል እንፈልጋለን። ምስክር መሆን (*ሽሃዳ? ዳዕዋ*) የክርስቶስ ተከታይ ሁሉ ስራ ነው።

## ውይይት

### የክርስቶስ ምስክር መሆን (ጥያቄ 1)

**1ኛ ጴጥሮስ 3:14-18 አንብብ**

• ከ 1ኛ ጴጥሮስ 3:14-15 ለምስክርነት የምንማራቸው አስፈላጊ ሦስት መመሪያዎች ምንድናቸው? *‘አትፍሩ’፣ ‘መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ’፣ ‘ በየዋህነት እና በአክብሮት ይሁን’::*

### ‘አትፍሩ’ (ጥያቄ 2-7)



**ጥያቄ 5:** ጥያቄውን አንብብ።

- ከሙስሊም ቤተሰቦችህ መካከል የክርስቶስ ተከታይ መሆንህን ያወቁ የትኞቹ ናቸው?
- አንተም ብዙ ጊዜ የምትጸልየው በስዕሉ ላይ እንደምታየው ሰውዬ ነው ወይስ ሴትዮ?

**ጥያቄ 6:** ጥያቄውን አንብብ። እዚህ ላይ ጽፈህ የነበረው መልስ ምንድነው?

- ሙስሊም ቤተሰቦችህ የክርስቶስ ተከታይ መሆንህን ሲያውቁ ‘የፈተና ጊዜ’ ገጥሞሃል? ከገጠመህም፣ የሆነው እና ውጤቱ ምን ነበር? *ይህ አስፈላጊ ውይይት ስለሆነ አትቻኮል*
- ይህ እስካሁን ካላጋጠመህ፣ ለሌሎች የምትናገርበትን ጊዜ መምረጥ ትችላለህ ወይም ከአንተ ቁጥጥር ውጪ ሊከሰት ይችላልን? *ባልጠበቅነው ጊዜ ሊሆን ስለሚችል ለማንኛውም መዘጋጀት አለብን።*

### ‘መልስ ለመስጠት ... የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥’ (ጥያቄ 8-13)

**ጥያቄ 8:** ተማሪዎች ሀ፣ ለ እና ሐ ን ምን ሊሉ እንደሚችሉ እንዲያካፍሉ ጠይቃቸው። *መልስ የሚሆኑ*

*ሀ. ልጅ የአባቱን ስልጣን እና ባህሪ ያሳያል። እኛም ‘ልጅ’ የሚለውን ቃል በቀጥታ ሳይሆን እንደ ስዕላዊ መግለጫ እንጠቀመዋለን። ለምሳሌ፥ በአረቢኛ ‘የመንገድ ልጅ’ ሲባል ተጓዥ ማለት ነው፣ እና በፋርሳውያን ‘የካቡል ልጅ’ ሲባል ከካቡል የሆነ ሰው ማለት ነው፥*

*ለ. እኛ አባቶቻችንን፣ ዘራችንን እና ቤተሰባችንን እንወዳለን። እኔ የተከተልኩት ኢየሱስ ክርስቶስ ምዕራባዊ ሳይሆን ምስራቃዊ ነበር። በመጀመሪያው አንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ በዓለም ላይ የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖች ምዕራባውያን አልነበሩም እና ይህ ዛሬም እውነት ነው!*

*ሐ. ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ቀይረውታል የሚባለው እውነት አይደለም። ዛሬ በዓለም ሙዚዬሞች (ቤተ መዘክር) ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅደመ ጽሑፎች ይገኛሉ። እነሱንም በማስተያየት ስለመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ጽህፈት ታላቅ ልበ ሙሉነት ሊኖረን ይችላል።*

**ጥያቄ 9:** የንግግር ሳጥኑን አንብብ። ለዚህች ሴት የምትሰጠው መልስ ምንድነው?

**ጥያቄ 10:** ጥያቄውን አንብብ እና በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ተለማመድ።

## ትግበራ: የእኛን መልካም የምስራች ለሰዎች መንገር

**ጥያቄ 13:** ሁሉንም ጥንድ ጥንድ በማድረግ ከፋፍላቸው።

- የመጀመሪያው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ምን እንዳደረገ ለመግለጽ ሦስት ደቂቃ ይወስዳል። ለጥ.13 የጻፋትን መልስ መጠቀም አለባቸው። ከፈለጉ ጭማሪ 2 ንም መጠቀም ይችላሉ።
- ቦታ በማቀያየር ደግሞ ሁለተኛው ሰው ለገለጻው ሦስት ደቂቃ ይወስዳል።
- በድጋሜ በጋራ ሁኑ። ይህ ልምምድ 'መልስ ለመስጠት የተዘጋጀ እንድትሆን' ረድቶህ ነበር?
- 1ኛ ጴጥሮስ 3:18ን ጌታ ኢየሱስ ለሰው ምን እንዳደረገ ለመግለጽ ጠቃሚ ሆኖ አግኝተኸዋል?

**ታሪካችንን ከነቢያት መናገር :**

- በቀጥታ ከኢየሱስ እና ከአዲስ ኪዳን መጀመር አያስፈልገንም። የብሉይ ኪዳን ነብያትን ወደ መሲው ኢየሱስ የሚመሩን መንገድ አድርገህ መጠቀም የምትችለው እንዴት ነው?

*ሙስሊም ጓደኞቻችን እንደ አዳም (አደም) ፣ ኖህ (ኑህ) ፣ አብርሃም (ኢብራሂም) ፣ የሴፍ (የሱፍ) ፣ ሙሴ (ሙሳ) እና ዳዊት (ዳውድ) ያሉ ነቢያትን ያውቃሉ። ቁራን ግን ስለእነሱ ዝርዝር ነገር አይነግረንም። ስለነዚህ ነብያቶች በተውራት ውስጥ ብዙ ሳቢ መረጃዎች እንዳሉ ለጓደኞቻችን መንገር እንችላለን። ከዚያም እነዚህን ታሪኮች በመጠቀም እንዴት ፍጹም ወደ ሆነው መስዋት እና ለአዳም እርግማን መፍትኼ ወደ ሆነው ክርስቶስ እንደሚመሩን ማሳየት እንችላለን።*

*ጊዜ ካለህ የኢየሱስ ፊልም መግቢያን እይ (ከፍጥረት ጀምሮ የሚያሳየውን) ፣ ወይም በዩቲዩብ ላይ ያለውን የነቢያት ታሪክ። ሁለቱም 8 ደቂቃ የሚፈጁ ሲሆኑ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ማግኘት ይቻላል።*

## 'በየዋህነትና በአክብሮት/በፍርሃት/' (ጥያቄ 14-18)

**ጥያቄ 16-17:** ጥያቄዎቹን አንብብ።

- በጥያቄ 17 ውስጥ፣ በእነዚያ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የምታደርገው ምንድነው? *የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሁኔታዎች በጊዜ ሂደት ሊለወጡ ይችላሉ፣ ሦስተኛው ግን ቋሚ አስከትሎት ስላለው በጣም ከባድ ነው።*
- ስለክርስቶስ ብለህ ሙስሊም ቤተሰቦችህን እምቢ ማለት ባለብህ ሁኔታ ውስጥ፣ ይህን 'በየዋህነት እና በአክብሮት' ማድረግ የምትችለው እንዴት ነው? *በቁጣ ሳይሆን በአክብሮት ተናገር። ቤተሰብህን በብዙ ተግባራዊ ነገሮች በመደገፍ እንደምትወዳቸው አሳይ። እነሱን ለማሳፈር ነገሮችን አታድርግ። ትክክለኛውን ጊዜ ምረጥ።*

## የሕይወት እንጀራ (ጥያቄ 19-20)

**ጥያቄ 19:**

- የእኛ ስራ "አንድ ለማኝ ለሌላ ለማኝ ዳቦ የት እንደሚገኝ ነገረው" ዓይነት የሆነው ለምንድነው?

*መሀዲ ዲባጅ በክስ በቀረበበት ጊዜ በፋርስ ምሳሌያዊ አባባል ተመሳሳይ ነጥብ አስቀምጧል። እንዲህም ብሏል፣ "እነሱ የእኔን ወንጌል ስርጭት ይቃወማሉ። ነገር ግን 'በጉርጓድ አጠገብ አይነ ስውር ሰው ብታገኝ እና ዝም ብትለው ኃጢያትን ሰርተሃል።" ከስድስት ወር በኋላም ተሰውቷል። ብርቱ ምስክርነቱ የሕይወት ዋጋ አስከፍሎታል። ምስክር (ሸሃዳ ዳዕዋ ) መስዋት (ሸሂድ) ይሆናል።*

- ይህ የተገባ ነበር? የምታስበው ምንድነው?

**ጥያቄ 20:** ታሪኩን እና ጥያቄውን አንብብ።

- ለቤተሰቦቻችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለመንገር ከመቻኮላችን በፊት በእነሱ ዝግጁ መሆን እና ዝም ብሎ ለረጅም ጊዜ በመጠበቅ መካከል ያለውን ሚዛን ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?

***የሚከተሉትን ጨምሮ ልምድ ባላቸው አማኞች ምክር፥***

▶ ሕይወትህ ለቤተሰቦችህ አዎንታዊ ለውጥን ያሳይ፤ ▶የቤተሰቦችህን ሃይማኖት በክፉ አትተች፤ ▶ክርስቲያን መሆንህን ወዲያውኑ አትናገር፤ ▶ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጠቃሚ ትምህርት እንዳገኘህ ቀስ በቀስ ጥቀስ፤ ▶ቤተሰቦችህ የክርስቶስ ተከታይ መሆንህን በቀጥታ ቢጠይቁህ፣ አትካድ ▶እግዚአብሔር የእነሱን ልብ እንዲያዘጋጅ ጸልይ ▶ በቅድሚያ ግድ ለሚላቸው የቤተሰብ አባላት ተናገር ▶አንተ የክርስቶስ ተከታይ መሆንህን ለቤተሰቦችህ ለመንገር ከማቀድህ በፊት፣ እነሱ ሊሰሙ ይችላሉ፤ እግዚአብሔር ግን ከሁኔታው በላይ ስለሆነ ለበጎ ሊያደርገው ይችላል።

| *ማጠቃለያ* | |
|---|---|
| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** ይህ ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?<br>• **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** ስለኢየሱስ የምታካፍለው ምንድን ነው? | **በአንድነት ጸልይ:** ተማሪዎች ጥንድ በመሆን ስለእምነታቸው ማን እንደሚያውቅ ይነጋገሩ እና ከዚያም በተለይ በቤተሰብ ውስጥ ጥሩ ምስክር እንዲሆኑ፣ ስለጥበብ እና ብርታት እርስ በርስ ይጸልዩ፥ ፥ |

# ትምህርት 14፥ ጥምቀት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ጥምቀት የሚያሳየውን ሦስት እውነታዎች መረዳት።
ለ. ከዚህ ቀደም ያደረጉትን ጥምቀት ወደ ኋላ ዞረው በጸጸት ያያሉ ወይም ወደ ፊት ስለሚጠብቃቸው ጥምቀት በጉጉት ያቅዳሉ።
ሐ. ማቴዎስ 28፡19 ን ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)።

**የባህል መገለጫዎች:**

- ከእ.የመ.አ እና ጥምቀት በእስልምና ውስጥ ያለ ሃይማኖታዊ መታጠብ

## *መክፈቻ*

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** በዚህ ሳምንት እምነትህን ለአንድ ሰው በአንድ መንገድ ለመመስከር ወይም ለማካፈል ያለህ ዕድል ምን ነበረ? *ላልነበራቸው ደግሞ ፣ እየጸለዩ መሆናቸውን ጠይቃቸው።*

**ትምህርት 14 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ (Matthew 28:19).
**ጥያቄ 2:** ሀ) እኔ በክርስቶስ፤ ለ) ኃጢያቴ ታጥቦልኛል፤ ሐ) የክርስቶስን ማህበረሰብ **ጥያቄ 3:** አስፈላጊ ነው

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:**



አንተም ምስሉ እንደሚታየው ሐሚድ ነህ? ስለጥምቀት ያለህ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?
ዛሬ ጥያቄህን ለመመለስ እንሞክራለን።
**ለዛሬው ትምህርት ጸልይ** *ወይም ተማሪ እንዲጸልይ ጠይቅ።*

## *ውይይት*

### 'መጠመቅ ያለብኝ ለምንድነው?' (ጥያቄ 2-3)

**ጥያቄ 2:** ጥያቄውን አንብብ።

- ለመጠመቅ መሠረታዊ ምክንያት የሚሆነው ምንድነው? *ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላዘዘ።*
- ክርስቶስ ይህንን ትዕዛዝ ሲሰጥ የነበረውን ሁኔታ ታውቃለህ? *ከትንሳኤው በኋላ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፣ እሱ የጀመረውን ስራ የቅርብ ተከታዮቹ እንዲቀጥሉት አዟቸው ነበር። የክርስቶስ ተከታዮች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ደቀ መዝሙር ያደርጋሉ እና እነሱንም ያጠምቃሉ።*
- በቃል የተጠናውን ጥቅስ ማቴዎስ 28:19 ን ማለት የሚችለው ማነው? *ይህንንም እያንዳንዱ ሰው እንዲለው ጥያቄህን መልሰህ አቅርብ.*

### 'ጥምቀት የሚያሳየው ምንድነው?' እኔ በክርስቶስ አዲስ ሰው ነኝ (ጥያቄ 4-8)

**ጥያቄ 4:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- ጥምቀት ስለ እኛ አሮጌው እና አዲሱ ፍጥረት የሚያሳየው ምን እንደሆነ በራስህ ቃላት ግለጽ። *አሮጌው ፍጥረታችንን ለሞት በመስጠት እና ለአዲስ ሕይወት በአዲስ ፍጥረትነት መነሳት ነው።*

**ጥያቄ 7:** የፊራዝን ታሪክ አንብብ።

- የውሃ ጥምቀት የወሰዳችሁ፣ ከውሃው በወጣችሁ ጊዜ እንደ ፊራዝ ተሰምቷችሁ ነበር?
- ስሜቶቻችሁ ምን ነበሩ?

### 'ጥምቀት የሚያሳየው ምንድነው?' *የእኔ ኃጢያት ታጥቦልኛል* (ጥያቄ 9-11)

**ጥያቄ 10:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- የጥምቀት ውሃ የእኛን ኃጢያት ለማጠብ ምትሃታዊ ኃይል አለው? *የለውም*
- የእኛን ኃጢያት የሚጥብልን ምንድነው? *1ኛ ዮሐንስ 1:7- የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል. ውሃ የሰውነታችንን ቆሻሻ ያጥባል፣ ጥምቀት ግን ክርስቶስ ከልባችን ላይ ኃጢያታችንን እንዳጠበልን የሚሳይ ብርቱ ምልክት ነው።*

## ‘ጥምቀት የሚያሳየው ምንድነው?’የክርስቶስን ማህበረሰብ ተቀላቅያለው (ጥያቄ 12-14)

**ጥያቄ 12-13:** የክርስቶስን ማህበረሰብ ስለመቀላቀል የነረበውን ጥያቄ በሙሉ አንብብ።

- ‘እኔ የተጠመኩት ለራሴ ስል ነው፣ ይህ ደግሞ በእኔ እና በእግዚአብሔር መካከል ነው እና ቤተክርስቲያንን መቀላቀል አያስፈልገኝም’ የሚል ሰው ቢገጥምህ የምትለው ምንድን ነው?

በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12:13 *መሠረት፣* ጥምቀት ሲባል የክርስቶስ አካል - የእሱ ማህበረሰብ አባል *መሆን* ማለት ነው። ይህም ባህል ተኮር ቤተክርስቲያን ሊሆንም ወይም ላይሆንም ይችላል፣ እኛ ግን የአማኞችን ህብረት በአንድ መንገድ ልንቀላቀል ይገባል። እኛ የእነሱ ነን እነሱም የእኛ ዓበአንድነት በእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ ነን።

**ጥያቄ 14:** የመማሪያ መጽሐፍህን ሳትመለከት፣ ጥምቀት የሚያሳየው ሦስት እውነታዎች ምንድናቸው?

- ከእነዚህም መካከል ለአንተ በጣም አስፈላጊ የሆነው የትኛው ነው?

## ‘ጥምቀት በጣም አስፈላጊ ነው?’ (ጥያቄ 15-17)

**ጥያቄ 15-16:**

- እያንዳንዱ አማኝ መጠመቁ በጣም አስፈላጊ ነው? ለምን? *ተወያዩ።* ( ዝርዝሩን በአስተማሪዉ የዉይይት ጊዜ ውስጥ ይገኛል )

**የራስህን ምስክርነት ስጥ:**

እንበልና ይህ የአንተ ጥምቀት ነው እና ለቡድኑ በአጠቃላይ ምስክርነትህን ትሰጣለህ። በአምስት ደቂቃ ውስጥ የምትለው ምንድነው? ለጥ. 16 ያዘጋጀኸውን ማስታወሻ ተጠቀም።

*ምስክርነታቸውን ለአጠቃላይ ቡድኑ እንዲያካፍሉ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰዎችን ጠይቅ ወይም እንደ አማራጭ ጥንድ በመሆን ይከፋፈሉ። አንተም የራስህን ለማካፈል ተዘጋጅ! ከእስ.የመ.አ ብዙ ጊዜ አዲስ እንደመጣ አማኝ ይህንን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። አንዳንድ ጊዜ በተደጋጋሚ ይህንን እንዲያደረጉ ስለሚጠየቁ ላለመቅረብ የመፈለግ አዝማሚያን ያሳያሉ። ስለዚህ ይህን በማወቅ ምስክርነታቸውን ለቡድኑ ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆነው ማን እንደሆነ ጠይቅ።*

## ‘መጠመቅ ያለብኝ መቼ ነው?’ (ጥያቄ 18-22)

**ጥያቄ 21:** ለዚህ ጥያቄ የጻፍከው ምን ነበር? *አንዳንድ አስተያየቶች በሁኔታ ላይ የተመረኮዙ ናቸው*

- በአደባባይ አትናገረው, ነገር ግን የታመኑ ሰዎችን በሚስጥር ጋብዝ፤
- ከውጪ ያሉ ሰዎች በማያዩበት ጸጥ ያለ ቦታ ጥምቀት አድርግ፤
- አንድ ካሜራ ብቻ ይኑር፣ የፎቶውም ቅጂ ማን ሊኖረው እንደሚገባ ተጠማቂው ሰው ይወስን፤
- በካሜራውም ተጠማቂው ሰው በውሃ ውስጥ ሆኖ ፎቶ አታንሳው (ፎቶ በኋላ በቡድኑ ውስጥ ካሉ ጓደኞች ጋር ቢሆን)፤
- የጥምቀት ሠርተፍኬት የሚሰጥ ከሆነ፣ ሚስጥራዊ በሆነ ቦታ አስቀምጠው።

**ጥያቄ 22:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር?

*በጋራ ተወያዩ። በሁኔታ ላይ የተመረኮዘ ስለሆነ ትክክለኛ ሚባል መልስ የለም። ከትዳር አጋራቸው ጋር ለመጠመቅ የበቁ ሰዎች ብዙ ጊዜ ደስተኞች ይሆናሉ። ከብዙ ዓመት በኋላ ግን የትዳር አጋራቸው ወደ ክርስቶስ ካልመጣ፣ አማኝ የሆነው የትዳር አጋር በራሳቸው መንገደ መሄዱ ትክክል እንደሆነ ሊሰማው ይችላል።*

**ማስታወሻ:** እነሱም በመማሪያው መጽሐፍ ውስጥ ለጥያቄ 21 እና 22 አንድ ነገር መጻፋቸውን አረጋግጥ። መጻፍ ስለዚህ በደንብ እንዲያስቡ እና በውይይት ጊዜ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል።

- **የመምህሩን የንግግር ሳጥን አንብብ።**
- አዎን፣ ምንም እንኳን ጥምቀት በተወሰነ መልኩ አስጊ ቢሆንም፣ በጣም ልንፈራ አይገባም። የደስታ ጊዜ ነውና!”

## ማጠቃለያ

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** የዛሬው ትምህርት በአንተ ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?

- **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** ከማን ጋር መነጋገር እንዳለበት የማያውቅ ሰው ካለ፣ የሚሆን ሰውን ልትጠቁማቸው ትችላለህ።
- ከዚህ በፊት ካልተጠመክ፣ የዚህን ሳምንት ስራ ልትፈጽም ይገባል። ከተጠመቅህ ደግሞ ስለዚህ እርምጃ የሚያስብ የቡድንህን አባል በዚህ ሳምንት ልታገኘው ትችላለህ። ለዛም ሰው ምክርህን ስጠውና በጋራ ጸልዩ።

**በአንድነት ጸልይ:** ተማሪዎች በዝግታ እንዲጸልዩ እና መቼ እና እንዴት መጠመቅ እነደሚችሉ ሃሳባቸውን እንዲሰነዝሩ ጥቂት የጥሞና ደቂቃ ተውላቸው። ከዚያም ተማሪዎችን አንድ የሚያመሰግኑበትን እና አንድ ደግሞ የተቸገሩበትን ጉዳይ ጠይቅ። እግዚአብሔርን በማመስገን ስለ ችግራቸው ጸልይ።

# ትምህርት 15፡ ቀጥተኛው መንገድ

| **ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:** | **የባህል መገለጫዎች:** |
|---|---|
| ሀ. ለራሱ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለመኖር ይሰጣል።<br>ለ. በራሳችን ጥረት በቀጥተኛው መንገድ ላይ መሄድ እንደማንችል ይስማማል።<br>ሐ. ለክርስቶስ ባሪያ መሆን ለምን እውነተኛ ነጻነት እንደሚያመጣ ይረዳል።<br>መ. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19-20 ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)። | ● በእስልምና ውስጥ ሽሪያ እና ህግን መጠበቅ<br>● ሙስሊሞች እና ቀጥተኛው መንገድ<br>● ዋና እና ንዑስ ኃጢያቶች |

## *መክፈቻ*

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** ጥምቀት ስለመፈጸም ምክር አግኝተሃል ወይስ በዚህ ላይ ምክር ሰጥተሃል? የወሰንከው ምንድነው? *በቅርብ መጠመቅ የሚፈልግ አባል ካለ፣ ከስብሰባው በኋላ የሚኖረውን ዝግጅት ተወያዩ።*

**ትምህርት 15 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሀ) የሙሴ ህግ፤ ለ) የክርስቶስ ህግ **ጥያቄ 2:** ቅዱስ

**ጥያቄ 3:** ሀ) ፣ ለ) እና ሐ) ሁሉም በክርስቶስ ሽሪያ (ህግ) የተከለከሉ ናቸው፤ ለ መ) እና ሠ) ደግሞ ምን እንደጻፉ ጠይቅ።

**ጥያቄ 4:** 1ኛ ቆሮንቶስ 6:19-20 ። ጥ.21 ን ተመልከት።

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** በክርስትና ውስጥ ያሉ ህጎች በእስልምና ካሉት ቀላል ወይስ ከባድ ናቸው ብለህ ታስባለህ? *አባላት ያላቸውን ሃሳብ ይግለጹ። በቀጣይ ሦስት ሳምንታት ስለተለያዩ ሽሪያዎች እንማራለን። ተወያዩ።*

## *ውይይት*

### ሰዎች ቀጥተኛውን መንገድ የማይከተሉት ለምንድነው? (ጥያቄ 1-4)



***የሰከረውን ሰው ምስል ተመልከት።***

- ይህ ሰው ቀጥ ብሎ መሄድ ያልቻለው ለምንድነው? *በአልኮል ቁጥጥር ስር ስለሆነ ነው።*
- የዚህ ምሳሌ መንፈሳዊ ትርጉሙ ምንድነው? *ሰዎች በኃጢያት ቁጥጥር ስር ናቸው እናም እንደ ሱስ ተይዘውበታል፥ ፥ ቢፈልጉም እንኳን ቀጥ ብለው መሄድ አይችሉም።*
- ሰዎች በሃይማኖታዊ ጸሎት (ሰላት) ውስጥ፣ 'በቀጥተኛው መንገድ ላይ ምራኝ' ብለው ይጸልያሉ። እነሱም እግዚአብሔር ለምሪት በሺዎች የሚቆጠሩ ነብያትን እንደላከ ያስባሉ። ይህ ምሪት ግን በቀጥተኛው መንገድ ላይ እንዲሄዱ በቂ ነበር? ለምን? *ጸሎት እና ነቢያት መልካም ናቸው፣ ሰዎች ግን ቀጥ ብለው እንዲሄዱ ኃይል ያስፈልጋቸዋል።*

**ጥያቄ 3:** ጥያቄውን አንብብ።

- መጽሐፉ መ) ትክክለኛ መልስ ነው ይላል፣ አንተ ግን ትስማማለህ?
- ለሙስሊም ጓደኛህ ተጨማሪ ህጎች፣ ተጨማሪ ጸሎቶች እና ተጨማሪ ስራዎች፣ ሰዎችን ከኃጢያት እስራት ነጻ ለማውጣት በቂ እንዳልሆኑ የምትገልጸው እንዴት ነው?

*እነዚህ ነገሮች በሰው ደረጃ በጥቂቱ ይረዳሉ ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይል የሚያስፈልገውን መሠረታዊ ችግሮች መፍታት አይችሉም።*

### ንጹህ እና የረከሰ (ጥያቄ 5-6)

**ጥያቄ 5:** ጥያቄውን አንብብ።

- በሳጥን ውስጥ ያሰመርክባቸው ቃላቶች የትኞቹ ናቸው?
- ሃላል (ንጹህ) ምግብ ፈሪሳውያንን በውስጣቸው ሊያነጻቸው ችሎ ነበር? ለምን?
- የበለጠ አሳሳቢው ምንድነው፣ የረከሰ ምግብ ነው ወይስ የረከሰ ሃሳብ?

*'ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤'።*

*አልቻሉም፣ ምክንያቱም በውስጣቸው ያለው ኃጢያት በውስጣቸው አርክሷቸው ነው።*

*የረከሰ ሃሳብ የበለጠ አሳሳቢ ነው ምክንያቱም ልባችን በማቆሸሽ፣ ከዚያም የረከሱ ቃላት እና ስራዎች ይወጣሉ።*

**ጥያቄ 6:** የጻፍከው ምን ነበር?

- ቀላል የሚሆነው እጃችንን ማንጻት ነው ወይስ ልባችንን?

*ተማሪዎች <u>የግል አስተያየታቸውን</u> ሲጽፉ የበለጠ በጥልቀት እያሰቡበት ለውይይት ይዘጋጃሉ።*

### ለረከሰ ልብ የሚሆን የእግዚአብሔር መድኃኒት (ጥያቄ 7-10)

**ጥያቄ 7:** ጥያቄውን አንብብ እና የእያንዳንዱ ሰው ስም በመጥራት ጥቅሱን በጋራ በለው።

- እኛ በቀጥተኛው መንገድ እንድንሄድ ፈልጎ ያደረገ ማነው? እንድናደርግ ያስቻለን ማነው? *የእግዚአብሔር መንፈስ።*

## ለእግዚአብሔር መኖር (ጥያቄ 11-16)

**ጥያቄ 15:** አማራጮቹን በጋራ ተመልከቱ።

- የ ሀ) መልስ በግልጽ እውነት ነው፣ ነገር ግን የ ለ)ስ ምንድነው? ጥቃቅን ኃጢቶች አሳሳቢ ናቸው? ለምን?
- የ መ) መልስ ፣ ሐሰትን መናገር ነው፣ ወይስ የ ሠ) ክፉ ሃሳብ፤ ምን ትላለህ?
- የኃጢያት ሃሳቡ ቢኖረን እና ባናደርገው፣ ይህ አሁንም ኃጢያት ነው?

*በእስልምና ባይሆኑም በክርስቶስ ሸሪያ ግን አሳሳቢ ናቸው ምክንያቱም የእሱ ልቀት በጣም ከፍ ያለ ነው።*

*ሰይጣን በክፉ ሃሳብ ቢፈትነን እና ብንቋቋመው፣ ይህ ኃጢያት አይደለም።*
*ሆን ብለን ለማድረግ አቅደን የምናስብ ከሆንን ግን፣ ይህ ኃጢያት ነው።*

**ጥያቄ 16:** ጥያቄውን አንብብ።

- በዝርዝር ውስጥ ከቀረቡት መልሶች መካከል አስፈላጊ የሚመስሉህ የትኞቹ ናቸው? ለምን? *ከ1ኛ ጴጥሮስ የሆኑት ለ) ፣ ሐ) ፣ ሠ) እና ሰ) ናቸው፣ እነዚህም በክርስቶስ ህግ ውስጥ ያሉ ናቸው። ሀ) ፣ መ) እና ረ) ከኢንጂል የሆኑ አይደሉም፣ ሰለዚህ ለክርስቶስ ተከታዮች እንደ ግዴታ አይደሉም። ለ) ፣ ሐ) ፣ ሠ) እና ሰ) ለሌሎች ካለን አመለካከት እና ባህሪ ጋር የሚያያዙ ናቸው፡ ፡ እነዚህ ነገሮች በክርስቶስ ሸሪያ ውስጥ፣ በውጫዊ ገጽታችን ላይ እንደ ሀ) ፣ መ) እና ረ) ከሚያነጣጥሩ ነገሮች ወይም ሃይማኖታዊ ግዴታዎች ይልቅ በጣም አስፈላጊ ናቸው።*

## እውነተኛ ነፃነት (ጥያቄ 17-22)

***ሮሜ 6:11-18 አንብብ:*** ይህ ክፍል ከባድ ስለሆነ ተማሪዎች መያዝ እንዲችሉ ሁለት ጊዜ ወይም በሁለት እትም ይነበብ።



- ዚህን ክፍል ዋንኛ ሃሳብ መግለጽ የሚችል ማነው?
- በቁ.11 ውስጥ፣ እኛ መሞት እና መኖር ያለብን ለምንድነው?
- በህይወታችን ውስጥ ከኃጢያት ጋር መዋጋት እንዳለብን ቁጥር 12፣ 13 እና 14 ሦስት ጊዜ ይነግረናል። እነዚህ ሦስት ትዕዛዞች ምንድናቸው?
- በቁጥር 14 መሠረት፣ ከዚህ በኋላ ኃጢያት የማይገዛን ለምንድነው?
- እኛ ‘ከጸጋ በታች’ ከሆንን፣ የምንፈልገውን ማድረግ እንችላለን ማለት ነው? ለምን? ቁጥር 15-16 ተመልከት።
- እኛ አሁን የጽድቅ ባሪያዎች መሆናችንን ቁጥር 17-18 ይናገራል። ይህ ከአንተ ልምድ አንጻር ሸክም ነው ወይስ ደስታ?
- ቆም በል እና አስብ፡ መሆን የምትፈልገው ለኃጢያት ባሪያ የሆነ ወይስ እግዚአብሔር ለመታዘዝ ነጻ የሆነ ሰው?

*ለኃጢያት በመሞት፣ ለእግዚአብሔር መኖር።*

*‘በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤’ (ቁ.12)፣ ‘ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥’ (ቁ. 13), ‘ኃጢአት አይገዛችሁምና፤’ (ቁ. 14)።*
*እኛ ከጸጋ እንጂ ከህግ በታች አይደለንም።*

*አንችልም! ምክንያቱም ራሳችንን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት አቅርበናል። ነጻ የወጣነው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንጂ ለኃጢያት አይደለም።*

*ደስታ ነው። ውይይቱም ኃጢያትን የመዋጋት ተግዳሮት ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር መኖር ያለውን አዎንታዊ ደስታ ያካትታል።*


**ጥያቄ 17:** ጥያቄውን በሙሉ አንብብ።

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር?

*1ኛ ጴጥሮስ 4:2-3 እንደ ሰው ምኞት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንኖር ይነግረናል።*

**ጥያቄ 19:** በስዕሉ ላይ ያለውን ሰው ተመልከት።

- ይህ ሰው በእውነት ነጻ ነው ወይስ አይደለም? የጻፍከው ምንድነው?



**ጥያቄ 20:** ከዚህ በፊት የነበረው ሰው በዚህ አለ።

- በእስራቱ ላይ የሆነው ምን ነበር? *በመስቀሉ ፊት መበጣጠስ*
- እውነተኛ ነጻነት የምናገኘው እንዴት ነው፣ ለራሳችን በመኖር ወይስ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመኖር:

*እወነተኛ ነጻነት የሚመጣው የክርስቶስ ባሪያ በመሆን ነው። ይህ እንግዳ ንግግር ግን ደግሞ እውነት ነው።*

- ኢየሱስ ከመጥፎ ልምምዶቻችን እንዴት ነጻ እንዳወጣን ከራሳችን ሕይወት ምሳሌዎችን እናካፍል።

*እንደ አማካሪ ከራስህ ሕይወት እውነተኛ ምሳሌን በመስጠት ለእግዚአብሔር የመኖር ደስታን ተናገር።*

**ጥያቄ 21:** በቃል የሚጠናውን ጥቅስ አንብብ ተለማመድ (ከ 1ኛ ቆሮንቶስ 6:19-20 የተወሰደ)። እያንዳንዱ የቡድን አባል ቀጥሎ የሚለውን ሰው ስም በመጥራት ጥቅሱን ሊናገር ይገባል። ለምሳሌ፡ ‘ኡመር፣በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።’

## *ማጠቃለያ*

| ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ | ንድነት ጸልይ |
|---|---|
| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** ዛሬ የተማርከው በጣም አስፈላጊ ነገር ምንድነው? በአንተ ሕይወት ላይ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?<br>**ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** በልዩ ልዩ ኃጢያቶች ለሌሎች ተጠያቂ እንድንሆን ሊረዳን ይችላል። ጥንድ በመሆን በግልህ ከቁጣ ጋር ያለብህን ትግል በግልጽ ተናገር። በዚህ ሳምንት ቁጣህን እንዴት እየተቆጣጠርከው እንዳለ (ታማኝ ሁን!) በየቀኑ መዝግበህ ያዝ። ስለዚህም እርስ በርስ መልክት ልትለዋወጡ ትችላላችሁ። | **ንድነት ጸልይ:** ከኃጢያት ባርነት ነጻ ጣንን እግዚአብሔር አመስግኑ። በዚህ ሳምንት ርስቶስ ባሪያ እንድንሆን እሱ እንዲረዳን ጠይቁት፡ |

# ትምህርት 16፥ የመውደድ ህግ

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ጌታን በፍጹም ልባችን እና ባልጀራችንን ደግሞ እንደ ራሳችን እንድንወድ
ለ. እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር፣ እኛ ለእሱ ባለን ፍቅር ላይ የተመረኮዘ አለመሆኑን ያረጋግጣሉ።
ሐ. ከምስጋና ጋር ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር እንደምናውል መረዳት።
መ. ማርቆስ 12፥30-31 ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)።

**የባህል መገለጫዎች:**

- ሙስሊሞች ለመታዘዝ ያላቸው ተነሳሽነት
- ሙስሊሞች፣ ከእ.የመ.አ እና አቀባበል

**ዝግጅት:** ከፈለክ፣ ለጌታ እራት እንዲሆንህ ህብስት እና ወይን አዘጋጅ

## መክፈቻ

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** በዚህ ሳምንት ቁጣህን የተቆጣጠርከው እንዴት ነው? ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ እንዳደረከው ቡድኑን በተመሳሳይ ጥንዶች ከፋፍልና እና እርስ በርስ ምን መልካም እንደ ነበር እና እንዳልነበር ይነጋገሩ። *ከአምስት ደቂቃ የእርስ በርስ ንግግር በኋላ፣ ተማሪዎች እያንዳንዱን ሐረግ ከአንተ በኋላ እንዲሉ በማድረግ ይህን ጸሎት ጸልይ፥*
እግዚአብሔር ኣባት ሆይ... ኃጢያታችንን ብንናዘዝ ለእኛ ስለሰጠኸው ተስፋ እናመሰግንሃለን... አንተ ታማኝ እና ጻድቅ ነህ... ኃጢያታችን ይቅር በማለት ከጽድቅ ከጎደልንበት ነገር ሁሉ አንጻን...እያንዳንዳችን ባለፈው ሳምንት ስለተናገርነው የቁጣ ቃል እባክህ ይቅር በለን... አንጻን እና በመንፈስህ ሙላን... በዚህ ሳምንት ደግሞ አንተን የበለጠ እንድናገለግልህ እርዳን። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።

**ትምህርት 16 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ***ፊተኛው:*** በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን
***ሁለተኛው:*** ባልንጀራህን እንደ ራስህ

**ጥያቄ 2:** የፍቅር

**ጥያቄ 3:** ሀ) ሀሰት፤ ለ) እውነት

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፥** እኛ አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ነን፣ የምንኖርበትስ ህግ ምንድነው? *የክርስቶስ ህግ ወይም የክርስቶስ ሸሪያ። የክርስቶስን ሸሪያ የፍቅር ህግ ብለን እንጠራዋለን። ዛሬ እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ፍቅር፣ እኛ ደግሞ ለእግዚአብሔር እና ለሌሎች ሰዎች ስላለን ፍቅር እንማራለን።*

## ውይይት

### እግዚአብሔር አስቀድሞ እኛን ወዶናል (ጥያቄ 1-5)

የሁለቱን አገልጋዮች ስዕል ተመልከቱ። ጌታውን ለማገልገል ደስተኛ የሆነው አገልጋይ የቱ ነው? ለእኛ ያለው ትርጉም ምንድነው? *እግዚአብሔርን የምናገለግለው እኛን ላዳነበት ምስጋና እንዲሆንልን ነው። ሌሎች ግን ቅጣትን በመፍራት ነው።*

**ጥያቄ 4:** ጥያቄውን አንብብ።

- እኛ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ተጠብቀናል?
- ለጊዜውም ቢሆን እሱ እኛን ወደ ገሃነም ይልከናል?
- ስለዚህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን የምናገለግለው ለምንድነው?

*አዎን፣ እኛ በክርስቶስ ከሆንን። አይልከንም፣ ክርስቶስ የኃጢታችን ዋጋ ከፍሏል። ብዙ ሙስሊሞች በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ ይሂዱ ወይም ለጥቂት ጊዜ በገሃነም ያሳልፉ እርግጠኛ አይደሉም።*

### እግዚአብሔር መውደዱን አረጋግጧል (ጥያቄ 6-10)

**ጥያቄ 7-8 :** በዓለም ዙሪያ ያሉ የክርስቶስ ተከታዮች ሁለት የተለዩ ስርዓቶች አሏቸው። ስለጥምቀት አስቀድመን ተምረናል፥፥ ሌላው ደግሞ የጌታ እራት ወይም ቅዱስ ቁርባን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለእኛ የሆነውን መሰዋትነት እንድናከብረው እና እንድናስታውሰው የምንካፈልበት ነው። **ጥያቄ 7-8 ን በሙሉ አንብብ።**

- የጌታ እራትን ምን ያህል ጊዜ ተካፍለሃል? ወይስ ዕድሉ አጋጥሞህ አያውቅም?

*አንዳንድ አማኞች ብዙ ጊዜ ሌሎች ደግሞ አልፎ አልፎ ያደርጉታል። አንዳንድ ተማሪዎችም እስካሁን አልተካፈሉ ይሆናል።.*



- አንተ ባለህበት የአማኞች ህብረት ውስጥ ይህንን ስርዓት ምን ብለው ይጠሩታል?
- ህብስቱን እና ወይኑን በምትወስድ ጊዜ ያለህ ስሜት ምንድነው?
- አንተ ባለህበት የአማኞች ህብረት ውስጥ የሚጠቀሙት ወይን ነው ወይስ ጁሱን? ወይን ቢሆን፣ ይህ ለአንተ ችግር ይሆንብሃል?

በሙስሊም ሀገሮች ውስጥ በርካታ ቤተክርስቲያናት አልኮል የሌለው ጁስ ይጠቀማሉ። በምዕራቡ ዓለም ግን እንደየ ቤተ-እምነቱ ይለያያል። አንድንድ ከእ.የመ.አ አልኮል ይጠጣሉ ሌሎች ደግሞ አይጠጡም፣ ስለዚህ ይህንን ጥያቄ ለተማሪዎቹ አቅርብ። ዘመናዊ ሰው ትንሽ ወይን ጎንጨት ማለት በሌላ ማእቀፍ ውስጥ ከመጠጣት ለየት አድርጎ ሊወስደው ይችላል፥

- የማያምኑ ሰዎች ህብስቱን እና ወይኑን እንዲወስዱ መፍቀድ አለብን? *በፍጹም። ይህ ለክርስቶስ ተከታዮች ብቻ ነው።*

## የመውደድ ህግ (ጥያቄ 11-13)

**1ኛ ዮሐንስ 4:7-13 አንብብ:**

- እግዚአብሔር ፍቅር ነው የሚለው ጥቅስ የቱ ነው? ይህ ምን እንዲሰማህ ይደርግሃል?
- እግዚአብሔር ምላሽ ሳንሰጠው እንደወደደን የሚያሳየን ጥቅስ የትኛው ነው?እግዚአብሔር ፍቅሩን ለእኛ ያሳየን እንዴት ነው?
- በቁጥር 7 እና 11 መሠረት፣ ለእግዚአብሔር ፍቅር ምላሽ መስጠት ያለብን እንዴት ነው?
- እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለም፣ እርስ በርስ ስንዋደድ ግን እነሱ ምን ማየት ይችላሉ? ቁ. 12



*ቁጥር 8።*
*ቁጥር 9-10.*
*እግዚአብሔር ልጁን ላከ (ቁ.9) እንደ ስርየት መስዋት (ቁ.10).*
*(እግዚአብሔር የሚወደው ራሳቸውን የሚያነጹትን ነው ከሚለው የቁራን ትምህርት ጋር አነጻጽር።)*
*እርስ በርሳችን በመዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እንደሚኖር እና ፍቅሩ በእኛ ውስጥ ሙሉ እንደሆነ ያያሉ፡፡*

**ጥያቄ 13: በቃል ያሰላሰልከውን ጥቅስ በመከለስ ተለማመድ:** ማርቆስ 12:30-31

- ይህ የክርስቶስ ህግ ማጠቃለያ ለማሰላሰል አጭር እና ቀላል ነው። ለመታዘዝ ግን የቀለለ ነው?
- ይህንን የፍቅር ህግ እንድንታዘዝ የሚያስችለን ማነው? *በህይወታችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ*

**ጥያቄ 14:** የመረጥከው ዝርዝር ነጥብ የትኛው ነው? ለምን? *አማካሪውም ሊያካፍል ይገባል።*

## ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ (ጥያቄ 15-25)

**ጥያቄ 17:** አራቱን ስዕሎች ተመልከት። የክርስቶስን ሸሪያ (ህግ) ማን እንደሚታዘዘው ተወያዩ።

- በስዕል ሀ ውስጥ፣ ባል ሚስቱን ለማስደሰት የሚፈልገው ምንድነው?
- በስዕል ለ ውስጥ፣ የክርስቶስን ህግ ለመታዘዝ፣ ባል ምን ማድረግ አለበት?
- በስዕል ሐ ውስጥ፣ የዚህችን ሴት ጸሎት እግዚአብሔር በምን ዓይነት መንገድ ሊመልስላት ይችላል?
- በስዕል መ ውስጥ፣ ልጅቷ የክርስቶስን ሸሪያ (ህግ) አልታዘዘችም። ውጤቱ ሊሆን የሚችለው ምንድነው?

**ጥያቄ 19:** ጥያቄውን አንብብና ተወያዩ።

**ጥያቄ 22:** በሳጥን ውስጥ ያለውን እውነተኛ ታሪክ አንብብ።

- ታሪኩ ካለበት ሳጥን ቀጥሎ ያለውን ክፍል አንብብ። እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር?

**ጥያቄ 24:** የፋሪድ እና አስጋርን ምስል ተመልከት።

- የወደድከው የትኛውን ነው?

**ጥያቄ 25:** ጥያቄ 25 ን በሙሉ አንብብ እና የንግግር ሳጥኑን አንብብ።

- ምን ታስባለህ? ጠላቶቻችንን መውደድ ይቻላል? *ፊልጵስዮስ 4:13 ተመልከት!*
- ከክርስቶስ ተከታዮች መካከል ጠላቶቻቸውን የወደዱ እውነተኛ ምሳሌን መስጠት ትችላለህ?

**በዚህ ዓለም እና በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ ጠላቶቻቸውን መውደድ ከጀመሩ፣ ውጤቱ የሚሆነው ምንድነው?**

*አንድ እውነተኛ ታሪክ በትምህርት 10 ውስጥ ያለው የፋሪድ ታሪክ ነው።. ሌላው ደግሞ ለእግዚአብሔር እብድ መሆን በሚለው የኒክ ሪፕከን መጽሐፍ ውስጥ ለዓመታት በእሰር ቤት፣ ጠባቂው እያሰቃየው ስላሳለፈው ሰው የተጻፈው ነው። ከእሰር ከተለቀቀ ከብዙ ዓመታት በኋላ ያንን ጠባቂ አርጅቶ እና ታሞ ያገኘዋል። ይህም አማኝ ለዚህ ሰው ጸልዮለት መድሃኒት ገዝቶለታል።.*

## *ማጠቃለያ*

| **ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:** | **በአንድነት ጸልይ:** አመቺነቱ ከተሰማህ የጌታን እራት በጋራ ውሰዱ። ከዚያም ኢየሱስን ስለሰጠን ስጋው እና ደሙ የምታመሰግኑበት እና እያንዳንዱ የመውደድን ህግ የሚከተልበት ልብ እንዲኖረው የሚጸልይበት ጊዜ ይኑራችሁ። |
| --- | --- |
| • 1ኛ ጴጥሮስ 4:7 'እርስ በርሳችን እንዋደድ' ይላል። የዛሬው ትምህርት በአንተ ሕይወት ውስጥ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?<br>• **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።**<br>• በቤት ውስጥ ያለህንን ጥናት እና ተግባራዊ ስራ በየሳምንቱ ማድረግህን ቀጥል። | |

# ትምህርት 17፡ ጾም እና መስጠት

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይችላል።
ለ. ጸሎት ሃይማኖታዊ ጉዳይ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር መሆኑን ይረዳል።
ሐ. የንስሐ፣ የምስጋና እና የልመና ጸሎቶችን ይማራል።
መ. የጌታን ጸሎት ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)።

**የባህል መገለጫዎች:**

- የጸሎት ስነ-መለኮት
- የሱፊ ተመስጦ
- የሙስሊሞች ጸሎት እና 'ውዱ' መንጻት
- የጸሎት ዝርዝር ማዘጋጀት

## *መከፈቻ*

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** በክርስቶስ ወንድሞቻችን ወይም እህቶቻችን ለሆኑ በችግራቸው መርዳት ቻልክ፤ ያደረከው ምን ነበር? የሰውዬው ምላሽ እንዴት ነበር? **ስለዛሬው ትምህርት አንድ ሰው እንዲጸልይ ጠይቅ።**

**ትምህርት 17 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ** 1: ቃል ፣ መንፈስ **ጥያቄ** 2: ጸሎት

**ጥያቄ** 3፡ ሀ) ሁሉም፣ ለ) የሚቻለውን ሁሉ **ጥያቄ** 4: ሀ) እግዚአብሔር፣ ህዝቡ; ለ) የመውደድ

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡**ስለ ክርስቲያናዊ ሸሪያ እስካሁን የተማርነው ምንድነው? *የመግቢያውን ትምህርት እይ።* እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ከድሮው ሸሪያችን በላቀ መልኩ በልዩ ልዩ ምክንያቶች እንጾማለን እና ገንዘብ እንሰጣለን።

## *ውይይት*

### እግዚአብሔር በቀጥተኛው መንገድ የሚመራን እንዴት ነው? (ጥያቄ 1-5)



**ጥያቄ 1:** የሁለቱን በጎች ስዕል ተመልከት።

- ከእነዚህ በጎች መካከል የድሮ እና የክርስቶስ ሸሪያችንን የሚመስለው የትኛው ነው? ልዩነቱስ ምንድነው?

*የእስልምና ሸሪያ በጎቹን በትክክለኛ ቦታቸው ለመጠበቅ በደንብ እንደ ተገነባ አጥር ነው። ዝርዝር ህጎቹ በተከለከሉ እና በተፈቀዱ ነገሮች መካከል ድንበርን ያበጃሉ። ከክርስትና ጋር ሲነጻጸር ጥቂት ዝርዝር ህጎች ስላሉት የትጋር ድንበሩ እንዳለ ማወቅ አይቻልም። እኛ ግን ክርስቶስ ራሱ እንደ እረኛ አብሮን አለ። እሱ በጎቹን ወደ መልካም ሁሉ ሊመራና ሊጠብቅ ቃል ገብቷል።*

**ጥያቄ 3-4:** ጥያቄ 3 እና የጥያቄ 4 ን የመጀመሪያ አንቀጽ አንብብ።

- ክርስቶስ በመንፈሱ አማካኝነት ሲናገረን መስማት የምንችለው እንዴት ነው? *በየቀኑ በምናነበው የእግዚአብሔር ቃል፣ ጸጥ ባለ ስፍራ ላይ ድምጹን በመላክ፣ ወደ አይምሮአችን ብርቱ ሃሳብን በማምጣት፣ ወይም በመንፈሳችን ውስጥ በሚሰማን ስሜት ይናገረናል፡፡ በሌሎች አማኞች ምክርም ተጠቅሞ ያናገረናል።*
- የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ከመስማት አኳያ ግን ስህተት ልንፈጽም እንችላለን? *አዎን! አንዳንድ ጊዜ ከራሳችን የኃጢአት ምኞት ብቻ የመጣውን ነገር እንደ እግዚአብሔር ድምጽ እናስበዋለን። እግዚአብሔር ለእኛ የሚነግረን ማንኛውም ነገር በቃሉ ከተጻፈው ጋር አይጣረስም። ስለዚህ ሁል ጊዜ የምንሰማው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይቃረን መሆኑን ልናጣራ ይገባል !*

### ጾም (ጥያቄ 6-14)



**ጥያቄ 6-7:** የጥያቄ 6 የመጀመሪያውን አንቀጽ እና የንግግር ሳጥኑን አንብብ።

- አንተም እንደ ፓርቨን ጥያቄ አለህ? ወይስ ስለጾም ሌሎች ጥያቄዎች አሉህ?
- ከጥያቄ 7 ላይ፣ ፓርቨን ለጥያቄዎቿ መልስ እንድታገኝ ሊረዷት የቻሉ ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?

**ጥያቄ 8: የምንጾመው ለምንድነው?** *ተማሪዎቹን በሦስት ቡድን በመከፈል፣ እያንዳንዱ ቡድን ከተሰጠው ክፍል መሠረት ጥያቄውን ይመልሳል። ወይም እያንደንዱ ክፍል በጋራ ማየት።*

- በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ፣ ሰዎች ይጾሙ የነበረው ለምንድነው?

**ዳንኤል** 9:3-5 – *ኃጢያትን ለመናዘዝ፣ ንስሐ እና ልመና።*

**መዝሙር** 35:13 – *ለተቸገረ ሰው ለመጸለይ*

**ሐዋ. ስራ** 13:2-3 – *ለአምልኮ፣ ለተልዕኮ ለመጸለይ እና ለውሳኔ የሚረዳ ጥበብን በመፈለግ.*

**ጥያቄ 12: መጾም ያለበን መቼ ነው?** ጥያቄውን አንብብ።

- *መጾም ያለብን መቼ ነው? ለእኛ ጾም እንደ ግዴታ ነው ወይስ እንደ አማራጭ?* *መንፈስ እንድንጾም ይመራናል።*

**ጥያቄ 13:** ጥያቄ 13 እና በደማቅ የተጻፈውን ቆም ብለህ አስብ ክፍል አንብብ።

- ለዚህ ጥያቄ የአንተ የግል መልሶችህ ምንድናቸው?

**ጥያቄ 14:** ይህ ጉዳይ በአንተ አውድ ውስጥ ተገቢ ከሆነ፣ ጥያቄ 14ን በሙሉ አንብብ።

- ፓርሽን ከቤተሰቧ ጋር በረመዳን ወቅት መጾሟን በመደገፍ እና በመቃወም ያስቀምጥካቸው ምክንያቶች ምንድነው?

***የምትደገፍበት ምክንያት:*** *የኢየሱስ ተከታይ ብትሆንም እንኳን ለቤተሰቦቿ ያላትን ታማኝነት ማሳየት ትችላለች። ቤተሰቦቿ እንዲደጉ መጾም እና መጸለይ ትችላለች። የማትጾም ከሆነ በእሷላይ አላስፈላጊ ችግሮች ሊፈጠሩ እና ቤተሰቦቿም የክርስቶስ ተከታዮችን እንደ ሰነፍ አድርገው ሊቆጥሩ ይችላሉ።* ***የምትቃወምበት ምክንያት:*** *እሷ አሁንም እስልምናን የምትከተል ወይም ስለሃይማኖቷ ስትል የምትፈጽመው አድርገው ሊያስቡ ይችላሉ። እሷም በቀድሞ ሃይማኖት እሳቤ ተጽህኖ ስር ልትሆን ትችላለች።*

- የፓርሽን ውሳኔ በሁኔታዋ ላይ ሊመሠረት የሚችለው በምን ያህል ገደብ ነው? *ለምሳሌ፡ ቤተሰቦቿ አክራሪ ከሆኑ እና እሷም ከእነሱ ጋር የምትኖር ከሆነች። ለብቻቸው የሚኖሩ ሰዎች ግን ብዙ አማራጭ አላቸው።*
- አንተስ ባለህበት ሁኔታ ውስጥ እንዴት ነህ?

## መስጠት (ጥያቄ 15-25)

**ጥያቄ 15:** የመጀመሪያውን አንቀጽ እና የንግግር ሳጥኑን አንብብ።



- ከካሊድ ጋር ተመሳሳይ ጥያቄ አለብህ? ወይስ ስለመስጠት ሌሎች ጥያቄዎች አሉህ?

**ጥያቄ 16-19:** ጥያቄ 16ን በሙሉ እና የጥያቄ 17ን የመጀመሪያ አጋማሽ አንብብ።

- ካለን ንብረት ውስጥ ምን ያህሉ ነው የእግዚአብሔር የሆነው?
- ለእሱ መልስን በመንሰጠው ላይ ገደብ ማስቀመጥ አለብን?

**2ኛ ቆሮንቶስ 9:6-15 አንብብ:**

የቡደን አባላቱ እያንዳንዳቸው አንድ ወይም ሁለት ጥቅስ እንዲያነቡ ጠይቅ፣ ሁሉም ሰው የሚያነበው ነገር እንዲኖር በቡድኑ መካከል እየተዟዟርክ ተመልከት።

*ከተነበበም በኋላ እያንዳንዱ ሰው ስለትርጉሙ እንዲያስብ፣ አንድ ደቂቃ የጥሞና ጊዜ ስጥ።*

- እያንዳንዱ ሰው የጥቅሱን ትርጓሜ በራሱ ቃል ይግለጽ።

**ጥያቄ 21:** ጥያቄውን አንብብ። ለጥያቄው የአንተ መልስ ምንድነው፣ ለምን?

**ጥያቄ 24:** ጥያቄውን አንብብ።

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር? ገንዘብን በተግባር ሳታጠፋ ለብቻው ማስቀመጥ የምትችለው እንዴት ነው?
- ገቢ ከሌለህ፣ ለእግዚአብሔር መስጠት የምትችለው ሌላ ነገር ምን አለ? *ለማሳሌ፡ ጊዜያችንን፣ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት እና የመሳሰሉት። ብዙ ሰዎች ግን ቢያንስ ጥቂት ገንዘብ አላቸው፣ ከዚያም መስጠትን መማር አለብን። ልጆችም ቢሆኑ ከሚያገኙት ጥቂት ሳንቲም መስጠት ይችላሉ።*

**ጥያቄ 25:** ጥያቄውን አንብብ። እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር? *ቤተሰቦቻችንን ብቻ ሳይሆን ድሆችንም መርዳት። የማያምኑ ሰዎችን ለመጥቀም ወንጌልን እና ስለኢየሱስ የሚናገሩ መጽሐፎችን መግዛት። በአካባቢያችን ላለ የአማኞች ህብረትን ወጪ መጋራት። የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆነው በሀገራችን ወይም ከሀገራችን ውጪ ያሉትን አማኞች በገንዘብ ማገዝ የሚሉትን ሃሳቦች ያካትታል።*

## የመውደድ ህግ (ጥያቄ 26)

**ጥያቄ 26:** ጥያቄውን አንብብ።

- ጾም የመውደድ ህግን ለመታዘዝ መንገድ መሆን የቻለው እንዴት ነው? *ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተነሳ ካለምግብ በመሆን ራሳችንን በማዋረድ በፊቱ እንሆናለን። በችግር ላይ ላሉ ሰዎችም በምንጸልይ እና በምንጾም ጊዜ፣ ይህ እኛ ለእነሱ ያለንን ፍቅር ያሳያል።*
- ገንዘብን መስጠት የመውደድ ህግን ለመታዘዝ መንገድ መሆን የቻለው እንዴት ነው? *ምክንያቱም ካለን ላይ መልሰን ለእግዚአብሔር በመስጠት ለእሱ ያለንን ፍቅር እና ሌሎች ሰዎችን በገንዘብ በመርዳት ፍቅራችንን እናሳያለን።*

## ማጠቃለያ

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:**

- የዛሬው ትምህርት በአንተ ህይወት ውስጥ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?
- **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** ለእግዚአብሔር ገንዘብ መልሰህ ለመስጠት አስቀምጣለው ብለህ አታስብ፣ ይልቁኑ በዚህ ሳምንት ጀምር!

*ከፈለጋችሁ እንደ ቡድን የጾም እና የጸሎት ቀንን ወስኑ። ቀኑን በሙሉ ስትጾሙ ውላችሁ በጸሎት የተወሰነ ጊዜ አብሮ ለማሳለፍ መገናኘት ትችላላችሁ። ለምሳሌ፡ ለአንድ ዓላማ ማድረግ ትችላላችሁ*

**በአንድነት ጸልይ:** ጥቂት የጽሞና ጊዜ በመውሰድ፤ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን እንዴት እና መቼ መጾም እንዳለብን እንዲያሳየን፣ እና ምን ያህል እንድንስጥ እንደሚፈልግ እንጠይቀው። ከዚያም እኛም ደጎች እንድንሆን እና በእነዚህ ነገሮች በስርዓት እንድንመላለስ እንዲረዳን በቡድን ጸሎት እንጠይቀው።

# ትምህርት 18፡ ዕጣ ፈንታ እና ምትሃት

| **ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:** | **የባህል መገለጫዎች:** |
|---|---|
| ሀ. ዕጣ ፈንታ እና ምትሃትን በተመለከተ ሃሰት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቁልፍ እውነታዎችን እርግጠኛ መሆን። <br> ለ. እግዚአብሔር ቅርብ እና ግድ እንደሚለው መረዳት። <br> ሐ. ካለፈው ህይወታቸው የመጣ ማንኛውም የመተት አስራርን ይፈታሉ፡ <br> መ. 1ኛ ጴጥሮስ 5፡7 ማሰላሰል (በቃል ማጥናት)። | • ሙስሊሞች እና ምትሃት <br> • ሙስሊሞች እና መንፈሳዊ ኃይላት <br> • ሀዘንን መግለጽ |

**ዝግጅት:** ይህንን ትምህርት ለመምራት ስትዘጋጅ፣ ክርስቶስ በአምልኮ እና በኃጢያት ኑዛዜ ውስጥ ያለውን ድል እንደ መሪ በማወጅ አረጋግጥ፡፡ ሌሎችም ለትምህርቱ እንዲጸልዩ ጠይቅ። ውይይቱም ተማሪዎችህ እንደመጡበት ያለባቸውን የመተት ተጽህኖ በመግለጥ፣ በመንፈስም ንቁ ለመሆን አስፈላጊ ነው።
**ትምህርቱንም የእግዚአብሔርን ድል አድራጊነት በጋራ በማወጅ በአምልኮና በጸሎት ጀምረህ መጨረስ አለብህ።**

## መክፈቻ

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** በየወሩ ለእግዚአብሔር መልሰህ የምትሰጠውን ገንዘብ ምንያህል እንደሆነ ወስነሃል፣ በወሰንከው ላይስ እርምጃን ወስደሃል? ወይስ በሌላ መንገድ በልግስና ለመስጠት አስበሃል?

**ትምህርት 18 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሀ) ዕጣ ፈንታ፤ ለ) ይጠላል፤ ሐ) ኃይላት

**ጥያቄ 2:** እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። (1ኛ ጴጥሮስ 5:7)

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡** በአጥናፍ ዓለሙ ውስጥ እጅግ ኃያል ማነው? እግዚአብሔር ፍጹም ኃያል ነው፣ እና ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንን እና የጨለማ ኃይቶች ሁሉ አሸንፏል። ዛሬ ደግሞ በእግዚአብሔር እንደተመረጠ ህዝብ ዕጣ ፈንታን ቢሆን፣ ጂኒ ቢሆን፣ ወይም ቡዳን- ምንም ነገር በመፍራት መኖር ለምን እንደሌለብን እንማራለን።

## ውይይት

### መግቢያ እና ጥያቄ 1

**ከጥያቄ 1 በፊት ያለውን ጸሎት በጋራ ጸልዩ።** ዲያቢሎስ ዕጣ ፈንታን እና ምትሃትን በተመለከተ ብዙ ውሸትን ነግሮናል። በርካታ ሰዎች ለዘመናት እነዚህን ውሸቶች በማመን፣ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ሆነው ቀርተዋል። ምንአልባት እነዚህ የውሸት ሃሳቦች በአይምሯችን ተቀምጠው ይሆናል። ዛሬ ግን በእግዚአብሔር እውነት እናፈርሳቸዋለን!

**ጥያቄ 1:** ጥያቄውን አንብብ። *ተማሪዎች የመጡበትን እና መረዳታቸውን እንዲያካፍሉ ጊዜ ስጥ።*

- የአንተ **ትክክለኛ** አስተያየት ምንድነው: 'አዎን/አይደለም ወይስ እርግጠኛአይደለሁም'? ይህንን አስተያየት የሰጠኸው እንዴት ነበር?

### ህይወታችን የሚመራው በእግዚአብሔር እንጂ በዕጣ ፈንታ አይደለም (ጥያቄ 2-9)

**ጥያቄ 2:** ጥያቄውን አንብብ እና ስዕሉን ተመልከት *(የሰዎች የውሸት ሃሳብ)።*

- እግዚአብሔር ስለእኛ ከማሰብ እጅግ የራቀ ነው ብለህ አምነህ ታውቃለህ? ይህ የተለወጠው እንዴት ነው?

**ጥያቄ 3:** ስዕሉን ተመልከት *(በባዶ ቦታው ከተሞሉ ቃላት ጋር)።*

- ዕጣ ፈንታ፣ ጂኒ እና ቡዳ የየዕለት ህይወታቸው ላይ ተጽህኖ እንደሚያደርግባቸው የሚያስቡ ሰዎችን ታውቃለህ?
- እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ፣ እነዚህ ነገሮች አሉን? *አዎን (ክርስቲያኖች በአተረጓጎም ቢለያዩም እንኳን)።*

**ጥያቄ 6:** ስዕሉን ተመልከት እና ጥያቄውን አንብብ።

- ለክፍል ሀ) እና ክፍል ለ) የጻፍከው ምን ነበር? እነዚህን መልሶች የሰጠኸው ለምንድነው?
- በቀጣይ ጊዜ አንተ ራስህ ትቸገራለህ፣ አንተን የሚያጽናናህ ዓረፍተ ነገር 1 ነው ወይስ 2?

**ጥያቄ 7:** ስዕሉን አንብብ: ' እግዚአብሔር በእውነት የሚመስለው ምንድነው'።

- በጥያቄ 3 ውስጥ ካየነው ይህን ስዕል የሚለየው ምንድነው? *እግዚአብሔር ከእኛ ርቆ በመኖር ፈንታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እኛ ወዳለንበት መጥቷል። እሱ በእውነት ስለእኛ ያስባል። ስለእኛም ለማሰብ ሩቅ አይደለም።*

**ጥያቄ 8:** ጥያቄውን አንብብ እና በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ተለማመድ። ይህን በቡድን ወይም በጥንድ ሞክር

- የመጀመሪያው ሰው ሁለተኛውን ሰው ይጠይቀው፣ "ስለነዚህ ቀናት አንተን የሚያስጨንቅህ ምንድነው?"
- ሁለተኛው ሰው የራሱን ምላሽ ይስጥ። የመጀመሪያው ሰው፡ "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። (1ኛ ጴጥሮስ 5:7)"። ሁለተኛውም ሰው ቀጥሎ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፣ እና እንደ ቡድኑ መሪ አንተን ጨምሮ እንዲህ እያለ ሁሉንም ያደርሳል።

## እግዚአብሔር ምትሃት እና ጣዖት አምላኪነትን ይጠላል (ጥያቄ 10-17)

**ጥያቄ 10:** ጥያቄውን አንብብ።

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር?

*በምዕራብ ያሉ ሙስሊሞች እነዚህን ነገሮች በአነስተኛ ደረጃ ያደርጓቸዋል፣ አሁንም ግን ብዙ ጊዜ በመሠረታዊ እምነታቸው ተጽህኖ ስር ናቸው። የቤተሰብም ባህል ጠይቅ*

**ጥያቄ 11-15:**

- በእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ የተጠቀሱት ተግባሮች ምንድናቸው? *ከእነዚህም አንዳንዶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃሎቻቸው ከባድ ሊሆኑ ስለሚችሉ ትርጓሜውን ለመግለጽ ዝግጁ ሁኑ። አሁን መጽሐፍ ቅዱስህን መክፈት አያስፈልግህም።*
- ለሁሉም እግዚአብሔር ያለው ሃሳብ ምንድነው? *እሱ እነሱን አይወድም፣ ይጠላል እና ይከለክላል።*
- እነዚህ ተግባራት ጣዖትን እንደማምለክ የሆኑት ለምንድነው (ጥያቄ 15)? *ሰዎች እነሱን ከእግዚአብሔር በላይ አድርገው ሲታመኑ እና ሲታዘዙ ነው፤ ምክንያቱም እነሱ የተፈጠሩ ነገሮችን በፈጣሪ ቦታ ስላስቀመጡ ነው።*

**ጥያቄ 16:** የንግግር ሳጥኑን አንብብ። ለዚህች ሴት የምትሰጣት ምክር ምንድነው?

***አንዳንድ አስተያየቶች:*** *ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር ስለእሷ እንደሚያስብ ልታውቅ ይገባል። እሱ ሀዘኗ ይሰማዋል። በእርግጥ እሷ በክርስቶስ ስለሆነች፣ ቅዱስ ከሚባው ሰው በላይ ለእግዚአብሔር ቅርብ ነች። ሁለት ጌቶችን ክርስቶስን እና ቅዱስ የሚባለው ሰው መከተል አትችልም፡፡ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት ሌሎች አማኞች ከእሷ ጋር እንዲጸልዩ ልትጠይቅ ይገባል። እሷግን ልጅ ኖራትም ወይም አልኖራትም፣ የእሱ ዓላማ የተሻለ ነው።*

## ጌታ ኢየሱስ መንፈሳዊ ኃይላትን ሁሉ ይገዛል (ጥያቄ 18-21)


**ጥያቄ 18-19:** **ሁለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብ እና ተወያዩ።**

- **ማርቆስ 1:21-27.** በቁጥር 22, ሰዎችን ስለኢየሱስ የሚያስገርማቸው ምንድነው? *በስልጣን ያስተምር ነበር*
- ኢየሱስ ስልጣኑን በተግባር ያረጋገጠው እንዴት ነበር? *እርኩሳን መናፍስትን ሲያዝ ይታዘዙ ነበር*
- በቁጥር 24 ውስጥ፣ መንፈሱ ስለኢየሱስ የለያቸው ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ምንድናቸው?

*1. ኢየሱስ የመጣው እርኩሳን መናፍስትን ለማጥፋት ነው 2. እሱ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነው*

- በቁጥር 27 ውስጥ የሰዎች ምላሽ እንዴት ነበር? *ከበፊቱ ይልቅ ይገረሙ ነበር።*

- በጥያቄ 19 ላይ ወዳለው ስዕል ሂድ እና **1ኛ ጴጥሮስ** 3:21-22 አንብብ *(ከቁ.21 አጋማሽ ጀምሮ)*
  በዚህ ክፍል ውስጥ ወደ ላይ በተቀመጠው ቀስት የተጠቀሰው እውነት የቱ ነው?
  *'የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ'፣ 'ወደሰማይ ማረጉን'፣ 'በእግዚአብሔር ቀኝ'።*



- በእንቁላል ቅርጽ ውስጥ የጻፍከው ምንድነው? *መላዕክት፣ ስልጣናት፣ ኃይላት*
- በስዕሉ ላይ፣ ከጂኒ እና መንፈሳዊ ኃይላት በላይ የሆነ ማነው?
- እኛ በስዕሉ ላይ የት ነን? *ከክርስቶስ ጋር ተቀምጠን እንገዛለን፣ ኤፌሶን 2:6.*
- አንድ ሰው ቢረግምህ፣ ከእርግማን በላይ ኃይል ያለው ማነው?

**ጥያቄ 21:** ክርስቶስ በእርኩሳን ኃይላት ላይ ያደረገውን ድል የተለማመድን አለን?

- ***በማዕዘናዊ ቅንፍ ውስጥ ያለውን ክፍል አንብብ።*** አንዳንዶቻችሁ እርኩሳን ኃይላትን ትፈሩ ይሆናል፣ ሌሎቻችሁ ደግሞ ላትፈሩ ትችላላችሁ። ፍርሃቱ ካለ ከዚህ በኋላ ከእኔ ወይም ሌላ ከቆየ አማኝ ጋር ተነጋገሩ።

## ሁለት ጌቶችን ማገልገል እንችላለን? (ጥያቄ 22-24)

**ጥያቄ 23:** ታሪኩን አንብብ። ጽፈህ የነበረው መልስ ምንድነው?

- ይህንን አባባል አስታውስ፣ 'ኢየሱስ በሁሉ ላይ ጌታ ካልሆነ፣ ባጠቃላይ እሱ ጌታ አይደለም ማለት ነው!'
- የዲቢሎስን ሽንገላ (ውሸት) ለማፍረስ ስለሦስት አስፈላጊ እውነታዎች ዛሬ ተነጋገረናል። እነማን ናቸው?

*1. ዕጣ ፈንታ ሳይሆን ህይወታችንን የሚመራው እግዚአብሔር ነው። 2. እግዚአብሔር ጣዖት አምለኮን እና ምትሃትን ይጠላል*
*3. ኢየሱስ በሁሉ መንፈሳዊ ኃይላት ላይ ገዢ ነው።*

- በዛሬው ውይይት መጨረሻ ላይ የተሰማህ እንዴት ነው?

## *ማጠቃለያ*

**ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:**

- የዛሬው ትምህርት በአንተ ህይወት ውስጥ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?

**ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** ጥያቄውን በጥንቃቄ ሂድበት። እነዚህ ነገሮች ህይወትህ ላይ ተጽህኖ በሚያደርጉጊዜ እግዚአብሔር ያለፈውን ሁኔታ እንዲያሳስብህ ጠይቀው። እንደዚህ ዓይነት ተጽዕኖ ከነበረ፣ ሌላ አማኝ በተቃውሞ ጸሎት አብሮህ እንዲሆን ጠይቅ።

**በአንድነት ጸልዩ:**

በአንድነት በመቆም እነዚህን እውነታዎች ዲያቢሎስን በመቃወም አውጁ፡ *ዕጣ ፈንታ ሳይሆን ህይወታችንን የሚመራው እግዚአብሔር ነው ፣ እግዚአብሔር ጣዖት አምለኮን እና ምትሃትን ይጠላል ፣. ኢየሱስ በሁሉ መንፈሳዊ ኃይላት ላይ ገዢ ነው።*

# ትምህርት 19፡ የእርስ በርስ አገልግሎት

| **ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:** | **የባህል መገለጫዎች:** |
|---|---|
| ሀ. አንዱ ሌላውን ለማገልገል በትህትና ስጦታውን ይጠቀማል። | • በሙስሊም ባህል የእግር መታጠብ |
| ለ. የቤተክርስቲያን መሪዎችን ያግዛል እና ያለባቸውን ኃላፊነት ይረዳል። | • ከእስ.የመ.አ ቡድን ውስጥ ያለ የአመራር ጉዳይ |
| ሐ. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡10 ማስላስል (በቃል ማጥናት)። | **ዝግጅት:** ፎጣዎች፣ ሳሙና፣ ማስታጠቢያ፣ ሙቅ ውሃ |

## መክፈቻ

**ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ መከለስ:** ባለፈ ታሪክህ ውስጥ ከማንኛውም ምትሃታዊ ወይም ቅዱስ ከሚባል ሰው ምንም ዓይነት ተጽኖ አድሮብህ እንደነበር አጣርተሃል? ከአንድ ሰው ጋር ጸልየሃል? ስለዚህም እስካሁን የምትጨነቅ ከሆንክ እባክህ በግል እንገናኝ።

**ትምህርት 19 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሀ) ስጦታ፤ ለ) እያንዳንዳችን፤ ሐ) ለአገልግሎት

**ጥያቄ 2:** "እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤" (1ኛ ጴጥሮስ 4:10)።

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ:** እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን ሰጥቶናል። ዛሬ እነዚያን ስጦታዎች እንዴት መጠቀም እንደምንችልና እግዚአብሔርንና እርስበርሳችን ማገልገል እንደምንችል እንማራለን። መሪዎችም ቢሆኑ ሕዝባቸውን ማገልገል ይገባቸዋል።

## ውይይት

### አንዱ ሌላውን ማገልገል (መግቢያ እና ጥያቄ 1-3)

**መጀመሪያ በቀረበው ስዕል ላይ የሚሰነዘር ሃሳብ:** ኢየሱስ ወደ መስቀል ሞት ከሚሄድበት ቀን አስቀድሞ ባለው ምሽት ላይ



የቅርብ ወዳጆቹን እግር አጥቦ ነበር። **ዮሐንስ 13:3-5,12-17 አንብብ።** *በዝግታና ቆም እያልክ አንብብ፡*
*"በስዕሉ ላይ ያሉትን እጆች ተመልከት። የክርስቶስ እጆች እንደሆኑ አስብ።"*
*"እግሮቹን ደግሞ ተመልከት እና የአንተ እግሮች እንደሆኑ አስብ። ክርስቶስ እግርህን እያጠበ ነው!"*
*"ስለዚህ የሚሰማህ እንዴት ነው? በልብህ በዚህ ጉዳይ የተሰማህን ለጌታህ አሁን ንገረው።"*
**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን እግር ቢያጥብ ብለን ባሰብን ጊዜ የተሰማን ስሜት ምን ነበር?**

**ጥያቄ 2:** ጥያቄውን አንብብ።

- እኛ የመጣንበት ባህል ውስጥ፣ መሪዎች ተከታዮችቻቸውን ያገለግላሉ?
- የእኛ ታላቁ መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እግር ለማጠብ ዝቅ ያለ ነበር። ስለዚህ፣ እኛ እንደ ምላሽ ማድረግ ያለብን ምንድነው?
- መሪዎች ክርስቶስ እንዳደረገው ሰዎችን ዝቅ ብለው ቢያገለግሉ የእነሱን አክብሮት ላያገኙ ይችላሉን?

*በጥ.1 ውስጥ ሳጥኑን ተመልከት። እሱም "ምሳሌን ሰጥቻችኋለው" ብሏል። ስላገለገለን እናመሰግነዋለን እና እኛም ለማገልገል እንደ እሱ ዝቅ ማለት አለብን። እንደዚህ ዓይነት መሪ በመጨረሻም ክብርን ያገኛል።*

### የአገልግሎት ስጦታ (ጥያቄ 4-5)

**1ኛ ጴጥሮስ 4:10-11 አንብብ እና በቃል የተጠናው ጥቅስ ይከለስ (1ኛ ጴጥሮስ 4:10)።**

- በቁ.10 ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሰጠንን ስጦታ መጠቀም ያለብን እንዴት ነው? *ለማገልገል*
- እኛ እንደ 'ታማኝ ባለአደራዎች' መሆን ያለብን ለምንድነው ብለህ ታስባለህ? *እኛ የጌታው ነገር ላይ ባለቤት እንደሆነ ሰው ሳይሆን እንደ እሱ ሆነን በሚገባ የምንጠቀም፣ ታማኝ አስተዳዳሪ ልንሆን ይገባል።*
- የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ብዙ ልዩ ልዩ ስጦታዎች ይገልጻሉ። በቁጥር 11 ውስጥ የምናገኛቸው ሁለት ስጦታዎች የትኞቹ ናቸው?
- በቁጥር 11 ውስጥ ያሉት ሁለት ሰዎች ስጦታቸውን መጠቀም ያለባቸው እንዴት ነው?
- የቁጥር 11ን የመጨረሻ ክፍል በአንድነት ከፍ ባለ ድምጽ እንበለው። ስጦታችንን ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀምበት ይገባል።

### የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ስጦታ አላቸው (ጥያቄ 6-9)

**ጥያቄ 9:** በሳጥን ውስጥ ያለውን ታሪክ እና ቀጥሎ ያለውን አንቀጽ አንብብ።

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር? *ለምሳሌ፡ እኛ ሁላችን ጥንካሬ አለን ግን ደግሞ ድክመም አለብን። እኛ ሁላችን በአንድም*

*ይሁን በሌላ መንገድ 'የታወርን' ወይም 'አንካሶች' ነን። እንዳችንም በራሳችን ሙሉ እና ፍጹም አይደለንም። የእኔ ድካም ግን አንተ የምትበረታበት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ባለንበት የአማኞች ህብረት ውስጥ አንዳችን ለሌላችን አስፈላጊ ነን።*

## እያንዳንዳችን ስጦታ አለን (ጥያቄ 11-14)

**ጥያቄ 11:** ስዕሉን ተመልከት።



- እግዚአብሔር ለፎዚያ የሰጣት የአገልግሎት ስጦታ ምንድነው?
- ለይላ ፎዚያ ያላትን ስጦታ እንድትለይ የረዳቻት እንዴት ነበር?

**ጥያቄ 13:**

- ስጦታዎቻችን ምን እንደሆኑ መለየት የምንችለው እንዴት ነው? *በቀስት ምልክት ያሉትን 3 ነጥቦች ተመልከት።*
- አንድ የቡድን አባል፣ የአገልግሎት አንዱን መንገድ ይጥቀስ።. ቀጣዩ አባል ደግሞ ይህንኑ ይድገምና ሌላ አንድ መንገድ ይጨምር። በዝርዝር ውስጥ የምንችለውን ያህል መጨመራችንን እንቀጥል። *ለምሳሌ: ስብሰባ መምራት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር፣ የሙዚቃ መሳሪያ መጫወት፣ እንግዳ መቀበል፣ ጸሎት፣ ግለሰቦችን ማበረታታት፣ የማያምኑትን በወንጌል መድረስ፣ ተግባራዊ እርዳታ፣ የገንዘብ እርዳታ፣ ምግብ ማብሰል፣ ወ.ዘ.ተ ናቸው።*
- እነዚህ የተለያዩ አገልግሎቶች የአማኞችን ህብረት ሊያሳድጉ የሚችሉት እንዴት ነው ?

## ስጦታችንን በትህትና ልንጠቀምበት ይገባል (ጥያቄ 15-18)

**ጥያቄ 15:** ጥያቄውን አንብብ።

- ሳሚርን እንደ ቡድን መሪ በመደገፍ የጻፍካቸው ምክንያቶች ምን ነበሩ? የተቃውሞ ምክንያቶችህስ ምን ነበሩ?
- ቡድኑ ሳሚር ወደ ኩራት ሳይገባ በመሪነት ውስጥ እንዲያድግ መርዳት የሚችለው እንዴት ነው?

*በእድሜ የገፋ አማኝ ከሳሚር ጋር ስለ ኩሩ ዝንባሌው ሊያወራው ይችላል። ሳሚርም በሌላ መሪ ስር በመሆን የጀማሪ ኃላፊነት ሊሰጠው ይችላል። ይህንንም በትህተና ማድረግ ከቻለ በኋላ ላይ የበለጠ ኃላፊነት ሊሰጠው ይችላል። መሪም ሲሆን ብቻውን ሳይሆን ከሁለት ወይም ከሚበለጡ ሌሎች መሪዎች ጋር በአንድነት በቡድን ውስጥ መስራት ነው።*

**ጥያቄ 17:** ጥያቄውን አንብብ።

- በእግዚአብሔር ፊት በጣም አስፈላጊው ማነው፣ የሚሰብከው ሰው ወይስ ማዕድ የሚገለግለው?

*ሁለቱም እኩል አስፈላጊ ናቸው። እኛ የሚሰብኩትን እና ማዕድ የሚያገለግሉትን ልናመሰግን ይገባል።*

## እንደ መሪ ማገልገል (ጥያቄ 19 -25)

**ጥያቄ 21:** በዚህ ጥያቄ ማብቂያ ላይ ያሉትን የባህሪ ዝርዝሮች ተመልከት።

- ዋናው እረኛ ኢየሱስ ከእነዚህ የመሪነት ልቀቶች ውስጥ ያሳየው የትኛውን ነበር? *ሀ) ፣ ለ) እና ሠ)።*
- ክርስቶስን የሚመስል መሪ እነዚህን ባህሪያት በተግባራዊ መንገዶች ማሳየት የሚችለው እንዴት ነው?

### Read 1ኛ ጴጥሮስ 5:1-6 አንብብ:

- በቁጥር 2-3 ውስጥ፣ ክርስቶስን የሚመስሉ መሪዎች በዓለም ካሉ መሪዎች የሚለዩባቸውን ሦስት መንገዶች ፈልግ። *ጥርጣሬ ካለ ጥያቄ 22 ተመልከት።*
- ቁጥር 4 ለእንደዚህ ዓይነት መሪዎች የሚሰጠው ተስፋ ምንድነው?
- አማኞች መሪዎቻቸው ባለባቸው ከባድ ኃላፊነት ሊረዷቸው የሚችሉት በምን ዓይነት መንገድ ነው?. *ለእነሱ በመገዛት (ቁ. 5)፣ ለእነሱ በመጸለይ እና በማክበር፣ እነሱን በማበረታታት፣ እነሱን በማመስገን፣ ከእነሱ ኋላ ባለማጉረምረም*
- በቁጥር 5 እና 6 ውስጥ፣ እኛ ሁላችን ስጦታችንን በመጠቀም ሊኖረን የሚገባው ዝንባሌ ምንድነው?

**ጥያቄ 25:** ሁለተኛውን አንቀጽ አንብብ።

- እዚህ ላይ የጻፍከው ምን ነበር?

**በጥያቄ 25 መጨረሻ፣ በሳጥን ያለውን የመምህሩ ንግግር ሁሉም ሰው በጋራ ያንብብ።.**

*ለምሳሌ፥ አገልጋይ መሪ አሁንም መሪ ነው። እነሱም ስለጣን ስላላቸው ሰው ይህን ሊያከብር ይገባል። አክብሮታቸው ከፍርሃት የመጣ ሳይሆን ከፍቅር ነው። መሪውም እነሱን ለመጥቀም ራሱን መስዋዕት አድርጎ ያገለግላል።*

## ማጠቃለያ

| ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ: | እርስ በርስ ማገልገልን መለማመድ፥ |
|---|---|
| • የዛሬው ትምህርት በአንተ ህይወት ውስጥ ያመጣው ልዩነት ምንድነው?<br>• ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።<br>• ሌሎችን በስጦታህ ልታገለግል የምትችልበት የተለየ ሃሳብ አለህ? | አንዱ የሌላውን እግር ይጠብ (ሴት እና ወንድ ተለይቶ)፥ ፥ አንተም እንደመሪ መጀመር አለብህ!<br>**በአንድነት ጸልይ:** ክርስቶስ የእኛን እግር እንዳጠበ አሰብ። እሱ እኛን እንዳገለገለ፣ ሰዎችን እንዴት እንድናገለግል እንደሚፈልግ እንዲያሳየን እና ሌሎችን እንድናገለግል እንዲረዳን በጸሎት ጠይቁት። |

# ትምህርት 20፡ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ መንግስተ ሰማይ

**ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረን ዓላማ:**

ሀ. ወደ መንግስተ ሰማይ በደህና እንደሚደርስ እርግጠኛ እንዲሆን እና እሱንም እንዲናፍቅ ነው።

ለ. የዲያቢሎስን ጥቃት ማወቅ እና መቃወም።

ሐ. 1ኛ ጴጥሮስ 5፡10-11 ማሰላሰል።

**የባህል መገለጫዎች:**

- ሙስሊሞች፣ መንፈሳዊ ጉዞ እና መንግስተ ሰማይ
- እየሩሳሌም እና ጽዮናዊ

**ዝግጅት:** እኛ የሚለውን ድምጸት የያዘውን ጥቅስ (ጥ. 22 እይ) እንጽፋለን ወይም እናትማለን። የትምህርቱን መጠናቀቅ ምክንያት በማድረግ ምስክርነት የምንሰማበትን እና ማዕድ የሚቆረስበት የአንድነት ጊዜ እንዲኖር አቅድ።

## መክፈቻ

**በጸሎት ጀምርና ያለፈውን ሳምንት ተግባራዊ ስራ ከልስ:** ምን ስጦታህ እንዳለህ ጓደኛህን ጠየክ? ያሉት ምን ነበር? በዚህ ሳምንት ሌሎችን የማገልገል ዕድሉ ነበረህ? *እያንዳንዱ ተሳተፊ መናገር አለበት*

**ትምህርት 20 - የቤት ውስጥ ጥናት ክለሳ:**

**ጥያቄ 1:** ሀ) እየሩሳሌም፤ b) መንግስተ ሰማይ (ወይም ገነት) **ጥያቄ 2:** ሀ) እኛ፤ ለ) ክርስቶስ

**ጥያቄ 3:** በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል። ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን። (1ኛ ጴጥሮስ 5:10-11)

**ጥያቄ 4:** በግል የሚሰጥ ምላሽ። *እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ እንድንሆን ይፈልጋል። እኛ በምንሞት ጊዜ በመጀመሪያ በስቃይ ውስጥ ሳናልፍ እግዚአብሔር ባለበት ለመሆን ወደ ገነት እንሄዳለን! እስካሁን ጥርጣሬ ያለበት ሰው ካለ፣ ኢየሱስ ለወንጀለኛው ሰው እንኳን በሉቃስ 23:39-43የገባለትን ተስፋ 'ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው' አሳያቸው!*

**የዛሬውን ርዕስ ማስተዋወቅ፡** እኛ ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም ገነት የዕድሜ ልክ ጉዞ ላይ ነን። እኛ ክብር ያለበት ፍጻሜ አለን፣ ጉዞው ላይ ግን ጠላታችንን ዲያቢሎስን ልንዋጋ ይገባል። ስለዚህም መንፈሳዊ ዛሬ እንማራለን።

## ውይይት

### የእኛ መንፈሳዊ ጉዞ (ጥያቄ 1-5)

**ጥያቄ 2-3:** ጥያቄ 2ን በሙሉ እና የጥያቄ 3 የመጀመሪያ አንቀጽ አንብብ።

- እንደ ክርስቶስ ተከታይ እኛ የምንጓዘው ሃጂ ወይም መንፈሳዊ ጉዞ ምን ዓይነት ነው? *እኛ ወደ ሰማያዊ ቤታችን የምናደርገው የእድሜ ልክ ጉዞ ነው።*
- በዚህ ዘመን የክርስቶስ ተከታዮች ሲጸልዩ፣ ወደ እየሩሳሌም ፊታቸውን የማያዞሩት ለምንድነው? *ምክንያቱም የእኛ ጸሎት እና ህይወታችን ወደ እግዚአብሔር እንጂ ወደ ምድራዊ ከተማ ሊያመለክት አይገባም።*

**ጥያቄ 4:** 'ቆም ብለህ አስብ' የሚለውን ጨምሮ ጥያቄውን አንብብ።

- ስለዚህም አሰበህበታል እና የወሰንከው ምንድነው?

### ዲያቢሎስን መቃወም (ጥያቄ 6-16)

**1ኛ ጴጥሮስ 5:6-11 አንብብ።**

- እኛ ኩሩ ስንሆን ቁጥር 6 ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው? *ትሁት እንድንሆን ይረዳናል።*
- እኛ ስንጨነቅ ቁጥር 7 ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው? *እግዚአብሔር ስለእኛ እንደሚያስብ ብርቱ ተስፋን ይሰጠናል!*
- በቁጥር 8 መሠረት፣ እንደ አንበሳ የተመሰለው ማነው?
- በቁጥር 9 መሠረት፣ እሱን መቃወም እንችላለን? *ዲያቢሎስ።'በእምነት ከጸናን'፣ አዎን።*



እያንዳንዱ ሰው በቃሉ ማለት እስኪችል ድረስ፣ ቁጥር 10-11 በአንድ ድምጽ በጋራ አንብቡ።

**ጥያቄ 7:** ሙሉ ጥያቄውን አንብብ እና በሦስቱ ክፍሎች ላይ የጻፋችሁትን አካፍሉ:

- የክርስቶስን ተከታዮች ደካማ ሊያደርጋቸው የሚችለው ምንድነው? *ለምሳሌ፡ እነሱ መጸለይን እና የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ካቆሙ። የክርስቶስ ተከታይ መሆናቸውን ለረጅም ጊዜ ከደበቁ (ለተወሰነ ጊዜ መደበቁ ችግር ባይኖረውም)።*
- የክርስቶስን ተከታዮች ንቁ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድናቸው? *ለምሳሌ፡ ዲያቢሎስ እየፈተናቸው መሆኑን አለማወቅ፡ ፡ ከዚያም እንደ ኩራት፣ ቁጣ ወይም ዝሙት የመሳሰሉት ኃጢያቶች ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ።*
- የክርስቶስን ተከታዮች ከመንጋው ሊለዩቸው የሚችሉ ነገሮች ምንድናቸው? *ለምሳሌ፡. ከሌሎች አማኞች ጋር ህብረት ማድረግ ሲያቆሙ፣ ለምሳሌ እነሱ የማያምኑ ሰዎችን በጋብቻ ሲጣመሩ።*

**ጥያቄ 11:** የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብብ።

- አንዳንድ ጊዜ የእኛ መከራ ምንም ልንቋቋመው የማንችለው በጣም ታላቅ ይመስላል!

**1ኛ ቆሮንቶስ**10:13 ን ግን አንብብ። ይህ ለእኛ የሚሰጠን ተስፋ ምንድነው?

- ምንም ልቋቋመው አልችልም ብለህ ያሰብክበትን ጊዜ ልትገልጸው ትችላለህ? ይህን እንድትቋቋም እግዚአብሔር ብርታትን የሰጠህ እንዴት ነው? *እያንዳንዱ ሰው ያለተጸህኖ ይህን እንዲያካፍል ዕድል ስጥ።*

**ጥያቄ 12:** በጥያቄ 12 ውስጥ ያለውን ስዕል ተመልከት።

- በውጫዊ ችግሮች የተጠቁት ሁለቱ አማኞች የትኞቹ ናቸው? *ጉል (ለ) እና ኢፍቲካር (መ)*።
- በውስጣዊ ችግሮች የተጠቁት ሁለቱ አማኞች ደግሞ የትኞቹ ናቸው? *አክታር (ሀ) እና ሺረን (ሐ)።*
- ሰይጣን በውጫዊ ችግሮች እና በውስጣዊ ፈተናዎች አንተን ያጠቃበትን ጊዜ ግለጽ። የሆነው ምንድነው? ከዚህም የተማርከበት ምንድነው? *ይህም አስፈላጊ ስለሆነ እያንዳንዱ እንዲያካፍል ጊዜ ስጥ*

**ጥያቄ 15-16:** በጥያቄ 15 ውስጥ ያለውን ስዕል ተመልከት። ጥያቄ 16ን በሙሉ አንብብ።

- በመንታ መንገድ ላይ በምንመጣ ጊዜ፣ የእኛ ምርጫ ምንድነው?
- ዲያቢሎስ የእሱን መንገድ እንድንከተል ይፈትነናል። ይህን ፈተና ለመቃወም ምርጫ ማድረግ ያለበት ማነው - እኛ ወይስ ክርስቶስ? *እኛ ነን መምረጥ ያለብን። በዲያቢሎስ መንገድ ከሄድን፣ የእኛ ስህተት እንጂ የክርስቶስ አይደለም።*
- በጥያቄ 12 ውስጥ ለአክታር እና ለሺረን፣ ከፈተና ዞር ማለትን መምረጥ ያለበት ማነው? *እራሳቸው መምረጥ አለባቸው፤* ፤ ትክክለኛ ምርጫን እንዲመርጡ ብርታት የሚሰጣቸው ማነው? *ክርስቶስ*
- ዲያቢሎስ እኛን በሚፈትነን ጊዜ፣ እሱን መቃወም ምርጫችን ከሆነ ማድረግ እንችላለ። **1ኛ ዮሐንስ 4:4 አንብብ፣** ክርስቶስ በእኛ ውስጥ አለ እና እሱም ከሰይጣን የበረታ ነው!

## ሰማያዊ ፍጻሜያችን (ጥያቄ 17-22)

**ጥያቄ 19:** ጥያቄውን አንብብ።

- እግዚአብሔር እኛን በገነት እንደሚቀበለን እርግጠኛ መሆን የምንችለው እንዴት ነው? *እኛን ወደ ገነት የምንሄድበበት ድልድይ የሆነልን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። እኛ እምነታችንን በእሱ ላይ ካደረግን እና እሱም አይጥለንም!*

**ጥያቄ 21:** በሳጥን ውስጥ ያለውን የኡመርን እውነተኛ ታሪክ አንብብ።

- በመንግስተ ሰማይ ለመሆን ያለህ መሻት ምን ያህል ነው፡ ጥቂት ወይስ ብዙ?

*በጋራ ተወያዩ። እግዚአብሔርን በምድር ላይ ደስተኛ በመሆን የሰጠንን አገልግሎት መፈጸም መልካም ነው፣ ፍጻሜያችን ከሆነው መንግስተ ሰማይ ግን ዓይናችንን ልናነሳ አይገባም! እንደ ኡመር ዕለት ዕለት እንናፍቀዋለን!*

**ጥያቄ 22:** ሙሉ ጥያቄውን አንብብ።

- በዚህ ክፍል ውስጥ አብዝተህ የወደድከው ቃል የቱ ነው ?
- በዚህ ክፍል ውስጥ አስደናቂ ተስፋዎች አሉ! ክፍሉ ውስጥ ራሳችንን በማስገባት ደግመን እናንብበው፡ ፤

*እያንዳንዱ ተማሪ እንዲናገር ጠይቅ እና አንተም አካፍል።*

***ተማሪዎችህን ለመርዳት፣ በቅድሚያ የሚተካውን በማመቻቸት ክፍሉን ጻፍ ወይም ይታተም** ለምሳሌ፡*

*"<u>እኛም</u> ሕዝቡ <u>እንሆናለን</u> እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ <u>ከእኛ</u> ጋር ሆኖ <u>አምላካችን</u> ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ <u>ከዓይኖቻችን</u> ያብሳል፣" እና ወ.ዘ.ተ፡*



**ጥያቄ 22:** በመጨረሻው ገጽ ላይ ያለውን ስዕል ተመልከት እና ቃላቱን አንብብ።

- የተሰማህ ስሜት ምንድነው?
- አስበው እግዚአብሔር የሁላችንን እምባ በገነት ያብሳል!

## *ማጠቃለያ*

***ለዛሬው ትምህርት መታዘዝ:***

- የዛሬው ትምህርት በአንተ ህይወት ውስጥ ያመጣው ለዩነት ምንድነው?
- **ተግባራዊ ስራው በጋራ ይነበብ።** በዚህ ሳምንት በየቀኑ አንድ ሐረግ ውሰድ። በጥልቀት አሰብበት። ልጆች ማስቲካን በአፋቸው ውስጥ እንደሚያላምጡ ይህንንም በአይምሮህ ውስጥ አላምጠው።
- **አክብር፡** ቡድኑ ይህንን ትምህርት በማጠናቀቁ እንዴት ነው ደስታውን የሚገልጸው? ለምሳሌ፡ በሚቀጥለው ሳምንት በአንድነት ማዕድ መቁረስ እና ከትምህርቱ ምን እንዳገኙ ምስክርነት የምንሰማበትን ቀን ለማመቻቸት መወያየት እና ማቀድ።
- **ውይይት፡** በደቀ መዝሙርነት የሚደረገው ጉዞ በቡድንም ይሁን በግል አማካሪ ግንኙነት ውስጥ እንዴት እንደሚቀጥል/መወያየት/ ነው።

***አንድነት ጸልይ:***

እያንዳንዱ 1ኛ ጴጥሮስ 5፡8-11 ያውጣ። በዚህ ክፍል የተለያዩ ክፍሎች መሠረት እያንዳንዱ ሰው አንድ አጭር ጸሎት ይጸልይ።

በተለይም በመላው ዓለም ላይ ያንኑ መከራ እየተቀበሉ ላሉ አማኝ ቤተሰቦቻችን ልንጸልይ ይገባል። (ቁ. 9)

# ማጣቀሻ፥ በዚህ ትምህርት ውስጥ የተጠቀምናቸው በቃል የሚጠኑ ጥቅሶች

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትምህርት 1 | ***ማቴዎስ 11:28***<br>"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።" | ትምህርት 11 | ***ዘፍጥረት 2:24***<br>"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።" |
| ትምህርት 2 | ***2ኛ ቆሮንቶስ 5:17***<br>"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።" | ትምህርት 12 | ***1ኛ ጴጥሮስ 3:11***<br>"ሰላምን ይሻ ይከተለውም፤" |
| ትምህርት 3 | ***1ኛ ዮሐንስ 3: 1***<br>"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን።" | ትምህርት13 | ***1ኛ ጴጥሮስ 3:18***<br>"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤" |
| ትምህርት 4 | ***1ኛ ጴጥሮስ 1:15***<br>"እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ. . .በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።" | ትምህርት 14 | ***ማቴዎስ 28:19***<br>"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ " |
| ትምህርት 5 | ***የጌታ ጸሎት***<br>"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥…" ወ.ዘ.ተ | ትምህርት 15 | ***1ኛ ቆሮንቶስ 6:19-20***<br>"በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" |
| ትምህርት 6 | ***የጌታ ጸሎት***<br>"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥…" ወ.ዘ.ተ | ትምህርት 16 | ***ማርቆስ 12:30-31***<br>"አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት።. . . ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" |
| ትምህርት 7 | ***1ኛ ጴጥሮስ 2:9***<br>"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤" | ትምህርት17 | ***ማርቆስ 12:30-31***<br>"አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት።. . . ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" |
| ትምህርት 8 | ***1ኛ ጴጥሮስ 2:17***<br>"ሁሉን አክብሩ፥ ወንድሞችን ውደዱ፥" | ትምህርት 18 | ***1ኛ ጴጥሮስ 5:7***<br>"እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።" |
| ትምህርት 9 | ***1ኛ ጴጥሮስ 2:21***<br>"ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።" | ትምህርት 19 | ***1ኛ ጴጥሮስ 4:10***<br>"እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤" |
| ትምህርት 10 | ***ማቴዎስ 5:44***<br>"ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤" | ትምህርት 20 | ***1ኛ ጴጥሮስ 5:10-11***<br>"በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል። ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።" |